የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

# መሰረታዊ የህግ ጉዳዮች ለማህበረሰቡ የህግ ንቃተ ህግ /ስልጠና/ የተዘጋጀ የንቃተ-ህግ የስልጠና ሰነድ

በንቃተ ህግ፣ ትምህርት እና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

መስከረም 2015 ዓ.ም

**ማውጫ**

## Table of Contents

**ማውጫ**

## Table of Contents

[ማውጫ ........ 1]

[ክፍል አንድ ........ 10]

[ስለህግ በጠቅላላው ........ 10]

[1.1 የህግ ምንነት ........ 10]

[1.2 የህግ መገለጫዎች ........ 11]

[1.3 የህግ አይነቶች ........ 12]

[1.3.1 የህዝብ ህግ (public law) ........ 12]

[1.3.1.1 ህገ መንግስታዊ ህግ (Constitutional law) ........ 12]

[1.3.1.2 አስተዳደራዊ ህግ (Administrative law) ........ 13]

[1.3.1.3 የወንጀል ህግ (Criminal law) ........ 13]

[1.3.2 የግል ህግ (private law) ........ 14]

[1.3.3 መሰረታዊ (substantive) እና ሥነ-ሥርአታዊ ህግ ( procedural law) ........ 15]

[1.4 የወንጀልና የፍትሀ ብሔር ህግ ልዩነት ........ 15]

[1.5 የህጎች ተዋረድ (hierarchy of laws) ........ 18]

ክፍል ሁለት ........ 19

2.1 የወንጀል ምንነት ........ 19

2.3.1 ህጋዊ ፍሬነገር  (legal element) 19

2.3.2 ሞራላዊ ፍሬ (የሀሳብ ክፍል) 20

2.3.2 ሞራላዊ ፍሬ (የሀሳብ ክፍል) 21

2.2 የወንጀል ህጉ አላማ እና ግብ----------------------------------------------------------------------------------------------------202

2.3 የወንጀል ህግ መርሆች ..........................................................................................................................23

2.4 የወንጀል ጉዳዮች ጥቆማና የፍትህ ሂደቱ የሚታዩበት አግባብ--------------------------------------------------------------- 27

2.4.1 በክስ አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል---------------------------------------------------------------------30

2.4.2 በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል ---------------------------------------------------------------------------31

2.4.3 ጠቋሚ ሳይታወቅ የሚቀርብ የወንጀል ክስ-----------------------------------------------------------------------32

2.1.4.1 እርቅ በወንጀል ጉዳዮች ያለው ፋይዳ --------------------------------------------------------------------------------32

2.1.5 ወንጀልን በመከላከል ረገድ ህብረተሰቡ ያለው ሚና--------------------------------------------------------------33

2.1.6 ለፍትህ ዕርዳታ የመስጠት ግዴታ እና ግዴታዎቹን አለመወጣት የሚያስከትለዉ ተጠያቂነት-----------------------------------35

2.1.6.1 ለፍትህ እርደታ መስጠት በፍትሐብሔር ጉዳይ------------------------------------------------------------------------35

2.1.6.2 ለፍትህ እርደታ መስጠት በወንጀል ጉዳይ--------------------------------------------------------------------------36

2.1.5 በእጅ ከፍንጅ ወንጀል የክስ አጀማመር---------------------------------------------------------------------------38

2.1.6 በወንጀል ምርመራ የፖሊስ ሚና-----------------------------------------------------------------------------------38

2.1.8 በወንጀል ምርመራ የዐቃቤ ህግ ሚና----------------------------------------------------------------------------39

2.1.9 በወንጀል ጉዳይ የፍርድ ቤቶች ሀላፊነት--------------------------------------------------------------------------39

2.1.9.2 መደበኛ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚኖራቸው ሀላፊነት ---------------------------------------------------40

2.1.9.2 የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ----------------------------------------------------------------------------------41

2.1.9.3 በወንጀል ጉዳዮች የፍርድ ቤቶች የስልጣን አይነት--------------------------------------------------------------41

2.1.9.3.1 ዋና ሥልጣን-------------------------------------------------------------------------------------------------41

2.1.9.3.2 ምትክ ሥልጣን----------------------------------------------------------------------------------------------42

2.1.9.3.3 የሥረ-ነገር ሥልጣን------------------------------------------------------------------------------------------42

2.1.9.3.4 አካባቢያዊ ሥልጣን------------------------------------------------------------------------------------------42

2.10 የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን---------------------------------------------------------------------- 42

2.10.1 የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የማየት ስልጣን---------------------------------------------------------------------43

2. 11 የቅጣት አይነቶች-----------------------------------------------------------------------------------------------44

2.11.1 የጥፋተኝነት ደረጃዎች ከወንጀል አድራጊው እድሜ አንፃር ----------------------------------------------------------------------46

2.11.2. ወጣት ጥፋተኝነት የሚያስከትለው ቅጣት ------------------------------------------------------------------------------------47

ክፍል ሶስት ........................................................................................................................... 19

ህገ መንግስታዊ መብቶች ......................................................................................................... 47

3.1 ስለሰብአዊ መብቶች ምንነት ................................................................................................. 47

3.2 የሰብአዊ መብት መርሆች ..................................................................................................... 48

3.3 በኢፌድሪ ህገ መንግስት የተካተቱ ሰብዓዊ መብቶች ......................................................................... 49

3.3.1 የተያዙ ሰዎች ሰብአዊ መብቶች ........................................................................................ 49

3.3.2 በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት ....................................................................... 50

3.3.3 የተከሰሱ ሰዎች መብት ................................................................................................. 50

3.3.4 በህይወት የመኖር መብት ............................................................................................... 50

3.3.5 የአካል ደህንነት መብት ................................................................................................. 51

3.3.6 የነፃነት መብት .......................................................................................................... 51

3.3.7 የእኩልነት መብት በኢትዮጵያ ህገመንግስት ............................................................................ 52

3.3.8 የክብርና የመልካም ስም መብት ......................................................................................... 53

3.3.9 የግል ህይወት መከበርና የመጠበቅ መብት ............................................................................... 53

3.3.10 የሀይማኖት፣ የዕምነትና የአመለካከት ነፃነት ............................................................................ 53

3.4 በኢፌድሪ ህገ መንግስት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ............................................................................ 54

3.4.1 የአመለካከትና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት ..................................................................... 54

3.4.2 የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት ....................................................... 55

3.4.3 የመደራጀት መብት ...................................................................................................... 56

3.4.4 የመዘዋወር መብት ...................................................................................................... 56

3.4.5 የዜግነት መብት .......................................................................................................... 57

የዜግነት መብት ከላይ በጠቀስናቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ጭምር ጥበቃ የተደረገለት መብት ነው፡፡ .............................. 57

3.4.6 የመምረጥና የመመረጥ መብት ............................................................................................ 58

3.4.7 የህፃናት መብት ............ 58

3.4.8 የሴቶች መብት ............ 62

3.9 ፍትህ የማግኘት መብት ............ 65

3.10 የንብረት መብት ............ 68

3.10.1 የንብረት ትርጉም ............ 68

3.10.2 የንብረት መብት አለም አቀፍ የህግ ማዕቀፍ ............ 69

3.10.3 የንብረት መብት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ............ 70

3.10.4 በንብረት መብት ላይ ያሉ ገደቦች ............ 71

ክፍል አምስት ............ 71

የቤተሰብ ህግ ............ 71

4.1. ጋብቻ እና የሚያስከትለው ውጤት ............ 72

4.1.1. ጋብቻ ለመፈፀመ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ............ 72

4.1.2 በጋብቻ ላይ ጋብቻ ............ 74

4.2 ጋብቻ የሚፈፈምባቸው ሥርአቶች ............ 74

4.2 .1 በክብር መዝገብ ሹም ፊት ............ 74

4.2 .2 የሀይማኖት ጋብቻ ............ 76

4.2 .3 የባህል ጋብቻ ............ 76

4.3 የጋብቻ ውል እና የጋብቻ ምስክር ወረቀት ልዩነት ............ 76

4.4 ጋብቻ የሚያስከትለው ውጤት ............ 77

4.4.1 ጋብቻ በተጋቢዎች በግላዊ ግንኙነት የሚያስከትለው ውጤት ............ 77

4.4.2 ጋብቻ በንብረት ረገድ የሚያስከትለው ውጤት ............ 78

4.5 የጋብቻ መፍረስ ............ 80

4.6 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት መኖር እና የሚያስከትለው ውጤት ............ 82

*4.6 .1 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት የሚያስከትለው ውጤት* ............ 82

*4.6.2 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር በንብረት ረገድ የሚያስከትለው ውጤት* ............ 83

*4.6.3 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት መቋረጥ* ..... 83

4.7 እናትነት፣ አባትነትና ልጅነት ..... 84

4.7.1 እናትነት ..... 84

4.7.2 አባትነት ..... 84

*4.7.3* ልጅነት ..... 87

4.8 ጉዲፈቻ ..... 88

4.9 ሞግዚትነት እና አሳዳሪነት ..... 91

4.10 ቀለብ ..... 92

ክፍል ስድስት ..... 95

የውርስ ህግ ..... 95

5.1 ወራሽ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ..... 96

5.2 ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ውርስ ..... 99

5.3 በኑዛዜ የሚደረግ ውርስ ..... 101

5.2 .1በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ፡- ..... 103

5.2.2 በተናዝዦ ፅሁፍ የሚደረግ ኑዛዜ፡- ..... 103

5.2.3 የቃል ኑዛዜ፡- ..... 103

5.3 ኑዛዜ ፈራሽ ወይም ውድቅ የሚሆንባቸው ምክንያቶች ..... 104

5.4 ወራሽነትን መተው (Renunciation) ..... 107

5.5 ውርስ ማጣራትና የውርስ ክፍፍል ..... 108

5.6 ወደ ውርሱ የሚመለሱ ንብረቶች (Collation by coheirs) ..... 109

5.7 ይርጋ ..... 111

ክፍል ሰባት ..... 112

የውል ህግ ..... 112

7.1 የውል ምንነት ..... 112

7.2 የውል ሕግ ዓላማ ..... 113

7.3 የውል ህግ ወሰን( Scope of Contract Law) ........ 113

7.4 የውሎች አመሰራርት(Formation of Contracts ........ 113

7.5 የውል ውጤት........ 116

7.6 ልዩ ውሎች ........ 116

7.7 .1 የሽያጭ ውል ........ 117

7.7.2 ውልን ያለመፀም ህጋዊ ውጤቶቹ ........ 119

7.7 .3 የማይንቀሳቀስ ንብርት ሽያጭ ውል........ 121

7.7.4 የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ህጎች........ 122

7.7.5 የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል አፈጻጸም........ 122

7.7.6 የብድር ውል (2471-2489) ........ 123

7. .7 የቤት ኪራይ ውል ........ 127

6.7 ውክልና........ 133

6.7.1 የውክልና ትርጉም........ 133

6.7.2 የውክልና አስፈላጊነት........ 133

6.7.3 የውክልና ውል አመሰራረት........ 134

6.7.4 የውክልና ወሰን ........ 135

6.7.6 የጥቅም ግጭት (conflict of interest)........ 141

6.7.7 ከራስ ጋር መዋዋል (contract with oneself)........ 142

6.7.8 የውክልና ስልጣንን አላግባብ መጠቀም........ 143

6.7.9 ጊዜው ባለፈበት የውክልና ሥልጣን መገልገል........ 143

6.7.10 ስለውክልና ሥልጣን መቅረት ወይም መቋረጥ ........ 143

ክፍል ስምንት ........ 145

አሰሪ እና ሰራተኛ ህግ ........ 145

.1 የሥራ ውል መንነት እና ይዘቱ........ 146

8.1.1 የአሰሪዎች ግዴታዎች ........ 146

8.1.2 የሰራተኞች ግዴታዎች ........ 147

8.2 የሥራ ውል መቋረጥ ........ 147

8.2.1 የስራ ውል የሚቋረጥባቸው ዋና ዋና መንስኤዎች፡........ 147

8.2.2 በሕገወጥ መንገድ የሥራ ውል  ሲቋረጥ ያለው ህጋዊ ውጤት........ 150

8.3 በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳትና በህጉ የተቀመጡ መፍትሄዎች........ 151

8.4 በሥራ ምክንያት ስለሚመጣ በሽታ ........ 152

ዋቢ ........ 153

መግቢያ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ህጎችን በማዉጣት ሕግን ሥርዓት ስታስከብር ኖራለች። ህጎች የሀገርንና የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲሁም መብትና ነጻነት ለማስከበር ይወጣሉ። እነዚህን መብትና ነጻነቶችን የሚየስከበር የህግ አስከባሪ ተቋማት እና አካላት አስፈላጊ ናቸዉ። ህግ የማስከበር ሃላፊነት የሁሉም ዜጋ ቢሆንም በተቋም ደረጃ ፍትህ ሚኒስቴር፤ ፍርድ ቤቶች፤ የፖሊስ ተቋምና አጋዥ ሃይሎች፤ ማረሚያ ቤቶች እንዲሁም ሌሎች የጸጥታ አስከባሪ አካላት ወዘተ ናቸዉ። የዜጎች የህግ ግንዛቤ ሳይኖራቸዉ ህግ እንዳይጥሱ የንቃተ ህግ፤ ትምህርት እና ሥልጣና ያስፈልጋቸዋል። ይህን ኃላፊነት ለመወጣት በፍትህ ሚኒስቴር የንቃት ህግ፤ትምህርትና ሥልጠና ዳይሬክቶሬት ተቋቁሞ በርካታ ሥራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል። ይህ ሰነድ  በዚህ ዳይሬክቶሬት ስር የተዘጋጀ ሲሆን ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለይ ለጎልማሶች የህግ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጀ ነዉ። በመሆኑም በዚህ ሰነድ ለጎልማሶች በሚመጥን መልኩ በርካታ የህግ ዘርፎችን አጠር መልኩ ተዘጋጅቷል። ስለሆነም በዚህ ሰነድ ስለህግ ጠቅላላ ምንነትና ይዘቱ፣ የወንጀልና የፍትሀ ብሔር ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ያላቸው አካላት፣ ስለ ህገ መንግስት፤ በህገ መንግቱ ዉስጥ የተካተቱ መርሆች፤ የዲሞካሪሲያዊ እና ሰብዓዊ መብቶች፤ የቤተሰብ ህግ ዙሪያ ስለ ጋብቻ አፈፃጸምና ውጤቱ፤ ውርስን በተመለከተ ያሉ የህግ ስርዓቶች፣ ስለውል ህግና ውክልና፣ አሰሪ እና ሰራተኛ ህግ ወዘተ በየቅደም ተከተላቸው ለመዳሰስ ተመክሯል።

ክፍል አንድ

## ሥለህግ በጠቅላላው ይዘት

### 1.1 የህግ ምንነት

ህግ የሚለው ቃል በማህበረሰቡ ዘንድ በስፋት የሚታወቅ ቃል ነው። በተለይ ህግ አስገዳጅ መሆኑን የተረዳ ማህበረሰብ በየዕለት እንቅስቃሰዉ ለሚገጥሙት አለመግባባቶች "በህግ አምላክ" በማለት ፀብ የማብረድ ልምድ የነበረው መሆኑ መረዳት ይቻላል። ሆኖም ግን ማህበረሰቡ ህግን የሚረዳበት አግባብ በዘልማድ እንጂ የዘርፉ ባለሞያዎች በሚረዱበት መልኩ እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል። የህግ ትርጓሜ በየጊዜው አንደ ዘርፉ ነው። በተለያዩ ሀገራት ለምሳሌ በህንድ የህግ ፍልስፍና ህግን "Dhama" and in Islamic system "Hukum" and Romans called it jus በማለት ይጠሩታል[1]። Germany and France, it is called as Recht and Droit respectively[2]:: ለህግ ቃላት ትርጉም በመስጠት የሚታወቀው ብላክስ ሎው የህግ መዝገበ ቃላት በተሻሻለው አራተኛ እትሙ (Black's law dictionary Revised 4th edition) ለህግ ትርጉም ሲሰጥ Law mean "A rule or method according to which phenomena or actions co-exist or follow each other that which must be obeyed and followed by citizens, subject to sanctions or legal consequences, is a law". በግርድፉ ስንተረጉመው ህግ ማለት ድርጊቶች ወይም ሁኔታዎች ያለመገፋፋት መቀጠል እንዲችሉ የሚያደርግ ስልት በዜኖችላይ አስገዳጅነት ባህሪ ያለዉ ወይም እንዲከበር የሚያስገድድ ሲሆን ተጥሶ ሲገኝ ቅጣትን የሚያስከትል ሥርዓት እንደሆነ ያመላክታል።

"Law is a system of rules created and enforced through social or governmental institutions to regulate behavior, with its precise definition a matter of longstanding debate፤ State-enforced laws can be made by a group legislature or by a single legislator, resulting in statutes; by the executive through decrees and regulations; or established by judges through precedent, usually in common law jurisdictions".ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ። ወደአማርኛ ሲተረጎም ህግ ማለት ስነ ምግባርን ለማስተካከል በማህበረሰብ እና በመንግስት ተቋማት የሚፈፀም ደንብ እና በሀገራት የሚተገበሩ ናቸው።

---

[1] Materials on Introduction to Law & Ethiopian Legal System Tesfaye Abate, Oct, 08

2. N.V. PARANJAPE 2001

እነዚህ በመንግስት የሚፈፀሙ ህጎች ከህግ አውጭው፣ በባለስልጣና የሚወጡ ደንብ እና መመሪያዎች እንዲሁም በፍርድ ቤቶች በኩል እንደህግ ሆነው የሚያገለግሉ የመጨረሻ ውሳኔዎች ናቸው።

### 1.1.1 የህግ መገለጫዎች

ህጎች በበህሪያቸዉ የተለያዩ መገለጫ አላቸዉ። ለአብነት ያክል፤

1. አጠቃላይነት፡ -ህጎች ስለማንም በስም አይገልፁም ምክንያቱም ሁሉም በህግ ፊት አንድ አይነት በሆነ እና በእኩልነት መርህ የሚመራ መሆኑን ለማመልከትነው። ለምሳሌ በ1987 ህግ መንግስት አንቀ 15 ማንኛዉም ሰዉ በሕወት የመኖር መብት አለዉ፤ ማንኛዉም ሰዉ ሰብዓዊ በመሆኑ የማይጣስ እና የማይገረሰስ በህይወት የመኖር፤የአካል ደህንነት እና የነጻነት መብት አለዉ።ማንም ሰዉ ማለቱ በጠቅላላዉ በዓለም ላይ ላሉ ለሰዎች ልጆች ሁሉ የሚሠራ ጠቅላላ መብት ሲሆን የህግ ጠቅላላነት ባህሪ ያሳያል[3]።
2. ልማድ (normativity)፡- ህግ በህብረተሰቡ ዉስጥ የነበረን መልካም ልማድ ህግ የማድረግ እሳቤ አላዉ። ይህም ልማድ የህብረሰተቡን ባህሪ እንዴት እንደሚገራ ወይም ከልካይ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ከልማዳዉ ህግ የሚወሰድ ሂደት ነዉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ህግ ፈቃጅ፤ አዛዥ እንዲሁም አስገዳጅ ተብሎ ሊከፈል ይችላል።

   ፈቃጅ ህግ የሚባሉት ለግለሰቡ የተሰጡ መብቶች ሲሆኑ ቢፈጽማዉ የሚጠቀመዉ እራሱ ግለሰቡ ነዉ። ለምሳሌ ማንም ሰዉ በነጻነት የማሰብ እና በነጻነት ሃሰቡን የመግለጽ መብት አለዉ[4]፤የተከሰሰ ሰዉ የተከሰሰበትን የክስ ቻርጅ የማግኘት እና ለክሱ መልስ የማዘጋጀት፤ የመከራከር መብት አለዉ ወዘተ ፈቃጅ ህጎች[5] ናቸዉ። በሌላ በኩል አዛዥ ነገር ግን አማራጭ ያልሆኑ ድንጋጌዎች የሚባሉት በዉል ዉሰጥ የተቀመጡ ግዴታዎች ወይም መብቶች እንዲፈጸሙ የሚያዝ ማለት ነዉ። ለምሳሌ ተበዳሪ ለፍርድ ባለመብት በዉሉ መሰረት የተበደረዉን ገንዘብ መክፈል አለበት።ሌላዉ የህግ ድንጋጌዎች ባህሪ ከልካይነት ነዉ። በህግ በግልጽ ድንጋጌ ተደንግጎ ይህን ተላልፎ የወንጀል ወይም የፍትሐብሄር ጥሰት የፈጸመ በግልጽ ይቀጣል። የወንጀል ህግ ከልካይ ህግ ነዉ። ለምሳሌ ስርቆት፤ ሀሰተኛ ሰነድ፤ ሙስና፤ ማታለል

---

[3] Introduction to Law and the Ethiopian Legal System Teaching Material Prepared by: Tesfaye Abate Oct 08/2009 page 5

[4] Proclamation of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia 1Year No.1 ADDIS ABABA - 21s August, 1995 article 29

[5] Proclamation of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia 1Year No.1 ADDIS ABABA – 21 August, 1995 article 20

ወዘተ ወንጀል ህገ ወጥነቱ እና አስቀጭነቱ ተደንግጎ ባለበት ሁኔታ ተላልፎ በተገኘ ጊዜ በእስራት፤ በገንዘብ ወይም በሌላ የቅጣት አይነት ይቀጣል።

3. ቅጣት፡- ህጎች የአስገዳጅነት ባህሪ አላቸዉ። ህግ ይወጣል፤ ከቅጣት በፊት በቅድሚያ ያስጠነቅቃል፤ ተላልፎ የተገኘ ሰዉ ይቀጣል። ስለሆነም ህጎች ተፈጻሚ የሚሆኑት አጥፊዉን ሲቀጡና ማስተማሪያ ሲሆኑ ነዉ። ከህጎች ልዩ ባህሪ የቅጣት ድንጋጌዎችን ማስቀመጡ ነዉ።

### 1.2 የህግ አይነቶች

ህጎችን ግልጽ በሆነ መልኩ ለይቶ መከፋፈል አስቸጋሪ ቢሆንም የዘርፉ ባለሙያዎች በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የህግጋትን ባህሪ፣ አላማ እና የግንኙነቱ ምንጭ በማየት በተለያየ መልኩ ከፋፍለው አስቀምጠውታል። ከነዚህም መካከል መሠረታዊ ህግ (substantive law) ሥነ-ሥርአታዊ ህግ (procedural law) እንዲሁም የህዝብ ህግ (public law) እና የግል ህግ (private law) ይገኙበታል። ህጎች የግል እና የህዝብ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ።

#### 1.1.2 የህዝብ ህግ (public law) እና የግል ህግ (private law)

##### 1.1.2.1 የህዝብ ህግ (public law)

የግል የህዝብ ህግ በዋናነት በመንግስትና በህዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገዙ እንዲሁም በግለሰቦች መካከል ያለ ግንኙነት ሆኖ ህብረተሰቡን ጥቅም የሚነኩ ጉዳዮችን የሚገዙ ህግጋትን ለመግለፅ የምንጠቀምበት ነው። በሌለ አነጋገር የህዝብ ህግ ማለት በህግ የህብተሰቡን አጠቃላይ ጥቅም የሚያስጠበቅ ህግ ነው። ይህ የህግ ዘርፍ በዋናነት የህብረተሰቡን የጋራ ጥቅም የሚያስከብሩ የወል ህግጋትን የሚያካትት ነው።[6] ለምሳሌ ህገ መንግስት፣ አስተዳደራዊ ህግ፤ የወንጀል ህግ፤ የፍትህብሔር ህግ፤ የቤተሰብ ህግ ወዘተ የሚካተቱ ናቸው።[7]

- ህገ-መንግስታዊ ህግ (Constitutional law)

በሀገራችን በዘመናዊ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ህገ-መንግስት የተዋቀረዉ በ1931 ዓ.ም ከህግ ምንጮች መረዳት ይቻላል። በየሀገራቱ ያሉ ህግ መንግስት መሠረታዊ የሚባሉ መርሆችን፤ ሀገር የሚኖራትን የመንግስት አይነት፣ የመንግስት አካላት የስልጣን ክፍፍልን፤መሰረታዊ የሆኑ የሰብአዊ እና ዲሞክሪያሲያዊ መብቶችን ድንጋጌዎችን፤ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸዉን ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችንና መብቶችን፤ የሀገሪቱን የፖለቲካ ግዛት፤ የማህበራዊ፤ የኢኮኖሚ መርሆች እና የፖሊሲ አቅጣጫዎችን፤ የምርጫ ሥርዓትን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን የሚደነግግ የበላይ ህግና የህዝብ

---

[6] Ion harel, public and private law, Jul 14 2014, page 1041

[7] Jaap Hage & Bram Akkermans, Introduction to law, April 2014, page 37

ዉክልና ያለበት የፖለቲካ ሰነድ ነው።ህገ መንግስት እንደየሀገራቱ ሁኔታ የተፃፈ ወይም ያልተፃፈ ሰነድ ሊሆን ይችላል። በ1987 ዓ.ም የወጣዉ ኢፌድሪ ህግ መንግሰት አንቀፅ 9/1/ መሰረት ህገ መንግሰቱ የሃገሪቱ የበላይ ህግ ነው ሲል ያስቀምጣል። ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ ድርጊት እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው ይደነግጋል አንቀጽ (2)። ስለሆነም ህግ መንግስቱ በህዝብ ተወካዮች የሚወጣ የህዝቦች የቃልኪዳን ሰነድ በመሆኑ፤ ለህጎች፣ ፖሊሲዎች፤ስትራቴጅዎች፤ መርሆች ሁሉ ምንጭ በመሆኑ የህዝብ ህግ ተብል ይጠቀሣል[8]።

ህገ-መንግስታዊነት ማለት ደግሞ በመንግስት የሚወሰዱ እርምጃዎች ህጋዊነት፤ ዲሞክሪያሲያዊነት፤ ፍትሐዊነትን የሚመዝን እና መንግስታዊ ክንዉኖች በተቀመጡት ህጎች መሰረት መተግበር እንዳለባቸው የሚያመለክት ስርዓት ነው። (Constitutionalism can be defined as the doctrine that governs the legitimacy of government action, and it implies something far more important than the idea of legality that requires official conduct to be in accordance with pre-fixed legal rules.[9])

- አስተዳደራዊ ህግ (Administrative law)

መንግስታዊ አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበትና ማናቸውም የመንግስት ባለሥልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን የተመለከተ ህግ ነዉ። አስተዳደራዊ ህግ ማለት የመንግስት አስተዳደራዊ አካላት ስልጣንና ተግባራት የሚወስኑ እንዲሁም የዕለት ተዕለት ሥራቸውንና ማህበረሰቡን የሚያስተናግዱበትን ሂደት የሚመለከቱ ህጎችን የሚያካትት ህግ ነው።[10] ለምሳሌ በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር፣ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትን ህግ፤ የህግ አስከባሪ፣ የመንግስት ገቢ ሰብሳቢ አካላት፣ ማህበራት ወዘተ አሰራራቸዉን የሚደነግግ ህግ በዚህ ክፍል የሚካተቱ ናቸው።

- የወንጀል ህግ (Criminal law)

የወንጀል ህግ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ድርጊቶችንና የሚያስከትሉትን የቅጣት አይነቶችና መጠን በዝርዝር የሚያስቀምጥ የህግ ክፍል ነው። ሀገራችን ወንጀል ፈፃሚዎችን በህግ የመቅጣት የረጅም ጊዜ ልምድ ቢኖራትም ዘመናዊ የወንጀል ህግ ፍልስፍናዎችን በማካተት ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው በአፄ ሀይለሥላሴ ዘመነ መንግስት በ1949 የወጣዉ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ 1949 ነበር። ይህ

[8] 1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢፌድሪ ህግ መንግሰት አንቀፅ 9/1/

[9] Constitutionalism‹https://www.ajol.info.

[10] Jaap Hage & Bram Akkermans, Introduction to law, April 2014, page 37

ህግ 1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ የተተካ ሲሆን አሁን ላይ የተለያዩ ልዩ አዋጆች የወንጀል ተጠያቂነትን አካተው ይገኛሉ። ለአብነት የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1176/2012፣ የጦር መሳሪያን አሰተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2014፤ የጥላቻ ንግግርን እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1185/2012 እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 ሊጠቀሱ ይችላሉ።

#### 1.1.2.2 የግል ህግ (private law)

የግል ህግ ማለት የግለሰቦችን እርስ በእርስ በላቸዉ ግንኙነት የራሳቸው ጥቅም የሚመሩበት ነው። የግል ህግ (private law) በግለሰቦች ወይም ህጋዊ ሰውነት ባላቸው ድርጅቶች መካከል ያለውን ግላዊ ግንኙነት የሚገዛ የህግ ዘርፍ ነው። ይህ የህግ ዘርፍ በዋናነት የግለሰቦችን መብት ከጣልቃ ገብነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ህጋጋትን የሚያካትት ነው። ለአብነትም የውል ህግ፣ የንብረት ህግ እና ከውል ውጪ ሃላፊነትን የሚገዛው ህግ በዚህ ዘርፍ የሚጠቀሱ ናቸው።[11]

- የውል ህግ (Law 0f contract)

ዉል ማለት ንብረታቸዉን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም፤ ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት፣ ባላቸዉ ተወዳዳሪ ግንኙት ሁለት እና ከዚያ በላይ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነዉ[12]። ተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ የሚፈጥሩበት አስገዳጅ ህግ ማለት ነዉ[13]። ስለሆነም የውል ህግ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ለተለያየ ህጋዊ አላማ በስምምነት አንዱ ተስማሚ ወገን ለሌላዉ ወገን መብትና ግዴታ የሚገቡበት ይህ ግዴታና መብት የሚፈፀምበትን እና ተፈጽሞ ባይገኝ የሚያስከትለዉን ውጤቶችን የሚገዛ ህግ ነው።

- የንብረት ህግ (Property law)

የንብረት ህግ ንብረት የሚፈራበትን፤ የንብረት ባለቤትነትን፤ የንብረት አስተዳደር እና አጠቃቀምን ሁኔታ የሚገዛ የህግ ዘርፍ ነው።

---

[11] Ion harel, public and private law, Jul 14 2014, page 1041

[12] የኢትዮጵ ንጉሰ ነገስት የፍትሐብሔር ሕግ, 1952 አንቀጽ 1675

➢ ከውል ውጪ ሃላፊነት ህግ (Extracontractual liability)

ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ከውል ውጪ ሃላፊነት ውል በሌለበት ሁኔታ በተለያዩ ድርጊቶች መነሻነት ከህግ የሚመነጭን ሀላፊነት የሚመለከት ነው። ከውል ውጭ ሀላፊነት ምንጮች ሶስት ናቸው። እነርሱም፡-

ሀ/ በጥፋት ላይ የተመሰረተ ፣

ለ/ ያለጥፋት (strict liability) ፣

ሐ/ በሌሎች ሰዎች የሚፈፀም (vicarious liabilty) ሀላፊነቶች ናቸው።

ለምሳሌ አንድ ሰው በሚኖርበት ፎቅ ላይ ያስቀመጠው አበባ ማስቀመጫ ወድቆ ሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ ወይም የሚያሳድገው ውሻ ሌላ ሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ ለደረሰው ጉዳት የወደቀውን የአበባ ማስቀመጫ ያስቀመጠው ሰው ወይም የውሻው ባለቤት እንደየቅደም ተከተላቸው ጉዳት ለደረሰበት ሰው የፍትሐብሔር ሀላፊነት አለበት። በዚህ መልኩ የሚኖር ሀላፊነት ከውል ውጪ ሃላፊነት ይባላል ማለት ነው።

### 1.1.3 መሠረታዊ (substantive) እና ሥነ-ሥርዓታዊ ህግ (procedural law)

መሠረታዊ ህግ መብትን በዝርዝር የሚደነግግና ቅጣትን የሚጥል ሲሆን ሥነ ሥርዓታዊው ህግ ደግሞ ይህንን በመሰረታዊ ህግ የተደነገገውን መብት ወይም ግዴታ የሚፈጸምበት ሥርዓት የሚያስቀምጥ ነው። ለምሳሌ የንግድ ህግ፣ የወንጀል ህግ፣ የውል ህግ ወሰረታዊ ህጎች ናቸው። ሥነ-ሥርአታዊ ህግ በዋናነት የፍርድ ቤቶችን አካሄድ የሚመራበት እና መብቶችን የምናስከብርበት ህግ ነው። የፍትህብሄር ሥነ ሥርአት ህግ፤ የወንጀል ሥነ ሥርአት ህግ ፤ የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ህግ ይጠቀሳሉ። ስለሆነም መሰረታዊ ህግ ከሥነ ሥርዓታዊው ህግ ተነጥሎ መተገበር አይቻልም።

## 1.2 የወንጀልና የፍትህ ብሔር ህግ ልዩነት

የወንጀል ህግ የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን ከሚያስከትሉት የወንጀል ተጠያቂነት ጋር አጣምሮ የያዘ የህግ ክፍል ነው። ያለወንጀል ህግ ወንጀል ስለመኖሩ ማረጋገጥ አይቻልም። የወንጀል ድርጊት የሚባለው አንድን አታድርግ የተባለ ድርጊት ወይም ተግባር ማድረግ ወይም መፈፅም (commission) ወይም አድርግ የተባለን ድርጊት አለማድረግ ወይም አለመፈፀም (omission) ነው፡የወንጀል ህግ እስራትና እና ሌሎች የቅጣቶችን ዓይነቶችን የሚያስቀምጥ ድንጋጌ አለው። ወንጀል ተፈጸመ የሚባለዉ የህግ የድርጊት እና የሀሳብ ህፍል ጥሰት ሲኖር ነዉ።[14] በሌላ በኩል የፍትሐብሔር ህግ በግለሰብ ወይም በተለያዩ አካላት መካካል ያለን ገንዘብ ነክ ግንኙነቶች የሚገዛ የህግ ዘርፍ ሲሆን ከወንጀል ህግ በተለየ መልኩ የገንዘብ ሀላፊነት ከማስከተል ውጪ እስራትን የመሰሉ ቅጣቶችን የሚያስከትል ህግ አይደለም።በፍትሐብሔር ህግ ሃላፊነትን በስምምነት፤ በእርቅ ማስቀረት ሲቻል

---

[14] በ1996 ዓ.ም የወጣዉ የኢ.ፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23

**በወንጀል ጉዳይ በግል አቤቱታ ከሚቀርቡ ወንጀሎች ዉጭ ወንጀልነቱን በስምምነት ማስቀረት አይቻልም።**

# የወንጀል ህግ እና የፍትሀ ብሄር ህግ ንፅፅር

| የወንጀል ህግ | የፍትሀ ብሄር ህግ |
| --- | --- |
| **ትርጉም፡**-ህብረተሰቡን ከጉዳት ለመጠበቅ ተብሎ የሚወጣ፣ወንጀሎችን እና ቅጣታቸውን የሚዘረዝር ህግ ነው፡፡ | በግለሰቦች መካከል የሚፈጠሩ የግል መብት ጉዳዮችን የሚያስተዳድር የህግ አካል ነው፡፡ |
| **አላማ፡**- ወንጀለኞችን በመቅጣት እና በማረም የህብረተሰቡን ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ ፡፡ | በግለሰቦች መካከል ባለግንኙነት በተፈጠረ አለመግባባት የደረሰን ጉዳት መካስ ወይም ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበሩበት መመለስ፡፡ |
| **ክስ አቅራቢ፡**- መንግስት | ግለሰቦች |
| **ማስረጃ፡**- ከጥርጣሬ የፀዳ (beyond reasonable doubt) | የተሻለ ያስረዳ (preponderance of evdence) |
| **የማስረዳት ሸክም፡**-ከሳሽ (ዐቃቤ ህግ)ተከሳሽ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር (presumed innocent) መብት አለው፡፡ | መብት አለኝ (vested interest) የሚል አካል ሲሆን ድርጊቱ አልተፈፀመም የሚል ወገን ካለ የማስረዳት ሸክሙ ወደሱ ይዞራል፡፡ |
| **ውሳኔ፡**- ጥፋተኛ መባል ወይም ነፃ መባል (convicted or acquitted) | ሐላፊነት አለበት ወይም የለበትም (liable or not liable) |
| **የቅጣት አይነት፡**- በገንዘብ መቀጮ፣እስራት፣ሞት | ለደረሰ ጉዳት የገንዘብ ካሳ ለተጎጂው መክፈል(compensation)፣ድርጊት ማገድ(injunction )፣እንዲፈፀም ማስገደድ(forced enforcement) |
| **ምሳሌ፡**- ስርቆት፣ግድያ፣ማታለል፣ስም ማጥፋት፣ስድብ፣አካል ጉዳት | ውል፣ፍቺ፣ቀለብ፣አሰሪና ሰራተኛ |

## 1.3 የህጎች ተዋረድ (hierarchy of laws)

የህጎች ተዋረድ (hierarchy of laws) የህጎች የበላይነት ደረጃን ወይም የትኛው ህግ ከየትኛው ህግ የበላይ ህግ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ይህም በህጎች መካከል የሚኖርን ተዛማጅ ተገዢነት እያንዳንዳቸው ከላይ ወደ ሚቀጥለው ያላቸውን የሀይል ደረጃ እና ስልጣን የሚያሳይ ነው። የህጎች ተዋረድ የኃይል እና የሥልጣን መጠን ከተለዋዋጭ የኃይል ግንኙነት መዋቅር ጋር ለመግለፅ ያገለግላል። ህጎች ሀይል ወይም ስልጣን የሚያገኙት ህጎቹን የሚያወጣቸው አካል ማለትም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወ.ዘ.ተ ካላቸው የስልጣን ደረጃ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም የበላይ እና የበታች አይነት የመገዛት ሰንሰለት ግንኙነት በህጎች መካከል አለ ማለት ነው።

እንዲሁም የህጎች ተዋረድ የአንድ ሀገር ህጎች ባላቸው የአስፈላጊነት ቅደም ተከተል መሰረት የሚኖራቸውን የተለያዩ ደረጃዎች የሚያመለክት ስርዓት ሲሆን ህጎቹን የሚያወጧቸው አካላት የስልጣን ደረጃም ነፀብራቅ ነው። በመሆኑም በህጎች የተዋረድ ደረጃ እና በህግ አውጪ አካላት መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዳለ መገንዘብ ይቻላል።

ኢትየጵያ የፌደራል ስርዓት የምትከተል ሀገር በመሆኗ ክልሎች በራሳቸው ጉዳይ ህግን መሰረት በማድረግ መወሰን እንደሚችሉ በህገ መንግስቱ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። በህገ መንግስቱ አንቀፅ 52/1 ስር እንደተደነገገው በህገ መንግስቱ ለፌደራሉ መንግስት በተለይ ወይም ለፌደራሉ መንግስትና ለክልሎች በጋራ በግልፅ ያልተሰጠ ስልጣን የክልል ስልጣን እንደሆነ ያስቀምጣል። በዚሁ መሰረት ክልሎች የክልል ህገ መንግስትንና ሌሎች ህጎችን የማውጣት እና የማስፈፀም ስልጣን አላቸው ።በሌላ በኩል ሕገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ህግ እንደሆነ እና ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ ድርጊት እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9/1 እና 2 ስር ተደንግጎ ይገኛል። ይህ ማለት በሀገሪቱ ውስጥ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ህገ መንግስቱ (constitution) ነው ማለት ነው። በመሆኑም የፌደራል ህገ መንግስት በፌደራልም ይሁን በክልል ደረጃ ያሉ ህጎች የክልል ህገ መንግስትን ጨምሮ የሁሉ የበላይ ህግ ነው። በመቀጠል የአገሪቱ የበላይ የህግ አውጪ አካል ማለትም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያወጣቸው ህጎች አዋጆች (proclamations) ይከተላሉ። የአለም አቀፍ ስምምነቶችን (international agreements) የህግ ተዋረድ በተመለከተ ወጥ የሆነ መግባባት ባይኖርም በህገ መንግስቱ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የአገረቱ ህግ አካል ይሆናሉ ስለሚል እንዲሁም ስምምነቶቹ የሚፀድቁት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሆነ ከአዋጅ ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ይቀመጣሉ የሚል ሀሳብ አለ።

በህግ ተዋረድ በመቀጠል የሚመጡት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡት ደንቦች (regulations)፣ በመቀጠል በሚኒስትር መስሪያ ቤቶችና በተለያዩ አስተዳደር መ/ቤት የሚወጡት መመሪያዎች

(directives) ናቸው። በአጠቃላይ የህጎች ተዋረድ ህጎቹን ከሚያወጧቸው አካላት ጋር እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል።

| ህጎች | legislations | ህጎቹን የሚያወጡ አካላት |
|---|---|---|
| ህግ መንግስት (የሀገሪቱ የበላይ ህግ) | Constitution | የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ህግ አውጪ) (parliament) |
| አዋጆች/አለም አቀፍ ስምምነቶች | Proclamation | የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት(ህግ አውጪ) (parliament) |
| ደንቦች | Regulation | የሚኒሰትሮች ምክር ቤት(የህግ አስፈፃሚ አካላት (Council of Ministers) |
| መመሪያዎች | Directive | ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ወይም የስራ ክፍሎች (ministry or a department within a ministry. |

በሌላ በኩል በተመሳሳይ ተዋረድ (hierarchy) ላይ ባሉ ህጎች መካከል መቃረን ሲኖር ተፈፃሚ የሚሆነው በጊዜ ዘግይቶ የወጣው ህግ ነው (latest prevails)። ይህ ማለት ዘግይቶ የወጣው ቀድሞ ከወጣው ይልቅ ተፈፃሚ ይሆናል ማለት ነው። ነገር ግን ለቅጣት ዓላማ ሲሆን ተከሳሹን ይበልጥ ቅጣት ሊያቀልለት በሚችለዉ የተሻለዉን ህግ ተፈጻሚ መሆን እንደሚገባዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 6 መርህ በግልጽ ደንግጎ እናገኛለን[15]።በሌላ በኩል ልዩ ህግ (special law) ከጠቅላላ ህግ (general law) ይልቅ ቅድሚያ ተቀባይነት ይኖረዋል (special law prevails over general law)።

## ክፍል ሁለት
## ወንጀል

[15] 1996 ዓ.ም የወጣዉ የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 6

## 2.1 የወንጀል ምንነት

ወንጀል ፡-ማለት አንድን አታድርግ የተባለ ድርጊት ማድረግ (መፈጸም) ወይም አድርግ የተባለ ድርጊት አለማድረግ (አለመፈፀም)። በወንጀል ህግ ህገ ወጥነቱ እና አስቀጭነቱ የተደነገገ ተግባር ወንጀል ነዉ።

## 2.2 የወንጀል ህጉ አላማ እና ግብ

የወንጀል ህጉ አላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፣ የህዝቦቹን፣ የነዋሪዎችን፣ ሰላም፣ ደህንነት፣ ስርአት፣ መብት እና ጥቅም መጠበቅ እና ማረጋገጥ እንደሆነ የወንጀል ህጉ መገቢያ ተቀምጧል።[16] የወንጀል ህግ አላማ የህብረተሰቡን ሰላም እና ደህንነት ማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን ወንጀል እንዳይኖር ከስሩ በመከላከልም ጭምር ነው፡   ይህም አስቀድሞ ስለወንጀል ግንዛቤ በመፍጠር እና ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሲሆን ነገር ግን ከመከላከል ባለፈ ወንጀል ከተፈፀመ ፈፃሚውን በመቅጣት ወንጀለኛውን ከሌላ ወንጀል ድርጊት እንዲቆጠብ በማድረግ እና ህብረተሰቡን ከወንጀለኛው እንዲማር በማድረግ ሌላ ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈፀም ማድረግ ነው። ስለዚህ ወንጀል አድራጊ የሚቀጣው ሌላ ወንጀል እንዳይፈጸም ብቻ ሳይሆን የማረም እና የማስተማር አላማን ይዞ። በሌላ በኩል የወንጀል ግብና አላማ ለማሳካት የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊስ  ሁነኛ ማስፍጸሚያ መሳሪያ ነዉ። ይህ ፖሊሲ በአንድ በኩል ለወንጀል መነሻ የሚሆኑ ምክንያቶችን በመቀነስ ወይም በማጥፋት፣ በሌላ በኩል የተፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮችን በመደበኛ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር እና ከዚያ ውጭ ባለ ሌሎች አማራጭ መንገዶች ተገቢና ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት ጊዜው የሚጠይቀውንና ደረጃውን የጠበቀ የኅብረተሰቡን ፍላጎት የሚያረካ በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆች ላይ የተመሠረተና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፍትሕ ሥርዓት ለመገንባት ነዉ። [17]

## 2.3 የወንጀል ተጠያቂነት

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ቁጥር 23 (2) መሰረት ወንጀል በሶስት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ሊፈጸም ይችላል። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች በአንድነት ካልተሟሉ ወንጀል ተፈፀመ ሊባል አይችልም። እነሱም፡-

1. **ህጋዊ ፍሬ ነገር (legal element)**
2. ግዙፋዊ ፍሬ ነገር (material element)
3. የሀሳብ ክፍል (ሞራላዊ) (moral element) ፍሬነገር ናቸው።

### 2.3.1 ህጋዊ ፍሬነገር (legal element)

---

[16] በ1996 ዓ.ም የወጣዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 1

[17] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ, ፍትሕ ሚኒስቴር, የካቲት 25/2003 ዓ.ም

አንድን ድርጊት ወንጀል ነዉ ለማለት አስቀጭነቱ እና ህገ ወጥነቱ በህግ የተደነገገ መሆን እንዳለበት (የህጋዊነት መርህ አንቀጽ 2/2/ ) እንዲሁም በአንቀጽ 23 (1) ስር ተደንግጎ እናገኘዋለን። ፍርድ ቤት ህገ ወጥነቱ በህግ ያልተደነገገን ድርጊት እንደወንጀል ሊቆጥረው እናቅጣት ሊወስንበት አይችልም። ለምሳሌ ስርቆት ወንጀል መሆኑ በህግ ካልተደነነገ በቀር ስርቆት የፈጸመ ሰዉ ወንጀለኛ አይሆንም። በማህበረሰብ እይታ በህግ ደረጃ በወንጀልነት ያልተፈረጁ ግን እንደህጢያት ወይም ውግዝ ከመ "አሪዮስ" ተደርገው የተቆጠሩ ድርጊቶች ሁሉ በወንጀል ህጉ በወንጀልነት ላይካተቱ ይችላሉ። ሕጋዊ ፍሬ ነገር በህጋዊነት መርህ ስር በህግ ፊት የእኩልነት መርህ፣ የወንጀል ህግ ተመልሶ ወደኋላ የማይሰራ መሆኑን፤ ወንጀል በይመሳሰላል( analogy) ሊያስቀጣ እንደማይችል፤የተለየ የተሻለ ህግ ለተከሳሽ ቅጣት የሚያቀል ሆኖ ሲገኝ ይህ ተፈጻሚ ሊሆን እንደሚገባዉ እና ስለይርጋ ወዘተ አካቶ ይዟል።[18] ከህጋዊ ፍሬነገሮች መገለጫች አንዱ የወንጀል የይርጋ ግዜ ነው። በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ.217 መሰረት ለእያንዳንዱ ወንጀል ውሳኔ ለማሰጠት እና ቅጣት ለመስጠት ማመልከቻ የሚቀርብበት እና ክስ የሚመሰረትበት እንደወንጀሉ አይነት እና ክብደት የራሱ የሆነ የግዜ ገደብ እንዳለው አስቀምጧል አለው። በዚህ ግዜ ውስጥ ክስ ካልቀረበ በወንጀል ህጉ ግዜ ገደብ መሰረት ክስ አይቀርብበትም።

በ1996 አ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 217 መሰረት ወንጀለኛን በህገ ለመጠየቅ ወይም ክስ ለመመስረት የግዜ ገደቦች ተቀምጠዋል እነዚህም፡-

- ለሞት ቅጣት ወይም ለእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል የይርጋ የግዜ ሀያ አምስት (25) አመት ሲሆን በዚህ ጊዜ ካልቀረበ ክስ ማቅረብ አይቻልም።
- ከአስር አመት በላይ እና ከሀያ አምስት አመት ያልበለጠ ፅኑ እስራት ለሚያስቀጣ ወንጀል በ20 ሀያ አመት ግዜ ውስጥ ካልቀረበ ክስ መመስረት ግዜ ይገድበዋል።
- አምስት አመት ያልበለጠ ግን አስር አመት ያላለፈ ለሚያስቀጣ ወንጀል ደግሞ የአስራ አምስት አመት የይርጋ ግዜ ተቀምጦለታል።
- ከአምስት አመት ለማይበልጥ ቅጣት ለሚያስቀጣ ወንጀል በአስር አመት ገደብ ይገደባል።
- ከአንድ አመት በላይ ለሚያቀጣ ወንጀል ገደቡ አምስት አመት፤
- ከአንድ አመት በለይ ለሚያስቀጣ ወንጀል በሶስት አመት ።
- በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ወንጀሎች ላይ የግዜ ገደቡ እስከ ሁለት አመት አቤቱታ መቅረብ አለበት።[19]

[18] በ1996 ዓ.ም የወጣዉን የወንጀል ህግ አንቀጽ 2፣4፣ 5፣6፣8

[19] በ1996 አ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 217

የቅጣት ወይም ሌሎች እርምጃዎችን በፍርድ ቤት አቅርቦ ለማስወሰን በወንጀል ህጉ ግዜ ገደብ የተቀመጠ ሲሆን እነርሱም፡-

- ለሞት ቅጣት ወይም የእድሜ ልክ እስራት ግዜ ገደቡ ሰላሳ (30) አመት ነው።
- ከአስር አመት ፅኑ እስራት በላይ ለሆነ ቅጣት በሀያ አመት ይገደባል።
- ከአንድ አመት በላይ ነፃነትን የሚያሳጡ ወንጀሎች ቅጣት ላይ በአስር አመት ይገደባል።
- አምስት አመት ለሌች ቅጣት መጠኖች ናቸው።

የይርጋ ዘመን የሚቆጠረዉ ወንጀሉ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ባሉት ዓመታት ነዉ። ነገር ግን ወንጀሉ እየተደጋገመ የተፈጸመ ከሆነ የመጨረሻዉ ወንጀል ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል። በተመሳሳይ የወንጀሉ ድርጊት ለረጅም ጊዜ የቆየ ከሆነ የይርጋ ጊዜዉ የሚጀምረዉ ወንጀሉ ከአቆመበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ። [20] ይህ እንዲህ እንዳለ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች በኢትየጵያ ህጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፣ የሰው ዘር ማጥፋት፣ ያለፍርድ የቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን መሰወር ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶች በፈፀሙ ሰዎች ላይ በይርጋ አይታገድም። በህግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግስት አካል ውሳኔዎች በይቅርታ እና በምህረት የማይታለፉ ወንጀሎች መሆናቸውን ህገ መንግስቱ ይደነግጋል።[21]

### 2.3.2 ሞራላዊ ፍሬ (የሀሳብ ክፍል)

የወንጀል ተጠያቂነት ለማምጣት የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ያለው መሆን (የሀሳብ ክፍል) ሊኖረው ይገባል። ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ያለው ወንጀል ፈፃሚ ይቀጣል ነገር ግን ባልታሰበ ሁኔታ በድንገት በአደጋ የተፈጠረ ነገር የሚያስቀጣ አይደለም። ወንጀል የማድረግ ሀሳብን በዋነኛነት የምንረዳው ወንጅሉ በተፈፀመ ሰአት ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት እና ከወንጀል ፈፃሚው ሁኔታ ተነስተን በማየት ነው። ወንጀል ሆን ተብሎ የሚፈጸም ሲሆን ይሕም ቀጥተኛ Direct intention ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ /Indirect intention/ መልኩ ሊፈፀም ሲችል እንዲሁም በቸልተኝነት ከሆነ ደግሞ በታሰበ (advertent ngligent እና ባልታሰበ /In advertent negligent/ በሆነ በመልኩ ሊፈፀም ይችላል። ዝርዝሩን እንደሚከተለዉ ይቀርባል።

1. ሆን ተብሎ የሚፈፀም ወንጀል ተጠያቂነት (Intention)

አንድ የወንጀል አድራጊ አስቦ ወይም ሆን ብሎ የሚፈፅማቸው ወንጀሎች በወንጀል ህጉ መሰረት በሁለት ይከፈላሉ። ይህም ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ሆን ተብሎ የሚፈፀም ወንጀል እንዲሁም አፈፃፀሙ

---

[20] በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 219

[21] በ1987 ዓ.ም የወጣዉ የወንጀል ህግ ህግ አንቀፅ 28

ወንጀል ድርጊቱ ሊያስከትለው የሚችለውን ውጤት ሙሉ በሙሉ በማወቅ የሚፈጸም ነዉ። ሆን ተብሎ የሚፈፀም ወንጀሎች ሊያደርሱና ሊያስከትሉት እንደሚችል በእርግጠኛነት የሚፈጸም ነዉ። ወንጀል ፈጻሚዉ ወንጀል ዉጤት እንደያመጣለት ፍላጎት አለው። ለምሳሌ አንድ ሰዉ አስቦ፤ ተዘጋጅቶ፤ ቦታ መርጦ፤ መሰሪያ አቀባብሎ ወደ ሟች ግንባር አነጣጥሮ ቢተኩስ ለመግደል አላማ እንዳለዉ እና ሟች እንዲሞት ፍላጎት ያለዉ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ሌላዉ የሐሳብ ክፍል ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሆን ተብሎ የሚፈፀም ወንጀል ነዉ።አፈፃፀሙም ሲታይ የወንጀል ድርጊቱ ሊያስከትለው የሚችለውን ውጤት ሙሉ በሙሉ እውቅና ያለው እና የሆነው ይሁን በማለት የወንጀል ድርጊቱን እስከመጨሻ የገፋበት እንደሆነ ነው። በቀጥተኛ ባልሆነ ሆን ተብሎ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ሊደርስ እና ሊያስቀጣ የሚችል እንደሚከሰት እርግጠኛነት ያለው ነው። ወንጀሉም እንደሚሆን ቢቀበልም እንዲፈጠር ግን ፍላጎት የለውም። ለምሳሌ አንድ አሽከርካሪ በአንድ ሰዓት ዉስጥ አዳማ ለመድረስ በፍተኛ ፍጥነት እያሽከረከረ ሲነዳ በፍትነቱ ምክንያት አደጋ ሊደርስ እንደሚችል እያወቀ ነገር ግን ቢደርስም ዉጤቱን በመቀብል ሰዉ ቢገጭ ወንጀል ይሆንበታል ማለት ነዉ። በአንዳንድ ወንጀሎች ለምሳሌ እንደሙስና ባሉ ወንጀሎች የሃሳብ ክፍል ማረጋገጥ አይጠበቅም። ግዝፋዊ እና የህግ ጥሰት ካለ የሙስና ወንጀሉ የተፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት እንደሆነ ይገመታል። በሙስና አዋጁ አንቀጽ 3 ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የሙስና ወንጀሎቹ የተፈፀሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ሌላውን ሰው ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከተው ግዙፋዊ ፍሬ ነገር መፈጸሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል።[22]

2. በቸልተኝነት (በግዴለሽነት) /Negligent/ የሚፈፀም ወንጀል ተጠያቂነት

በግድየለሽነት የሚመጡ የወንጀል ተጠያቂነቶች ወንጀል አድራጊው ወንጀሉ ሊከሰት እንደሚችል ባለመገመት ወይም ሊሆን እንደሚችል መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ባለመገመት እና ባለማመዛዘን ወይም በመተው ሊፈፀም ይችላል። የቸልተኝነት ወንጀል በወንጀል አድራጊዉ የግል ህይወት፤ እድሜ፤ የኑሮዉ ሁኔታ፤ የትምህርት ደረጃዉ፤ ማህብራዊ ኑሮዉ ሲመዘን በጉዳዩ ሁኔታዎች ሊደረጉ ይገባል ተብሎ በአግባቡ የሚጠበቁበትን ጥንቃቄዎችን ያላደረገ ከሆነ ነዉ።[23] ለምሳሌ አንድ አሽከርካሪ የመኪናዉን ፍሬን ወይም መሪ ሳያረጋግጥ መኪናዉን አስነስቶ ሲነዳ መሪ አስቸግሮት

---

[22] የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3

[23] 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 59

መኪናዉ ተገብጦ ሰዉ ቢሞት ወይም ሰዉ ቢጎዳ በቸልተኝነት ወንጀል ይጠይቃል። በዚህ ጉዳይ አሽከርካሪዉ ማድረግ የሚጠበቅበት ከማሽከርከሩ በፊት የመኪናዉን ሙሉ ይዘትና ደህንነቱን መፈተሽ አለበት። ተጨማሪ ምሳሌ በቸልተኝነት ወንጀል ዉስጥ ወንጀል እንደሚፈጽም እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው ባለመገመት ሊፈጸም ይችላል። መኪናዉን ሲያሽከረክር የመሪ ችግር እያለበት ነገር ግን በመሪ እቆጣጠራለሁ በማለት ሲነዳ ሰዉ ቢጎዳ በዚህ ወንጀል ይጠየቃል።

### 2.3.3 ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች

ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች ሌላው ለወንጀል ተጠያቂነት መሟላት ያለበት አንዱ ቅድመ ሁኔታ ነው። በመነሻነት በህግ እንደሚያስጠይቅ የተደነገገ ወንጀል እና ወንጀሉን የማድረግ ሀሳብ ኖሮ ግዙፋዊ ፍሬነገሮች ካልተሟሉ ወንጀል ተፈፅሟል ሊባል እና ቅጣት ሊወሰን አይችልም። ወንጀሉ በድርጊት የተፈፀመ መሆን አለበት። ግዙፋዊ ፍሬነገር በተግባር መፈጸም ብቻ ሳይሆን በዝግጅት እና በሙከራ ደረጃ ለተፈፀሙ ወንጀሎችም ልንገልፀው እንችላለን። በግዙፋዊ ፍሬነገሮች ሌላው ማሳያ የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት መኖር አስፈላጊ ነገር ነው። ምክንያት እና ውጤት አንድን ድርጊት በመፈፀሙ ምክንያት የሚያስከትል ውጤት መኖር ጋር የሚያስረዳ ነዉ። ግዙፋዊ ፍሬነገሮች በተፈፀመው የወንጀል ድርጊት አድርግ የተባለውን አለማድረግ ወይም አታድርግ የተባለውን ማድረግን ይጨምራል። ለምሳሌ አንድ ሰዉ በአካል ላይ ጉዳት /ሰዉን ለመደብደብ/ የግድ በቁሳዊ ነገሮች፤ ድንጋይ መጠቀም፤ በቦክስ መምታት ወይም ድንጋይ ላይ በመጣል ወዘተ መፈጸም አለበት። ስለሆነም ሰዉን ለመጉዳት የግድ ድርጊት መኖር አለበት። ነገር ግን የተደረገዉ ወንጀልና የተደረሰዉ ዉጤት ተመሳሳይ መሆን አለበት።[24]

## 2.3 የወንጀል ህግ መርሆች

የወንጀል ህግ መርሆች በወንጀል ህግ መጀመሪያ ምእራፍ ውስጥ ያሉ በወንጀል ህጉ ለጠቅላላ እና ልዩ ህጎች አፈጻጸም መሰረት የሚሆኑ ድንጋጌዎች ናቸው። እንዚህ መርሆች ፍርድ ቤቶች ህግ ለመተርጎምም ሆነ አስፈፃሚ አካላት ህግ በማስፈፀም ሂደት ላይ ለሚያጋጠማቸዉ ተግዳሮቶች እንደ መርሆ የሚጠቀሟቸዉ ናቸዉ። እነሱም

- የህጋዊነት መርህ (The Principle of Legality)
- የእኩልነት መርህ (The Principle of Equality)
- .የግላዊነት መርህ (The Principle of Individual Autonomy)

1. የህጋዊነት መርህ

የህጋዊነት መርህ ህግ በሌለበት የሚያስቀጣ ወንጀል የለም የሚል ፅንሰ ሀሳብ ያለው ነው። የወንጀል ክስ ለማቅርብ እና ቅጣት ለመጣል የህጋዊነት መርህ መኖር አለበት። በህግ ህገወጥነቱ እና አስቀጭነቱ

---

[24] 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 24

ያልተደነገገ ድርጊት በስተቀር ሰው ለፈፀመው ድርጊት ሊቀጣ አይችልም። ስለሆነም በ1996 አ.ም የወጣው የወንጀል ህግ ስለህጋዊነት መርህ ሲያነሳ በሶስት እይታ ያቀምጠዋል።

- በወንጀል ህግ አንቀፅ 2(2 እና 3) መሰረት ወንጀልነቱ በግልፅ ያልተቀመጠን ድርጊት ወይም ግድፈት ፍርድ ቤቱ እንደ ወንጀል ሊቆጥረው አይችልም እንዲሁም ወንጀልን ከሌሎች ወንጀሎች ጋር ይመስላል በማለት ሊተረጎም አይችልም። በወንጀል ህጉ እንደተደነገገው አገላላፅ ለተቀመጠው ወንጀል ብቻ የምንጠቀመው ነው። ነገር ግን እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው የወንጀል ህጉ አሻሚ በሚሆንበት ወቅት የወንጀል ህጉን መንፈስ እና ሊደርስበት ካሰበው አላማ አንፃር በመነሳት ፍርድ ቤት ሊተረጎም እንደሚገባም ያስቀምጣል። ለምሳሌ ሰዉ መጥላት መልከም ባይሆንም ነገር ግን ወንጀል ነዉ ተብሎ በህግ አልተቀመጠም። ነገር ግን የጥላቻ ንግግር ማድረግ ወንጀል መሆኑ በህግ ተቀምጧል። ስለሆነም ወንጀል ነዉ ተብሎ ያልተደነገገ ድርጊት ወንጀል አይሆንም።
- ፍርድ ቤቱ በህግ ከተደነገጉት በቀር ሌሎች ቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎችን መወሰን እንደማይችል ደንግጓል።
- በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 23 እንዲሁም በወ/ህግ/አንቀፅ 2(5) አንድ ወንጀለኛ በወንጀል ህግ ተከሶ ከተቀጣ ወይም ነፃ ከተባለ በኃላ በዚሁ ጉዳይ ድጋሜ አይከሰስም፣አይቀጣም። ለምሳሌ፡ - አበበ ከበደን በዱላ ማጅራቱን መቶት ተከሶ ፍርድ ቤት ቀርቦ ዐቃቤ ህግ በበቂ ሁኔታ ባለማስረዳቱ ምክንያት በነጻ ተሳነበተ። በዚሁ ጉዳይ ነፃ ስለወጣ በድጋሚ አበበ ላይ ክስ አይቀርብበትም ማለት ነው። ስለሆነም የግለሰቡን ድጋሜ ያለመከሰስ ወይም ያለመቀጣት ዜጎች በፍትህ ሥራዓቱ ላይ አመኔታ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል።
- በህግ መንግስቱ በአንቀጽ 22 እና በወ/ህግ/ አንቀጽ 5 መሰረት የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ ተመላክተዋል። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 "ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣራ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም" ይላል። ይህ ድንጋጌ ሁለት ዓይነት መሠረታዊ ውጤቶችን ያስከትላል። እነዚህም አንድ ድርጊት በሚፈፀምበት ወቅት ድርጊቱ በጊዜው የማያስቀጣ ከነበረ ይኸው አስቀድሞ የተፈፀመው ድርጊት ከጊዜ በኋላ በወጣ ሕግ ወንጀል ነው ሊባል አይችልም። በተጨማሪም ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ወንጀል ቢሆንም እንኳ ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በሚፈፀምበት ወቅት ተፈጻሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በደነገገው የቅጣት ጣራ መሠረት መሆን አለበት። ስለዚህም ከድርጊቱ በኋላ የወጣ ሕግ የቅጣት ጣራውን ከፍ ቢያደርገው ይህ ቅጣት ሕጉ ከመታወጁ በፊት ለተፈፀመ ወንጀል ተፈጻሚ መሆን የለበትም።

በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ለአንድ ወንጀል በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው የቅጣት ወለልና ጣራ ውጭ ቅጣት ሊጣል አይችልም። እንዲሁም ለአንድ የወንጀል ድርጊት ሊጣል የሚችለው ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ከተፈፀመበት ወቅት አስቀድሞ በተደነገገ የወንጀል ድንጋጌ በተመለከተው መሠረት ነው። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 22 ድንጋጌ መሠረት አስቀድሞ ወንጀል መሆኑ ባልተደነገገ ድርጊት ማንኛውም ሰው ሊቀጣ አይችልም፤ እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ከነበረው የቅጣት ጣራ በላይ ሊቀጣ አይችልም። ይህ ሕገ መንግሥታዊ መርሕ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5 ላይም ተካትቶ እናገኘዋለን። ከዚህም አንጻር የአዲሱ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ ሕጉ ሥራ ላይ ከዋለበት ከግንቦት 01 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ነው ። በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ድርጊት በአዲሱ የወንጀል ሕግ ወንጀል ነው ቢባልም በቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ግን በወንጀልነት ያልተፈረጀ ድርጊት የነበረ ከሆነ ድርጊቱ የተፈፀመው በቀድሞ ህግ ከሆነ የሚጠየቀዉ በዚሁ ህግ ነዉ። በሌላ አነጋገር ድርጊቱ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ወንጀል ስለመሆኑ የተደነገገ ቢሆንም ነገር ግን ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ተፈጻሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በተደነገገው የቅጣት ጣራ እና የቅጣት ወለል መሰረት መሆን አለበት።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ማለትም አንድ የወንጀል ሕግ ከመውጣቱ በፊት ለተፈፀመ ድርጊት ተፈጻሚነት የለውም የሚለው አጠቃላይ መርሕ ቢኖርም በተለዩ በሕግ በተፈቀዱ ልዩ ሁኔታዎች (exceptions) ግን የወንጀል ሕጉ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ይችላል። እነርሱም፡-አዲሱ የወንጀል ሕግ ከቀድሞው ሕግ ይልቅ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቃልለት በሚሆንበት ጊዜ ተከሳሹ ወንጀሉን በፈፀመበት ወቅት ሥራ ላይ ያልነበረ ሕግ ቢሆንም ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

አዲሱ የወንጀል ሕግ ከወጣ በኋላ በቀድሞው ሕግ መሰረት ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰኑት የቀድሞውን ሕግ መሰረት በማድረግ ሳይሆን በአዲሱ ሕግ መሰረት ነው። የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረነት ጊዜ ቢሆንም ውሳኔው የተሰጠው አዲሱ የወንጀል ሕግ ወጥቶ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰኑት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ይሆናል ማለት ነው።

የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ወቅት ለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ክስ የማቅረብና እና ቅጣት ቀሪ የመሆን የይርጋ ጊዜ የሚታሰበው (የሚሰላው) አዲሱ የወንጀል ሕግ በሚደነግገው መሠረት ነው። በሌላ በኩል በቀድሞው ሕግ መሠረት የተሰጡ ፍርዶች የሚፈፀሙት በአዲሱ የወንጀል ሕግ መሠረት ነው። የቀድሞው ሕግ ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ለተፈፀመ ወንጀል የሚሰጥ የገደብ ዉሳኔ እና በአመክሮ ከእስር የመፍታት ውሳኔ የሚወሰነው አዲሱ የወንጀል ሕግ ያስቀመጣቸውን

መመዘኛዎች በመጠቀም ነው። በቀድሞው ሕግ መሠረት የተፈረደባቸው ሰዎች የወንጀል ሪከርዳቸው የሚሰረዘውና የሚሰየሙት አዲሱ የወንጀል ሕግ ያስቀመጣቸውን መመዘኛዎች በመጠቀም ነው።[25]

2. የእኩልነት መርህ

ሰው ሁሉ በህግ ፊት እኩል ነው። በህግ ፊት እኩል መሆን እና እኩል የህግ ጥበቃ የማግኘት መብት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው። በህግ ፊት እኩል መሆን ማለት በአንድ በተለየ ህግ ጉዳይ የተወሰነን መብትና ጥቅምን ያለአንዳች ልዩነት በሁሉም ፍትህ አስተዳደር እኩል ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ነው። በወንጀል ህግ አንቀፅ 4 መሰረት የወንጀል ህግ የሰውን፣ የሰውን የማህበራዊ የኑሮ ደረጃ፣ የዘርን፣ የብሔርን፣ የብሔረሰብን፣ የቀለምን፣ የፆታን፣2የቋንቋን፣ የሀይማኖትን፣ የፖለቲካን ወይም የሌላ አስተሳሰብን፣ የሀብትን፣ የትውልድን፣ ወይም የሌላ አቋምን ልዩነት ሳይደረግ በሁሉም ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ ይሆናል። በተመሳሳይ በኢ..ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 25 ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል እንደሆነ እና ህጉ እኩል ጥበቃ እንደሚያደርግለት አስቀምጧል። በዚህ መሰረት ላይ ለመልካም የሆኑ ልዩ ሁኔታዎች በወንጀል አድራጊው ላይ ልዩንት ሊፈጠር እንደሚችል የወንጀል ህጉ ተካቷል። ለወንጀል ህግ ኣላማና ግብ በወንጀል አድራጊዎች መካከል ልዩነት ሊደረግ። ስለሆነም መብቶች ወይም ነጻነቶች ተጠሰዉ ሲገኙ እንደ ወንጀሉ ክብደትና ቀላልነት የተከሳሽ እድሜ እንዲሁም አፈፃፀሙ ሁኔታ ታይቶ በክስ ዉሳኔ ወይም በቅጣት ላይ ልዩነት ሊደረግ ይችላል ። ነገር ግን በእኩልነት ፍትህ ማግኘት መብትን የሚጥስ አይደለም። [26]

3. የግላዊነት መርህ (The Principle of Individual Autonomy) ሁሉም ሰው ለሚያደርገው ድርጊት የራሱ የሆነ ሀላፊነት እንዳለበት የሚያሣይ መርህ ነው። ሰው የሚያደርገውን አመዛዝኖ የሚለይ እንደመሆኑ መጠን መልካምም ሆነ ክፉን ነገር የማድረግ ፍቃድ አለው።

የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ያላቸው የህግ አካላት ይለያያሉ። በኢፌዲሪ ህገ መንግስት እንደተደነገገው ማንም ሰው ፍትህ የማግኘት መብት[27]ያለው ሲሆን ይህንም ፍትህ ከመደበኛ (የፍትህ አካላት) እንዲሁም በባህል ወይም በሀይማኖት[28] መሰረት በተቋቋሙ አማራጭ የዳኝነት አካለት ማግኘት እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል እና የፍትሐብሔር ጉዳዮች እንደመለያየታቸው መጠን ጉዳዮቹን ተቀብለው የሚያዩት የመንግስት የህግ አካላት እና ጉዳዮቹ የሚስተናገዱበት ሁኔታም የተለያየ ነው።

---

[25] ህግ መንግስቱ በአንቀጽ 22 እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 5

[26] ህግ መንግስቱ በአንቀጽ 25 እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 4

[27] 1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢ.ፌድሪ ህግ መንግሰት አንቀፅ 37

[28] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 34/5 እና 78/5

## 2.4 የወንጀል ጉዳዮች ጥቆማና የፍትህ ሂደቱ የሚታዩበት አግባብ

የወንጀል ጉዳይ የሚታየው በወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ሲሆን የወንጀል ፍትህ ስርዓት (criminal justice system) በፖሊስ ደረጃ የሚወጣና አፈጻጸሙም በዚያ የሚለካ ይሆናል። የወንጀል ሕግን ማስፈፀም የወንጀል መከላከል አንድ ገፅታ ሲሆን ሂደቱ ሊፀሙ የሚችሉ ወንጀሎችን ከማጥናትና ከመከታተል ጀምሮ የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ሪፖርት መቀበልን፣ የወንጀል ምርመራን፣ የክስ ምስረታን፣ የክርክርና የውሣኔ አሰጣጥ አሠራሮችን የሚያጠቃልል ሆኖ የወንጀል ቅጣትን ማስፈፀምና ከቅጣት በኋላ ታራሚን ከኅብረተሰቡ ጋር እስከ ማቀላቀል ያሉትን ሂደቶች ሁሉ የሚያጠቃልል[29]። የወንጀል ህግ አላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን፤ የመንግስት፣ የህዝቦችን፣ የነዋሪዎችን ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው[30]። ይህ ማለት የወንጀል ህግ በዋናነት የህብረተሰቡን አጠቃላይ ጥቅም የሚያረጋግጥ ህግ ነው:: ለምሳሌ የስርቆት የወንጀል ድርጊት በአንድ ግለሰብ ላይ ቢፈፀምም ድርጊቱ የህብረተሰቡን ጠቅላላ ጥቅም የሚነካ እንደሆነ ይቆጠራል። በግለሰብ ላይ የደረሰው የስርቆት ወንጀል ጉዳት በሁሉም ማህበረሰብ በቀጥታም ይሁን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ላይ ጉዳት እና ተፅዕኖ ያሳድራል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ስለሆነም ጥፋት ፈፃሚው ላይ ተገቢው ቅጣት ወይም እርምጃ ካልተወሰደ ተመሳሳይ ድርጊቶች ማህበረሰቡ ላይ የመከሰት እድላቸው ከፍ ያለ ስለሆነ ይህ ደግሞ ቂም በቀልን የማስፋፋት እድሉ ሰፊ ነዉ። ስለዚህ መንግስት በግለሰብ ላይ ለሚያደርሰዉ የወንጀል ድርጊት ሃላፊነቱን በመዉሰድ የወንጀል ምርመራ እንዲጣራ በማድረግ ክስ መስርቶ ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ ተገቢዉን ቅጣት እንዲቀጡ በማረድግ ህብረተሰቡ ከስጋት ሊታደግ ይገባል። ነገር ግን በወንጀል ጉዳይ ዜጎች መብታቸዉ የሚረጋጥበት የህግ ሂደቱ አንዱ ምንም አይነት ክፍያ ሳይከፍሉ በወንጀል ጉዳዮች በመንግስት በሚያቀርብላቸው ነጻ የህግ ባለሙያ በመወከል መብታቸው እንዲከበር ማድረግ ነዉ።

እያንዳንዱ የወንጀል ፍትህ ተቋም በወንጀል ፍትህ ሥርኣቱ ዉስጥ የሚጫወተው የራሱ ሚና ያለው ሲሆን እነዚህ አካላት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግን ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ አይደሉም። ተቋማት ተናበዉ ካልሰሩ የፍትህ ስርዓቱ ግቡን አይመታም። ከዚህ አኳያ የወንጀል ክስ በፖሊስ ምርመራ ተደርጎ በዐቃቤ ህግ ክስ ቀርቦበት ፍርድ ቤቶች የሚወስኑት ጉዳይ ሲሆን ማረሚያ ቤቶች የማረም እና የማነጽ ሥራ ይሰራሉ። ማረሚያ ቤቶች ታራሚዎችን የሚያርሙበት ሂደት መሰል ጥፋት በአጥፊና በሎሎች እንዳይፈጸሙ በማስተማር መሆን አለበት። ይህ ለፖሊስ፣ ለዐቃቤ ህግ እና ለፍርድ ቤት ተቋም ወንጀልን በመከላከል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለዉ። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በወንጀል

---

[29] ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ,ፍትሕ ሚኒስቴር, የካቲት 25/2003 ዓ.ም ገጽ 8

[30] 1996 ዓ.ም የወጣዉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2

ጉዳይ ውስጥ የሚሳተፉት የመንግስት አካላት ፖሊስ፣ ዐቃቤ ህግ፣ፍርድ ቤት እና ማረሚያ ቤቶች ናቸው። አንድ የወንጀል ክስ ፍርድ ቤት ቀርቦ ከመሰማቱ በፊት በርከት ያሉ ሂደቶችን ማለፍ ይኖርበታል። የመጀመሪያ ሂደት ለወንጀል ምርመራ መነሻ የሚሆን ጥቆማ ይቀርባል።ስለአንድ ወንጀል ጉዳይ ሊከናወን የሚገባዉን ጠቅላላዉን ሂደት ጉዳዩን ከመቀስቀስ ወይም ከመጀመር አንስቶ በዚህ ሂደት ዉስጥ ተገቢውን ዉሳኔ መስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮችን ፈልጎ ማግኘትንና በነዚህም ላይ እስከ ክስ ማቅረብ ያሉትን የተለያዩ ዉሳኔዎች መስጠት የሂደቱ አካል ናቸዉ። ይህ የማስታወቅ ሁኔታ በተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች የሚመራ ነዉ። ይህንን ጉዳይ በዋናነት የሚገዛው የወንጀል ስነ ስርዓት ህጉ ነው። በስነ ስርዓት ህጉ መሰረት ማንኛውም ሰው ወንጀል ሲፈፀም ካየ ወይም ወንጀሉ ሲሰራ ያልተመለከተም ቢሆን የወንጀል ክስ እንዲቀርብ ወንጀሉን የማሳወቅ መብት አለው[31]። ወንጀልን አለማሳወቅ ማሳወቅ ግዴታ እንደሆነ በተለያዩ ልዩ አዋጆችና የስነ ስርዓት ህጎች ተደንግጎ ይገኛል። ለምሳሌ የጸረ ሙስና ልዩ የስነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 434/97 በአዋጅ ቁጥር 882/07 አንቀጽ 48[32]፤ በተሻሻላው የፌደራል ፀረ- ሙሽና ኮሚሽን ማቋቋምያ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 883/2007 አንቀፅ 26 እና 27(8) መሰረት ማንኛዉም የመንግስት መ/ቤት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ባለስልጣን ወይም ሰራተኛ በሚሰራበት መስርያ ቤት ወይም ድርጅት የሙስና ወንጀል ስለመፈጸሙ እያወቀ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ስልጣን ላለዉ አካል ሳያሳዉቅ የቀረ እንደሆነ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና እስከ ብር አስር ሺህ  በሚደርስ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል።[33]

የሽብር ወንጀልን ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 1176/12 አንቀጽ15[34] ሽብርን አለማስታወቅ እና ተጠርጣሪን መርዳት:- የሽብር ወንጀሎች ውስጥ አንዱ ሊፈጸም፣ እየተፈጸመ ወይም የተፈጸመ መሆኑን እያወቀ ወይም የወንጀል ፈጻሚውን ማንነት እያወቀ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ወዲያውኑ ለፖሊስ ወይም አግባብ ላለው ህግ አስፈጻሚ አካል ያላስታወቀ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል ሲል ያስቀምጣል። ወንጀልን አለማስታወቁ

---

[31] የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት  ህግ  1954 ዓ.ም አንቀጽ 11

[32] የጸረ ሙስና ልዩ የስነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 434/97 በአዋጅ ቁጥር 882/07 አንቀጽ48

[33] በተሻሻላው የፌደራል ፀረ- ሙሽና ኮሚሽን ማቋቋምያ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 883/2007 አንቀፅ 26 እና 27(8)

[34] የሽብር ወንጀልን ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 1176/12 አንቀጽ 15

ከባድ ሲሆን በተለይም መረጃው ቀድሞ ደርሶ ቢሆን የወንጀሉን መፈጸም መከላከል ወይም መቆጣጠር የሚቻል ዓይነት ሲሆን ቅጣቱ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።[35] በሰዉ የመነገድና ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 13 መሰረት በሰዉ መነገድና ሰዉን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀሎችን የሚመለከት መረጃ ያለው ማንኛዉም ማለትም ወንጀሉ እየተፈጸመ ወይም የተፈጸመ መሆኑን እያወቀ ወይም የወንጀል ፈጻሚውን ማንነት እያወቀ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ወዲያውኑ ለፖሊስ ወይም አግባብ ላለው ህግ አስፈጻሚ አካል ያላስታወቀ ወይም ሐሰተኛ መረጃ የሰጠ እንደሆነ ከሶስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት የሚቃጠ ሲሆን ድርጊቱ ከባድ ከሆነ ደግሞ ቅጣቱ ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ሊሆን እንደሚችል ተደንግጓል።

ለህብረተሰቡ ጠቅላላ ጥቅም ሲባል የወንጀልን መፈፀም ማሳወቅ ግዴታ የሚሆንበት እና ወንጀል መፈፀሙን እያወቁ ለሚመለከተው አካል ያለመሳወቅ በህግ የሚያስጠይቅበት ሁኔታ በወንጀል ህጉ እና የተለያዩ አዋጆች ስር ተደንግጎ ይገኛል። ግላዊ ባህሪ ያላቸዉ በመሆኑ በግል አቤቱታ ከሚቀርቡ ቀላል ወንጀሎች በስተቀር በባህሪያቸው ከግላዊ ይልቅ ህብረተሰባዊ ጉዳቶችን የሚያስከትሉ፣ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ወንጀሎችን በሚመለከት ጥቆማዎችንና መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል መስጠት የዜግነት ሃላፊነት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። ግላዊ ባህሪይ የሌላቸውና በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚጣሩ ወንጀሎችን በሚመለከት ጥቆማና አቤቱታ የማቅረብ መብት ለሁሉም የተሰጠ ቢሆንም፤ ከወንጀሎቹ ባህሪና ሊያደርሱት ከሚችሉት የማይተካ ጉዳት አንጻር እነዚህን ወንጀሎች አለማስታወቅ በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት ተደርጎ በተለያዩ ህጎች ተደንግጓል። ለምሳሌ፡- በወንጀል ህጉ አንቀፅ 443 መሰረት ማንም ሰው በቂ ምክንያት ሳይኖረው በሞት ወይም በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል መፈፀሙን ወይም የወንጀለኛውን ማንነት እያወቀ ለሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ሳያስታውቅ የቀረ እንደሆነ ወይም በሕግ ወይም በሙያዉ ደንቦች ለህዝብ ደህንነት ወይም ሰላምና ስርዓት ሲባል አንዳንድ ወንጀሎቸን ወይም ከባድ ሁኔታዎችን ለሚመለከተዉ ባለስልጣናቶች የማስታወቅ ግዴታ እያለበት ግዴታዉን ያልፈጸመ እንደሆነ ከብር አንድ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት እንደሚቀጣ ይደነግጋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በወ/ህ/አንቀጽ 254 መሰረት በሀገሪቱ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት፣ የፖለቲካና ግዛት ሉዓላዊነት፣ የውስጥና የውጭ ደህንነት ላይ የተፈጸመ/ሊፈጸም የተሞከረ ወይም ወንጀሉን ለመፈጸም የመሰናዳት ተግባር መከናወኑን አለማስታወቅ ከ5 አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ወይም ወንጀሉ

---

[35] በሰዉ መነገድና ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 13

የተፈጸመዉ የአገሪቱ የዉስጥ ወይም የዉጭ ደህንነት በአስጊ ሁኔታ ላይ አያለ ከሆነ ከ10 አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

እንዲሁም በወ/ህ/አንቀጽ 335 መሰረት በመከላከያ ሰራዊት እና ወታደራዊ ግዴታዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አለማስታወቅ በቀላል እስራት፣ ነገሩ ከባድ ሲሆን ደግሞ ከ3 አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ያስቀጣል።

### 2.4.1 በክስ አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ ወንጀል

በወንጀል ህጉ በክስ አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ እንደሚያስቀጣ የተደነገገ ወንጀል የተፈፀመ እንደሆነ የክስ አቤቱታው ለፖሊስ ወይም ለአቃቤ ህግ ይቀርባል[36]። አቤቱታው ለዐቃቤ ህግ የቀረበ እንደሆነ ዐቃቤ ህጉ ስልጣን ያለው ፖሊስ ወንጀሉን እንዲመረምር የሚያስተላልፍ ሲሆን ዐቃቤ ህጉም በምርመራ ሂደቱ ይሳተፋል። አስፈላጊው ምርመራ ተከናውኖ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ማስረጃ ሲኖር ዐቃቤ ህጉ ክስ በመመስረት ለፍርድ ቤት ያስተላልፋል፤ይከራከራል። በክስ አቅራቢነት የሚቀርቡ ወንጀሎች በባህሪያቸው ከግላዊነት ይልቅ የህዝብ ጥቅምን ማዕከል የሚያደርጉ ስለሆነ የተበዳዩ የመክሰስ እና ያለመክሰስ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ አይደሉም።

| ምሳሌ |
| --- |
| በአንድ ሰው ላይ የስርቆት ወይም የውንብድና ወንጀል ቢፈፀም ንብረት የተወሰደበት ሰው ንብረቱ የግሌ ነው ክስ አላቀርብም ማለት አይችልም። ምክንያቱም ወንጀሉን የፈፀመው ሰው ካልተቀጣ ሌሎች ተመሳሳይ የስርቆት ድርጊቶች የመፈፀም እድላቸው ከፍተኛ ነው። ይህም የኃላ ኃላ በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት ያስከትላል። |

በመሆኑም ማንኛውም ሰው ስለወንጀሉ መፈፀም ጥቆማ ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን ወንጀሉ የተፈፀመበት ሰው ደግሞ የወንጀል ድርጊቱን የማስረዳት ወይም የወንጀል ምስክር በመሆን ለፍትህ ሂደቱ በመስጠት ከፍተኛ ሚና አለው።

### 2.4.2 በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል

ወንጀሉ በግል አቤቱታ አቅራቢነት ብቻ የሚያስቀጣ መሆኑ በወንጀል ህጉ በግልፅ የተደነገገ እንደሆነ ተበዳዩ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ የግል አቤቱታ ካላቀረበ በቀር የወንጀል ክስ ማቅረብ አይቻልም።

[36] የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ 11፣ 14፣ 16

[37]የወንጀል ድርጊቶች ወንጀሎቹ ስለመፈፀማቸው የሚያውቅ ሰው ለባለስልጣኖች ቢያሳውቅም ወንጀሉ የተፈፀመበት ሰው የግል አቤቱታ ያላቀረበ እንደሆነ የወንጀል ምርመራ ሂደት አይጀመርም[38]። ምርመራ ከተጀመረ በኃላም ተበዳዩ ክሱን እንደማይፈልግ ከገለፀ ምርመራዉ ይቋረጣል ማለት ነው። ክስ ቀርቦ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከደረሰም በኃላ የግል ተበዳይ ክሱ እንዲነሳ ሊያመለክት ይችላል።
ለምሳሌ፡- በአንድ ሰው ላይ የዛቻ ወንጀል[39] ቢፈፀም የዛቻው ድርጊት የሚያስፈራራው እና ስጋት ላይ የሚጥለው ዛቻ የተፈፀመበት ሰው ላይ ብቻ ነው። በመሆኑም ከተበዳይ ፍቃድ ውጪ የወንጀል ምርመራ ወይም ክስ የሚጀመርነት ሁኔታ የለም። በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች ተበዳዩ የወንጀል ድርጊት ወይም ወንጀል አድራጊውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ 3 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ለህግ አስከባሪ አካላት ማቅረብ አለባቸው። ያለበቂ ምክንያት የዘገየ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ማለት ነው። ዓቃቤ ህግ ክስ ለማቅረብ በቂ ማስረጃ የለም በማለት ክስ የማይመሰርት ከሆነ ተበዳዩ በግሉ የግል ክስ (private prosecution) እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት ይችላል[40]።

### 2.4.3 ጠቋሚ ሳይታወቅ የሚቀርብ የወንጀል ክስ

የአንድን ወንጀል መፈፀም ጠቋሚው ማንነቱን ሳይገልፅ ማስታወቅ እንደሚችል በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 12 ስር ተደንግጎ ይገኛል። ይሁንና በእንዲህ አይነት ጥቆማ የሚደረግ ምርመራ በጥንቃቄ መደረግ አለበት፡ ፡ስለሆነም ጠቋሚው ማንነቱን ካላሳወቀ ምርመራ የሚጣራው ጥቆማው ከፍ ያለ የህግ መጣስን የሚመለከት ሆኖ በአካባቢያዊ ሁኔታዎች የተደገፈና የሚታመን መስሎ ከተገኘ ብቻ ነው፡

2.1.4 በእርቅ የሚያልቁ እና የማያልቁ ወንጀሎች

በ1996 ኢ.ም የወጣው የወንጀል ህግ በመሰረታዊነት ክስ አቀራረብ በወንጀል ክስ አቅራቢነት እና በግል አቤቱታ እንደሚቀርብ ያስቀምጣል። በግልጽ በግል አቤቱታ አቅራቢነት መሆኑ በህጉ ካልተገለጸ ወንጀሉ በዓቃቤ ህግ አቅራቢነት ይቀረባል /የወ/ሕግ/አንቀጽ 211/።[41]

- ❖ በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚቀርቡ ወንጀሎች፡-

በአቃቢህግ ክስ አቅራቢነት በኩል ይቀረባሉ፣ ቅጣቱ እስከ ስድስት ወር የሚያስቀጣ መሆን አለበት፣ የተበደለው ግለሰብ ክስ ባያቀርብ እንኳን በሌላ ሰው ጠቋሚነት ይቀርባል እንዲሁም በእርቅ ማለቅ የማይችሉ ወንጀሎች ናቸው የወ/ሕግ/አንቀጽ 211/።[42]

---

[37]በ1996 የወጣዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 212

[38]1954 ዓ.ም የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ 13

[39] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 580

[40] 1954 ዓ.ም የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ 44፣ 47፣ 150 - 153

[41] በ1996 ዓ.ም የወጣዉ ወንጀል ህግ አንቀጽ 211

❖ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ወንጀሎች፡-

ወንጀል ተፈፀመብኝ የሚለው በግለሰቡ አቤቱታ አቅራቢነት የሚቀርብ ነው። ግለሰቡ ወንጀሉ ከተፈጸመበት ጊዜ አንሰቶ አቤቱታዉን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ክሱ የማቅረብ እድሉ ቀሪ ይሆናል/የወ/ሕግ/አንቀጽ 212/።[43] በግል አቤቱታ የሚታዩ ወንጀሎች በእርቅ ሊያልቁ የሚችሉ ወንጀሎች ናቸው።

### 2.1.4.1 እርቅ በወንጀል ጉዳዮች ያለው ፋይዳ

በተለያየ በኢትዮጵያ ክፍለ ታሪክ እርቅ ተቀባይነት ያለው አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገድ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ መልካም የሆነ ታሪክ እና ባህል በህጉም እውቅና ተሰጥቶት የነበረ ሲሆን በፍርድ ቤቶችን ጭምር በወንጀል አድራጊው እና ተበዳይ መካከል እርቅ ሲበረታታ ይታያል። በሁሉም ወንጀል አይነቶች እርቅ መታረቅ ያልተከለከለ ሲሆን ነገር ግን እንደወንጀል አይነቱ እና በጠቅለላዉ እርቁ ፍትህን የማያረጋግ ከሆነ እርቁ ተፈጻሚ አይሆንም። ነገር ግን ከተፈፀመው ወንጀል ክብደት አንጻር ፍ/ቤቶች ፍርድ ከሰጡ በኀላ ለቅጣት ማቅለያነት ይጠቀሙታል። በወንጀል ህጉ በእርቅ ሊያልቁ የሚችሉ ወንጀሎችን በአፈፃፀሙ እና ቅጣቱ ቀላል በመሆኑ የህብረተሰቡን ሰላም እና መልካም ግንኙነት ተጠብቆ ለማቆየት እንደሚጠቅም ተመልክተዋል። ሌላው በወንጀል ጉዳይ መታረቅ ጥቅሙ፡-የመዝገብ ክምችትን ይቀንሳል፣ ከእስራት ይልቅ በእርቅ ማለቁ ለሁለቱም ወገን ዘላቂ ሰላም ያመጣል፣ በወንጀል አድራጊው ላይ የባህሪ ለውጥ ሊመጣ ስለሚችል፣ እንዲሁም የፍርድ ቤቶችን የስራ ጫና እና የተከራካሪዎችን ግዜ ፣ ወጭ እና ጉልበት ያቀላል።

### 2.1.5 ወንጀልን በመከላከል ረገድ ህብረተሰቡ ያለው ሚና

➢ ወንጀል መከላከል

የወንጀል ድርጊት የመፈፀሙን እድል እና የወንጀል ስጋትን ጨምሮ በግለሰቦች ወይም በማህበረሰቡ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አደጋ ዘርፈ ብዙ የወንጀል ምክንያቶች ላይ ያተኮሩ ስትራቴጂዎችና ተግባራትን በማከናወን ወንጀል መቀነስን የሚያጠቃልል ነው።

በአንድ ሀገር ዉስጥ ሰላምና ደህንነት ለመፍጠር የህብተሰቡ ሚና ከፍተኛ ነዉ። ወንጀልን ለመከላከል ጠንካራ የወንጀል ፍትህ አካላትና ተቀዋማት የስፈልጋሉ። ጠንካራ የፍትህ ስርዓት ለመዘርጋት ህግና አደረጃጀት ያስፈልጋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ከህብረተሰቡ ጋር በቁርኝት መስራት ፍትህን ለማስፈን በተሻለ መልኩ ያግዛል። በህብረተሰብ ደረጃ ወንጀል እንደአጠቃላይ ፀያፍ ተግባር መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና ከዚሁ ማህበረሰብ የወንጀል ድርጊት ፈሚዎች ሲወጡ ይስተዋላል። ወንጀለኛ ወንጀልን

---

[42]ዚኒ ከማሁ

[43] 1996 ዓ.ም የወጣዉ ወንጀል ህግ አንቀጽ 213

ለማድረግ የተለያየ የስነልቦና እና ማህበራዊ ቀውሶች እንደምክንያት የሚጠቀስ ቢሆንም ለዚህ ሁሉ ዉጤት ግን ከህብረተሰቡ ይመነጫል።ወንጀልን በመከላከል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃም ከፍተኛዉን ሚና ይጫወታሉ።

| |
|---|
| መወያያ ጥያቄ ፡- ወንጀልን በመከላከል ረገድ ማህበረሰቡ በአካባቢዉ የሚጠቀመዉ ዘዴን ምንድ ናቸዉ? ተወያዩ |

ወንጀል መከላከል ህብረተሰቡ ለፍትህ ስርዓቱ እርዳታ ወይም እገዛ ከሚሰጥባቸዉ ሁኔታዎች አንዱና ዋነኛዉ ነዉ። በአገራት የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የተለያዩ የወንጀል መከላከያ ዘዴዎች ይተገብራሉ። በአብዛኛው ግን 4 አይነት የወንጀል መከላከል ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። እነሱም

1ኛ ህግን ማስከበር የወንጀል መከላከል ስልት፡-ይህምበወንጀል ህግ አንቀጽ 1 ላይ መነሻ ያደረገ ስልት ይህም ወንጀል እንዳይፈጸም በህግ ማስጠንቀቅ፣ተፈጽሞ ሲገኝ ወንጀል አድራጊውን መቅጣት፣ ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈጽም ቁጥጥር ስር በማዋል እና እሱን መሰል ሌሎች ሰዎችም ከዚህ ቅጣት እንዲማሩ በማድረግ ወንጀል መፈጸም አስቀጪ እንደሆነ በማስተማር ወደፊት ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል ነው።

2ኛ እድገትን መሰረት ያደረገ (Developmental) የወንጀል መከላከል ስልት።የወንጀል አጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎች እና የወንጀል ባህሪዎችን መቀነስየወንጀል አጋላጭ የሆኑ ሁኔታዎች እና የወንጀል ባህሪዎችን መቀነስ፣ ወደ ጥፋተኝነት፣ ወንጀል ወደ መፈጸም እና ለማህበረሰቡ ጎጂ ወደሆኑ ባህሪያት የሚያመሩ አጋላጭ ሁኔታዎችን በመለየት እነዚህን አጋላጭ ሁኔታዎች በመቀነስ ላይ ያተኮሩ የወንጀል መከላከል ሥራዎችን መስራት ላይ ያተኩራል። ምሳሌዎች የወላጆችን ልጅ የማሳደግ ክህሎት ማበልጸግ፣ የሕፃናትን አካላዊና አእምሯዊ ጤና መጠበቅ፣ የተማሪዎችን ውጤት ማሳደግ፣በሕፃናት ላይ እንግልት እና ጥቃት እንዳይፈፀም መከላከል እና በአጠቃላይ ሕፃናት ወደፊት የተሻለ ኑሮ ለመኖር እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማብቃት የሚሉት በስፋት ይጠቀሳሉ።

3ኛ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ (societal) የወንጀል መከላከል ስልት፡- ይህም የአንድን ማሕበረሰብ ሁኔታዎች መቀየር በዚያ ማሕበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ባህሪ ይቀይራል፣በመኖሪያ ሰፈሮችና መንደሮች የወንጀል ክስተት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማህበራዊ ሁኔታዎች በተለይም ቁሳዊ እና አደረጃጀትን የተመለከቱትን በመቀየር ወንጀልን መከላከል ነው። ምሳሌዎች የማህበረሰብ አባላትን በማደራጀት ወንጀልን መከላከል፣ የወጣቶች ማህበራት፣ የታክሲ ማህበራት ፤ የፓርኪንግ አገልግሎት ሰጪ ወጣቶችን የወንጀል ስፍራዎችን ለልማት

4ኛ የአካባቢ ሁኔታዎች ላይ ያተኮረ (situational) የወንጀል መከላከል ስልት የወንጀል ድርጊቶች ሁኔታዎችን እና አጋጣሚዎችን ተንተርሰው የሚፈጸሙ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ የሚቀረጽ እና የሚተገበር ስልት ነው። በዚህ ስልት ወንጀል ሊፈጸም የሚችልበትን እድል በመቀነስ እና የወንጀል

ፈፃሚዎችን የመያዝ እድል በመጨመር ላይ ያተኮሩ የወንጀል መከላከል ስራዎች እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው። ለምሳሌ ከፍተኛ የወንጀል ምጣኔ በሚታይባቸውን አካባቢዎች እና የወንጀል ዒላማዎችን በመለየት፣ የህብረተሰቡን የወንጀል ንቃት መጨመር፣ የጥበቃ ካሜራዎችን እና ሌሎች የክትትል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ብዙ ሰዎች በሚንቀሳቀሱባቸው እና ለወንጀል ዒላማ ሊሆኑ በሚችሉ ቦታዎችን በመለየት የጥበቃ አሰራሮችን መዘርጋት የሚሉት ወንጀል መከላከያ ስልቶች ይጠቀሳሉ።

በተጨማሪም በተለያየ የእምነት ተቋማት ፈጣሪን መፍራት የወንጀል ድርጊት ውግዝ መሆኑን በማስተማር ከወንጀል ድርጊት እንዲቆጠቡ ማስተማር፣ በምስክርነት እንዲሁም ቃል መስጠት ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት ከወንጀል መከላከል አካላት ጋር መስራት፡ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ ወንጀል መከላከል ተግባር ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት የሚመጣ ተግባር ነው። በወንጀል የተጠረጠሩትን ከህግ አካላት እንዳያመልጡ እንዲቀርቡ ማጋለጥ እና የሚገባቸውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ አንዱ ወንጀልን ለመከልከል የምንጠቀምበት ስለሆነ የህብረተሰቡ ሚና የሚተገበርበት መንገድ ነው።

### 2.1.6 ለፍትህ ዕርዳታ የመስጠት ግዴታ እና ግዴታዎቹን አለመወጣት የሚያስከትለዉ ተጠያቂነት

የሀገራችን የበላይ ህግ የሆነውን ሕገ መንግስትን የማስፈፀም ግዴታ የተሰጠው ለመንግስት ተቋማትና በመንግስት ስራ ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች ብቻ አይደለም። ይልቁንም ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግስት አካል፣ የፖለቲካ ድርጅትና ማህበር ሕገ መንግስቱን የማስከበርና ለሕገ መንግስቱ ተገዢ የመሆን ሀላፊነት ተጥሎበታል። ዜጎች የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ከሚያስፈፅሙባቸው መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው ደግሞ በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ ነው። በህዝብ አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ቀጥተኛ ተሣትፎ የማድረግ መብት (The Right to take part in Public Affairs) አይነተኛ መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ ለፍትህ ስርዓቱ የሚሰጠው ድጋፍ በበጎ ፈቃደኝነት ከሚደረጉ ተግባራት አንስቶ በህግ የታዘዙ ግዴታዎችን የሚያጠቃልል ነዉ። እነዚህን ግዴታዎች አለመወጣት የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል። ለፍትህ ስርዓቱ ዕርዳታ የሚሰጥባቸውም መንገዶች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ ማዬት ይቻላል። ወንጀልን ማጋለጥና ምስክር መሆን እንዲሁም ለፍርድ ቤት ተገቢውን ክብር መስጠት ይተቀሳሉ። ለፍትህ እርዳታ መስጠት በወንጀል ጉዳይ፤ በፍትህብሔር እና በተለያዩ አስተዳደር መ/ቤት ሊቀርብ ይችላል።

#### 2.1.6.1 ለፍትህ እርደታ መስጠት በፍትሐብሔር ጉዳይ

በፍትህብሔር የሚሰጠዉ ማሰረጃ በ1958 ዓ.ም በወጣው የፍትሐ ብሔር ሥነ-ስርዓት ህግ መሰረት የምስክርነት ቃል መስጠትና የተጠየቀን ማስረጃ ማቅረብ ግዴታ መሆኑን ይገልፃል (የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/አንቀጽ 119)። መጥሪያ በፍርድ ቤት የተሰጠ ትዕዛዝ እንደመሆኑ መጠን

መጥሪያው የደረሰው ሰው በቀነ ቀጠሮው የመገኘት ግዴታ አለበት። ነገር ግን በተባለዉ ጊዜና ቦታ ተገኝቶ ነገር ግን በህግ የተደገፈ በቂ ምክንያት ሳይኖረው የምስክርቱን ቃል ለመስጠት ወይም በእጁ የሚገኙ ማስረጃዎችን በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ ፍርድ ቤቱ ወድያውኑ ይፈርድበታል (የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.267).

### 2.1.6.2 ለፍትህ እርደታ መስጠት በወንጀል ጉዳይ

በ1996 የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ "ለፍትህ ዕርዳታ መስጠትን እንቢ ማለት" በሚል ርዕስ ስር፡ - ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን ያለው አካል በያዘው ጉዳይ ላይ እንዲመሰክር ወይም ማስረጃ እንዲያቀርብ የታዘዘ ሰው በቂ ምክንያት ሳይኖረው ሳይቀርብ የቀረ፣ ማስረጃውን ያላቀረበ ወይም ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆን እስከ 1000 ብር በሚደርስ መቀጮ ወይም 2 ወር በሚደርስ እስራት ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል(የወንጀል ህግ አንቀፅ 448)። በተመሳሳይ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰው ማንኛውንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሐሰተኛ ምስክርነት ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት የሰጠ እንደሆነ ወይም እውነቱን የደበቀ እንደሆነ፣ ያቀደው ሃሳቡ ከግብ ባይደርስለትም እንኳን በቀላል እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል። ምስክሩ እውነቱን ለመናገር ምሎ ወይም ማረጋገጫ ሰጥቶ እንደሆነ በተለይም የተፈለገው ውጤት በከፊል ወይም በሙሉ ተገኝቶ እንደሆነ ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራት ነው። በዚህ ጉዳይ የዳኝነት ነክ የተባለዉ ፈርድ መስጠት በሚችል አካል ፊት መሆኑን በቅጽ 23 መ/ቁ 153228 አንድ ምስክር በፖሊስ በወንጀል ምርመራ ወቅት የሚሰጠዉ ቃል እንደመደበኛዉ የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነት ወይም መሰል /quasi-judicial/ ተቋም ቃለ መሃላ ፈጽሞ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል ባለመሆኑ ምስክሩ በፖሊስ የምርመራ መዝገብ የሰጠው የምስክርነት ቃል ፍ/ቤት ቀርቦ በመለወጡ ምክንያት የሀሰት ቃል የትኛዉ እንደሆነ በትክክል በሌላ ማስረጃ ሳይረጋገጥ የምስክሩ ቃል መለያየት ብቻዉን በቂ ማስረጃ በማድረግ ምስክሩ በሀሰተኛ የምስክርነት ቃል መስጠት ወንጀል የሚጠየቅበት የህግ መሰረት ስላለመኖሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሥልጣኑ ይህን ወስኗል[44]። በሌላ በኩል ስለ ወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ በወጣ አዋጅ 699/2003[45] ጥቆማ ማቅረብ መስክርነት መስጠት ግዴታ መሆኑን የስቀምጣል። መነሻ ቅጣቱ ከግምት ሳይገባ 10 እና ከዛ በላይ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች የወንጀል ምስክሮርነትና ጥቆማ የሰጠ ሰዉ የህግ ጥበቃ ይደረግለታል። በሌላ በኩል በራስ ላይ ማስረጃ ያለመሆን መብት (privilege against self-incrimination ህግ መንገስት እንቀጽ 19)፣ ከሙያ ጋር በተገናኘ

---

[44] የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 23 መ/ቁ 153228

[45] የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ 699/2003

የነበረዉን መረጃ፤ ግለሰቦች በትዳር አጋሮቻቸው ላይ መመስከር እንዳይገደዱ የሚከለክሉ ህጎች በሥራ ላይ ያሉ ከሆነ (Spousal Immunity) መመስከር ግዴታ አይደለም። በአጠቃላይ ህብረተሰቡ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ የሚኖረውን ተሳትፎ ከፍ በማደረግ ፍትህን ማስፈን ተገቢ ነዉ።

### 2.1.5 በእጅ ከፍንጅ ወንጀል የክስ አጀማመር

አንድ ወንጀል እጅ ከፍንጅ ነው የሚባለው ወንጀል አድራጊው ወንጀሉን ሲሰራ የተያዘ ሲሆን ወይም ለመስራት ሲሞከር ወይም ወንጀሉን እንደፈፀመ ወዲያውኑ የተያዘ እንደሆነ ነው።[46] በተጨማሪም ወንጀል አድራጊዉ ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላ ሲሸሽ፤ ህዝብ ሲከተለዉ እንዲሁም ጩህትና እሪታ ካለ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል እንተፈጸመ ይቆጠራል (የወ/መ/ሥ/ ሕግ ቁ 19)።

በዚህ አይነት ሁኔታ ወንጀል መፈፀሙንና ፈፃሚውን በቀላሉ ለመለየት የሚያስችል ሲሆን ንፁሕ ሰው ያለአግባብ ሊወነጀል የሚችልበት አጋጣሚ ጠባብ ነው። በግል አቤቱታ ብቻ ለሚያስጠይቁ የወንጀል ተግባራት ግን ምንም እንኳን እጅ ከፍንጅ የተፈጸመ ቢሆንም ፖሊስ የተበዳዩን ይሁንታ ሳያገኝ ጉዳዩን ማስተናገድ አይችልም። አጠቃላይ በመጀመሪያ ወንጀል ተፈፅሞብኛል የሚል አካል ወይም ወንጀል መፈፀሙን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው የወንጀል ጥቆማ ለፖሊስ ማቅረብ አለበት። ፖሊስ የቀረበለትን ጥቆማ ወይም አቤቱታ ከዐቃቤ ህግ ጋር በመመርመር አቃቤ ህግ ክስ በመመስረት ፍርድ ቤቶች ደግሞ ውሳኔ ይሰጣሉ። ይህ በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ የሚፈፀመው በማረሚያ ቤቶች ነው።

### 2.1.6 በወንጀል ምርመራ የፖሊስ ሚና

መርማሪ ፖሊስ የወንጀል ጥቆማን ከመቀበል ጀምሮ የተለያዩ የምርመራ ስራዎችን በማከናወን ለፍትህ ስርዓት መስፈን ጉልህ ሚና አለው። በምርመራ ሂደት ፖሊስ ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል የምስክር ቃል መቀበል፣ ብርበራ ማከናወን (በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ)፣ ከተጠርጣሪ አካል ላይ የሚወሰድ ማስረጃ ለምሳሌ የጣት አሻራ፣ የደም ናሙና ወ.ዘ.ተ ማሰባሰብ፣ ተጠርጣሪን መያዝና የተከሳሽነት ቃል መቀበል፣ በአጠቃላይ የወንጀሉን መፈፀም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማስረጃዎችን የማሰባሰብ ስራን ይሰራል።በተጨማሪም ፖሊስ የያዘውን ተጠርጣሪ በዋስ (የፖሊስ ጣቢያ ዋስ) ሊለቀው የሚችል ሲሆን ይህን ለማድረግ ወንጀሉ በጽኑ እሥራት የማያስቀጣ ሊሆን ወይም ደግሞ ተጠርጣሪው ወንጀሉን ለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል (የወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.28)። የወንጀል ድርጊት ሲፈፀም ህብረተሰቡ በመጀመሪያ በቀጥታ የሚገናኘው ከፖሊስ ጋር ስለሆነ የወንጀል ምርመራ እንዲከናወን የወንጀል ጥቆማውን ወይም አቤቱታውን በፖሊስ ጣቢያ ማቅረብ ይችላል ማለት ነው።

[46] 1954 ዓ.ም የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.19

## 2.1.8 በወንጀል ምርመራ የዐቃቤ ህግ ሚና

የወንጀል ምርመራ በዋናነት የሚከናወነው በፖሊስ ተቋም ውስጥ ቢሆንም የምርመራ ሂደቱን በመምራት እና የህግ ድጋፍ በማድረግ ዐቃቤ ህግ በመርመራ ሂደቱ ይሳተፋል[47]። ለዚህም በፍትህ ሚኒስቴር የተመደቡ ዐቃቤያን ህግ ከፖሊስ ጋር በመሆን፣ የወንጀል ምርመራ ከመጀመሩ በፊት የቀረበው አቤቱታ ወይም ክስ የወንጀል ድርጊት መሆን አለመሆኑን እና ወንጀል ተጠያቂነት ማስከተል አለማስከተሉን መለየት፣ ተገቢ የምርመራ አይነቶችን እና የማስረጃ ማሰባሰብ መመሪያ ለፖሊስ መስጠት፣ክስ ለማቅረብ እና ተከሳሽን ለማስቀጣት የሚያስችል ማስረጃ ተሟልቶ ሲገኝ ክስ መመስረት እና በፍርድ ቤት ተከራክሮ የቅጣት ውሳኔ ማሰጠት፣ በተሰጠው ቅጣት ላይ ቅሬታ ካለ ወይም ተከሳሽ በነፃ ከተሰናበተ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ዐቃቤ ህግ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ ይገኙበታል። እንዲሁም በወንጀል ህጉ መሰረት በግል አቤቱታ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተፈፅመው የተገኙ እንደሆነ የግል ተበዳይ እና ተከሳሽ ጉዳያቸውን በእርቅ እንዲጨርሱ በማግባባት ባለጉዳዮቹ ከተስማሙ የምርመራ መዝገቡን በእርቅ የመዝጋት ስራን ይሰራል። በሌላ በኩል ዐቃቤ ህግ የወንጀል ምርመራ መዝገብ የመዝጋት ስልጣና ያለው ሲሆን ይህም የሚሆነው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.39 ሥር የተመለከቱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው። እነዚህም የተከሳሽ መሞት፣ የእድሜው ከዘጠኝ አመት በታች መሆን፣በ አለም አቀፊ ህግ የዲፕሎማቲክ ያለመከሰስ ከለላ መኖር፣ እና በልዩ ብሄራዊ ህግ ያለመከሰስ መብት የተሰጠ መሆኑ ናቸው። ነገር ግን ዐቃቤ ህግ ክስ የማያቀርብባቸዉ ምክንያቶች ሲኖሩ እነሱም በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 42 የተዘረዘሩ ሲሆን ይህም ተከሳሽን ጥፋተኛ ለማድረግ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ከሌለ፣ የተከሰሰውን ሰው ለማግኘት የማይቻል ከሆነ ወይም ጉዳዩ በሌለበት መታየት የማይችል ከሆነ፣ በይርጋ የታገደ ወይም ለተፈፀመው ወንጀል ይቅርታ ወይም ምህረት የተደረገ እንደሆነ ናቸው[48]።

## 2.1.9 በወንጀል ጉዳይ የፍርድ ቤቶች ሀላፊነት

### 2.1.9.1 የጊዜ ቀጠሮ ፍርድ ቤት/የጊዜ ቀጠሮ ውሳኔ አሰጣጥ

በወንጀል የተጠረጠረ ሰው በፖሊስ ከተያዘ በኋላ ፍ/ቤት መቅረብ መብት አለዉ። ፖሊስ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ዜጎችን ያለአግባብ በመያዝ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተግባር እንዳይፈጽም ለመከላከል ሐገራት በህግ ከሚያደርጉት ጥበቃ አንዱ የተያዘ ሰው በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ማድረግ ነው። በሀገራችንም ይህ መብት በህገ መንግሥስቱ አንቀፅ 19/3

---

[47] የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቀ. 943/2008 አንቀፅ 6/3/

[48] 1954 ዓ.ም የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.39፤ 42

እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 29/1 መሰረት በወንጀል ተጠርጥረው ለተያዙ ሰዎች በ48 ሰዓት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት የተረጋገጠ ነው።

ተጠርጣሪው ከተያዘ በኋላ ፍ/ቤት ወዲያውኑ እንዲቀርብ የሚያስፈልገው የእስሩን ህጋዊነት ለማረጋገጥ ነው። ይህም ማለት ተጠርጣሪዉ ሲያዝ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊሆን ስለሚችል ለመያዝ የሚያበቃ ምክንያት መኖሩን ፍርድ ቤት ስላልተቆጣጠረ ይህን ቁጥጥር ሊያደርግ የሚችለዉ በዚህ ጊዜ ነዉ። ተጠርጣሪው እንደቀረበ ፍ/ቤቱ ማንነቱን አረጋግጦ ከመዘገበ በኋላ በምን ዓይነት ወንጀል ተጠርጥሮ እንደተያዘ ለተጠርጣሪው ሊገልፅለት ይገባል።ከዚህ በኋላ ፖሊስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ ምክንያቱን ከፖሊስ በማጣራት የተጠርጣሪውም ሐሳብ ይሰማል። ተጨማሪ ጊዜ የሚፈቀድበት በቂ ምክንያት ከሌለ እና የተጠረጠረበት ወንጀል ዋስትና የማያስነፍግ ከሆነ ተጠርጣሪው በዋስትና እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ያዛል።
የጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ፖሊስ ያቀረበው ተጨማሪ ምርመራ የማጣሪያ ጊዜ ላይ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት የተጀመረ የፖሊስ ምርመራ የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ፣ የቀረውን ምርመራ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዜ፣ የተጠርጣሪው በእስር ላይ መቆየት አስፈላጊነት ለማረጋገጥ ፖሊሱን በመጠየቅ እና እንደ አሰፈላጊነቱ የፖሊስ ምርመራ መዝገብን በመመልከት ማጣራት ያደርጋል። ይህንንም መሰረት በማድረግ የተጠርጣሪው የዋስ መብት እንዲከበር በማድረግ በዋስ መልቀቅ ወይም በእስር ላይ ቆይቶ ምርመራ እንዲከናወን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

### 2.1.9.2 መደበኛ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚኖራቸው ሀላፊነት

ፍርድ ቤቶች አንድ ክስ ከቀረበላቸው በኋላ በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ማየትና ማረጋገጥ ያለባቸው ጉዳይ ቢኖር ክሱን ለማየት ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን ነዉ። የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ወንጀሎችን በሚመለከት ያላቸው ስልጣን ሁለት ባህሪያቶች ይዞ ይገኛል::
የመጀመሪያዉ የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ተፈጻሚ በሚሆንባቸዉ ወንጀሎች ምንነት እና የአጥፊዎች ማንነት ላይ የተመሰረተ ነዉ። የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚ የሚሆንባቸዉ ሰዎች ላይ ሁሉም የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን አላቸው:: በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ሰዎች እና ወንጀሎች ጉዳይ በወንጀል ሕግ ከቁ 11 እስከ 20 ተዘርዝሮ ይገኛል::
ሁለተኛዉ ሁኔታ ደግሞ ከላይ በተመለከተዉ አይነት በተገኘዉ ሥልጣን መሰረት የትኛዉ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ሥልጣን ይኖረዋል ከሚለዉ ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነዉ። ይህም ፍርድ ቤቶች በቦታና በደረጃ የተዋቀሩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚወሰን ነዉ። የት ቦታ ያለ የትኛዉ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሊሰማ ይችላል በሚለዉ መሰረት የተለያዩ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የወንጀል ጉዳይን ለማየት ያላቸው ስልጣን ይወሰናል። ይህ ጉዳይ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 4፣6፣7 እና ከ99-107 በተደነገጉት የሚመራ ነዉ:: ከዚህም በቀር አሁን ባለዉ የፌዴራልና የክልል መንግሥት አወቃቀር ምክንያት በሁለቱ መንግሥታት ፍርድ ቤቶች መካከል የሥልጣን ክፍፍል ስላለ ይህን ክፍፍል በሚደነግጉ

ህግጋት መሰረት ሥልጣናቸዉ ይወሰናል (የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 1234/13) ሊጠቀሱ ይችላሉ።

### 2.1.9.2 የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ተፈጻሚ የሚሆንባቸዉ ጉዳዮችና ሰዎች፡-የወንጀል ሕግ ተፈጻሚ የሚሆንበት መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችሉት፣ ሀ) ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታ፣ ለ) የተከሳሹ ወይም የተጎጂዉ ዜግነት፣ እና ሐ) የተፈፀመው ወንጀል ዓይነት ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ኢትዮጵያ በጉዳዩ ላይ የሚኖራትን ሥልጣን መሰረት ዋና ስልጣን (Principal Jurisdication) ወይም ምትክ (አነስተኛ) ሥልጣን (Subsidiary Jurisdication) እንዲሆን ሊያደርጉት ይችላሉ።

### 2.1.9.3 በወንጀል ጉዳዮች የፍርድ ቤቶች የስልጣን አይነት

#### 2.1.9.3.1 ዋና ሥልጣን

የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ዋና ስልጣን አላቸዉ::

ሀ) ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈፀመ ወንጀል፣

ለ) በውጭ አገር በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ በተፈጸመ ወንጀል፣

ሐ) የማይደፈር ወይም ያለመከሰስ መብት ያለዉ ኢትዮጵያዊ በውጭ አገር በፈጸመዉ ወንጀል እና

መ) የኢትዮጵያ መንግስት የመከላከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር በፈጸመዉ ዓለም አቀፍ ወይም ወታደራዊ ወንጀል

#### 2.1.9.3.2 ምትክ ሥልጣን

የምትክ ስልጣን ሃሳብ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለዉ ተሰራ የተባለው ወንጀል ኢትዮጵያን በዋናነት የማይነካ ወይም የማይጎዳ ሲሆን ነው። የሚከተሉት ወንጀሎች በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ስልጣን ስር የወንጀል ህጉ የሚፈጸምባቸዉ ናቸው:: ወንጀሎቹም እስካሁን ካየናቸዉ ወንጀሎች ውጪ የሆኑ ናቸዉ።

ሀ) በውጭ አገር የተፈጸመ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚጥስ ወይም የህዝብን ጤንነትና ሞራል የሚጎዳ ወንጀል፣ ለ) በውጭ አገር በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ የተፈጸመ ወንጀል፣ሐ) በዉጭ ሃገር በኢትዮጵያዊ ዜጋ በሆነ የተፈጸመ ወንጀል፣ መ/ በውጭ አገር በማንኛውም ሰው ላይ በዉጭ ሃገር ሰዉ የተፈጸመ ከባድ ወንጀል/በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ከአስር ዓመት ባላነሰ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ወይም ሠ/ በውጭ አገር በሚገኝ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባል የዚያን አገር ተራ ሕግ በመጣስ የተፈጸመ ወንጀል ናቸው። ከዝርዝሩ እንደምንረዳው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በምትክ ሥልጣን የሚዳኟቸዉ ወንጀሎች በዉጭ ሃገር የተፈጸሙ መሆን ይገባቸዋል፡

### 2.1.9.3.3 የሥረ-ነገር ሥልጣን

ከፌዴራልና ከክልል የትኛዉ ፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳለዉ በህግ ከተወሰነ በኋላ የተኛዉ ፍርድ ቤት፤ በየትኛዉ ደረጃ ላይ ያለ ፍርድ ቤት /የመጀመሪያ ደረጃ/ የወረዳ ፍርድ ቤት፣ የዞን/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት/ ነገሩን ለማየት ሥልጣን እንዳለዉ ይወሰናል፡ይህም አይነቱ ልዩነት የሥረ-ነገር ሥልጣን ይባላል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በመጀመሪያ ደረጃ፣ በከፍተኛና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃዎች የተዋቀረ ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶችም ሥልጣን በተመሳሳይ ሁኔታ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተከፋፈለ ነው[49]። አንዳንድ ቀላል የሆኑ እና በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ወንጀሎች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ሊቀርቡ ይችላሉ። በተመሳሳይ አንዳንድ ክልሎች ቀላል የወንጀል ጉዳዮችን በማህበራዊ ፍርድ ቤት እንዲዳኙ ስልጣን የሰጡበት ሁኔታም አለ።

### 2.1.9.3.4 አካባቢያዊ ሥልጣን

ይህ ዓይነት ስልጣን ነገሩ በክልል ፍርድ ቤት የሚዳኝ ከሆነ የት ክልል ወይም በአንድ ክልል ዉስጥ የቱ የወረዳ ወይም ዞን ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው የሚለውን የምንወስንበት ነው። በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/6 እንደሚያመላክተው በተለያዩ አከባቢ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 99-107 የተወሰነላቸውን ቦታ መሠረት አድርገው የዳኝነት ተግባራቸውን የማከናወን ስልጣን አላቸው። ማንኛውም የወንጀል ክስ ወንጀሉ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የሥረ ነገር ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ እንደሚታይ የወ/መ/ሕ/ስሥ/ሥ/ህ/ ቁ 99 ይደነግጋል።ለምሳሌ የወንጀሉ ዓይነት በወረዳ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚታይ ሊሆን ይችላል። ይህ የወረዳ ፍርድቤት በሁሉም ቦታ የሚገኘዉን ወረዳ ፍርድ ቤት ሳይሆን ክሱ የቀረበበት ወረዳ ዉስጥ የሚገኝ የወረዳ ፍርድ ቤት ብቻ ነዉ። በሌላ በኩል ወንጀሉ የተፈፀመበትና የወንጀሉ ውጤት የታየበት አከባቢ የተለያየ የሚሆንበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ይህም ማለት ወንጀሉ የተፈፀመው በአንድ ወረዳ ወይም ዞን ሲሆን የወንጀሉ ውጤት የታየበት ደግሞ በሌላ ወረዳ ወይም ዞን ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ ሁለቱ ፍ/ቤቶች ማለትም ወንጀሉ በተፈፀመበት አከባቢ የሚገኝ የወረዳ ወይም የዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት ወይም የወንጀሉ ውጤት በተገኘበት አካባቢ የሚገኝ የወረዳ ዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ አካባቢያዊ ስልጣን አላቸው ማለት ነዉ (የወ/መ//ሥ/ሥ/ህ/ቁ 99)።

## 2.10 የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን

የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሲያገኙ በአገሪቱ ካሉት እጅግ በርካታ ፍርድ ቤቶች የትኛዉ ነገሩን ለመዳኘት ሥልጣን እንደሚኖረዉ ሊወሰን ይገባል። አሁን በሃገሪቱ ባለዉ የፍርድ ቤቶች

---

[49] በ1987 ዓ.ም በወጣዉን ህገ መንግስት አንቀፅ 78

አወቃቀር መሰረት ሊወሰን የሚገባዉ የመጀመሪያዉ የሥልጣን ጥያቄ ከፌዴራል እና ከክልል ፍርድ ቤቶች የትኛዉ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሊኖረዉ እንደሚችል ነዉ። የክልል ፍ/ቤቶች ስልጣን በየክልሉ ብቻ የተወሰነ ነዉ። የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ግን በአ/አበባና ድሬዳዋ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በጉዳዮች ዓይነት ተለይቶ ወደ ሁሉም ክልሎች ሊደርስ ይችላል። በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ሆነው በክልሎች ውስጥ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች የክልል ፍ/ቤቶች በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 78 (2) ባገኙት ውክልና መሰረት ከራሳቸው ስልጣን በተጨማሪ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን የሆነውን የወንጀል ጉዳይም የማየት ስልጣን ይኖራቸዋል።

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/13 አንቀፅ 4 ስር የፍርድ ቤቶቹ የወንጀል ጉዳይ ሥልጣን በዝርዝር ተቀምጧል። ዝርዝሩም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የሚሸፍናቸዉን ወንጀሎች የሚወስን ነዉ። ስለዚህ ከነዚህ ወንጀሎች ዉጪ ያሉት ወንጀሎች በክልሎች ዉስጥ ተፈጽመዉ ሲገኙ የሚዳኙት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን የክልሉ ሥልጣን ይሆናል ማለት ነዉ። እነዚህ ወንጀሎች ሁሉም በወንጀል ህጎች የተደነገጉ ወንጀሎች ናቸዉ። እነዚህም በዋናነት በፌዴራል መንግሥት ህግ አዉጪ ባለሥልጣን የሚወጡ ናቸዉ። በህገ መንግሥቱ እንደተመለከተዉ የወንጀል ህግጋትን የማዉጣት ሥልጣን የፌዴራል መንግሥት ህግ አዉጪ አካል ነዉ( ህገ መንግስት አንቀጽ 51 እና 55)። በእነዚህ ህጎች ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ካጋጠሙ የክልል የወንጀል ህግ ሊያወጡ ይችላሉ (ህገ መንግስት አንቀጽ 55/5)። በእነዚህ የክልል የወንጀል ህግጋት መሠረት ዳኝነት የሚሰጡት ፍርድ ቤቶች ደግሞ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ይሆናሉ[50]።

### 2.10.1 የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የማየት ስልጣን

የፍትሐብሔር ህግ በግለሰቦች መካከል፣ በግለሰቦች እና በድርጅቶች መካከል፣ በመንግስት እና በግለሰቦች እንዲሁም ድርጅቶች መካከል ያለን ግንኙነት የሚገዛ ህግ ነው። የፍትሐ ብሔር ክስ የሚቀርበው ጉዳዩ ይመለከተኛል (vested interest) ወይም የፍትሐብሔር ጉዳት ደርሶብኛል በሚል ወገን (ግለሰብ) ሲሆን ክስ አቃራቢው የደረሰበትን ጉዳት መጠን በመግለፅ ጉዳቱ እንዲካስ ክስ ማቅረብ ይችላል። በተጨማሪ በፍትሐብሔር ጉዳይ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ክስ ማቅረብ የሚችለው በውክልና ስልጣን ብቻ ነው። ይህም በሌላ ሰው ወይም በጠበቃ በመወከል ክርክር ማድረግ ይችላል ማለት ነው። የፍትሐብሔር ህግ አላማ የደረሰን ጉዳት መካስ ወይም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበሩበት መመለስ ሲሆን በተጨማሪም ያለአግባብ እየተፈፀሙ ያሉ ድርጊቶችን ማገድ ለምሳሌ ሁከት ማስወገድ እና መፈፀም ያለበት ነገር ግን ያልተፈፀመ ድርጊት ካለ ለምሳሌ ንብረት ለመሸጥ በተደረገ

[50] 1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢፌድሪ ህግ መንግሰት አንቀፅ 51፣55

ስምምነት ላይ ሻጩ ገንዘብ ከተቀበለ በኃላ ንብረቱን ለገዢው ካላስረከበው ንብረቱን እንዲያስረክበው ማስገደድን ያካትታል።

በአጠቃለይ የፍትሐብሔር ህግ ከገንዘብ እና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን በተጨማሪም ግለሰባዊ ግንኙነቶችን ለምሳሌ ፍቺ፣ የልጆች አያያዝና ቀለብ የመሳሰሉት የተካተቱበት ነው። በፍትሐብሔር ህግ የሚካተቱ ጉዳዮችን እንደ ምሳሌ ብናይ የቤተሰብ ህግ፣ የውርስ ህግ፣ የውል ህግ፣ የንብረት ህግ፣ ከውል ውጪ ሀላፊነት ህግ፣ አሰሪና ሰራተኛ ህግ እና ሌሎችም ናቸው። በፍትሐብሔር ጉዳይ አንድ ሰው እራሱ በፈፀመው ወይም ባልፈፀመው ድርጊት ብቻ ሳይሆን እሱ ሀላፊ የሆነባቸው ሰዎች ወይም ንብረቶች ባደረሱት ጉዳት ተጠያቂ ወይም ሀላፊ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። በመሆኑም ከላይ የተገለፁት እና ሌሎች የፍትሀ ብሄር ጉዳዮች ያለው ሰው ጉዳዩን የት መውሰድ እንዳለበት ማወቅ ጠቃሚ ነው። የፍትሐብሔር ጉዳይ ከወንጀል ጉዳይ ከሚለይባቸው ባህሪያት አንዱ በፍትሐብሔር ጉዳይ ክስ የሚቀርበው ቀጥታ በፍርድ ቤት መሆኑ ነው። ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ሰው ክሱን ከማስረጃዎች ጋር በማጠናቀር ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት በማቅረብ ክስ መክፈት ይችላል።

በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 80 ስር እንደተደነገገው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን አለዉ። የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ በክልሉ ጉዳይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል። በተጨማሪ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ሲኖረዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን የሚኖረው ሆኖ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል። በተጨማሪ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት" ማለት እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት ያለበትን በፋዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታዩ የሚችሉ የመጨረሻ ዉሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን፣ትእዛዝ፣ ናቸው ። ቀጥለዉ የተዘረዘሩትም በሰበር የሚታዩ ጉዳዮች ናቸዉ። እነሱም

ሀ) የሕገ መንግሥቱን ዴንጋጌዎች የሚቃረን

ለ) ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ከጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ሕግ የሚጠቅስ፤

ሐ) ለክርክሩ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፤

መ) በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፤

ሠ) በፍድዴ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፤

ረ) ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የተወሰነ፤

ሰ) የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠው ውሳኔ፤

ሸ) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተሰጡ ዉሳኔ በሰበር ችሎት ይታያል (በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ።

በህግ መንግስቱ ስለፌደራል እና ክልል ፍርድ ቤቶች ከተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል ባሻገር በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ስልጣን፣ የወንጀል ዳኝነት ስልጣን እና የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ስልጣን በዝርዝር ሰፍሮ ይገኛል። በተለምዶ ማህበረሰቡ ውስጥ የሚታየው ችግር ሰዎች የተለያየ የመብት ጥሰት ሲፈፀምባቸው በመጀመሪያ የሚሄዱት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ነው። ይህ የሚሆነው የወንጀል ህግ እና ፍትህ ብሄር ህግን ልዩነት ካለማወቅ እንዲሁም ፖሊስ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን የማየት ስልጣን እንደሌለው ካለማወቅ የተነሳ ነው። በመሆኑም የፍትሐብሔር ጉዳዮች የሚታዩት እና አፈፃፀማቸዉ የሚከናወነው በፍርድ ቤቶች በኩል መሆኑን ማወቅ ሰዎች ጉዳያቸውን ሳይንገላቱ በሚመለከተው አካል እንዲፈፀምላቸው ለማድረግ ያስችላቸዋል።

## 2.11 የቅጣት አይነቶች

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ የተለያዩ ቅጣት አይቶች ተምጠዋል። እነዚህም ቅጣቶች የሞት፤ የጹኑ አስራት፤ የቀላል እስራት፤ የግዴታ ስራ፤ የገደብ ቅጣት እንዲሁም የጥንቃቄ እርምጃዎች ናቸዉ፡ ቅጣቶች እንደተከሳሹ የእድሜ፤ የአፈጻጸም ሁኔታ እና እንደ ወንጀሉ ክብደትና ቀላነት ይለያያ። ተፈጻሚነታቸዉም የአዋቂዎች መደበኛ ቅጣት፣ የወጣት ጥፋተኛ ቅጠትና የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲሁም የደንብ መተላላፍ ቅጣቶች ናቸው፡ የቅጣት አይነቶች የሚከተሉት ሲሆኑ

1/ ዋና ቅጣት (primary punishment)፡- ይህ አይነቱ ቅጣቱ የገንዘብ መቀጮን፣ ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች የእስራት እና የሞት ቅጣትን ያካተተ ነው። የገንዘብ ቅጣት የሚያካትተው ለተፈፀመው ወንጀል ቀጥታ በገንዘብ መልክ ወንጀለኛው ሲከፍልእና ወንጀል ለተፈፀመበት ተበዳይ በካሳ መልክ ወንጀለኛው ገንዘብ ሲከፍል ነው። ነፃነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች ወንጀለናዉ በፈጸመዉ ጥፋት ተፈርዶበት በማረሚያ ቤት ሆኖ የሚፈጽመዉ ቅጣት ሲሆን ቀድሞ እንደበረዉ ኑሮ ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ መኖር፤ መንቀሳቀስ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን የመከወን ነጻነትን ሲያጣ ነዉ። የአስራት ቅጣት ነፃነትን ከሚያሳጡ ወንጀሎች አንዱ ሲሆን በወንጀል ህጉ ቅጣቱ ቀላል ወይም ፅኑ አስራት ሊሆን ይችላል። ቀላል እስራት ወንጀሉ ቀለል ያለ ሆኖ በመርህ ደረጃ ከአስር ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት አመት በልዩ ሁኔታ እስከ አምስት አመት የሚያስቀጣ ነው። ፅኑ እስራት ደግሞ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል ከባድ በሆኑ ወንጀሎች ላይ የሚጣል ቅጣት ነው። የቅጣቱ ርዝመት በመርህ ደረጃ ከአንድ አመት

እስከ ሀያ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ አስራት ሲሆን በልዩ ሁኔታ እንደ ወንጀሉ ክብደት ታይቶ ቅጣቱ የእድሜ ልክ እስራት ሊደርስ ይችላል ነው። ሌላው የሞት ቅጣት ሲሆን ይህ ቅጣት የሚወሰነው ከባድ ለሆኑ ወንጀሎች ነው። የሞት ቅጣት ከተወሰነ በኃላ እንዲፈፀም በህገ መንግስቱ መሰረት የሀገሪቱ ረእሰ ብሄር(ፕሬዘዳንት) መፈረም አባቸዉ። በአለም አቀፍ የሰበዓዊ መብት ተከራካሪዎች የሞት ቅጣት በህይወት የመኖር መብት በተፈጥሮ የተሰጠ የማይገረሰስና የማይጣስ መጣስ ስለሚሆን ሊፈጸም አይገባ ሲሉ ይከራከራሉ። በሌላ በኩል የወንጀል ህግ አላማ አጥፊዉንና ሌላዉን ማስተማር ስለሆነ የሞት ፍርድ ከተፈረደ ወንጀል አድራጊዉን ሊያስተምር አይችልም የሚል ክርክር ይነሳል። ነገር ግን በኢ.ፍ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 15 በሕይወት የመኖር መብት የተረጋገጠ ቢሆንም በከባድ ወንጀሎች አማካኝነት ሰዉ ህይወቱን ሊያጣ እንደሚችል ይደነግጋል። ስለሆም ከተፈፀመው ወንጀል አንፃር ተመጣጣኝና ሚዛናዊ ቅጣት እስከሆነ ድረስ ሊፈጸም እንደሚገባ በህጉ ተቀምጧል። በወንጀል ህጉ አንቀጽ 117 የሞት ቅጣት የሚወሰነዉ ወንጀሉ ፍጻሜ ያገኘ፤ አጅግ በጣም ከባድ፤ አደገኛ መሆኑ እና የቅጣት ማቅለያ በታጣ ጊዜ ሲሆንና ወንጀለኛዉ ወንጀሉን ሲፈጽም አስረ ስምንት ዓመት የሞላዉ መሆን አለበት።[51] ። የሞት ቅጣት ያረገዘች ሴት ህይወት ያለዉ ልጅ ስትወልድ ና ይህንኑ ህጻን መመገብ.ማሰደግ ሲኖርት ቅጣቱ ወደ እድሜ ልክ ጽኑ አስራት ይቀየርላታል (የወንጀል ህግ አንቀጽ 120)። የሞት ቅጣት  በህዝብ ፊት፤በአደባባይ በስቅላት ወይም በሌላ በማናጨዉም ኢሰብዓዊ ሁኔታ አይፈጸምም።

የመወያያ ርእስ፡- የሞት ፍርድ በኢትጵያ ህግ የሚፈፀም እንደሆነ ተደንግጓል
የሞት ፍርድ ይገባል ወይስ አይገባም?

2/ ሁለተኛ ቅጣት (secondary punishment)፡- ፍርድ ቤቶች ሁለተኛ ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ዋናውን ቅጣት መወሰን አለባቸው። የሚሰጡት ውሳኔም የወንጀል አድራጊ ላይ  የባህሪ ለውጥን እንዲያመጣ በማስብ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፣ የሰራው ሰራ ትክክል እንዳልሆነ መውቀስ፣ በችሎት ወይም በአደባባይ ቦታ ተበዳይን ይቅርታ እንዲጠይቅ ማድረግ እንዲመለስ ማድረግ እንደሚቻል በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 122 ላይ ተቀምጧል። በሁለተኛ ቅጣት ሊጠቀስ የሚችለው በወንጀል ህጉ አንቀጽ123 መሰረት ከፍትሐብሄራዊ መብቶች ለተወሰ ግዜ ማራቅ፤መከልከል፣ ከቤተሰብ መብት ለምሳሌ ሞግዚት በሆነ ግዜ ከሞግዚትነት መብት ማሳት፣ከስራው እንዲርቅ ፍቃዱን ለተወሰነ ግዜ መከልከል፤ ከመምረጥ መመረጥ፤ ምስክር፤ ዋስ ከመሆን መከልከል እንዲሁም ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ ወዘተ ናቸዉ።[52]

---

[51] 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 117

[52] 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 122፣ 123

### 2.11.1 የጥፋተኝነት ደረጃዎች ከወንጀል አድራጊው እድሜ አንፃር

ወንጀሎች በተለያየ የእድሜ ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰዎች ሊፈጸም ይችላል። የወንጀል የቅጣት አጣጣል ምጣኔ ፍትሃዊና ሚዛናዊ እንዲሆን የወንጀል አድራጊን የእድሜ ሁኔት ህጉ ከግምት ዉሰጥ አስገብተዋል። ወንጀል አድራጊዎች በሶስት የእድሜ ክልል የሚከፍል ሲሆን፡-

1ኛ እድሜያቸው ከ9 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት፡- ህጻናት የወንጀል ድርጊት ቢፈፅሙ በእድሚያቸው ምክንያት የድርጊታቸውን ውጤት ስለማያውቁ ከክስ ነጻ ናቸዉ (የወ/ህግ/አንቀጽ52)

2ኛ እድሜያቸው ከ9 ዓመት እስከ 15 ዓመት ወጣት ጥፋተኛ ይባላሉ። በወንጀል ህግ አንቀፅ 53(1) መሰረት በልዩ ሁኔታ እንደጥፋታችው የሚቀጡ ናቸው።

3ኛ እድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ዓመት የሆኑት እንደማንኛውም አዋቂ ወንጀል አድራጊ የሚጠየቁ ናቸው።

### 2.11.2. ወጣት ጥፋተኝነት የሚያስከትለው ቅጣት

ወጣት ጥፋተኛ እድሜያቸው ከዘጠኝ (9) አመት እሰከ አስራ አምስት (15) ያሉ ናቸው። ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉ በመደበኛ ቅጣቶች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም ሲል። ቅጣት ሲተላለፍባቸዉ ከአዋቂዎች ጋር በጋራ አይታሰሩም ። ፍርድ ቤቶች ከአዋቂ ጥፋተኞች በተለየ መልኩ ለወጣት ጥፋተኛ ጥቅም ሲባል የሰጡትን ትእዛዝ ሊለውጡት ይችላሉ። በወጣቶች ላይ ቅጣት ከመጣል ይልቅ አንድ ቦታ ተወስኖ እንዲቀመጡ ፍርድ ቤት ሊያዝ ይችላል። ይህንንም ሲወስን ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባው የወጣት ጥፋተኛውን እድሜ፣ ባህሪው፣ወንጀል ለመፈፀም ያስቻለው የአእምሮ ሁኔታ ከግምት ውሰጥ ማስገባት ያስፈልጋል አንቀፅ 55)። ከተጠያቂነት አንፃር እንደአዋቂ ሳይሆን በተለየ መልኩ በወንጀል ህጉ ከአንቀፅ 157-168 ባሉት ድንጋጌዎች ስር እንደሚቀጡ ህጉ አስቀምጧል።

በወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላይ የሚፈጸሙ ቅጣቶች በማረሚያ ቤት ከመፈጸም ይልቅ ፍ/ቤቶች የተሻለዉን አመረጭ በመጀመሪያ ደረጃ ይመርጣሉ። ለምሳሌ ህክምና ወደሚደረግበት ተቋም በመላክ አእምሮው እንዲታከም ወይም ከሱስ ነጻ እንዲሆን ማድረግ፣ የመልካም ጠባይ ክትትል እና ትምህርት ወደሚያገኝበት ተቋም መላክ፣ በፍርድ ቤቱ ስላደረገው ወንጀል መጥፎነት በመናገር ተግሳፅ እና ወቀሳ በመስጠት የሚታለፍ መሆኑን፣ በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ተወስኖ እንዲቆይ ውሳኔ መስጠት፣ ለወጣት ወንጀል አድራጊዎች በተቋቋመ ልዩ ተቋም እንዲገቡ በማድረግ አስተማሪ ቅጣት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲፈፅሙ ፍርድ ቤት ሊወሰን ይችላል ። እነዚህ እርምጃዎች በወጣት ጥፋተኛው ላይ ውጤት ካላመጡ በመቀጮ ይቀጣል። የመቀጮውን ቅጣት መክፈል ካልተቻለ ወደሌላ የጥንቃቄ እርምጃ ይቀየራል። ወጣት ጥፋተኛው አደገኛነት ያለው፣ ከአስር አመት ጽኑ እስራት በላይ

እና የሞት ቅጣት ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ከፈፀመ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል ፍርድ ቤቱ ጠቅላላውን የጥንቃቄ እርምጃ የሚፈፅምበት ወደጠባይ ማረሚያ ወይም በመደበኛ የእስራት ቅጣት ሊወስን ይችላል። በማረሚያ ቤት እያለ ጠባዩ የተቀየረ ከሆነ በአመክሮ እስሩን ሳይጨርስ ሊወጣ ይችላል። [53] እድሚያቸዉ 15 እስከ 18 ያሉት ጥፋተኞች ፍ/ቤት መደበኛ የሆኑ ቅጣት አይነቶችን ተፈጻሚ ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን 18 ያልሞለዉ ወጣት የሞት ቅጣት አይፈጸምበትም።

## ክፍል ሶስት

## ህገ መንግስታዊ መብቶች

### 3.1 የሰብዓዊ መብቶች ምንነት፣ ጥበቃና ገደብ

ሕገ መንግስቱ ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር ከአምስቱ የሕገ መንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ አድርጎ ያካተተ ሲሆን፣ ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ መሆናቸውን በህግ መንግሰቱ አንቀጽ 10 ሥር ተደንግጓል። ሰብዓዊ መብቶች መብትን ብቻ ሳይሆን ተነጻጻሪና ተመዛዛኝ ግዴታ ወይም ኃላፊነት የሚጥሉ ሁሉን አቀፍ በዓለም ላይ ለሚገኙ ለማንኛዉም ሰው የሚሰጡ መብቶች ናቸው። ለግዴታው እና ለሀላፊነቱ ገደብ ተቀምጦለታል ። ገደብ ማለት የተሰጠውን መብት በይዘቱ ወይም በአፈፃፀሙ በቋሚነት የሚጣል ህግ ሲሆን እገዳ ግን በተለያዩ ሁኔታዎች እና ግዜያዊት የሚደረግ ህግ ነው። ገደቡ የሌሎችን መብት ማስጠበቅን ያካትታል። ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ዙሪያ የሚደረገው እገዳ ማለትም ለግዜው የተወሰኑ ሁኔታዎች እስኪያልፉ ድረስ የሚደረግ ነው።

> ለምሳሌ፡- ማንም ሰዉ የመናገር መብት አለዉ። በህገ መንግስቱ እውቅና ያለው ይህ መብት ከገደብ ነጻ አይደለም። ሰዉ የራስን የመናገር መብት ሲጠቀም የሌሎችን ሰዎችን መብት መጣስ እንደ ሌለበት ገደብ ተጥሎበታል። ከበደ የሚባል ሰው የመናገር መብቱን በመጠቀም አበበን ሊሰድበው ወይም ስሙን ሊያጠፋ አይችልም። የመናገር መብት በህግ የተገደበ ነው ። ምክንያቱም ከበደ መብቱ የተሰጠው የመናገር መብቱን ተጠቅሞ የራሱን መብት ሊጠቀም እና በአካባቢው ላይ ያለውን መብት ሊያስከብርበት ነው።

ሰብአዊ መብቶች በተፈጥሮ ሰው በመሆን ብቻ የተገኙ ቢሆኑም ዋስትናቸው ሰው ሰራሽ ሕግ ነው። ሰብአዊ መብቶች በሕግ እውቅናና ጥበቃ የሚደረግላቸው መብቶችና ነጻነቶች ናቸው። ለምሳሌ፡-

[53] በ1996 ዓ፣ም የወጣዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 56፣ 157፣158፣159፣160.161፣162፣163፣164

በህይወት የመኖር መብት በህገ መንግስቱ ውሰዋ የተካተተ ለሰው ልጆች በተፈጥሮ የተሰጠ ሰብዓዊ መብት ቢሆንም መንግስት ጥበቃ ካላደረገለት በቀላሉ ሊነካ እና ሰዎች በወንጀለኞች በቀላሉ ህይወታቸዉን ሊያጡ ይችላሉ።

የሰብዓዊ መብቶች ለሁሉም የሰው ልጆች በእኩልነት የተሰጡ መብቶች እንጂ በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና በመንግስት ችሮታ ላይ የተመሰረቱ ልዩ እድሎች አይደሉም። በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካላት በሕገ መንግስቱ የተካተቱትን ሰብዓዊ መብቶች የማክበርና ማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ በሕገ መንግስቱ ተጥሎባቸዋል። የሕገ መንግስቱ አንድ ሶስተኛው ክፍል ስለ ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች የሚዘረዝር ሲሆን፣ እነዚህም መብቶች ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መብቶችን ያካተተ ሲሆን ይህም የሲቪልና ፖለቲካ፤ የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና የባሕል ለመብቶችን እንዲሁም የአካባቢ ደህንነትና የልማት መብቶችን አጠቃሎ ይዟል። ከዚህም በተጨማሪ በአንቀፅ 9(4) መሠረት ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል እንደሆኑ፤ የመሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ትርጉምም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ስምምነቶችና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶችና መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የሚተረጎሙ መሆኑን ሕገ መንግስቱ አንቀፅ 13(2) በግልጽ አስቀምጧል። ለምሳሌ እትዮጵያ እ.አ.አ 1948 የወጣዉን ዓለም አቀፍ የሰበዓዊ መብቶች ድንጋጌ ዎችን ተቀብላ አጽድቃለች። በመሆኑም በህገ መንግሰቱ የተቀመጡት የሰብዓዊ መብቶችንና ነጻነቶች ከዓለም አቀፉ ድንጋጌዎች ጋር ባልተቀረነ መልኩ መፈጸም ይገባቸዋል።

ሰብአዊ መብቶችን የተፈጥሮ ህግ፣ የልማድ ህጎች፣ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ተቋማት ውሳኔዎች፣ የዓለም አቀፍ ወይም አህጉር አቀፍ ፍርድ ቤቶች ወይም ፍርድ ሰጪ አካላት ውሳኔዎችና ህጋዊ ቅቡልነት ያላቸው አስተያየቶች ሚመነጩ ናቸው። ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሊገደቡ የማይቻልበት ሁኔታ በህገ መንግሰቱ ተቀምጠዋል። በኢትዮጵያ ህገ-መንግስቱ አንቀጽ 93 መሰረት አስቸኳይ ግዜ አዋጅ በሚታጅበት ወቅት ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሊገደቡ አይችሉም። ሊነኩ ከማይችሉ መብቶች ዉስጥ፡-የመንግስት ስያሜ የኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 1፣ የብሔር ብሔረሰቦች መብት አንቀጽ 39(1)(2) ፣ የእኩልነት መብት አንቀጽ25 እንዲሁም አንቀጽ 18 ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ክልከላን በተመለከተ በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ እንደማይነኩ ተገልፀዋል።

## *3.2* የህገ መንግሰት መሠረታዊ መርሆች

- ✓ የህዝቦች ሉዓላዊ ስልጣንና ተሳትፎ አንቀጽ 8
- ✓ የሕግ መንግስት የበላይነትነ አንቀጽ 9

- ✓ የሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች የማይጣሱ እና የማይገፈፉ መሆናቸዉ አንቀጽ 10
- ✓ የሀይማኖት እና የመንግስት ልዩነት፣ ጣልቃ አለመግባት፣ መንግስታዊ ሀይማኖት አይኖርም አንቀጽ 11
- ✓ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት የመንግስት አሰራር የመሳሰሉት ናቸው አንቀጽ 12

## 3.3 በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የተካተቱ ሰብዓዊ መብቶች

### 3.3.1 የተያዙ ሰዎች ሰብአዊ መብቶች

በመርህ ደረጃ ማንኛውም ተጠርጣሪ የሚያዘው በፖሊስ መጥሪያ ወይም በፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ ነው ። ሰዉን ለመያዝ ምክንያታዊ ጥርጣሬ እና በመረጃ የተደገፈ መሆን አለበት። ማንኛውም ሰው በነፃነት የመኖር እና ከኢሰባዊ አያያዝ የመጠበቅ መብት አለው። የተያዘ ሰው በህግ የተጠበቁለትን ሰብአዊ መብቶቹ ሊከበር ይገባል። ሰዎችን ከመያዛቸዉ አስቀድሞ የሚከተሉት ሁኔታዎች መመዋላታቸውን ማረጋገጥ ይገባል። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 17 ማንኛዉም የተያዘ ሰዉ በህግ ለተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ ክስ ሊቀርብበት እንዲሁም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም ። በዚሁ ህግ አንቀጽ 18 መሰረት ማንኛዉም የተያዘ ሰዉ ኢሰብአዊ ከሆነ ጭካኔ ከተሞላበት እና ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ የመከልከል መብት አለዉ። ሰዉን ለባርነት፣ ለግዴታ አገልጋይነት፡ ለግዴታ ስራ እንዲሁም በሰዉ መነገድ ወንጀል የተከለከለ ነው። ነገር ግን በእስራት ላይ ያለ ሰዉ የተጣለበትን የግዴታ ሥራ፣ ለወተዳራዊ አገልግሎት፣ በአስከዋይ ጊዜ የሚጣሉ ግዴታዎች እንዲሁም ለልማት ስራዎች ሰዉ ተገዶ ሊሰራ ይችላል። በተመሳሳይ አንቀጽ 19 መሰረት የተያዙ ሰዎች ለምን እንደተያዙ፣ የተያዙ ሰዎች ያለመናገር መብት እንዳላቸዉ፣ የሚሰጡት ቃል በፍርድ ቤት ማስረጃ እንደሚሆንባቸዉ፣በሚገባቸዉ ቀንቀ ሊነገራቸዉ ይገባል። ፍርድ ቤት በ48 ሰኣት ዉስጥ ቀርበዉ ፍርድ ቤቱ የተጠረጠሩበት ጉዳይ ለመያዝ የሚያበቃ ስለመሆኑ ማብራሪያ የመጠየቅ፣ መርማሪ ፖሊስ ወይም የያዛቸዉ አካል የተያዙበትን ጉዳይ ካላሰረደ ፍ/ቤቱ የአካል ነጻነት እንዲሰጣቸዉ፣ ተገደው ቃል እንዳይሰጡ ያለመገደድ እንዲሁም በዋስ የመዉጣት ህገ መንግስታዊ መብት አላቸዉ። የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 19 (6) የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው ቢገለጽም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ለማዘዝ እንደሚችል በግልፅ ተመልክቷል። በመርህ ደረጃ ዋስትና መብት ሲሆን የዋስትና መከልከል ግን በህግ ወየም በሁታዎች ይሆናል። ስለሆነም የዋስትና መብት በህግ ሊከለከል የሚችል በመሆኑ ፍጹማዊ መብት አይደለም።[54]

---

[54] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 17፣ 18 እና 19

### 3.3.2 በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

ከቃሉ መረዳት እንደሚቻለው በጥበቃ ስር ያሉ ማለት በፖሊስ ጣቢያ በጊዜያዊነት ወይም በማረሚያ ቤት ፍርድ እስኪያገኙ ድረስ የተያዙ፣ ተከሰው በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ናቸው። በጥበቃ ስር ያሉ ሰዎች ከተያዙ በኃላ በአሳማኝ ምክንያት ዋስትና የተነፈጉ ሲሆን፣ ዋስትና ተፈቅዶም መከፈል ሲያቅታቸው፣ ተጨማሪ ግዜ ቀጠሮ ለምርመራ ሲባል ከተሰጠ እና ቢወጡ ማስረጃ በማጥፋት ፍትህ እንዳይጓደል ሲባል የሚቆዩ ናቸው። በፍርድ የታሰሩ ማለት ደግሞ የፍርድ ሂደት አልቆ በፍርድ ቤት ፍርድ ተሰጥቶባቸው በመፈጸም ያሉ ሰዎች ናቸው።

በጥበቃ ሥር ያሉ እና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖትና ከህግ አማካሪዎቻቸው እንዲሁም ከሃኪሞቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸው እድል የማግኘት መብት አላቸው[55]። እንዲሁም የተያዙ ሰዎች በጥበቃ ስር ሲቆዩ ንጹህ ሆኖ የመገመት መብት፣ ያለህጋዊ ሥነ-ሥርዓት ነጻነታቸውን ያለማጣት/ያለመነፈግ፣ የመሰማት፣ ፈጣን፣ ውጤታማና ሚዛናዊ ፍትሕ የማግኘት መብት በህገ መንግስቱ እውቅና ተሰጥቶቻዋል።

### 3.3.3 የተከሰሱ ሰዎች መብት

የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኃላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት የመቅረብ እና ለህዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመዳኘት መብት፣ በፍርድ ሂደት በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፤ እንዲሁም በምስክርነት እንዲቀርቡ ያለመገደድ፤ የቀረበባቸውን ማስረጃ የመመልከት፤ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፤መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ (የማስቀረብ) እና ምስክሮች እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት፤ በመረጡት የህግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትህን የሚያጓድል ሲሆን ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት ፤ ጉዳዩን በሚመለከተው ፍርድ ቤት ትዕዛዞች እና ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ፤ ክርክሩ በማይረዱት ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግስት ወጪ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ሥር ተደንግጎ ይገኛል።[56]

### 3.3.4 በህይወት የመኖር መብት

በህይወት የመኖር መብት ከሰዎች ልጆች የተፈጥሮ መብት አንዱ ነዉ። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 14 መሰረት ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ፍጡር በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት

---

[55] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 21

[56] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 20

የመኖር መብት ያለው መሆኑ ተደንግጓል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀፅ 15 መሰረት ማንኛውም ሰው በህይወት የመኖር መብት እንዳለው ገልፆ በህግ የተደነገገ ከባድ ቅጣት ካለ ግን ይህ በህይወት የመኖር መብት እንደሚነሳ ገደብ አስቀምጧል።

የሞት ቅጣትን አስመልክቶ ቅጣቱ በተወሰኑና እጅግ ከባድ በሆኑ ወንጀሎች ላይ ብቻ እንዲጣል የሚደረግ ሆኖ ቅጣቱ በሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ከጸደቀ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን ቅጣቱ የተወሰነበት ሰው ይቅርታ ወይም ምህረት እንዲደረግለት ሊያመለክት የሚችልበት ስርዓት ተዘርግቷል። የሞት ቅጣት ዕድሜያቸው 18 አመት ባልሞላ ህጻናትና ነፍሰ ጡር ሴቶች ላይ እንዳይፈጸም በህግ ተደንግጓል። የሞት ቅጣት ሲፈጸም ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ መሆን እንደማይገባና የሞት ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት በተቀጪው ላይ ማናቸውንም የስቃይ፣ የበቀል እርምጃ ወይም የአካል ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ የተከለከለ መሆኑ ተደንግጓል[57]። በተጨማሪም በህይወት የመኖር መብት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ገደብ ሊጣልበት የሚችልና ሰዉ በዚህ ጊዜ ህይወቱን ሊያጣ ይችላል።

### 3.3.5 የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ ህገመንግስታዊ መብት አለው። የአካል ደህንነት ከመጠበቅ ጋር ተያይዞ መነሳቱ የማይቀረው ሌላው ሰብአዊ መብት ኢ-ሰብአዊ አያያዝ መከልከል የሚለው በአንቀፅ 16 እና 18 ስር እናገኘዋለን። ይኸውም ማንኛውም ሰው የአካል ደህንነት መብት ያለው መሆኑንና ከማንኛውም ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢ-ሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት፣ በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት የመያዝ እና ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር ክልከላ እንዲሁም በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ሥራ የማሰራት ክልከላዎችን መብት አለዉ። በተጨማሪም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ብሔራዊ ህጎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ በመደረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን አገራችን መብቱን ለማስከበር የሚያስችሉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን አጽድቃ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች። የአካል ደህንነት መብት ከአከል ነጻነት ጋር የተያያዘ ነዉ። የተያዘ ሰዉ በፍርድ ቤት ቀርቦ የአካል ነጻነቱ እንዲረጋገጠለት( habus corpus) የመጠየቅ መብት አለዉ።[58]

### 3.3.6 የነፃነት መብት

ነጻነት የሰዉ ልጅ ሰዉ በመሆኑ ብቻ በተፈጠሮ የተቸረዉ መብት ነዉ። ነጻነት ሲባል የመንቀሳቀቅ፣ የመደራጀት፣ የመምረጠና መመረጥ፣ የመስራት፣ ንብረት የማፍራት፣ የመናገር፣ሃሳብን በነጻነት የመያዝ እና ሃሳብን በተለያዩ መንገዶች የመግለጽ፣ ማዳበር፣ ማስተማር ወዘተ ያጠቃልላል። ስለሆነም

---

[57]በ1996 ዓ.ም የወጣዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 117

[58] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 16፣ 20

ማንም ሰው በህግ ከተደነገገው ውጭ ነፃነቱን ሊያጣ አይችልም። ለምሳሌ ወንጀል የሰራ ሰዉ በጊዚያዊነት ወይም በቀዋሚነት የመንቀሳቀስ መብቱን ሊያጣ ይችላል። የተፈረደበት ሰዉ ተዘዋዉሮ የመስራት መብቱ ተገድቦ በማረሚያ ቤት ሊቆይ ይችላል። ነገር ግን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 17 ማንኛዉም የተያዘ ሰዉ በህግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ ክስ ሊቀርብበት እንዲሁም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይችል ህጋዊ እዉቅና ተሰጥቶታል።

### 3.3.7 የእኩልነት መብት በኢትዮጵያ ህገ መንግስት

እኩልነት ስንል ሁሉም ሰዎች ሰዉ በመሆናቸዉ ብቻ በህግ ፊት እኩል ስለመሆናቸው የሚያረጋግጠ መብት ነዉ።

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 25 መሰረት ማንኛውም ሰዉ የዘር፣የብሔር፣ብሔረሰብ፣ቀለም፣ፆታ፣ ቋንቋ፣ሀይማኖት፣ፖለቲካ፣ማህበራዊ አመጠጥ፣የሀብት፣የትውልድ ወይም ሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግለታል።

በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ እንደምናገኘው እኩልነትን ሲገልፅ እኛ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች የግለሰብና የብሄር፣ ብሄረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸውን፣የፆታ እኩልነት መረጋጋጡ፣ባህሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረግ አስፈላጊነት ፅኑ እምነት እንዳላቸዉ በአፅኖት አስፍሯል። ለአብነት፡- በህገ መንግስቱ አንቀፅ 7 በህገ መንግስቱ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ እንደሚያካትት እና እንዲሁም በአንቀጽ 36 ሴቶች ከወንዶች እኩል መሆናቸውን የሚደነግጉ የህግ አንቀፆች ለእኩልነት መብት የተሰጠውን እውቅና ያመለክታሉ።በሌላ በኩል ስለ አስቸኳይ ግዜ አዋጅ በሚደነግገው አንቀፅ 93(4)ሐ ስር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ ስር የሚያወጣቸው ድንጋጌዎች እና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በአንቀፅ 25 የእኩልነት መብት ላይ ገደብ እንደማይጣል መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም በየትኛዉ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ የእኩልነት መብት የተረጋገጠ ነዉ። ዜጎች በሀገሪቱ ዉስጥ በሚገኙ የማህበራዊ፣ የፖለቲካዊ፣ የኢኮኖሚ እንዲሁም የባህል ጥቆሞች እኩል የመጠቀም መብት አላቸዉ

በአጠቃላይ የተሻለ እኩልነት መብትን ለማረጋገጥ ሁሉም የመንግስት አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እንዲሁም ህብረተሰቡ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይገባል። በዚሁ መሰረት የሕግ አውጭ በየግዜው የሚወጡ ህግጋት የሁሉንም ዜጋ እኩልነትን ያማከለ ህግ እንዲያወጣ፤ አስፈፃሚ አካላት ደግሞ የህጎችን ተፈጻሚነት ሳይዛነፍ እንዲከበር ካደረገ እና የህግ ተርጓሚ አካላትን ደግሞ ህግንና ህሊናቸውን ተጠቅመው ለትክክለኛ ፍትህ እንዲሰሩ የተመቸ ሁኔታዎችን በመፍጠር ከአድሎዊ የፀዳ አሰራር በማከናወን የተገልጋይ እኩልነት ማረጋገጥ ይገባቸዋል።[59]

---

[59] በ1987 ዓ.ም የወጣዉ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 25

### 3.3.8 የክብርና የመልካም ስም መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩ እና መልካም ስሙ የመጠበቅ መብት አለው። የራሱን ስብእና ከሌሎች ዜጎች መብቶች በተጣጣመ ሁኔታ የማሳደግ መብት አለው። ማንኛውም ሰው በማንኛውም ቦታ በሰብአዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት እንዳለው በህገ መንግስቱ ተደንግጓል።[60]

### 3.3.9 የግል ህይወት መከበርና የመጠበቅ መብት

በህገ-መንግስቱ ማንኛውም ሰው ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው ይልና ግላዊነትን ሲያብራራ መብቱ መኖሪያ ቤቱን፣ሰውነቱን እና ንብረቱን ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለን ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል። ማንኛውም ሰው በግል የሚፅፋቸውና የሚፃፃፋቸው፣በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎችን፣በተሌግራም ወዘተ መብትን ያካትታል። ይሁን እንጂ አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር እና ለሀገር ደህንነት፣ ሰላም፣ ወንጀልን ለመካላከል ኣላማ እናየሌሎቹን መብትና ነጻነት ለማክበር የግል ህይወት መብት ሊጣስ ይችላል።[61]

### 3.3.10 የሀይማኖት፣ የዕምነትና የአመለካከት ነፃነት

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 27 ላይ ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት እንዳለው በግልፅ ያስቀምጣል። ይህም መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል።የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም እንደሚችሉና ወላጆችና ህጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታዊና የመልካም ሥነ-ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት እንዳላቸው ተቀምጧል። ይህ መብት የሃይማኖት እና የባህል ፍርድ ቤት የማቀዋቀዋም መብትን ያጠቃልላል (ህገ መንግሰት አንቀጽ 78/5/ እና 34/5/)።[62] በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 11 መሰረት መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን፤ መንግስት በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳዮች ላይ ጣልቃ እንዳይገባ ከመከልከሉም ባሻገር መንግስታዊ ሃይማኖት እንደማይኖር ይደነግጋል። ነገር ግን ለልማት በሰላም እንዲሁም በሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮች ጋራ የሚሰራበት አግባብ አለ።

---

[60] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 24

[61] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 26

[62] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 11፣27፣ 34/5/ ፣ 78/5/

### 3.4 በኢ.ፌድሪ ህገ መንግስት ዲሞክራሲያዊ መብቶች

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በክፍል ሁለት ምእራፍ ስር ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሚል ከአንቀጽ 29 እስከ 44 ባሉት ድንጋጌዎች መብቶችን ደንግጎ ይገኛል። ምንም እንኳን ርዕሱ ዲሞክራሲያዊ መብት ይበል እንጂ መሰረታዊ የሚባሉ እንደ ህፃናትና የሴቶች መብቶች ከማካተቱም በተጨማሪ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተብለው የሚታወቁ መብቶችን አካቶ የሚገኝ ነው።በዓለም ዐቀፉ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋዎች ህግ መሰረት ሁሉም የሰዉ ልጆች መብቶች ሰብዓዊ ናቸዉ። መብቶች ዲሞክሪያሲያዊ እና ሰብዓዊ ተበለዉ ሊከፈሉ እንደማይገባ ከበድንጋጌዉ መረዳት ይቻላል።

#### 3.4.1 የአመለካከትና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

ሰው ከሌሎች ህይወት ካላቸው ፍጡራን የሚለየው በማሰቡ ነው። እያንዳንዳችን የሚኖረን የህይወት ልምድና ሌሎች አካባቢያዊ ሁነቶች አስተሳሰባችን ሊወስኑ የሚችሉ እንደመሆናቸው አመለካከታችንንና አስተሳሰባችን የተለያየ መሆኑ የገሀዱ አለም እውነታ ነው። በመሆኑም የአመለካከትና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት አለም አቀፍ እውቅና የተቸረው መብት ነው። የህገ መንግስቱ አንቀጽ 29፣ ሀገራችን አባል የሆነችበት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights, UDHR) አንቀፅ 19 እና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት (International Covenant on Civil and Political Rights, ICCPR) በአንቀፅ 19 መብቱ የሚያካትታቸውን ነገሮች በዝርዝር ደንግገዋል። ይኸውም ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት የመያዝ እና ሀሳቡን የመግልፅ መብት እንዳለው የደነገጉ ሲሆን ይህ መብት ወሰን ሳይደረግበት በሀገር ውስጥ ሆነ ከሀገር ውጪ በቃል፣ በፅሁፍ፣ በህትመት፣ በስነጥበብ መልክ ወይም በማንኛውም በመረጠው የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም መረጃ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን የሚያካትት ነው። በዚህም መሰረት ማንኛውም አካል ይህንን መብት የማክበር ሀላፊነት አለበት። ሆኖም ይህ መብት በዘፈቀደ እንደፈለጉ የሚሆኑበት ሳይሆን ይልቁንም በሀላፊነት መንፈስ ሊከወን የሚገባ ነው ።

አለፍ ሲልም በህግ ገደብ ሊጣልበት የሚችል ሲሆን ይህ ገደብ የሌሎች ሰዎችን ክብር ለመጠበቅ፣ የህዝብ ሰላምና ደህንነትን እንዲሁም ሞራልን ለመጠበቅ ሲባል የሚደረግ ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ የህግ መንግስቱ አንቀፅ 29(6) ይህ መብት ለወጣቶች ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሊገደብ እንደሚችል ደንጓል። በተጨማሪም የጦርነት ቅስቀሳዎችና ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ ቅስቀሳዎች እንደሚከለከሉም ተመልክቷል። ለምሳሌ የጥላቻ ንግግር የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1185/2012 በዚህ መብት ላይ በገደብነት የተቀመጠ አዋጅ ነው። ይሁንና ገደቡ መብቱ ጥቅም ላይ እንዳይውል በማድረግ ወይም በሚሸራርፍ መልኩ ሳይሆን የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱ ሊያስከትል በሚችለው

አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርቶ በሚወጡ ህጎች ብቻ መሆን እንዳለበት ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 29(6) መረዳት ይቻላል። በሌላ አገላለፅ ገደብ የሚለው በጠባቡ የሚተረጎምና የመብቱን ተግባራዊነት የሚጎዳ መሆን የለበትም። ከአለም አቀፍ ስምምነቶቹ ሰፋ ባለ መልኩ ህገ መንግስቱ ስለ ፕሬስ ነፃነትና በመንግስት በሚተዳደሩ ሚዲያዎች ጭምር የተለያዩ አስተያየቶችን በሚስተናግድ መልኩ መመራት እንዳለበት በመንግስት ላይ ግዴታ ጥሏል።[63]

### 3.4.2 የመሰብሰብ ና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

ሰው በባህሪው ማህበራዊ ፍጡር እንደመሆኑ ለተለያዩ ጉዳዮች ማህበራዊ መስተጋብሮች እንደሚኖሩትና ለተለያዩ አላማዎች የመሰብሰና ሰላማዊ ሰልፍ ማደረግ ይፈልጋል። ለመሰብሰብ ኣላማ ብቻ ሳይሆን ተቃውሞም ሆነ ድጋፍ ሲኖረው ሰላማዊ ሰልፍ መውጣትና ሀሳቡን በጋራ ማሰማት ሊፈልግ ይችላል። ይህን ታሳቢ ያደረጉት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶችን እንዲሁም በሀገራችን በሥራ ላይ ያለው ህግ መንግስት እውቅና እና የህግ ጥበቃ የሚሰጠው መብት እንዲሆን አድርገዋል። በህግ መንግስቱ በአንቀጽ 30 ማንኛውም ሰው በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው ደንግጓል። ሆኖም ይህን ማድረግ የሚቻለው መሳሪያ ሳይዙ በሰላማዊ መንገድ ብቻ ነው። ከቤት ውጪ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በህዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝብን ሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርአቶች ሊደነገጉ እንደሚችሉም ተደንግጎ ይገኛል።

ከላይ የአመለካከትና የሀሳብ ነፃነት መብት ላይ እንደተገለፀው ሁሉ የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰው ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎችን እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል ህግጋት ሊወጡ እንደሚችሉና ተላልፎ መገኘትም ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ ከድንጋጌው መረዳት ይቻላል። የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት (ICCPR) በአንቀፅ 21 መሰረት የመሰብሰብ መብት ለሀገር ደህንነት፣ ለህዝብ ደህንነት፣ ለህዝብ ጤና እና ሞራል እንዲሁም የሌሎችን መብትና ነፃነት ለመጠበቅ ሲባል በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑ እና በህግ ከተደነገጉ ገደቦች ውጪ ምንም አይነት ገደብ ሊጣልበት እንደማይገባ በግልፅ አመላክቷል።[64]

---

[63] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 29፣ (Universal Declaration of Human Rights, UDHR) አንቀፅ 19 እና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት (International Covenant on Civil and Political Rights, ICCPR)፣ የጥላቻ ንግግር የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1185/2012

[64] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 30፣የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት (ICCPR) በአንቀፅ 21

### 3.4.3 የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም አላማ በማህበር የመደራጀት መብት እንዳለው ህገ መንግስቱ አንቀፅ 31 የደነገገ ሲሆን  ነገር ግን ህግን በመጣስ የተመሰረቱ ድርጅቶች የተከለከሉ መሆናቸውን አመልክቷል። የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት (ICCPR) በአንቀፅ 22 መሰረት የመሰብሰብና የመደራጀት መብት ለሀገር ደህንነት፣ ለህዝብ ደህንነት፣ ለህዝብ ጤና እና ሞራል እንዲሁም የሌሎችን መብትና ነፃነት ለመጠበቅ ሲባል በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑ እና በህግ ከተደነገጉ ገደቦች ውጪ ምንም አይነት ገደብ ሊጣልበት እንደማይገባ በግልፅ አመላክቷል። በስምምነቱ መሰረት የሰራተኞች ማህበር ማቋቋም እና ፍላጎታቸውን ማስጠበቅ መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። በሌላ በኩል መደራጀት ብቻ ሳይሆን ያለፈቃድ የማህበር ወይም ድርጅት አባል አለመሆንም መብት መሆኑን ከአለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀፅ 20 መረዳት ይቻላል።[65]

### 3.4.4 የመዘዋወር መብት

የህገ መንግስቱ አንቀፅ 32 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በህጋዊ መንገድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የውጪ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወር፣ የመኖሪያ ቦታ የመመስረት እና በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት እንዳለው እንዲሁም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወደ ሀገሩ የመመለስ መብት እንዳለው ይደነግጋል።

ከሰብአዊ መብት የቃልኪዳን ሰነዶች ቀደምት የሆነው ዓለም አቀፍ ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ወይም (UDHR) አንቀፅ 13 ስለመንቀሳቀስ መብት ደንግጎ ይገኛል። በዚህ ስምምነት መሰረት የመንቀሳቀስ መብት ማንም ሰው በየሀገሩ ውስጥ የመንቀሳቀስና የመኖር መብትን እንዲሁም የራሱን ሀገር ጨምሮ ሀገርን የመልቀቅ እና የመመለስ መብትን የሚያካትት ነው። ሌላው የሰብአዊ መብት ሰነድ የሆነው የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች (ICCPR) ይህን መብት በተሻለ እና ግልፅ በሆነ መልኩ በዝርዝር የያዘ ነው። በኮንቬንሽኑ መሰረት የመንቀሳቀስ መብት ማንም ሰው ህጋዊ በሆነ መልኩ በአንድ ሀገር ግዛት ውስጥ የመንቀሳቀስና የመኖሪያ ቦታውን የመምረጥ፣ የራሱን ሀገር ጨምሮ ሀገርን ለቆ የመውጣት እንዲሁም ወደ ሀገሩ እንዳይገባ ለማድረግ ከሚፈፀም ካልተገባ ጫና ነፃ ለመሆን ያለውን መብት የሚያካትት ሲሆን ይህ መብት በህግ ከተመለከተው ውጪ ሊገደብ እንደማይችል ይገልፃል።

ከአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች በተጨማሪ በአህጉር ደረጃ የወጣው የአፍሪካ የሰብአዊና የህዝቦች መብት ቻርተር ወይም African Charter on Human and Peoples Rights ከአለም አቀፍ ሰነዶቹ ሰፋ ባለ መልኩ በአንቀፅ 12 በዝርዝር አካቷል። በዚህም ስምምነት መሰረት የመንቀሳቀስ

---

[65] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 20

መብት ማንም ሰው ህጋዊ በሆነ መልኩ በአንድ ሀገር ግዛት ውስጥ የመንቀሳቀስና የመኖሪያ ቦታውን የመምረጥ፣ የራሱን ሀገር ጨምሮ ሀገርን ለቆ የመውጣትም ሆነ የመመለስ መብትን ያካተተ ነው።
በተጨማሪም ከአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች በተለየ መልኩ በAfrican Charter on Human and Peoples Rights የመንቀሳቀስ መብት ሶስት ተጨማሪ ነጥቦችን ያካተተ ሆኖ እናገኘዋለን። ይኸውም ማንም ሰው ባለበት ሀገር ተገቢ ያልሆነ በደል (persecution) የሚደርስበት ከሆነ በአለም አቀፍ ህግ እና በሚሄድባቸው ሀገራት ህግ መሰረት በሌሎች ሀገራት ጥገኝነት የመጠየቅ እና በቻርተሩ አባል ሀገራት ውስጥ በህጋዊ መንገድ የገባ ዜጋ ያልሆነ ሰው በህግ መሰረት ከሚወሰድ ውሳኔ በስተቀር በገባበት ሀገር መቆየትን የሚያካትት ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሀገሩ ዜጋ ያልሆኑ ሰዎች ወይም የውጪ ዜጎችን ዜግነትን፣ ዘርን፣ ጎሳን ወይም ሀይማኖትን መሰረት ያደረገ የጅምላ ማባረር የተከለከለ ነው።[66]

### 3.4.5 የዜግነት መብት

ዜግነት የአንድ ሀገር አባልነትን፣ዜግነትን የሚያረጋግጥ ነው። ዜግነት የሚገኝባቸው ሁኔታዎች እንደሀገራቱ ህግ የሚለያይ ነው። በአዋጅ ቁጥር 378/1996 መሰረት በሀገራችን ኢትዮጵያ ዜግነት በትውልድ ወይም በህግ ሊገኝ ይችላል። ወላጆች ወይም ከወላጆች አንዱ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ካለው ወይም ልጁ ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝቶ ወላጆቹ ካልታወቁና የውጪ ዜጋ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ከኢትዮጵያዊ እንደተወለደ ተቆጥሮ በትውልድ ዜግነት ማግኘት ይችላል። ዜግነት በህግ የሚሰጠው ለውጪ ሀገር ዜጎች ሲሆን በአዋጁ ከአንቀፅ 5 እስከ 12 የተጠቀሱትን ቅድም ሁኔታዎች ሲያሟላ የሚሰጥ ይሆናል።[67] ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማይቃረን መንገድ በሚወጣ ህግና በሚደነገግበት ሥርዓት መሰረት የኢትዮጵያ ዜግነት ለውጪ ሀገር ሰዎች ሊሰጥ እንደሚችል በህገ መንግስቱ አንቀፅ 33 ጭምር የተካተተ ጉዳይ ነው።
በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ዜግነት ያገኘ ማንኛውም ሰው ኢትዮጵያዊ ዜግነት በህግ የሚያስገኘውን መብት፣ ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለው። አለፍ ሲልም ዜግነቱን ወደ ሌላ አገር የመቀየር መብት ያለው ሲሆን ይህም በፈቃዱ የሚያደርገው እንጂ ያለፈቃዱ ሊገፈፍ አይችልም። የውጪ ዜጋ ጋር ጋብቻ መፈፀም ያለ ግለሰቡ ፈቃድ ዜግነቱን የሚያሳጣ አይሆንም። የዜግነት መብት ከላይ በጠቀስናቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ጭምር ጥበቃ የተደረገለት መብት ነው።

---

[66] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 32፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ወይም (UDHR) አንቀፅ 13

[67] አዋጅ ቁጥር 378/1996

3.4.6 የመምረጥና የመመረጥ መብት

ይህ መብት በዋናነት ከፖለቲካ መብት ጋር የተያያዘ ነው። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያለምንም ልዩነት

- በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ
- እድሜው 18 ሲሞላው የመምረጥ
- በማናቸውም የመንግስት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ መምረጥና የመመረጥ

መብት ያለው ሲሆን ይህ ምርጫ ሁሉን አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልፅበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል። ከዚህም በተጨማሪ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሰራተኞች፣ በአሰሪዎች፣ በንግድ፣ በሙያ ማህበራት ተሳታፊ ለመሆን ድርጅቶቹ የሚጠይቁን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ዜጋ በፍላጎቱ አባል መሆን መብቱ ሲሆን በእነዚህ ድርጅቶች ለሀላፊነት ቦታዎች የሚደረጉ ምርጫዎች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፈፀም እንዳለባቸው ተደንግጓል።

3.4.7 የህፃናት መብት

ሕፃናት እንደ ማንኛውም ተፈጥሮአዊ ሰው መብት ያላቸው ቢሆኑም በሥነ-አዕምሮአዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲሁም አካላዊ ብቃት ሁኔታ ምክንያት ተጨማሪ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው ዓለም አቀፍ ፣ ህጉር አቀፍ እና በአገር ደረጃ ወጡ ሕጎች ተደንግገዉ እናገኛቸዋለን።

3.4.7.1 የህፃን ትርጉም

ህፃን ማን ነው ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ አገራት ሕጎች የተለያየ ትርጓሜ ሰጥተዋል። ለሕፃንነት የሕግ ትርጓሜ መስጠትን አስፈላጊ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ዋነኛው የመብትና ግዴታ ወሰን (scope of rights and duties) ለማወቅ ስለሚያስችል ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ ሕጻናት ለአደጋ ተጋላጭ ከመሆናቸው አኳያ ልዩ ጥበቃ (special protection due to vulnerability) ስለሚያስፈልጋቸው ነው።

ምንም እንኳን አንድ ወጥ የሆነ የሕፃን ትርጓሜ ባይኖርም ሕፃን የሚለው ቃል ብዙ አገራት ዕድሜን ግምት ውስጥ ያስገባ ትርጉም ይጠቀማሉ። ከዚህም ባሻገር በአንዳንድ አገሮች ሕፃን ለሚለው ትርጓሜ ለመስጠት ማኅበራዊ አረዳድን (social construction of age) ግምት ውስጥ ያስገባሉ፣ ለምሳሌ በጉርምስና ወቅት የሚታዩ አካላዊ ለውጦች እና የድምፅ መጎርነን እንደ አንድ ማሳያ ይጠቀማሉ።

በዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 1 የተመለከተው ዕድሜን መሠረት ያደረገ ትርጉም ሲሆን፣ "ሕፃን ማለት ማንኛውም ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ የተፈጥሮ ሰው" እንደሆነ ይገልፃል።[68] ሆኖም በምን ጉዳይና ምን ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ዝቅ ማድረግ ወይም

[68] በዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 1

18 ዓመት ሳይሞላ ለአካለ መጠን መድረስ እንደሚቻል ባያስቀምጥም አገራት በሚያወጡት ሕግ መሠረት ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች መውረድ የሚቻልበት አጋጣሚም እንዳለ በኮንቬንሽኑ ተገልጧል። በዚሁ መሰረት ለምሳሌ በኢትዮጵያ ለጋብቻ ሊባል ማለትም ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ የአንዳቸው ወላጆች ወይም አሳዳሪ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት ፍትህ ሚኒስትሩ ከመደበኛ የጋብቻ እድሜ (18 ዓመት) ከሁለት አመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ ሊፈቅድ ይችላል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 7/2/። [69]

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሕፃኑ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንደወጣ (emancipated) ይቆጠራል። ይህ የዕድሜ ጣራ መድረሻ (አሥራ ስምንት ዓመት) ከየት እንደሚጀምር በግለፅ የተደነገገ ነገር ባይኖርም በኮንቬንሽኑ መግቢያ ላይ እንደተገለፀው ከመወለድ በፊትም ማለትም በጽንስ ወቅትም ጥበቃ እንዳለ ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል (protection may be given before birth during conception)።

በሌላ በኩል የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር አንቀፅ 2 ሕፃን ለሚለው ትርጓሜ የሚከተለውን ደንግጓል። ለዚሁ ቻርተር ዓላማ ሲባል "ሕፃን ማለት ማንኛውም ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ የተፈጥሮ ሰው ነው።"[70]

በኢትዮጵያ ለሕፃን ያለውን ትርጉም ስንመለከት ሀገሪቱ ፌዴራላዊ ስርዓት የምትከተል በመሆኑ የተለያየ የሕፃን ትርጓሜ ሊኖር የሚችልበት ዕድል ተፈጥሯል። በ1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢ.ፌ.ዲ.ህ መንግሰት ዕውቅና በመስጠት፣ የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት የየራሳቸውን የቤተሰብ ሕግ እንዲያወጡ ይፈቅዳል። በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 215 መሠረት አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው ሲል ያስቀምጣል።[71] ይህ የዕድሜ መነሻ በዚህ ሕግ በግልፅ ባይቀመጥም በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1 እና 2 ከመወለድ በፊት ገና ለተፀነሰ ልጅ ጥበቃ ተደርጓል። ነገር ግን ሕፃኑ ሲወለድ በሕይወት መወለድ እንዳለበትና ቢያንስ ለ48 ሰዓት በሕይወት ሊቆይ የሚችል (viable) ሊሆን እንደሚገባ በፍትሀ ብሄር ሕግ አንቀፅ 2 እና 4 ተደንግጓል።[72] በወንጀል ህግ አንቀጽ 52፣53 እና 56 ህጻናት ወንጀል ሲፈጽም በምን አግባብ እንደሚጠየቁ ህጉ ሲያስቀምጥ በእድሜ ከፋፍሎ አስቀምጠዋቸዋል። እስከ 9 አመት ያሉትን በወንጀል እንደመየጠየቁ፣ ከ9 እስከ 15 ዓመት በወጣት አጥፊዎች

---

[69] በ1992 የወጣዉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 7/2

[70] የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር አንቀፅ 2

[71] 1992 የወጣዉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 215

[72] በ1952 ዓ.ም የወጣው የፍትሐብሔር ሕግ አንቀፅ 1 እና 2

እንደሚጠየቁ፣ እንዲሁም ከ15 እስከ 18 ያሉትን አጥፊዎች ደግሞ መደበኛ የህግ ቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ገልጾ አስቀምጠዋል።[73]

3.4.7.2 የህፃናት መብት መርሆዎች

የሕፃናት መብቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በማሰብ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እንዲሁም የአገር አቀፍ ሕጎች መርሆዎችን ወጥተዋል። እነዚህ መርሆዎች ደግሞ የሕፃናት መብቶች ለማስከበር እና ማስተግበር ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው። ከእነዚህ መርሆዎች ዋነኛው የሆነው ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት (Best interest of the child) የሚለው መርህ ነው። በዚህ ረገድ እ.ኤ.አ በ1959 የወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሕፃናት መብቶች መግለጫ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕፃናት ጥቅም እና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት የሚለውን መርህ አካቶ የወጣ ዓለም አቀፍ ሰነድ ነው፡ ፡ በመሆኑም ሕፃናት ነክ ውሳኔዎች ሲወሰኑ(ለምሳሌ ወላጆቻቸው የሚለያዩ ከሆነ ከማን ጋር መኖር እንዳለባቸው ሲወሰን) ውሳኔ ሰጭ አካላት ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት የሕግ ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። በተያያዘ ሁኔታ የኮንቬንሽኑ አራት ዋና ዋና መርሆዎች በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ውስጥ የተዘረዘሩትን ሌሎች መብቶች ለማስፈፀም እና ለመተርጎም የሚያገለግሉ ናቸው ። እነርሱም

ሀ) የእኩልነት መብት (The Non-discrimination clause)፣ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 2

ለ) ለህፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት (The Best Interest of the Child) የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 3)

ሐ) የመሳተፍ መብት (The Right to participation) ኮንቬንሽኑ አንቀጽ 12 እና

መ) በሕይወት የመኖር እና የመልካም አስተዳደግ መብት (The Right to life, survival and development)፣ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 6፣ ናቸው።

3.4.7.3 መሰረታዊ የህፃናት መብቶች በኢትዮጵያ

ህገ መንግስት መርህን የሚያስቀምጥ ጥቅል ህግ ከመሆኑ የተነሳ ለህፃንነት ትርጉም ያልሰጠና የእድሜ ገደብ ያላስቀመጠ ቢሆንም የህፃናትን መብት ዝርዝር በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 36 ስር ደንግጎ ይገኛል። እነሱም ማንኛውም ህፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት

1. በህይወት የመኖር መብት፣
2. ስምና ዜግነት የማግኘት መብት፣፣
3. ወላጆቹን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት መብት

[73] በ1996 ዓ፣ም የወጣዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 52፣53 እና 56

4. ጉልበት ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣በትምህርት፣በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ስራዎች እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመስራት የመጠበቅ፣
5. በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን ናቸው።[74]

በተጨማሪም በህገ መንግስቱ እንደተደነገገው ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል በጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት። ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግስት ወይም በግል እጓለ ማውታን ተቋሞች(የህፃናት ማሳደጊያዎች) ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው። እንዲሁም ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወላዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲህም መንግስት ለእጓለ ማውታን ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው እና በጉዲፈቻ የሚያድጉበት ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ፣ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ እንደሚያበረታታ ይደነግጋል። በአጠቃላይ ህፃናት የሚከተሉት አለም አቀፍ መሠረታዊ መብች ሊጠበቁላቸው ይገባል።

- ✓ የእኩልነት መብት:- በጾታ ፣ በዘር ፣ በጎሳ ፣ በቋንቋ ፣ በኢኮኖሚ አቋም ፣ በብሔር ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም አድሎዓዊ በሆነ በማንኛውም ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ልዩነቶች ሊደረጉ አይገባም።
- ✓ መብላት እና መጠለያ የማግኘት መብት:-ሁሉም ልጆች ለትክክለኛው እድገታቸው አስፈላጊ የሆነውን ምግብ የማግኘት እንዲሁም ከቤተሰቦቻቸው ጋር በሚኖሩበት ቤት የማግኘትና የመደሰት መብት አላቸው ።
- ✓ የትምህርት መብቶች:-ሁሉም ልጆች ችሎታቸውን ለማዳበር እና የራሳቸውን የወደፊት ዕድል ለመፍጠር ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው። ምክንያቱም ለትክክለኛው ሥነ-ልቦናዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገታቸው አስፈላጊ ነው ።
- ✓ የጤንነት መብት:- ልጆች ጤንነታቸውን ለመንከባከብ እና ለማቆየት እንዲሁም በሽታን ለመከላከል አስፈላጊ የሕክምና ክትትል እና እንክብካቤ ማግኘት አለባቸው ።
- ✓ በሕይወት የመኖር መብት፡- ሕፃናት ህይወታቸውን አደጋ ላይ ሊጥሉ ከሚችሉ ነገሮች የመጠበቅ እና የመቆየት( right of protection and survival) መብት አላቸው። በተጨማሪም በቂ የኑሮ ደረጃ (adequate standard of living) የማግኘት መብት አላቸው።

በአጠቃላይ ህፃናት በተለይ በእድሜያቸው ምክንያት ለተለያዩ አደጋዎች የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ስለሆነ መንግስት በሂደት(progressively) የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በፈቀደ መጠን የህፃናትን ደህንነት

[74]በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 36

ለማስጠበቅ የህፃናትን መብት ለማክበር፣ ለመጠበቅ እና ለማሟላት(to respect, to protect, and to fulfill) ግዴታ አለበት።

### 3.4.8 የሴቶች መብት

#### 3.4.8.1 የሴቶች መብት በአለም አቀፍ ህጎች

ሴቶች ባለፉት ጊዚያት አድሏዊ ልዩነት እየተደረገባቸው እና ሰብዓዊ መብቶቻቸው ሳይከበሩላቸው መቆየታቸውን ከታሪክ መመልከት እንችላለን። እነዚህን የመብት አለመከበር እና ፆታን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶችን ለማስወገድ በርካታ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና አገር አቀፍ ህጎች በስራ ላይ ውለው ይገኛሉ። ለሁሉም የሰው ልጆች ሰብዓዊ መብቶች እውቅናን ከሰጡት እንደ ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብት መገለጫ(UDHR)፣ ዓለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት(ICCPR)፣ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ፣ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት(ICESCR)፣እንዲሁም በልዩ ሁኔታ ለሴቶች መብት ልዩ ትኩረት ያደረጉት የሴቶች የፖለቲካ መብቶች ስምምነት(CPRW)፣በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ መግለጫ(Declaration on Elimination All Forms of Discrimination Against Women)የመሳሳሉ ሰነዶች ለሴቶች መብት እውቅና የሰጡ አለምአቀፍ ስምምነቶች ናቸው።

በኢትዮጵያ የሴቶች መብት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት ጀምሮ በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ውስጥ እውቅና ተሰጥቶት ይገኛል። እንዲሁም በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9/4 መሰረት ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ የህግ አካል ይሆናሉ በማለት የደነገገ በመሆኑ በስምምነቶቹ የተዘረዘሩትን የሴቶች መብት የማክበር እና የማስከበር ሀላፊነት በመንግስት ላይ ወድቋል ማለት ነው። መንግስት የሴቶችን መብት ለማክበር እና ለማስከበር ከሚወስዳቸው መሰረታዊ እርምጃዎች መካከል ለመብቶቹ በቂ የህግ ማዕቀፍ መስጠት ይገኝበታል። በዚሁ መሰረት ለሴቶች መብት ሰፊ ሽፋን ከሰጡ ህጎች የተሻሻለው የኢ.ፌ.ድ.ሪ የቤተሰብ ህግ ተጠቃሽ ነው። በክልሎችም እንደ ክልሎቹ ማህበረሰብ ነባራዊ ሁኔታ የቤተሰብ ህግ አውጥተው እየተገበሩ ይገኛል።

#### 3.4.8.2 የሴቶች መብት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክሪያሲያዊ ህገ መንግስት

በህገ መንግስቱ አንቀፅ 35 ስር እንደ ተደነገገው ሴቶች የሚከተሉት መብቶች አላቸው።

- ህገ መንግስቱ በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ እና በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፣
- በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች(affirmative measures) ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፣
- ከጎጂ ባሕል ተፅዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግስት ማስከበር አለበት፣

- የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደሞዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፣
- በብሄራዊ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፣
- ንብረት የማፍራት፣የማስተዳደር፣የመቆጣጠር፣የመጠቀምና የማስተላለፍ በተለይ መሬት በመጠቀም፣በማስተላለፍ፣በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፣
- የቅጥር ፣የስራ እድገት፣የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፣
- በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት እንዳላቸው ተገንግጎ ይገኛል።[75]

3.4.8.3 የሴቶች መብት በተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ

በአዋጅ ቁጥር 213/1992 ዓ.ም በወጣው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ መሰረት የተካተቱ የሴቶች መብቶችን ያቀፉ ድንጋጌዎችን ስንመለከት በጋብቻ ወቅት ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻን ለመመስረት ነፃ ፍቃዳቸውን መስጠት እንዳለባቸው ያስቀምጣል። ይህም መመዘኛ መሰረታዊ እና ጋብቻን በህግ ፊት እንዲፀና የሚያደርግ ነው። ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት በአብዛሀኛው የሀገሪቱ የገጠር ክፍል ጋብቻ የሚፈፀመው በተጋቢዎች ነፃ ፍቃድ ሳይሆን በቤተሰብ በተዘጋጀ ጋብቻ(arranged marriage) ሲሆን ሴቶች ከማይፈልጉት ሰው ጋር እንዲኖሩ የሚያስገድድ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም በቤተሰብ ህጉ የተጋቢዎች የጋብቻ እድሜ ለሁለቱም እኩል 18 ዓመት መሆኑ ተጋቢዎች የኑሮ ጫናን በእኩል ሀላፊነት እንዲጋሩ የሚያስችላቸው ነው።

ሌላው በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 49/1 ስር እንደተደነገገው ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው መከባበር፣ መተጋገዝ እና መደጋገፍ አለባቸው። ይህም ሴቶች ተገቢውን ክብር የማግኘት መብት እንዳላቸው አመላካች ነው። ቤተሰብ አመራርን በተመለከተ ባልና ሚስት እኩል መብት እንዳላቸው እና በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ፣ልጆቻቸውን በመልካም ስነ ምግባር እንዲታነፁ፣ተገቢውን ትምህርት እንዲቀስሙና ሀላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ መተባበር እንዳለባቸው በአንቀጽ 50 ስር ሰፍሮ ይገኛል።ይህም በቀድሞው የፍትሐ ብሄር ህግ የቤተሰብ አስተዳደሩን ለባል ሰጥቶ የነበረውን ያሻሻለ ህግ ሲሆን ሴቶች ከጋብቻ በፊት ያገኙትን የግል ንብረታቸውን፣በጋብቻ ውስጥ ያፈሩትን የጋራ ንብረታቸውን እንዲሁም ልጆቻቸውን የማስተዳደር መብት አላቸው።

[75] ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 35

ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሳቸው ቢቀበሉም አንደኛው ተጋቢ ሲጠይቅ ሌላኛው ተጋቢ ያገኘውን የገቢ መጠን የማሳወቅ ግዴታ አለበት። ይህም የሚያመለክተው ሴቶች የባሎቻቸውን ገቢ የማወቅ መብት እንዳላቸው ነው። እንዲሁም ሴቶች በጋብቻ ውስጥ እያሉ በቀጥታ በስጋ ወይም በጋብቻ ለሚዛመዷቸው ዘመዶቻቸው ማለትም ከጋብቻ በፊት ለነበራቸው ልጃቸው፣ለእናት፣ለአባት፣ለአያት፣ለእህት ወይም ለወንድማቸው የቤተሰብ ህጉ የሚያስቀምጠውን መስፈርት በመከተል ቀለብ የመስጠት መብት ያላቸው ሲሆን ከባላቸው ቀለብ የማግኘት መብትም አላቸው (የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 198 እና 49)።

በሌላ በኩል ሴቶች በፍቺ ወቅት ከጋራ ንብረታቸው እኩል የመካፈል መብት እንዳላቸው የሚያመለክተው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 90 ስር የተቀመጠው ድንጋጌ ነው። በመሰረቱ በፍቺ ጊዜ ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን መልሰው መውሰድ የሚችሉ እንዲሁም ንብረታቸውን በስምምነት መካፈል የሚቻል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም እኩል የሚካፈል ይሆናል። የንብረት ክፍፍሉም በአይነት ወይም በገንዘብ ሊደረግ የሚችል ሲሆን በአይነት ክፍፍሉ ሲገረግ ለእያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸው ንብረቶች እንዲያገኝ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። በመሆኑም ሴቶች በፍቺ ወቅት በንብረት ረገድ እኩል የተጠቃሚነት መብት አላቸው።

በተጨማሪም ፍቺ ሲወሰን የልጆች አጠባበቅና አያያዝን የሚመለከት ውሳኔ ፍርድ ቤት እንደሚሰጥ በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 113 ስር ሰፍሮ ይገኛል። በዚሁ መሰረት ልጆች ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ፣ ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው አጠባበቅ፣ስለቀለባቸውና ባጠቃላይ ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸውን ለመጠየቅ ስላላቸው መብት ይወስናል። ውሳኔውንም በሚወሰንበት ጊዜ ከሚያገናዝባቸው ጉዳዮች ዋናው ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት (Best interest of the child) መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ያለበት ሲሆን የልጆቻቸውን ዕድሜ፣ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸው በሚጠበቅበት ሁኔታ መሆን አለበት። ስለሆነም ለምሳሌ ልጃቸው በጣም ህፃን በመሆኑ የእናቱ እንክብካቤ ይበልጥ የሚያስፈልገው ከሆነ ሴቷ ህፃኑን/ኗን የማሳደግ መብት እንዲሰጣት ለፍርድ ቤት ልታመለክት ትችላለች።

በመጨረሻም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሴቶች በቤተሰብ ህጉ የተከበረላቸውን መብት ከማየታችን በፊት ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በህጉ የተሰጠውን ትርጉም ማየት ጠቃሚ ነው። አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሳዩት ሁኔታ በህግ እንደተጋቡ ሰዎች ዓይነት መሆኑ እና ቤተዘመዶቻቸው እና ማህበረሰቡ እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው። በእንዲህ ያለ ግንኙነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈራቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናል

(የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 102 )። ይህ በህጉ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በአብዛሀኛው ማህበረሰብ የሶስት ዓመት ሳይሆን ሶስት ወራት እንደሆነ የተሳሳተ ግንዛቤ ተይዞ እንመለከታለን። ከላይ ከተጠቀው የህግ ድንጋጌ የምንገነዘበው ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት አብረው የኖሩ ሴቶች ግንኙነቱን በተቋረጠ ጊዜ(ግንኙነቱን ለማቋረጥ የፍቺ ሂደትን መከተል አይኖርባቸውም) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከተፈራው ንብረት እኩል የመካፈል መብት አላቸው። እንዲሁም ጋብቻን በተመለከት በቤተሰብ ህጉ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ሴቶች በነዚህ የህግ ድንጋጌዎች እውቅና ከተሰጣቸው መብቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ ማለት ነው።[76] ይሁንና እንደማልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል የጋብቻ ዝምድና የማይፈጠር መሆኑ ከተጋቡ ሰዎች ልዩ ያደርጋቸዋል።[77]

*3.9 ፍትህ የማግኘት መብት*

በወንጀልም ይሁን በፍትህ ብሄር ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ዉስጥ የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብት መሰረታዊ መብት በመሆኑ በእኛም ሀገር የህጎች ሁሉ የበላይ ሕግ በሆነው ህገ-መንግስት ተካቶ ይገኛል፡ ፡ ፍትህ የመግኘት መብትን በጥልቀት ከማየታችን በፊት ፍትህ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን መረዳት ጠቃሚ ነው። ይሁንና ለፍትህ የሚሰጠው ትርጉም እንደየሙያ ዘርፉ የሚለያይ ሆኖ እናገኘዋለን። በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ አዋቂዎች ፍትህን የሚመለከቱት ከማህበረሰባዊ እኩልነት አክዋያ በመሆኑ ፍትህ ሲባል በግለሰቦች ይሁን በማህበረሰቦች መካከል ሊኖር የሚችለውን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ልዩነትን ወደ ጎን በመተዉ በእኩልነት ሊስተናገዱ፣ማህበራዊ ተሳትፏቸዉም በእኩልነት ሊረጋገጥላቸው እንደሚገባ እና እኩል ሆነው እንዲታዩ ከማድረግ አንፃር ትርጉም ይሰጡታል።

በሌላ በኩል የኢኮኖሚ ዘርፍ ባለሞያዎች ፍትሃዊነትን ከሃብት አያያዝና አጠቃቀም ጋር በማቆራኘት የሚያዩት በመሆኑ ፍትሃዊነት ሲባል ተቀራራቢነት ያለው የሃብት አጠቃቀም ወይም ደግሞ ሚዛናዊ የኑሮ ደረጃ መምራት ብለው ይተረጉሙታል።

በህግ ዘርፍ ባለሞያዎች እይታ ደግሞ ፍትህ የማግኘት ጽንሰ ሃሳብ በመሰረቱ በሕጉ መሠረት ሰዎች ያላቸውን የፍትሐብሔራዊ ፍትህ (civil justice) እና የወንጀል ፍትህ (criminal justice) ሁኔታ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ግልጽ እና ፍትሃዊ በሆነ ሂደት የመዳኘት እና ተቀባይነት ባለው ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ የሚያገኙበትን አግባብ የሚያመለከት ሆኖ ይገኛል ። በመሆኑም በዚህ ክፍል የምንመለከተው በህግ ፍትህ ዘርፍ (legal justice ) የሚኖረውን ሰዎች ፍትህ

---

[76] አዋጅ ቁጥር 213/1992 ዓ.ም የወጣው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 18፣ 49፣50፣90፣ 102፣ 198፣ 113፣14

የማግኘት መብት ይሆናል። በዚሁ መሰረት በህግ ዘርፍ ያለውን ፍትህ የማግኘት መብት ስንመለከት የመብቱ በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ዕውቅና ከማግኘት ጀምሮ የፍትህ ሂደት ውስጥ ያለውን የተደራሽነት ሁኔታና ተግባራዊ አፈጻጸም በእኩልነትና ምክንያታዊነት ላይ አስቀምጦ የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ ይገኛል። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ በመሰረታዊነት የዜጎች ፍትህ ማግኘት መብት የሚመነጨው ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ነው።

በህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ላይ በግልፅ እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ይላል። ይህም ዜጎች በህግ በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይ (justicable matters) ሲያጋጥማቸው ወደ ፍ/ቤት በመውሰድ ወይም ጉዳዩን ለማየት በህግ ስልጣና ለተሰጠው አካል በማቅረብ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ ፍትህን ማግኘት እንደሚችሉ በግልጽ በህግ ዕውቅና የተሰጠው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ይህ መሰረታዊ ፍትህ የማግኘት መብት የህጎች ሁሉ የበላይ ከሆነው ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ይመንጭ እንጂ በተለይም የዜጎች ፍትህ ማግኘት መብት እጅጉን የሚገለጠውና የሚስተዋለው ጉዳዮች ለፍርድ ከቀረቡ በኋላ ባለው የፍርድ ወይም የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ነዉ'።

በመሆኑ የፍርድ አሰጣጥ ሂደቱን ሁኔታ የሚመሩና ፍትሃዊነት የሚገለጽባቸው በህገ-መንግስቱ ያሉ ሌሎች ድንጋጌዎች ጨምሮ በተለያዩ ህጎች ላይም ሰፊ የህግ ማዕቀፍ ያለው መብት ነው።

ለአብነት ያክል በወንጀል ስነ ሥርዓት ህጉ እንደተደነገገው በአንድ የወንጀል ምርመራ ጉዳይ ተጠርጣሪው ቃል መስጠት የሚጀምረው በፖሊስ ጣቢያዎች ነው። ይህ ደግሞ የመደበኛዉ የፍትህ ሂደት የሚጀመርበት ጊዜና ቦታ መሆኑን እንረዳለን ። ስለዚህ አንድ ተጠርጣሪ በሚገባው ቋንቋ ቃሉን ባለመስጠቱ ሊደርስበት የሚችለውን የፍትህ እጦት መከላከል ይቻል ዘንድ ተጠርጣሪዎች በሚገባቸው ቋንቋ ክሱ እንዲነገራቸው እንዲሁም ቃላቸውን እንዲሰጡ በህግ መብት ተሰጥቷቸዋል። በተመሳሳይ በፍ/ቤት በሚደረግ ክርክር ተጠርጣሪዎች የፍርድ ሂደቱን በአስተርጓሚ አማካኝነት በሚረዱት ቋንቋ እንዲከታተሉ የሚደረግበት ሁኔታ ይስተዋላል።

በመሆኑም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 19/1/ መሠረት ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸውን ክስ ምክንያቶች በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው። ይህ አገላለጽ ሕገ-መንግሥቱን ለብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ለግለሰቦች በቋንቋ የመጠቀም መብት ካረጋገጠው መብት አኳያ ሲታይ ተከሣሽ የክርክሩን ቋንቋ ባለማወቁ ፍትህ መጓደል እንደሌለበት የሚያመለክት ነው።

ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ማሳያዎችን ስናይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 20(1) ስር የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀርበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለህዝብ ገልፅ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት ያላቸው መሆኑ ተመልክቷል።ከዚህ የሕገ መንግስት

ድንጋጌ እንደምንረዳዉ የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት መረጋገጥ ያለበት እንደየጉዳዩ ሁኔታ ግልጽ በሆነ ችሎት ሲሆን ይህ ሲባል ከተከሳሹ በተጨማሪ ማህበረሰቡም ስለ ጉዳዩ ሂደት በቂ ግንዛቤ እንዲኖረዉና ፍትህ ሲሰጥ ለመታዘብ ወይም ለማየት እድል ይሰጠዋል።[78]

በተጨማሪም ዜጎች በቂ የህግ እውቀት ስለሌላቸው ወይም በጠበቃ ለመወከል የመክፈል አቅም ስለሌላቸው ፍትህ የማግኘት መብታቸው እንዳይጓደል በወንጀል ጉዳይ በተከላካይ ጠበቃ ሊወከሉ የሚችሉበት እንዲሁም በፍትሀ ብሄር ጉዳይ ነፃ የህግ ድጋፍ እንዲያገኙ የሚደረግበት ሁኔታ በህጋችን ተካቶ ይገኛል።በዚህም መሰረት ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎቶች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት፣ በፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴር ምድብ ጽ/ቤቶችና ድሬዳዋ ቅርንጫፍ፣ በክልል ፍትህ ቢሮዎች፣ በጠበቆች፣ በተወሰኑ የህግ ኮሌጅ ባላቸው ዩኒቨርሲቲዎች፣ በሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣ በበጎአድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፣የኢትዮጵያ የህግ ባለሙዎች ማህበር፣ በኢትዮጵያ ሴት የህግ ባለሙያዎች [79]ማህበር፣ አክሽን ፕሮፌሽናል አሶሴሽን ፎር ዘ ፒፐል እና ሌሎችም ይሰጣል።

የፌዴራል ጠበቆች ይህን የነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ እና ማህበራዊ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ በቀድሞውም ሆነ ተሻሽሎ በወጣው የፌዴራል ጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249/2013 አንቀፅ 31/1/ መሰረት እያንዳንዱ ጠበቃ በአመት ቢያንስ ሶስት ጉዳዮችን ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲሰጥ ይጠበቃል። በዚህም መሰረት ነፃ የህግ ድጋፍ የሚሹ ዜጎች ወደ ፍትህ ሚኒስቴር የጠበቆች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመሄድ አገልግሎቱን ሲጠይቁ ጉዳዮቹ ለጠበቆች እየተመሩ አገልግሎቱ በመሰጠት ላይ ይገኛል።

በአጠቃላይም ዜጎች በጠበቃ የመወከል መብታቸውን በመጠቀም መብትና ጥቅማቸውን ቢያስከብሩ፣ አቅም ለሌላቸው ዜጎች ደግሞ ከላይ በተጠቀሱት ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ሰጪ አካላት በመጠቀም ቢገለገሉ ፍትህን ለመረጋገጥ፣ ፍትህ ተደራሽ ለማድረግ፣ እኩልነትን ለማስፋት፣ እውነት ላይ ለመድረስ ይጠቅማል።

በሕገ መንግስቱ ከተካተቱ ድንጋጌዎች በተጨማሪ በንጀል መቅጪ ስነ ስርዓት ህግ ላይ ፍትህ የማግኘት መሰረታዊ መብት አፈጻጸም የሚያረጋግጡ የተለያዩ ድንጋጌዎች ይገኛሉ። ለምሳሌ ከጊዜ ቀጠሮ ጋር በተገናኘ፣ ከምርመራ ጊዜና ሪፖርት አደራረግ ጋር በተገናኘ እንዲሁም ምርመራ ከተጠናቀቀ በኃላም በአቃቤ ህግ በኩልም ሆነ ከፍርድ ቤት በኩል በጉዳዩ ላይ በጊዜ ዉሳኔ መስጠት ስለማስፈለጉና ፍትህን በጊዜ ከመስጠት ጋር የሚገኛኙ ድንጋጌዎችን እናገኛለን(የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ አንቀጽ 59፣37፣109 እና አንቀጽ 94 እና ተከታዮቹ)።

---

[78] ህገ መንግሰት አንቀጽ 37፣19፣20

[79] የፌዴራል ጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249/2013 አንቀፅ 31/1/

በተያያዘ ጉዳይ በአፋጣኝ ፍትህ የማግኘት (The right to speedy trial) መብት ዳኝነት ወይም የፍትሕ ጥያቄ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ያለመዘግየት ምክንያታዊ በሚባል አጭር ጊዜ ውስጥ ዳኝነት ወይም ፍትሕ የማግኘት መብት ነው። ይህ መብትም አላስፈላጊና የተንዘዙ ቀጠሮዎች እንዳይኖሩ በማድረግ የዳኝነት ጥያቄ በቀረበበት ጉዳይ ላይ ፈጣን ውሳኔ የማግኘት መብትን ይጨምራል። በተጨማሪም የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት የሚረጋገጠው በህግ የተዘረጋን ስነ ስርዓት ተከትሎ ጉዳዩን ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ መምራት ሲቻል እንደሆነ እንገነዘባለን። እጅግ የተራዘመና የዘገየ የፍትህ ወይም የዳኝነት አሠጣጥ ሂደት ተከራካሪ ወገኖች ላይ ጥርጣሬ የሚፈጥር እና እምነት ማጣትን ከማሳደሩ በተጨማሪ የፍትሕ ስርዓቱን ውጤታማነት እና ብቃት አጠያያቂ ማድረጉ አይቀሬ ነው።" የዘገየ ፍትሕ እንደተከለከለ ይቆጠራል" የሚላዉ የሕግ ምሁራን አባባል የሚጠቀሰውም በዚህ የተነሳ ነው።

በመሆኑም ቀልጣፋና ፈጣን ዳኝነት ማግኘት በዋናነት የተከሳሹ መብት ቢሆንም የተጐጂዎችና የሕብረተሰቡ ጥቅሞችንና ፍላጐቶችን የሚጠብቅ ነው። ተከሳሹ ጉዳዩ በተቻለ ፍጥነት ዉሳኔ እንዲያገኝለት እንደሚፈልግ ሁሉ ተበዳዮች/ተጐጂዎችም ጉዳዩ በጊዜ እንዲወሰንላቸዉ ይፈልጋሉ። ሕብረተሰቡም ቢሆን ጉዳዩ በተራዘመ ቁጥር የህዝብ እና የመንግሥትን ወጪና ጉልበት የሚያባክን በመሆኑ ቶሎ ዕልባት እንዲያገኝ ይፈልጋል። ስለሆነም የቀልጣፋ እና የፈጣን ዳኝነት ወይም ፍትህ የማግኘት መብት መርህ እጅግ በጣም ጠቃሚና ወሳኝ የሥነ-ሥርዓት ሕግ መርህ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

### 3.10 የንብረት መብት

ንብረት ለሰው ልጆች የመኖር ህልውና ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ነው።ምክንያቱም ንብረት በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብት መረጋገጡን ( realisation of the right to an adequate standard of living) የሚያረጋግጡ መብቶችን ለምሳሌ ምግብ ፣መጠለያ እና የመሳሰሉትን ለማግኘት እንደ መሰረት ሆኖ ያገለግላል። የንብረት ባለቤትነት መብት ብዙውን ጊዜ የተፈጥሮ ሰዎች ንብረታቸውን በሚመለከት እንደ ሰብዓዊ መብት የሚጎናፀፉት ሲሆን ንብረቱ በሕግ ሰዎች (ማለትም በድርጅቶች) ባለቤትነት የተያዘ እስከሆነ እና ለፍጆታ ሳይሆን ለምርትነት በሚውልበት ጊዜ በጣም የተገደበ ነው። ንብረት እና የንብረት ህግ ምንነት፣ ንብረት የማፍራት እና የመጠቀም መብት እንዲሁም በንብረት መብት ላይ ያሉ ገደቦች በአለም አቀፍ እና በኢትዮጵያ ያለውን ሽፋን በጥቂቱ ይዳሰሳል።

#### 3.10.1 የንብረት ትርጉም

የንብረት ህግን እና የንብረት ማፍራት መብትን ለመረዳት ንብረት ምን ማለት ነው ለሚለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት ተገቢ ነው:: ንብረት የሚለው ቃል በእንግሊዝኛው "Property" እየተባለ የሚገለፀው

ሆኖ " Proprius" ከሚለው ላቲን ቃል መምጣቱ የሚነገር ሲሆን ትርጉሙም የራስ የሆነ ነገር ማለት ነው። የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ስለንብረት ምንነት ያስቀመጠው ትርጉም ባይኖርም ከተለያዩ ፅሑፎችና ስለንብረት ሕግ ከሚደነግገው የፍትሐ ብሔር ሕግ መረዳት እንደሚቻለው ፤አንድ ነገር ንብረት ለመባል ፦

- ➢ በባለቤትነት ሊያዝ የሚችል (appropriable) መሆን አለበት፣
- ➢ ይህ በባለቤትነት ሊያዝ የሚችል ነገር ጠቃሚነት ያለው (useful) መሆን አለበት። ይህ ማለት ግን ሁሉም ጠቃሚ ነገሮች የንብረት ትርጉም ይሰጣቸዋል ማለት አይደለም። ለምሳሌ ፦ ፀሐይ፣ አየር ወደ ሌላ ሓይል ካልተቀየረ በስተቀር ንብረት ሊሆኑ አይችሉም።
- ➢ ያ ነገር ዋጋ ያለው ወይም ዋጋ የሚያወጣ መሆን አለበት። ይኸውም በገንዘብ ሊገዛ የሚችል ወይም በሌላ ንብረት ሊለወጥ የሚችል መሆን አለበት (The thing must have pecuniary value) ።

በአጠቃላይ ንብረት ማለት በባለቤትነት ሊያዝ የሚችል፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና ዋጋ ያለው ነገር ማለት ነው።

በሌላ በኩል የንብረት ሕግ ማለት የንብረት መብት እንዴት እንደሚገኝ፣ እንዴት እንደሚተላለፍ፣ እንዴት እንደሚቋረጥ፣ የባለሃብትና የባለይዞታ መብቶች ምን እንደሆኑ … ወዘተ የሚገዛ ሕግ ሆኖ በአንድ አገር ኢኮኖሚ /ምጣኔ ሃብት/ ላይ የሚኖረው ቦታና የሚያደርገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። በብዙ አገሮች ውስጥ ግለሰቦች በአጠቃላይ የግል ንብረት መብቶችን ወይም ንብረታቸውን የመሰብሰብ፣ የመያዝ፣ ውክልና የመስጠት፣ የማከራየት ወይም የመሸጥ መብቶች ይጠቀማሉ።

### 3.10.2 የንብረት መብት አለም አቀፍ የህግ ማዕቀፍ

ንብረት የማፍራት መብት በአለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም በአገር አቀፍ ህጎች ውስጥ ተካቶ ይገኛል። የንብረት ባለቤትነት መብት በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መገለጫ (Universal Declaration of Human Rights) ድንጋጌ አንቀጽ 17 ላይ እውቅና ያገኘ ሲሆን በአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን እና የአለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የባህል መብቶች ቃል ኪዳን ውስጥ ግን እውቅና አልተሰጠውም። በመሆኑም የንብረት መብት ሰብዓዊ መብት ስለመሆን ክርክር የሚያነሱ አሉ። ይሁንና በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መገለጫ ድንጋጌ መሰረት ማንኛውም ሰው ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመሆን ንብረት የማፍራት መብት አለው፤ ማንም ሰው ንብረቱን በዘፈቀደ አይነጠቅም( (Everyone has the right to own property alone as well as in association with others. No one shall be arbitrarily deprived of his property) ። የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚወሰድ ቢሆን እንኳ በቂ ካሳ ሊሰጥበት ይገባል።

3.10.3 የንብረት መብት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት

በኢትዮጵያ እንደሌሎች መሰረታዊ መብቶች ሁሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ለንብረት መብት እውቅና በመስጠት ጥበቃ ያደርጋል። በዚሁ መሰረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ እንደሚከበርለት፣ በሕግ መሰረት ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም፣ የሌሎች መብት ሳይቃረን ንብረቱ የማስተላለፍ መብቶችን ያጐናፀፈው ሲሆን የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ብቻ ለንብረቱ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ እንደሚችል ይደነግጋል።

የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40 የግል ንብረት ሲል እንደ ዓላማ አድርጎ የወሰደው ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ኢትዮጵያዊ ማሕበራት ወይም ሌሎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማህበረሰቦች በጉልበታቸው ፣ በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና ተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት መሆኑን ይገልፃል። ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ሰዎች በሶስት መንገዶች ንብረት ማፍራት ይችላሉ። ይህውም፡-

- ጉልበታቸውን ተጠቅመው የሚያፈሩት፣
- በትምህርት ወይም በልምድ በሚያገኙት እውቀትና ክህሎት ተጠቅመው የሚፈጥሩት ነገር፣
- ካፒታላቸውን አፍስሰው ወይም ኢንቬስት አድርገው የሚያገኙት ትርፍ ወዘተ ሊሆን ይችላል።

በእነዚህ የሃብት ማግኛ መንገዶች የሚፈጥሩት ወይም የሚያፈሩት ንብረቶች ተጨባጭነት ያላቸው (corporeal things) ወይም የተጨባጭነት ጠባይ የሌላቸው (incorporeal things) ሊሆኑ እንደሚችሉም በሕገ መንግስቱ 40(2) ስር ተደንግጎ ይገኛል። የኮርፖሪያል ንብረት በአለም ላይ ተጨባጭ ህልውና ያለው(የሚታይ ወይም የሚጨበጥ) ሲሆን እንደ መሬት፣ቤት፣ ጌጣጌጥ፣ብር ወዘተ ካሉ ቁሳዊ ነገሮች ጋር የተያያዘ ነው። የማይጨበጥ ንብረት ደግሞ ሕልውናው ወይም መኖሩ የማይታይና የማይዳሰስ ሲሆን የቅጅ መብት እና የንግድ ምልክት መብት እንደምሳሌ ሊታይ ይችላል። እንዲሁም  በህገ በመንግስቱ እንደተደነገገው ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህም የመሸጥ ፣የመለወጥ፣የማውረስ፣የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን እንደሚያካትት ህገ መንግስቱ ያስቀምጣል።[80]

በህገ መንግስቱ ከተደነገጉት የንብረት መብቶች በተጨማሪ በፍትሀ ብሄር እንዲሁም በወንጀል ህጉ የባለንብረቶችን መብት ለማስከበር የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካተዋል።በዚሁ መሰረት ስለንብረት በጠቅላለውና ስለይዞታ በርካት ደንጋጌዎች ከፍትሀ ብሄር ህጉ አንቀፅ 1126 ጀምሮ የተካተተ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ደግሞ ንብረትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በስድስተኛው መፅሀፍ ላይ

[80] የወንጀል ህግ አንቀጽ 40

በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚመለከት ከአንቀፅ 666-684፣ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ከአንቀፅ 685-688፣ በሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ከአንቀፅ 689-691 እንዲሁም በንብረት መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚመለከት ደግሞ ከአንቀፅ 692-705 በዝርዝር ተመልክተው ይገኛሉ።[81]

### 3.10.4 በንብረት መብት ላይ ያሉ ገደቦች

በመርህ ደረጃ ሰዎች ንብረት የማፍራት እና የመጠቀም መብት ያላቸው ቢሆንም ይህን መብት መጠቀም ከገደብ የፀዳ አይደለም። በመሆኑም የአንድ የተወሰነ ንብረት ባለቤት ለመሆን ወይም በፈለገው መንገድ ለመጠቀም እንደ ፍጹም መብት እንዳልሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። በዚህ መሰረት በግል ንብረት በመጠቀም መብት ላይ ከሚጣሉ ገደቦች አንዱ ለህዝብ ጥቅም ሲባል ንብረት በመንግስት ወይም በባለስልጣን የሚወሰድበት (expropriation) ስርዓት ነው። ይሁንና በዚህ መልኩ የግል ንብረት ሲወሰድ ተገቢው ካሳ መከፈል ይኖርበታል።

በንብረት መብቶች ላይ የተጣለው ሌላው ገደብ በፌዴራል፣ በክልል እና በአካባቢ ደረጃም ሊወጡ የሚችሉ የአካባቢ ህጎች እና ደንቦች (environmental laws and regulations) ናቸው። ይህም ለአካባቢ ጥበቃ ሲባል የሚደረግ ጥንቃቄን የተመለከተ ነው። በተጨማሪም ሰዎች የንብረት መብታቸውን ሲጠቀሙ የሌሎችን ሰዎች መብት በማያውክ ወይም በማይጎዳ መልኩ መሆን አለበት። በሌላ በኩል ህጋዊ መብትን የመጠቀም ገደብ በይርጋ መረሰታዊ መርህ ይገዛል። ይህ ማለት ሰዎች የንብረት መብታቸውን ለማስጠበቅ በህግ የተቀመጠውን የይርጋ ጊዜ ማክበር አለባቸው።

በአጠቃላይ የንብረት መብት ማለትም ንብረት የማፍራት እና የመጠቀም መብት ከሰው ልጆች መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ወስጥ አንዱ በመሆኑ በአለም አቀፍ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ህጎች ውስጥ እውቅና እና ሽፋን አግኝቷል። ሀገራትም ለመብቱ ተፈጻሚነት የሚያስችሉ ዝርዝር ህጎችን እና ደንቦችን በማውጣት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

## ክፍል አራት

## የቤተሰብ ህግ

ቤተሰብ የማህበረሰብ ተፈጥሮአዊ መሰረት እንደመሆኑ ቤተሰብ ከሌለ ማህበረሰብ ሊኖር አይችልም። ቤተሰብ መኖሩ ብቻ ሳይሆን ጤናማ እና ሰላሙ የተጠበቀ መሆኑ ለሀገር ጭምር አስፈላጊ ነው። ጤነኛ፣ ሰላማዊ፣ መልካም ዜጋ የሚያፈራ ቤተሰብ ይኖር ዘንድ ደግሞ የቤተሰብን ግንኙነት የሚገዛ ህግ እንዲኖር ሆኗል። እንደሚከተለው የምንመለከተው ይሆናል።

---

[81] የወንጀል ህግ አንቀጽ 666-705

### 4.1. ጋብቻ እና የሚያስከትለው ውጤት

ቤተሰብ ህጉ ለጋብቻ ትርጓሜ አልሰጠም። ይልቁንም ጋብቻ ለማቋቋም ሊሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ መርጧል። ሆኖም የቤተሰብ ህጉ በአንቀፅ 2 ጋብቻ የሚፈፀመው በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል እንደሆነ በግልፅ አስቀመጧል። ማንኛውም ጋብቻ የሚፈፀመው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟላ ብቻ ነው። ነገር ግን በማህበረሰቡ ልማዳዊ አጠራር "ጋ" ብቻ ማለት ከሆነ ሰዉ "ጋ "ብቻ የሚል ትርጉም ይሰጡታል።

#### 4.1.1. ጋብቻ ለመፈፀመ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

##### 4.1.1.1 ፈቃድ

የሚፀና ጋብቻ ይፈፀም ዘንድ ሁለቱም ተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው።[82] ይህ በሀገራችን ደጋግሞ የሚነሳውን በወላጆች ፍላጎት ብቻ ያለተጋቢዎች ፈቃድ የሚደረግ ጋብቻን ለማስቀረት የታሰበ ነው።

ምሳሌ

ስመኝ በገጠር ቀበሌ ውስጥ የምትኖር ታዳጊ ነች፡፡ እድሜዋ 14 አመት ሲሆናት ወላጆቿ ሊድሯት በሚስጥር ይስማማሉ፡፡ ከዛም ከትምህርት ቤት እንድትቀር አድረገው የሰርጉን ዝግጅት ይጀምራሉ፡፡ ይህ የሰማችው ስመኝ ለመምህራት ትናገርና መምህራት ለህግ አካላት ያሳውቃሉ፡፡

##### 4.1.1.2 እድሜ

ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል ነፃ እና ሙሉ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ ነፃ እና ሙሉ ፈቃድ መስጠት አስፈላጊ ነው። ለአካለ መጠን በመድረስ በጋብቻ ግዜ ላሉ ሀላፊነቶች እና ውሳኔዎች ለመወሰን ለአካለ መጠን መድረስ እና ሙሉ የእድሜ ደረጃ መድረስ አለባቸው። ይህ አካለ መጠን መድረሻ በአለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ልክ እና ደረጃ ወቶለታል። በሀገራችን ደረጃ በህገ መንግስቱ እና በተሸሻለው የቤተሰብ ህግ መሰረት በመርህ ደረጃ የጋብቻ እድሜ 18 (አስራ ስምንት) አመት ነው። በልዩ ሁኔታ ግን ይህ 18 (አስራ ስምንት አመት) ከባድ ምክንያት ሲኖር በሁለት አመት ሊቀነስ ይችላል።

---

[82] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ እትም 1፣ አንቀፅ 6

**ለምሳሌ**

**አንድ አባት አስራ ስምንት አመት ሳይሞላው ልጅ ቢወልድ እና አስራ ስድስት አመቱ ቢሆንምንም እንኳን አስራ ስምንት አመት ባይሞላውም እንደሞላው ተቆጥሮ ለወለደው ህፃን ሀላፊነትእና ጋብቻ መግባቱ ሊፈቀድለት ይችላል ።**

*ጋብቻ ሁለቱም ተጋቢዎች አስራ ስምንት አመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መመስረት አይችሉም ።*[83] *ይህም በሀገራችን ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረውን ያለእድሜ ጋብቻ ለማስቀረት የታሰበ ነው።*

### 4.1.1.3 የሥጋ ዝምድና

*ይህ በሥጋ እና በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ እንዳይፈፀም ክልከላ የሚጥል ነው። ክልክላውን ለመረዳት እንዲቻል የዝምድናን ምንነት በአግባቡ መረዳት ተገቢ ነው።ይኸውም በሥጋ ዘመዳሞች መካከል ያለው ዝምድና ቀጥታ እና ወደ ጎን የሚቆጠር ተብሎ በህጉ ተለይቷል ። ቀጥታ የስጋ ዘመዳሞች የሚባሉት በወላጆችና በተወላጆች መካከል ማለትም በወላጆች፣ በልጆቻቸው፣ በልጅ ልጆቻቸው ወዘተ መካከል ያለው ግንኙነት ነው። ወደ ጎን የሚቆጠረው ደግሞ አንድ ሰው ከእህትና ወንድሞቹ ጋር እንዲሁም ከአክስትና ከአጎቶቹ ጋር ያለው ዝምድና ነው።*

*በሌላ በኩል የጋብቻ ዝምድና በስጋ ሳይሆን በጋብቻ ምክንያት የሚፈጠር ዝምድና ሲሆን እንደ ስጋ ዝምድና ሁሉ በጋብቻ ዘመዳሞች መካከልም ቀጥታ እና ወደ ጎን የሚቆጠር ዝምድና አለ። ቀጥታ የጋብቻ ዝምድና የሚባለው አንድ ሰው ከሚስቱ ወላጆችና ተወላጆች ማለትም ወላጆች፣ ልጆች ወዘተ ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ወደ ጎን የሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና ደግሞ አንድ ሰው ከሚስቱ ወንድምና እህቶች ወይም ሚስት ከባሏ ወንድምና እህቶች ጋር ያሚኖር ዝምድናን ነው።*

*በዚህም በቀጥታ እና ወደ ጎን በሚቆጠር የስጋም ሆነ የጋብቻ ዝምድና መካከል ጋብቻ ሊፈፀም እንደማይችል የህግ ክልከላ የጣለ በመሆኑ ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ሊጣራ የሚገባ ነው።*[84] *ይህ ክልክላ ተወላጅነቱ በህግ ባይረጋገጥም በማህበረሰቡ ዘንድ በተወላጅነት የሚታወቅ ከሆነ በስጋ እና በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል የተቀመጠው ክልክላ ተፈፃሚ ይሆንበታል።*[85]

ምሳሌ

አቶ እንግዳ ባለትዳር እና የአምስት ልጆች አባት ናቸው፡፡ ነገር ግን እቤታቸው በተመላላሽ ሰራተኝነት ከምትሰራው ሰራተኛ ጋር ድብቅ ግንኙነት አላቸው፡፡ ከጊዜ በኋላ ሰራተኛዋ መስራት ታቆማለች ልጅም ትወልዳለች፡፡ የተወለደው ልጅ ከፍ እያለ ሲመጣ መልኩ ፍፁም የአቶ እንግዳን መልክ ይይዛል፡፡ እናቱም ለሚቀርቧት ሰዎች ልጁን የወለደችው ከአቶ እንግዳ መሆኑን ትናገራለች፡ ።

ህብረተሰቡ ይህ የልጁ አባት አቶ እንግዳ ስለመሆናቸው ያምናል፡፡ ስለዚህ የስጋ ዝምድናም ሆነ የጋብቻ ዝምድና ክልከላ ተፈፃሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡

---

[83] ዝኒ

[84] ዝኒ

[85] ዝኒ

4.1.2 በጋብቻ ላይ ጋብቻ

በመሰረታዊነት ደረጃ ጋብቻ በህግ ፊት የፀና የሚሆነው በአንድ ወንድ እና ሴት መካከል ሲፈፀም ነው። ጋብቻ ማንም ሰው በህግ ፊት የፀና ጋብቻ እያለው ሌላ ጋብቻ መፈፀም አይችልም።[86] ይህን ክልከላ መተላለፍ የጸና ጋብቻ እያለው ሌላ ጋብቻ በመሰረተውም ሆነ የፀና ጋብቻ እንዳለው እያወቀ ጋብቻ ካለው ሰው ጋር ጋብቻ በሚመሰርተው ሰው ላይ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው።[87] ነገር ግን ጋብቻ እያለ ሌላ ጋብቻ መመስረት የሚፈቀድባቸው ሁኔዎች በባህል እና በሀይማኖት የተፈቀደ ሲሆን የወንጀል ተጠያቂነት አያስከትልም።

4.2 ጋብቻ የሚፈጸምባቸው ሥርዓቶች

በሁሉም የጋብቻ አይነቶች ልደት፣ ሞት እና ጋብቻ በሚመዘግበው በወሳኝ ኩነቶች መስሪያ ቤቶች መመዝገብ አለባቸው። ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ከተሟሉ ጋብቻ በሚከተሉት በሶስት መንገዶች ሊፈፀም ይችላል። ይኸውም፡-

4.2 .1 በክብር መዝገብ ሹም ፊት

ይህ የጋብቻ አፈፃፀም ተፈፃሚ የሚሆነው ተጋቢዎች በክበር መዝገብ ሹም ፊት ጋብቻ ለመፈፀም ፈቃዳቸውን ሲገልፁ እና የክብር መዝገብ ሹሙም ሲቀበላቸው ነው።

---

86 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 11

87 1996 የወጣዉ የወንጀል ህግ፣ አንቀፅ 650

## የክብር መዝገብ እና የክብር መዝገብ ሹም ምንድን ናቸው?

*ለዚህ ጥያቄ መልስ የምናገኘው በአዋጅ ቁጥር 760/2012 ነው። ይኸውም የክብር መዝገብ ማለት የወሳኝ ኩነት መረጃዎች የሚመዘገቡበት መዝገብ ነው።[88] ወሳኝ ኩነት ማለት የልደት፣ሞት፣ ጋብቻ፣ ፍቺ፣ ጉዲፈቻ፣ ልጅነትን መቀበል ወይም አባትነትን በፍርድ ቤት ማወቅን የሚያካትት ነው።[89] በተያያዘም የክብር መዝገብ ሹም ማለት ወሳኝ ኩነትን እንዲመዘግብ የተመደበ ሀላፊ እንደሆነ ከአዋጁ መረዳት ይቻላል።[90]*

*ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ለመፈፀም ሲያስቡ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ቀን አንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማሳወቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ይህን የሚሳውቁት ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎች ወላጆች ወይም ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈፀምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ያለማቋረጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኝ የክብር መዝግብ ሹም ፊት ይሆናል ይሆናል ።[91]የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄውን ከተቀበለ ከተጋዎቹ ጋር በመነጋገር የጋብቻውን ቀን ከወሰነ በኋላ አመቺ ነው ብሎ በሚያምንበት መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል።[92] ይህ ማስታወቂያ ጋብቻው መፈፀም የለበትም ብሎ የሚያምን ሰው ምክንያቱን ለክብር መዝገብ ሹሙ ማቅረብ እንዲችል የሚያደርግ ነው። የሚቀርቡ ምክንያቶችም፡- ተጋቢዎች እድሜአቸው ያልደረሰ ከሆነ የተጋቢዎች ወላጆች፣ ዐቃቤ ህግ ወይም ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው፤በተጋቢዎች መካከል የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ካለ የተጋቢዎች ወላጆች፣ እስራ ስምንት አመት የሞላቸው ወንድምና እህቶች ወይም ዐቃቤ ህግ፤*

*በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈፀም ከሆነ ሌላ ጋብቻ ሊፈፅም ካላው ሰው ጋር የፀና ጋብቻ አለኝ የሚል ሰው ወይም ዐቃቤ ህግ፤ በፍርድ ቤት ምክንያት ከሆነ አሳዳሪው ወይም አቃቤ ህግ ጋብቻው እናዳይፈፀም መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል። የቀረበ መቃወሚያ ከሌለ ወይም መቃወሚያ ቀርቦ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ በሁለቱም ተጋቢዎች በኩል ሁለት ሁለት ምስክሮች በተገኙበት ተጋቢዎች ለመጋባት ያላቸውን ሙሉ ፈቃድ እንዲገልፁ ከተደረገ እና ጋብቻ ለማፈፀም የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው*

---

[88] የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2012፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 18ኛ አመት ቁጥር 58፣ ነሐሴ 16፣ 2004 ዓ.ም፣ አንቀፅ 2(2)

[89] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 2(1)

[90] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 2(3)

[91]የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ እትም 1፣ አንቀፅ 22፣ 23

[92] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 24

ከተረጋገጠ በኋላ ሁሉም ማለትም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገብ ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል። በመጨረሻም የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎች በጋብቻ የተሳሰሩ መሆኑን አሳውቆ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።[93]

4.2.2 የሀይማኖት ጋብቻ

በአለማችንም ሆነ በሀገራችን ላይ የተለያዩ ሀይማኖቶች አሉ። የፈለጉትን እምነት መከተል መብት መሆኑ ደግሞ በአለም አቀፍ ስምምነቶችም ሆነ በሀገራችን ህገ መንግስት ተደንግጎ ይገኛል። ሁሉም ሀይማኖቶች የራሳቸው የሆነ ስርአት ያላቸው ከመሆኑም በላይ የየራሳቸው የሆነ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርአትም አላቸው። አብዛኛው የሚባለው የሀገራችን ህዝብ ሀይማኖትን አጥብቆ የሚከተል በመሆኑ የቤተሰብ ህጉ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት በሀይማኖት ሥርአት ለሚፈፀም ጋብቻ እውቅ ስጥቷል። በሀይማኖት መሰረት የሚደረጉ ጋብቻዎች በአንዳቸው ተጋቢዎች ሀይማኖት አማካኝነት የሚካሄድ እና በሀይማኖቱ መደበኛ ስነ-ስርአት መሰረት የሚፈፀም ሆኖ ነገር ግን ጋብቻ ለመፈፀም የተቀመጡ ቅድም ሁኔታዎች ግን በሀይማኖት ጋብቻም መሟላታቸው የግድ ነው።[94]

4.2.3 የባህል ጋብቻ

ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደሀይማኖት ሁሉ የበርካታ ባህሎች ባለቤት ነች። እነዚህ ባህሎች የየራሳቸው የጋብቻ ሥርአት ጭምር ያላቸው ናቸው። ጋብቻ ለመፈፀም የተቀመጡ መስፈርቶች እስከተሟሉ ድረስ በእነዚህ ባህሎች(የተጋቢዎች ባህል በሚፈቅደው አካሄድ እና ስርአት) መሰረት የሚፈፀም ጋብቻ እኩል የህግ ጥበቃ የሚያገኝ ይሆናል።[95]

*4.3 የጋብቻ ውል እና የጋብቻ ምስክር ወረቀት ልዩነት*

የጋብቻ ውል እና የጋብቻ ምስክር ወረቀትን አመሳለስሎ የመረዳት ችግር በብዙዎች ዘንድ የሚስተዋል ችግር ነው።

በእርግጥ ሁለቱ ተመሳሳይ ናቸው?

የጋብቻ ምስክር ወረቀትና የጋብቻ ውል በህጋችን መሰረት የተለያዩ ናቸው። ይኸውም የጋብቻ ምስክር ወረቀት ጋብቻው ስለመፈፀሙ ጋብቻውን ባስፈፀመው አካል የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው። በሌላ በኩል

[93] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 25

[94] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 26

[95] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 27

የጋብቻ ውል ተጋቢዎች በህጉ የተቀመጡ አስገዳችጅ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በመሀከላቸው ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የሚገቡት የውል ስምምነት ነው።

### 4.4 ጋብቻ የሚያስከትለው ውጤት

ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነትም ሆነ እና በንብረት ላይ የራሱ ውጤት የሚያስከትል ነው። ጋብቻው ከላይ በጠቀስናቸው ሶስት የጋብቻ መፈፀሚያ ሥርአቶች ቢፈፀምም ልዩነት አይደረግብትም፣ በውጤት ደረጃም ተመሳሳይ ይሆናል።[96]

#### 4.4.1 ጋብቻ በተጋቢዎች በግላዊ ግንኙነት የሚያስከትለው ውጤት

##### 4.4.1 .1 አብሮ መኖር

ባልና ሚስት ጋብቻ ከፈፀሙ በኋላ አብረው እንዲኖሩ በህግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።[97] የመኖሪያ ቦታቸውንም አብረው የሚወስኑ ይሆናል።[98] ሆኖም ባልና ሚስቱ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተለያይተው ለመኖር መስማማት አይከለከሉም። ይህ ስምምነት መቀየሩ አግባብ ካልሆነ በስተቀርም ተጋቢዎች ወይም ከሁለት አንዳቸው አስበው ሊቀይሩትም ይችላሉ።[99] ለምሳሌ የባልና ሚስቱ የሥራ ቦታ ሊለያይ የሚችልበት አጋጣሚ ሲፈጠር ሁለቱም በያሉበት ሆነው ሥራቸውን ለመሥራት ሊስማሙ የሚችሉ ሲሆን አመቺ ሆኖ ካላገኙትም ሀሳባቸውን መቀየር ይችላሉ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ተጋቢዎች ጋብቻ ተሳስረው ሲኖሩ ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛ የሩካቤ ሥጋ መፈፀምም ይጠበቅባቸዋል። ይህን የሚቃረን ስምምነት ውጤት አይኖረውም።[100] በተጨማሪም በማንኛውም ሁኔታ አንዳቸው ለሌላኛው ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው።[101] ይህ ሳይሆን ቀርቶ አንዳቸው ሳይታመኑ የአመንዝራነት ድርጊት ቢፈፅሙ በተበደለው ተጋቢ አቤቱታ አቅራቢነት በእስራት ወይም በመቀጮ ሊያስቀጣ የሚችል የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው።[102]

---

[96] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 30

[97] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 53(1)

[98] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 54

[99] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 55(1)

[100] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 53(2) እና (3)

[101] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 56

[102] የወንጀል ህግ፣ አንቀፅ 652

#### 4.4.1.2 መከባበር፣ መተጋገዝና መደጋገፍ

ባልና ሚስት በትዳር በሚኖሩበት ጊዜ እንዳቸው ሌላኛውን የማገዝና የመደገፍ እንዲሁም ተከባብሮ የመኖር ሀላፊነት ተጥሎባቸዋል። ይህንን ሀላፊነት በስምምነት ፈፅሞ ሊያስቀሩት ህግ አይፍቅድላቸውም።[103]

#### 4.4.1.3 ቤተሰብን በጋራ መምራት

ጋብቻ በሁለቱ ተጋቢዎች ተወስኖ የሚቀር አይደለም። ይልቁንም ልጆችን የሚፈጥርና የቤተሰብ መሰረት የሚሆን ተቋም ነው። በዚህም የልጆች አስተዳደግ፣ ትምህርት፣ ጤና ወዘተ የመሳሰሉ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በተጋቢዎች እንዲሟሉ ይጠበቃል። ለዘማናት መሰል የቤተሰብ ጉዳዮች መምራትና ማስተዳደር ለወንዶች ወይም ለባሎች የሚሰጥ ሀላፊነት ሆኖ ቆይቷል። በ1960 በወጣው የፍትሐብሔር ህግ ውስጥ በካተተው የቤተሰብ ህግ ቤተሰቡን የመምራት ዋናው ሀላፊነት ለባል የተሰጠ መሆኑን ለዚህም ማሳያ ነው።[104]

አዲሱ የቤተሰብ ህግ ካረማቸው ነገሮች መካካል አንዱ ይህን የተመለከተ ሲሆን ቤተሰባቸውን በመምራት ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት እንዳላቸው ደንግጓል። በዚህም በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ፣ ልጆቻቸው በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነፁ፣ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ሀላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ ባልና ሚስቱ መተባበር ይጠበቅባቸዋል።[105]

### 4.4.2 ጋብቻ በንብረት ረገድ የሚያስከትለው ውጤት

ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ውጤት እንዳለው ሁሉ በንብረት ረገድም የራሱ የሆነ ውጤት የሚያስከትል ነው። ንብረትን በተመለከተ ጋብቻ የግል እና የጋራ ንብረት ውጤት የሚያስከትል ነው።

#### 4.4.1.1 የግል ንብረት ምንነትና አስተዳደር

የግል ንብረት የምንለው ሁለቱ ተጋቢዎች ከጋብቻው በፊት በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻው በኋላ በውርስ ወይም በየግላቸው በስጦታ ያገኟቸው ንብረቶች ናቸው። እነዚህ ንብረቶች በጋብቻውም ዘመን የግላቸው ሆነው ይቀጥላሉ።እነዚህን ንብረቶች ሸጦ የሚገዛው ንብረት የራሱ የሚሆን ሲሆን ይህ የሚሆነው ግን በፍርድ ቤት የግሌ ይባልልኝ ብሎ ሲጠይቅና ሲፀድቅለት ነው።[106]

---

[103] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 49

[104] የፍትሐ ብሔር ሕግ 1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952 በተለይ የወጣ፣ አንቀፅ 635፣ 637

[105] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ እትም 1፣ አንቀፅ 50

[106] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 57፣ 58

የግል ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ የግል ንብረቱ ባለቤት የሆነው ተጋቢ ሊያዝበት የሚችል ሲሆን ሌላኛው ተጋቢ እንዲያስተዳድረው በጋብቻ ውል ሊስማሙ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ ውክልና በመስጠት ሌላኛው ተጋቢ እንዲያስተዳድር ሊያደርግ ይችላል።[107]

4.4.1.2 የጋራ ንብረት ምንነትና አስተዳደር

የጋራ ንብረትን በተመለከተ የጋራ ንብረት የሚባለው ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኟቸው ንብረቶች፣ ባልና ሚስት በግል ጥረታቸው የሚገኝ ገቢ፣ ከግል እና ከጋራ ንብረታቸው የሚገኟቸው ገቢዎች ሁሉ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በስጦታ ወይም በኑዛዜ በጋራ የተሰጧቸው ንብረቶች የጋራ ንብረቶች ናቸው። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር በአንደኛው ተጋቢ ስም የተመዘገበ ሀብትም ቢሆን እንኳን የተጋቢዎች የጋራ ሀብት እንደሆነ የህግ ግምት የሚወሰድበት መሆኑ ነው።[108]

በንብረት አስተዳደር ረገድ የጋራ ንብረታቸውን አንደኛው ተጋቢ እንዲያስተዳድረው ካልተስማሙ፣ ችሎታ የለውም በሚል ካልተወሰነ፣ ንብረት የማስተዳደር መብቱ ካልተገፈፈ፣ ወይም በማናቸውም ምክንያት ንብረታቸውን ማስተዳደር የማይችል ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የጋራ ንብረታቸውን በጋራ ያስተዳድራሉ። ሆኖም በተጠቀሱት ምክንያቶች አንደኛው ተጋቢ ብቻውን ንብረቱን የሚያስተዳድር ከሆነ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ሃላፊነት አለበት።[109] በገቢ ረገድ ሁለቱም ተጋቢዎች ገቢያቸውን በየራሳቸው መቀበል የሚችሉ እንዲሁም በግል ወይም በጋራ የባንክ ሂሳብ ከፍተው ማስቀመጥ ይችላሉ። ይህ ማለት ግን አንደኛው ተጋቢ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልለት ስልጣን ለመስጠት የሚከለክለው ነገር የለም። በየግል የሚያገኙትንም ገቢ ሌላኛው ተገቢ ሲጠይቅ ማሳወቅ ግዴታ አለበት።[110]

ከንብረት በተጨማሪ በጋብቻ ውስጥ እዳ ሊኖር እንደሚችል የሚጠበቅ ነው። ልክ እንደንብረት ሁሉ እዳም የግል ወይም የጋራ ተብሎ የሚከፈል ነው። እዳው ለባልና ሚስት እና ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማሟላት ወይም ባል ወይም ሚስት ቀለብ የመስጠት ግዴታቸውን ለመወጣት የተገቡ እዳዎች እንዲሁም ከባልና ሚስት በአንደኛው ወይም በዕዳ ጠያቂው አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመሆኑ ፍርድ ቤት የተቀበለው እዳ በጋራ የሚከፍሉት ነው። ከዚህ ውጪ የሚኖረው እዳ የግል ይሆናል ማለት ነው። አከፋፈሉ የጋራ እዳ ከባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት የሚከፈል ሲሆን ዕዳውን

[107] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 59፣ 60፣ 61

[108] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 62፣ 63

[109] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 66፣ 67

[110] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 64

ለመሸፈን በቂ በማይሆን ግዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሀብት የሚከፈል ይሆናል። በአንፃሩ የግል ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሀብት የሚከፈል ሲሆን ዕዳው ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብት የሚከፈል ይሆናል። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ከጋራ ሀብት ሲባል በድርሻው ልክ እንጂ የሌላኛውን ተጋቢ ጥቅም በሚነካ መልኩ ሊሆን እንደማይችል ነው።[111]

4.5 የጋብቻ መፍረስ

በቤተሰብ ህጉ መሰረት ጋብቻ በሶስት መንገዶች ሊፈርስ ይችላል። ይኸውም ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥበት፣ ጋብቻ ሲፈፀም መሟላት ካለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን እና የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ነው።[112] ጋብቻ ሲፈርስ በንብረት ረገድም ሆነ በግላዊ ግንኙነቶች ረገድ ውጤቶች ይኖሩታል። ጋብቻው በየትኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርአት የተፈፀመ ቢሆንም የጋብቻው መፍረስ የሚኖረው ውጤት ተመሳሳይ ነው።[113] በሌላ አገላለፅ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት፣ በሀይማኖት ሥርአት ወይም በባህል የተፈፀመ ቢሆንም ጋብቻው ሲፈርስ የሚኖረው ውጤት የተለያየ እንዲሆን አያደርገውም።

የጋብቻ ቅድመ ሁኔታ ባለመሟላት የሚፈርስ ጋብቻን በተመለከተ ፈቃድ፣ እድሜ፣ የሥጋ እና የጋብቻ ዝምድና እንዲሁም የቀድሞ ጋብቻ መኖር አለመኖር አስመልክቶ የተቀመጡ መስፈርቶች ሳይሟሉ ሲቀሩ ነው።[114] በሌላ በኩል የፍቺ ውሳኔ የሚሰጠው ባልና ሚስቱ በስምምነት ወስነው ለፍርድ ቤት በማቅረብ ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱም በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስላቸው ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው።[115] ሆኖም ተጋብተው ስድስት ወር ያልሞላቸው አዲስ ተጋቢዎች በስምምነት ጋብቻቸውን ማፍረስ የማይችሉ ሲሆን በስምምነትም ሆነ በአንዳቸው አመልካችነት ፍቺ በሚጠየቅ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ የማሰላሰያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።[116]

---

[111] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 70

[112] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 75

[113] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 74

[114] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 31፣32፣33፣35

[115] ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 76

[116] ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 78፣82

ፍርድ ቤት በስምምነት ፍቺ እንዲያፅድቅም ሆነ በአንዳቸው የፍቺ ጥያቄ ቀርቦለት ፍቺ ሲወስን የፍቺውን ውጤት አብሮ መወሰን ይጠበቅበታል። የስምምነት ፍቺ በሚሆንበት ጊዜ የቀረበለትን ስምምነት የልጆቻቸውን ጥቅምና ደህንነት የሚጎዳ ወይም የአንደኛውን ተጋቢ ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ካገኘው ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ውሳኔ ይሰጣል።[117]

ሌላው ከፍቺ ጋር በተያያዘ የሚነሳው የግል የንብረት ክፍፍል ጉዳይ ነው። የተጋቢዎቹ የግል ንብረታቸውን መልሰው መውሰድ ይችላሉ።[118] የግል ንብረት የሚባለው ተጋቢዎች ጋብቻቸውን በሚፈፅሙበት ጊዜ በየግል የነበራቸው ወይም ከጋብቻው በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች ናቸው።[119] ስለዚህ እነዚህን ንብረቶች የራሳቸው እንደሆኑ ስለሚቆዩ የንብረቱ ባለቤት የሆነው ተጋቢ መልሶ መውሰድ ይችላል ማለት ነው። በጋብቻቸው ጊዜ ያፈሯቸውን ንብረቶች ደግሞ የጋራቸው ስለሆን እኩል እንዲካፈሉ ይደረጋል።[120] የጋራ ንብረታቸውን በአይነት የሚከፋፈሉ ሲሆን እኩል ማካፈል የማይቻል ከሆነ ልዩነቱ በገንዘብ ይካካሳል። ክፍፍሉን በተመለከተ እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ሊደረግ ይገባል።[121] ይህ ማለት ለምሳሌ አንደኛው ተጋቢ አናፂ ቢሆን ይህንን ሥራውን ለመስራት የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎችን እንዲወስድ ሊደረግ ይገባል ማለት ነው። በአይነት ለማከፋፈል የማይመች ወይም የማይቻል ከሆነ እና ተጋቢዎቹ ለአንዱ እንዲሰጥ ያልተስማሙ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ እንዲካፈሉ ይደረጋል።[122]

በመጨረሻም ከፍቺ ጋር በተያያዘ የግጭትና የተራዘመ የፍርድ ቤት ክርክር መንስኤ እየሆነ ያለው ባልና ሚስት መለያየት ሲፈልጉ በህጉ መሰረት ፍቺ በፍርድ ቤት ሳይወሰን የሚለያዩነበት ሁኔታ ነው። ይህንን በተመለከተ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መስጠት ስልጣን ያለው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል ባልና ሚስት ተለያተው የየራሳቸውን ኑሮ ከመሰረቱ በፍርድ ቤት ባይወሰንም በተግባር እንደተፋቱ እንደሚቆጠር ውሳኔ ሰጥቶ ነበር። ሆኖም በዚህ ውሳኔ መብታችን ተነካ የሚሉ ሴቶች የሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ የህገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በሚል ፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀረቡት ሲሆን ምክር ቤቱም በቤተሰብ ህጉ ጋብቻ የሚፈርስባቸው ብሎ

---

117 ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 80

118 ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 86

119 ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 57

120 ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 90

121 ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 91

122 ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 92

ያስቀመጣቸው ምክንቶያች ሶስት ብቻ እንደሆኑ እና ሰበር ሰሚው ችሎት በቤተሰብ ህግ ያልተካተተ ሳይፋቱ ፍቺ በሚል ውሳኔ መስጠቱ ህግ ማውጣት በመሆኑ ችሎቱ ህግ መተርጎም እንጂ ህግ ማውጣት ስልጣን የለውም በሚል የሰበር ውሳኔውን ሽሮታል። በመሆኑ አንዱ ተጋቢ ሲሞት በወራሾችና በሚስቶች መካከል የተራዘመ ክርክር የሚፈጥር መሆኑን በመገንዘብ መለያየት የግድ ከሆነ በህግ መሰረት በፍርድ ቤት ፍቺ አስወስኖ መፋታት ተገቢ ነው

4.6 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት መኖር እና የሚያስከትለው ውጤት

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር ማለት አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ከላይ በተመለከቱት ሶስት የጋብቻ መመስረቻ መንገዶች ግልፅ ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደ ባልና ሚስት የሚኖሩበት ሁኔታ ነው።[123] ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር በህጉ ተመረጭ ባይሆንም እየቆየ ሲሄድ ቤተሰብ የሚፈጥር ከመሆኑ አንፃር ቤተሰብን ጥበቃ ለመስጠት ሲባል እንደ ጋብቻ ባይሆንም በህጉ እውቅና ሊሰጠው ችሏል።

4.6.1 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት የሚያስከትለው ውጤት

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖር ከጋብቻ እኩል ጥበቃ የሚሰጠው አይደለም። ይልቁንም በሀገራችን በስፋት የሚስተዋል እና ቤተሰብም የሚፈጥር በመሆኑ እውቅና ተሰጠው እንጂ በህጉ ከጋብቻ እኩል ተቀባይነት ሰጥቶ የሚያበረታታው አይደለም። በዚህም ህጉ በግላዊ ግንኙነት ረገድ እንደ ጋብቻ ዝርዝር ያሉ ነገሮችን አላካተተም። ከቤተሰብ ህጉ እንዲሁም ከሌሎች የሀገራችን ህግጋትና ሀገራችን አባል ከሆነችባቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መንፈስ መረዳት እንደሚቻለው ግን ግላዊ ግንኙነታቸው በሁለቱም በእኩልነት መንፈስ መተዳደር የሚገባው መሆኑን ይገባዋል። ከዚህ በተጨማሪም የጋራ ኑሯቸው ወጪ ለመሸፈን ሁለቱም እንደአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።[124]

በሌላ በኩል ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር የጋብቻ ዝምድና አይፈጥርም። በመሆኑም በሴቲቱ እና በወንድየው የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በወንድው እና በሴቲቱ የስጋ ዘመዶች መካከል ዝምድና አይፈጥርም። ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ለጋብቻ መመስረት እንደቅድመ ሁኔታ የተቀመጠው ክልከላ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር ላይም ተፈፃሚ ይሆናል።[125]

---

[123] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 98

[124] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 101

[125] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 100

4.6.2 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር በንብረት ረገድ የሚያስከትለው ውጤት

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት መኖሩ በንብረት ረገድ የራሱ ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ከቤተሰብ ህጉ መረዳት ይቻላል። ይኸውም ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር የጋራ ንብረት ውጤት የሚያስከትለው ሴቲቱና ወንድየው ከ3 (ሶስት) አመት ላላነሰ ጊዜ ጊዜ አብረው ከኖሩ ሲሆን ለተጠቀሰው ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነታቸው ውስጥ ያፈሯቸው ንብረቶች የጋራ ንብረቶቻው ይሆናሉ ማለት ነው። ሆኖም በንብረት ረገድ የሚኖራቸው ግንኙነት የንብረት አስተዳደርን በተመለከተ በሁለቱ መሀከል ውል የሚኖር ከሆነ የውሉ ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።[126]

አብረው በመኖር ላይ እያሉ የሚኖሯቸው ንብረቶች በግንኙነቱ ውስጥ የተፈሩ ንብረቶች እንደሆኑ የህግ ግምት የሚወሰድበት ሲሆን ተቃራኒ ማስረጃ አቅርቦ ይህን ግምት ቀሪ ማድረግ ይቻላል።[127] በሌላ በኩል እንደንብረት ሁሉ እዳ ሊኖር እንደሚችል የመጠበቅ ነው። ይህ እዳ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሯቸው እና በግንኙነታቸው የተወለዱ ልጆችን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟት የተገባ ከሆነ ለአከፋፈሉ ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ሀላፊ የሚሆኑ ይሆናል። ከዚህ ጋር በተያዘ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት በመኖር ውስጥ የጋራ ሀብት ከተፈጠረ በኋላ የሚኖራቸው ግንኙነት በምን ይገዛል የሚል ነው። የቤተሰብ ህጉ ለዚህ መልስ የሰጠ ሲሆን አንድ ጊዜ የጋራ ንብረት ከተፈጠረ በኋላ በጋብቻ ውስጥ ያለውን የንብረት ግንኙነት በተመለከተ በህጉ ውስጥ የተካተቱ ድንጋዎች ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት በሚኖሩ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።[128]

4.6.3 ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት መቋረጥ

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር ከጅምሩም በሴቲቱ እና በወንድየው ፍላጎት መደበኛ የጋብቻ መፈፀሚያ ስነ ሥርአቶችን ሳይከተል የሚመሰረት ግንኙነት ነው። በዚህም ግንኙነቱ ህግ ፊት ቀርበው የሚመሰርቱት አይደለም። በተመሳሳይ ግንኙነቱ ሲቋረጥም እንደ ጋብቻ መደበኛ ሂደቶችን ላይከተል ይችላል። በግንኙነቱ ውስጥ የሚኖሩት ሴትና ወንድ በሚፈልጉበት ጊዜ ግንኙነታቸውን ማቋረጥ ይችላሉ።[129] ይህ ማለት ጋብቻ ሳይፈፅሙ እንደባልና ሚስት ሲኖሩ የነበሩ ሰዎች ከንብረትና ከልጅ አስተዳደግ ጋር የተያያዘ አለመስማማት ካልገጠማቸው በስተቀር ግንኙነታቸውን ለመቋረጥ ብቻ ፍርድ ቤት መሄድ አይጠበቅባቸውም ማለት ነው።

---

[126] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 102

[127] ዝኒ ከማሁ

[128] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 103

[129] ዝኒ ከማሁ፣አንቀፅ 105

## 4.7 እናትነት፣ አባትነትና ልጅነት

እናትነት፣አባትነትና ልጅነት በተፈጥሮ ወላጅና ልጅ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው፡ በእናት፣ አባት እና ልጅ መካከል ያለው ግንኙነት በግልፅ መታወቁ በዋናነት ለልጁ መልካም አስተዳደግ አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር በግንኙነቱ ምክንያት የህግ የተመለከተው ግዴታና መብት በቀላሉ እንዲተገበር የሚረዳ ነው። በመሆኑም የቤተሰብ ህጉ ይህ ግንኙነት ሊታወቅባቸው የሚችልባቸውን መንገዶች በዝርዝር ደንግጓል። እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

### 4.7.1 እናትነት

እናትነት ለሴቶች በተፈጥሮ የተሰጠ ስጦታ ሲሆን የአንድ ልጅ እናት ማን ናት የሚለውን የሚመለከተ ነው። አንዲት ሴት ልጅ ስትወልድ እናት ትሆናለች። መውለድ የሚታይ እውነት እንደመሆኑ እናትነትን ማወቅ በአብዛኛው ቀላል ይሆናል። በመሆኑም አንዲት ሴት ልጅ በመውለዱ እናትነቷ እንደሚታወቅ ይታወቃል።[130]

### 4.7.2 አባትነት

አባትነት የአንድ ልጅ አባት ማን ነው የሚለውን የሚመለከት ሲሆን ብዙ ጊዜም የክርክር መነሻ ሲሆን ይስተዋላል። ይህም ለእናቶችም ሆነ ለህፃናት እንግልት ምክንያት ሆኗል። ለዚህ መፍትሄ ይሆን ዘንድ ህጉ መፍትሄ አስቀምጧል። በፌደራል የቤተሰብ ህጉ መሰረት አባትነት በሶስት መንገድ ሊታወቅ ይችላል።[131] ይኸውም።-

#### *4.7.2.1 በህግ ግምት*

አንድ ልጅ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናትየዋ እና በአንድ ወንድ መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ አባትነት ሊታወቅ ይችላል። በህግ እውቅና ያለው ግንኙነት ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት መኖር ስለመሆኑ ከቤተሰብ ህጉ መረዳት ይቻላል። በዚህም ልጁ በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ከሆነ የልጁ አባት የሚባለው ባልየው ሲሆን ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ከሆነም የልጁ አባት የሚሆነው በዚሁ ግንኙነት ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው።[132]

---

[130] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 124

[131] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 125

[132] ዝኒ ከማሁ፣ በአንቀፅ 126፣ 130

የእርግዝና ጊዜን በተመለከተ ጋብቻ ከተፈፀመ 180 ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ300 ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻ ውስጥ እንደተወለደ የሚቆጠር ሲሆን ይህን የህግ ግምት የሚቃረን ማስረጃ ተቀባይነት የለውም። ይህ የህግ ግምት ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት ለሚኖሩም ሰዎች ተፈፃሚ የሚሆን ነው።[133]

4.7.2.2 ልጅነትን በመቀበል

አንድ ሰው አንድን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ እንደሆነ አምኖ ቃሉን ከሰጠ የልጁ አባት መሆኑን ተቀብሏል ይባላል። ከላይ በተጠቀሰው የህግ ግምት የልጁ አባት ሊታወቅ ያልቻለ እንደሆነ ልጅነትን በመቀበሉ አባትየው ሊለይ የሚችልበት መንገድ ነው።[134]

ልጅነትን መቀበል የፈለገ ሰው በክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ቃል በመስጠት፣ በፅሁፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸውም ስልጣን በተሰጠው ባለስልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አባትነቱን በመግለፅ ልጅነትን መቀበል ይችላል። ባለስልጣን የተረጋገጠ ሰነድ የቅጥር፣ የጡረታ እና መሰል ሰነዶች ላይ አባትየው  ልጄ ነው ሲል የሚሰጠውን ማረጋገጫ የሚያካትት እንደሆነ በቤተሰብ ህጉ ሀተታ ዘምክንያት ተመላክቶ ይገኛል።

አባትየው ለአካላ መጠን ያልደረሰ ቢሆን እንኳን ልጄ ነው ሲል ቃል መስጠት የሚችለው እራሱ ብቻ ነው። ሆኖም በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ ውክልና በመስጠት ብቻ ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ ይችላል። የልጁ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን መስጠት የማይችል ከሆነ ከአባትየው ወላጆች አንዱ በአባትየው ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል።  አባት ነኝ በሚል የተሰጠው ቃል የህግ ውጤት ይኖረው ዘንድ እናትየው እውነትነቱን አምና መቀበል ይኖርባታል። ካልሆነ ግን በህግ ፊት ውጤት አይኖረውም። ፡ እናቲቱ በህይወት የሌለች ወይም ፈቃዷን መግለፅ የማትችል ከሆነ ከወላጆቿ በአንዱ ፈቃዱ ሊሰጥ ይችላል። እነሱ የሌሉ ከሆነ ደግሞ ወደ ላይ በሚቆጠሩ ወላጆች ማለትም ወላጆቿ ሊሰጥ ይችላል። አባትየው ልጅነቱን የተቀበለው ልጁ ለአካመጠን ከደረሰ በኋላ ከሆነ መቀበሉ ውጤት የሚኖረው ልጁ አባትነቱን ሲቀበል ነው። ልጁ የሞተ ከሆነ ደግሞ ልጅነትን መቀበል የሚችሉት የልጁ ተወላጆች ብቻ ይሆናሉ።

አባትየው የሚፈፅመውን አባትነትን የመቀበል ተግባር መቀበል ወይም አለመቀበል እንደሚችሉ እናት፣ የእናት ወላጆች፣ አካለመጠን የደረሰ ልጅ እራሱ ወይም የእሱ ተወላጆች በግልፅ መቀበላቸውን

---

[133] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 128

[134] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 132

የሚገልፁ ከሆነ መልካም ነው። ሆኖም የማይገልፁ ከሆነ መቀበል በህግ ግምት የሚወሰድበት እንደሆነ በቤተሰብ ህጉ ተመልክቷል። ይኸውም ልጅነትን መቀበል የሚችሉት ሰዎች አባትየው አባትነቱን መቀበሉን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አባትነቱ ላይ ክርክር ያላነሱ እንደሆነ አምነው እንደተቀበሉ ይቆጠራል።[135] እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው የዚህ አንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀመረው አባትየው አባትነቱን ከተቀበለበት ቀን ሳይሆን ልጅነቱን መቀበል ወይም አለመቀበል የሚችሉት ሰዎች አባትነት የመቀበል ድርጊት መፈፀሙን ካወቁበት ቀን ጀምሮ መሆኑ ነው።

አካለመጠን ላልደረሰ ሰው ካልሆነ በስተቀር አንድ ሰው አንድን ልጅ ልጄ ነው ሲል የሰጠውን ቃል መሻር አይችልም። አካለመጠን ያልደረሰ ሰውም ቢሆን ቃሉን መሻር የሚችለው በህጉ ላይ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው። ይኸውም አካለመጠን ከመድረሱ እና ከደረሰ በኋላ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ሲሆን ይህም ተፈፃሚ የሚሆነው አሳዳሪው አስቀድሞ ስምምነቱን ካልገለፀ ብቻ ነው። ልጄ ነው ሲል የሰጠውን ቃል መሻር የሚችለውም እራሱ ብቻ ሲሆን ህጋዊ መኪሎቹም ሆኑ ወራሾቹ ይህን ቃል መሻር አይችሉም።[136] ልጅነትን የተቀበለው በሀይል የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት የተሰጠው ቃል እንዲፈርስ ማድረግ ይቻላል። በአንፃሩ ልጁ አባትነትን ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይችል መሆኑን በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነትን የተቀበለው በማታለል ወይም በስህተት በሚል ሊፈርስ አይችልም።[137] በሌላ በኩል አንድ ሰው ልጄ ነው ሲል ቃል የተሰጠበት ልጅ ይህ ቃል ካፈረሰ በስተቀር በሌላ ሰው ልጄ ነው የሚል ቃል ሊሰጥበት አይችልም።[138]

4.7.2.3 በፍርድ ቤት አባትነት እንዲታወቅ ማድረግ

በፍርድ ቤት አባትነት የሚረጋገጥበት ሂደት ሲሆን ከላይ በጠቀስናቸው መንገዶች አባትነት ያልታወቀ እንደሆነ እና በህጉ የተቀመጡት ሁኔታዎች ሲሟሉ ጥቅም ላይ የሚውል ነው። በህጉ የተቀመጡት ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ልጁ በሚፀነስበት ጊዜ እናቲቱ የመደፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር ከተፈፀመባት

[135] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 138

[136] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 140

[137] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 141

[138] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 142

- ልጁ በተጸነሰበት ጊዜ እናቲቱ ላይ ሆነ ብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት፣ ስልጣንን አለአግባብ በመጠቀም፣ አገባሻለሁ ብሎ የተስፋ ቃል በመስጠት ወይም ተመሳሳይ የማሳት ድርጊት ከተፈፀመባት
- በህግ የታወቀ ግንኙነት ማለትም ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳፈፀም እንደ ባልና ሚስት መኖር ሳይኖር የልጁ እናትና አባት ነው የሚባለው ግለሰብ በህግ በተቀመጠው እርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት አብረው ከኖሩ
- አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባብ ወይም በማስተማር ወይም በማሳደግ ላይ በማሳደግ ላይ እንደአባት ከተሳተፍ ወይም
- በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን በማረጋጥ የፃፋቸው ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ፅሁፎች ካለ አባትነት በፍርድ ሊረጋጥ የሚችል ሲሆን ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ሊታወቅ አይችልም።[139]

### *4.7.3* ልጅነት

ከላይ እንደተገለፀው አባትነት እና እናትነት የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ህጉ ያስቀመጠ ሲሆን በተመሳሳይ ልጅነት የሚረጋገጥበትን ሁኔታም አመልክቷል። በዚህም ልጅነት በሶስት መንገዶች ሊረጋገጥ ይችላል። ይኸውም፡-

#### 4.7.3 .1 በልደት ምስክር ወረቀት

አንድ ልጅ የአንድ እናት ወይም አባት ልጅ መሆኑ የሚረጋገጠው በልደት ምስክር ወረቀት ነው። ይህም የአንድ ልጅ ወላጆች ጭምር የሚገልፅ በወሳኝ ኩነት ጽ/ቤቶች የሚሰጥ ምስክር ወረቀት ነው።[140]

#### 4.7.3 .2 የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት

በሀገራችን የልደት ምስክር ወረቀት ማውጣት እምብዛም የተለመደ አይደለም። ህጉ ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይመስላል የልደት ምስክር ወረቀት በማይኖርበት ጊዜ የልጅነት ሁኔታ ሊረጋገጥ እንደሚችል ደንግጓል። የልጅነት ሁኔታ ማለት አንድ ልጅ የአንድ ሰው ልጅ ነው ለማለት የሚስችል ግንኙነት መኖርን የሚያመላክቱ ሁኔታዎችን የሚወክል ሲሆን ይህ ሁኔታ አለ የሚባለው በማህበረሰቡ ዘንድ የእከሌ ልጅ ነው ተብሎ የሚገመትበት ሲሆን ነው። ይህ ሁኔታን ማስረዳት ከተቻለ ፍርድ ቤት

---

[139]ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 143 እና 145

[140]ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 154

ልጁ ወላጅ የተባለው ሰው ልጅ እንደሆነ ግምት ይወስዳል። ነገር ግን ይህ ግምት በተቃራኒ ማስረጃ ሊፈርስ የሚችል ነው።[141]

### 4.7.3 .3 በሌሎች ማስረጃዎች

የልደት ምስክር ወረቀት ማቅረብ ወይም የልጅነት ሁኔታ ማሳየት ያልቻለ ሰው ልጅነቱን መጠየቅ አይችልም አይባልም። ይልቁንም ክስ በመመስረት ልጅነት በምስክር ወይም በሌላ ማናቸውም አይነት ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል። ሆኖም መሰል ክስ መቅረብ የሚችለው ፍርድ ቤቱ ክሱ እንዲቀርብ ሲፈቅድ ብቻ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክስ እንዲቀርብ የሚፈቅደው ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት ሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።[142]

ልጅነትን ለማረጋገት ክስ በማንና መቼ ይቀርባል?

ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ክስ በራሱ በልጁ፣ በአሳዳሪው፣ በወራሾቹ ወይም የልጁ እናት ወይም አባት ነን በሚሉ ሰዎች ሊቀርብ ይችላል። ልጁ በህይወት እስካለ ድረስ ልጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ማቅረብ የሚችል ሲሆን አሳዳሪው ወይም ወላጁ ማቅረብ የሚችለው ልጁ አካለ መጠን እስካልደረሰ ጊዜ ድረስ ነው። ልጁ አስራ ስምንት አመት ሳይሞላው ሞቶ እንደሆነ የወራሾች ክስ የማቅረቢያ ጊዜ በአንድ አመት ጊዜ የተወሰነ ነው።[143]

## 4.8 ጉዲፈቻ

ጉዲፈቻ አንድ ሰው በስጋ ያልወለደውን ልጅ እንደ ልጁ ተቀብሎ የሚያሳድግበት ልማድ ነው። በሀገራችንም ለረጅም ጊዜ የቆየ እና በስፋት የተለመደ ሲሆን ምንም እንኳን የህግ የተመለከተውን የስምምነት ሂደት የጠበቀ ባይሆንም በሀገራችን በተለምዶ ሲከወን የነበረ የመረዳዳት ተግባር ነው። ወደ ህግ ማዕቀፉ ስንመጣ የቤተሰብ ህጉ ጉዲፈቻ በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በስምምነት የወላጅና የልጅ ዝምድና የሚፈጠርበት ሂደት እንደሆነ እውቅና ይሰጣል።[144] የጉዲፈቻ ልጅ መሆን የሚችለው ከአስራ ስምንት አመት በታች ያለ ልጅ ሲሆን በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ልጅ እራሱን ችሎት

---

[141] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 157

[142] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 158

[143] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 161

[144] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 180

ህጋዊ ተግባራትን መከወን የማይችል በመሆኑ ጉዲፈቻ ስምምነቱ በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል የሚፈጸም ነው።[145]

የጉዲፈቻ ስምምነት በፍርድ ቤት መፅደቅ ያለበት ሲሆን ካልፀደቀ ውጤት አይኖረውም። ፍርድ ቤት የጉዲፈቻ ስምምነት ሲቀርብለት ጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ እንዲሁም የአሳዳሪውን ወይም የወላጆቹን አስተያየት ከመስማት ጀምሮ ጉዲፈቻ አድረጊው ልጁን ተንካባክቦ ለማሳደግ ያለውን አቅም እንዲሁም ልጁን እንደልጁ እንደሚያሳድገውና መጠቀሚያ እንደማደርገው የሚያሳዩ መረጃዎችን ማየት ይጠበቅበታል።[146]

የጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ እድሜን በተመለከተ ከላይ እንደተጠሰው እድሜው አስራ ስምንት አመት ያልሞላው መሆን ያለበት ሲሆን በፅንስ ያለ ያልተወለደ ልጅን ይጨምራል። ሆኖም ልጁ ከተወለደ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ስምምነቱን መሰረዝ ትችላለች።[147]

አንድ ሰው ጉዲፈቻ ማድረግ የሚችልው በህጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች ሲያሟሉ ብቻ ነው። በተለይ ጉዲፈቻ አድራጊውም የእድሜና ፈቃድ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። ይኸውም አንድ ሰው ጉዲፈቻ ማድረግ ይችል ዘንድ 25 አመት የሞላው መሆን ይገባዋል። ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ባልና ሚስት ከሆኑ አንዳቸው ሀያ አምስት አመት ከሞላቸው ጉዲፈቻ ማድረግ ይችላሉ።[148] ከዚህ በተጨማሪ ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ባልና ሚስት በሚሆኑ ጊዜ የሁለቱም ስምምነት ሊኖር ግድ ነው። ከተጋቢዎቹ አንደኛው ፈቃዱን መስጠት የማይችል ከሆነ ጉዲፈቻ ማድረግ አይቻልም።[149]

ሌላው ከጉዲፋቻ አድራጊ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ከዜግነት ጋር የተያዘ ጉዳይ ነው። የቤተሰብ ህጋችን በውጪ ዜጎች የሚደረግ ጉዲፈቻን ያካተተ ነበር። ሆኖም በጉዲፈቻ ከሀገር የወጡ ልጆች ላይ እየደረሰ ያለው ኢሰብአዊ ድርጊት የውጪ ዜጎች የሚያደርጉትን ጉዲፈቻ ህጉ እንዲሻሻል ምክንያት ሆኗል። በዚህ እና መሰል ተደጋጋሚ ድርጊቶች ምክንያት በማሻሻያ አዋጁ በቤተሰብ ህጉ ተካተው የነበሩ

[145] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 190

[146] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 194

[147] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 185፣ 187

[148] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 184

[149] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 186

በውጪ ዜጎች የሚደረግን ጉዲፈቻ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሻሩ ተደርጓል፡፡[150] ነገር ግን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 189202 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይህ አዋጅ ትውልደ ኢትዮጵውያን ሆነው የውጪ ዜግነት ያላቸውን ሰዎች ጉዲፈቻ ከማድረግ የሚከለክላቸው እንዳልሆነ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

የጉዲፈቻ ስምምነት ህጉን ጠብቆ ከተፈፀመ በኋላ ጉዲፈቻ የተደረገው ልጅ በማናቸውም ረገድ የጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ እንደሆነ የሚቆጠር በመሆኑ በማንኛውም ሁኔታ የጉዲፈቻ አድራጊው የተፈጥሮ ልጆች ያላቸውን መብት ይኖረዋል፡፡[151] ይህ ማለት ግን ጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ ከቀድሞ ቤተሰቦቹ ጋር ያለው ዝምድና ይቀራል ማለት አይደለም። ይልቁንም ዝምድናው ይቀጥላል። ከዚህም አልፎ ጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ ትዳር ሲመሰርት የጉዲፈቻው ልጅ ሚስት ወይም ባል እንዲሁም ተወላጆቹ ከቀድሞ ቤተሰቡ ጋር ዝምድና ይኖራቸዋል፡፡[152]

ጉዲፈቻ አድራጊው ጉዲፈቻ ደረገውን ልጅ በአግባቡ ሳይዘው ቢቀር ምን ይደረጋል?

ጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን በባርነት ወይም ባርነት በሚመስል ሁኔታ ከያዘው፣ ከግብረገብ ውጪ በሆኑ ተግባራት በማሰማራት መጠቀሚያ ካደረገው ወይም በማንኛውም መንገድ የልጁን የወደፊት ህይወት በሚጎዳ መልኩ ከያዘው ፍርድ ቤት የጉዲፈቻ ስምምነቱን ይሰርዘዋል። ከዚህ ውጪ ግን የጉዲፈቻ ስምምነት ሊሰረዝ አይችልም፡፡[153] ይህ ሆኖ ሲገኝ እራሱ የጉዲፈቻ ልጁ፣ የህፃናትን ደህንነት ለመከታተል ስልጣን ያለው የመንግስት አካል ወይም ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ለፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡[154]

---

[150] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1070/2010፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 24 አመት ቁጥር 26ኛ፣

[151] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 6ኛ አመት ልዩ እትም ቁጥር 1፣ አንቀፅ 181

[152] ዝኒ ከማሁ183

[153] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 195

[154] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 196

## 4.9 ሞግዚትነት እና አሳዳሪነት

አስራ ስምንት አመት ያልሞላው ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ በመሆኑ ህጋዊ ድርጊቶችን ለመፈፀመ አይችሉም።[155] የዚህ ምክንያት ከአስራ ስምንት አመት በታች ያሉ ልጆች ገና በእድገት ላይ ያሉ በመሆናቸው እድገታቸው ድጋፍ ሊደረግልት የሚገባው በመሆኑና እንደ አዋቂ ሰዎች ክፉና ደጉን በበቂ ደረጃ ላይረዱ የሚችሉ ስለሆነ ግምት ውስጥ በማስገባት የተደረገ እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህ ማለት ግን ከአስራ ስምንት አመት በታች ያለ ልጅ የህግ ደርጊቶችን መፈፀም የሚጠይቁ ጉዳዮች የሉትም ማለት አይደለም። ይልቁንም አሳዳሪነት እና ሞግዚትነት ለዚህ መፍትሄ እንዲሰጥ በህጉ የተቀመጡ መፍትሄዎች ናቸው።

አሳዳሪነትና ሞግዚትነት በህጉ ለተለያየ አላማ የተቀመጡ እንደሆነ ከቤተሰብ ህጉ መረዳት ይቻላል። አሳዳሪነት አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ስለሚኖረው መልካም አስተዳደግና ደህንነት የመጠበቅ ሀላፊነት ያለው ነው። መልካም አስተዳደግ ሲባል አሳዳሪው ስለልጁ የመኖሪያ ቦታ፣ ጤና እና ትምህርት የመሳሰሉ በልጁ እድገት ጋር ሚገናኙ ጉዳዮችን ይወስናል። ሞግዚትነት ደግሞ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት ነክ ጥቅሞቹን እና የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት ሀላፊነት ያለው ነው።[156] ምንም እንኳን ሁለቱ ተግባራት የተለያዩ እንደሆኑ ቢገለፅም ከሚሾመው ሰው አንፃር ግን የልጁ አሳዳሪ እንዲሆን ሥልጣን ተሰጥቶት በአሳዳሪነት የተረከበ ሰው ሞግዚቱም ይሆናል። በዚህም አባት ወይም እናት ወይም በፍርድ ቤት የሚሾም ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ሁለቱም ስልጣን እንደያዘ ይቆጠራል። ሆኖም አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ከአሳዳሪ በተጨማሪ ሞግዚት ሊሾም ይችላል።[157]

እናትና አባት ጋብቻቸው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ አካለመጠን ላልደረሱ ልጆቻቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት የጋራ ስልጣን ያላቸው ሲሆን ለልጃቸው ጠቃሚ መስሎ በታያቸው ጊዜ የአሳዳሪነቱን ስልጣን ይዘው ሞግዚት ሊሾሙ ይችላሉ። ከሁለቱ አንዱ ከሞተ፣ ችሎታ ወይም ተገቢነት ካጣ ወይም የቤተሰብ አስተዳዳሪነት መብቱ ከታገደ አስተዳዳሪነትና ሞግዚትነቱን የሚወጣው ሌላኛው ወላጅ ብቻ ይሆናል። ባልና ሚስት ፍቺ የሚፈፅሙ ከከሆነ ደግሞ አሳዳሪነትንና ሞግዚትነትን በተመከተ ስምምነት ማድረግ የሚችሉ ሲሆን ስምምነት ማድረግ ካልቻሉ ፍርድ ቤት የሚወስነው ይሆናል።[158]

---

[155] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 216

[156] ዝኒ ከማሁ

[157] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 231፣233

[158] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 219፣ 220፣ 221

ወላጆች በማይኖሩ ጊዜስ?

ወላጆን በማይኖሩ እና በኑዛዜም ሞግዚት ሳየሾሙ ቀርተው ከሆነ ህጉ በሚያስቀምጠው ቅድም ተከተል ዘመዶቹ ይህን ስልጣን ያገኛሉ። ይኸውም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ማለትም በሁለቱም ወላጆጁ መካከል ያሉ አያቶች ናቸው። እነሱ ከሌሉ በመቀጠል ሞግዚት መሆን የሚችሉት አካለ መጠን የደረሱ የልጁ እህትና ወንድሞች ሲሆኑ እነሱም ከሌሉ የልጁ አክስትና አጎት ይሆናል። ነገር ግን ሞግዚትነት ይሰጠኝ በሚል በሚያመለክት የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ የሞግዚትነት ስልጣን ይሰጠኝ ሲል አቤቱታ ካቀረበ ይህ ቅደም ተከተል ሊለወጥ ይችላል። ሆኖም እነዚህ ሁሉ የሌሉበት አጋጣሚ ቢከሰት ፍርድ ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅትን ጨምሮ ለመረጠው ሰው ሊሾም ይችላል።[159]

በሌላ በኩል አሳዳሪው እና ሞግዚቱ ሀላፊነታቸውን በአግባቡ ካልተወጡ ሊሻሩ ይችላሉ። ከላይ እንደተገለፀው አሳዳሪ ከልጁ አስተዳደግን በተመለከተ ሀለፊነት እንደመሆኑ ጊዜውን እና የሚኖርበትን አካባቢ ሁኔታ አንፃር ቅቡልነት ያለው አስተዳደግ ሊተገብር ይገባል። በአንፃሩ ለልጁ አስፈላጊ የሆነ ጥበቃ ካላደረገ፣ ከሞራል ጋር የሚስማማ አእምሮ አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ ካላደረገ በተለይ ደግሞ ልጁ ወንጀል ከሰራና ወንጀሉን የፈፀመው በመጥፎ አስተዳደግ ወይም በአሳዳሪው ጉድለት ተገቢውን ግብረ ገብ ትምህት ባለማግኘቱ ከሆነ አሳዳሪው ሊሻር ይችላል።[160] በተመሳሳይ ሞግዚት ከንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ስልጣን ሲሆን የልጁን ንብረትና ሀብት በተሰጠው መመሪያና በንብረት አስተዳደር ስርአት ሳይጠብቅ የቀረ ወይም እዳ ለመክፈል አለመቻሉ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ ይሻራል። ይህንን ሀላፊነቱን ሳይወጣ ቀርቶ በልጁ ላይ ለሚደርሰው ሀላፊነት ተጠያቂ ነው።[161]

4.10 ቀለብ

ቀለብ ማለት ሰርቶ ለኑሮ የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ ነገሮች ለማሟላት የሚያስፈልገውን ገቢ ማግኘት አቅም ሲያጣ እና ችግር ላይ ሲወድቅ ከቅርብ ዘመዶቻቸው የሚሰጥ ድጎማ ነው። ይህ አቅም ማጣት በእድሜ (ለስራ ባለመድረስ ወይም በእርጅና)፣ በጤና ችግር ወይም አደጋ በመሳሰሉት ምክንያት ሰርቶ እራስን ለማስተዳደር አቅም የማይኖርበትን ሁኔታ የሚመለከተ ነው። ለኑሮ

---

[159] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 225፣ 226፣ 227፣2 29

[160] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 245

[161] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 245፣ 246፣ 309

የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ሲባል ደግሞ ለምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ ጤና እና በተለይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማሟላትን የሚያጠቃልል ነው።[162] ተቀባዩ ሲሞትም የቀብር ወጪን የጨምራል።[163] አንድ ሰው በዚህ አይነት ችግር ውስጥ ሲወድቅ በህጉ የተመከቱት የቅርብ ዘመዶቹ ቀለብ እንዲሰጡት በህግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል። በህጉ መሰረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለው

- በቀጥታ ወላጆችና ተዋላጆች፡- በወላጆችና በልጆቻቸው መካከል
- በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል፡- በተጋቢዎች እና በሌላኛው ተጋቢ ወላጆች እንዲሁም ልጆች መካከል
- በወንድማማቾችና እህትማማቶች መካከል ነው።[164]

እነዚህ ሁሉ አንዳቸው ለሌላቸው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ከመሆኑ አንፃር ለአንድ ሰው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ ቀለብ የሚየስፈለገው ሰው ልጆች፣ መንድሞች ወይም እህቶች ሊኖሩት ይችላሉ። መሰል ሁኔታ ሲያጋጥም እነዚህ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ከመካከላቸው አንዱ እንዲሰጥ መስማማት የሚችሉ ሲሆን ተቀበዩ ይህን ስምምነት በፈቃዱ የተቀበለ እንደሆነ ስምምነቱን የማያከብርበት ከባድ ምክንያት ካልገጠመው በስተቀር ከሌሎቹ መጠየቅ አይችልም። ስምምነት የሌለ ከሆነ ደግሞ ህጉ ቅደም ተከተል አስቀምጧል። በዚህም፡-

- በመጀመሪያ ደረጃ የተቀባዩ ባል ወይ ሚስት
- በሁለተኛ ጀረጃ ተመላጆች እንደየደረጃቸው ማለትም ልጆች፣የልጅ ልጆች… በየደረጃቸው
- በሶስተኛ ደረጃ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው ማለትም መለጆች፣ አያቶች … በየደረጃቸው
- በአራተኛ ደረጃ ወንድሞችና እህቶች
- በአምስተኛ ደረጃ የጋብቻ ተወላጆች እንደየደረጃቸው ማለትም የሚስት ወይም የባል ልጆች፣ የልጅ ልጆች … እንደየደረጃቸው
- በስድስተኛ ደረጃ የጋብቻ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው ማለትም የባል ወይም የሚስት ወላጆች፣ አያቶች … እንደየደረጃቸው

ቀለብ የመስጠት ግዴታውን እንደየቅደም ተከተላቸው መወጣት አለባቸው።[165] ሆኖም በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ያለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ጋብቻው ከሞት ውጪ በሆነ ምክንያት ከፈረሰ

[162] የቤተሰብ ህጉ ሀተታ ዘምክንያት፣

[163] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ እትም 1፣ አንቀፅ 213

[164] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 198

ቀለብ የመስጠት ግዴታው ቀሪ ይሆናል።[166] ከዚህ ጋር በተያዘ ሊታይ የሚገባው በቀለብ ረገድ የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት እና ከጉዲፈቻ ቤተሰቡ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ነው። የጉዲፈቻ ልጅ ቀደምት ወይም የተፈጥሮ ቤተሰቦች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ከዘመዶቻቸው መጠየቅ የማይችሉ ካልሆነ በስተቀር ጉዲፈቻ የሰጡትን ልጅ ቀለብ መጠየቅ አይችሉም። በተመሳሳይ የጉዲፈቻ ልጁ ባል ወይም ሚስት እንዲሁም የቀጥታ መስመር ተወላጆች ጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘመድ ቀለበት መስጠት የማችሉ ካልሆነ በስተቀር የሥር ወይም የተፈጥሮ ወላጆቹን ቀለብ መጠየቅ አይችልም።[167]

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈፃሚ የሚሆነው ወይም የሚሰጠው የቀለብ መጠን የሚወሰነው የቀለብ ሰጪውን አቅም እንዲሁም የተቀባዩን ችግር መሰረት በማድረግ ነው።[168] የቀለቡ መጠን ከታወቀ በኃላ አፈፃፀሙ በዋናነት ገንዘቡን ለተቀባዩ በመስጠት ሲሆን ቀለብ ሰጪው ተቀባዩን ቤቱ በመስቀመጥ ግዴታውን መፈፀመ ከፈለገ በዚህ መለኩ ግዴታን ከመወጣት አይከለከልም።[169] የቀለቡ መጠን ወይም የተቀባዩ መኖሪያን በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ በተቀባዩ ጠያቂነት ሊሻሻል ይችላል። ለምሳሌ የቀለብ ሰጪው ገቢ ከጨመረ እና ተቀባዩ የሚሰጠው ቀለብ በኑሮ ውድነት ምክንያት መሰረታዊ ፍላጎቱን ማሟላት ባይችል ተቀባዩ የቀለብ መጠኑ እንዲሻሻልለት መጠየቅ ይችላል።[170] በተጨማሪም ቀለቡ የሚሰጠው በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው ቦታ ሊሆን ይገባል።[171] ይህ ሲባል ግን ህጉ ለማለት የፈለገው የተቀባዩን የመኖሪያ ቦታ የሚመለከት እንደሆነ የተሳሳተ ግምት እንዳይኖር ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ምክንያቱም ህጉ በዚህ መልኩ ያስቀመጠው የተቀባዩን የመኖሪያ ቦታ ብቻ በማሰብ ሳይሆን የሰጪው የመኖሪያ ቦታም ለተቀባዩ ከተመቸው ቀለብ የሚሰጥበት ቦታ የቀለብ ሰጪው መኖሪያም ጭምር ሊሆን እንደሚችልና ዋናው ትኩረት የትኛው ቦታ የሚለው ሳይሆን የቦታው ለተቀባዩ አመቺነቱ ላይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።[172]

---

165 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 210

166 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 199

167 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 212

168 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 212

169 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 207

170 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 203

171 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 204

172 የቤተሰብ ህጉ ሀተታ ዘምክንያት፣ ገፅ 53

በሌላ በኩል ቀለብ ተቀባዩ ለኑሮ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ቀለቡን ለተከታታይ ሶስት ወራት ውስጥ ሳይጠይቅ ወይም ሳይቀበል የቀረ እንደሆነ የተጠራቀመው ይሰጠኝ ማለት አይችልም። በተጨማሪም የቀለብ ከንዘብ ለተቀባዩ ኑሩ አስፈላጊ በመሆኑ ተቀባዩ ላለበት ችግር ድጋፍ ለሚያደርጉ የዕርዳታ ድርጅቶች ወይም ደግሞ ለተቀባዩ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ካበደሩ አበዳሪዎች በስተቀር ለሌላ ሰው ሊተላለፍ ወይም በመያዣነት ሊያዝ አይችልም። [173]

በመጨረሻም ቀለብ ተቀባዩ መልካም ባህሪ ሊኖረው ያስፈልጋል። ይህን ሳያደርግ ቀርቶ በቀለብ ሰጪው፣ በቀለብ ሰጪው ወደላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆችና ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ወንጀል ከፈፀመ ወይም ለመፈፀም ከሞከር ቀለብ የመቀበል መብቱን ያጣል። ይህ ወንጀል በቀለብ ሰጪው ወይም በተጠቀሱት ቤተሰቦቹና ዘመዶቹ ህይወት ወይም ንብረት ላይ የሚፈፀም ያነጣጠሩ የወንጀል ድርጊቶችን ያጠቃልላል።[174]

## ክፍል አምስት

### የውርስ ህግ

ውርስ በህጉ ላይ በተገለፀው መልኩ በጥልቀትም ባይሆን ጠቅለል ባለ መልኩ የተለያዩ ንብረቶችና የገንዘብ ጥቅሞች ከወላጅ ወደ ልጅ የሚተላለፍበት ሂደት መሆኑን በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። ይህ በተለምዶ ያለ አረዳድ ህጉን በተሟላ ሁኔታ ያልተረዳ እንደመሆኑ ህጉ ውርስን በተመለከተ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች እንደሚከተለው የምንመለከት ይሆናል።

ውርስ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ የሚነሳ ጉዳይ ነው። ከሞተ በኋላ በዋና መኖሪያ ስፍራ ውርሱ ይከፈታል። በዚህም ከሟቹ ግለሰብ ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው ሞቱ ከሚያቋርጣቸው መብቶችና ግዴታዎች ወጪ ሌሎች መብቶች ለወራሾችና ለኑዛዜ ባለስጦታዎች ይተላለፋሉ።[175] ውርስ በአውራሹ ኑዛዜ፣ ያለ ኑዛዜ (በህግ) ወይም በሁለቱም ሊፈፀም ይችላል።[176] ይህ ማለት ሟች ከሞተ በኋላ የውርስ ሃብት እንዲከፋፈል የሚፈልግበትን ሁኔታ በተመለከተ በህጉ በተመለከተው መሰረት የፀና ኑዛዝ አድርጎ ከሆነ ውርሱ በኑዛዜው መሰረት የሚፈፀም ሲሆን ሟች ኑዛዜ የሌላው ከሆነ በህጉ በተቀመጠው የዝምድና

[173] የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ እትም 1፣ አንቀፅ 205

[174] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 200

[175] የፍትሐ ብሔር ሕግ 1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952 በተለይ የወጣ፣ ቁጥር 826

[176] ዝኒ ከማሁ፣ 829

ቅደም ተከተል መሰረት ውርሱ ሚከፋፈል ይሆናል ማለት ነው። በተጨማሪም ሟች ኑዛዜ ኖሮት ነገር ግን ሁሉንም ንብረቶቹን ያላካተተ ከሆነ በኑዛዜው ያልተሸፈኑ ንብረቶች በህጉ መሰረት ለወራሾች የሚከፋፈል ይሆናል።

### 5.1 ወራሽ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ለመውረስ በህጉ የተመለከቱ ሁለት ዋና ዋና ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው። የመጀመሪያው በህይወት መኖር ሲሆን አንድ ሰው ወራሽ መሆን የሚችለው ሟቹ ሲሞት በህይወት ያለ ከሆነ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሶስት ጉልህ ጥያቄዎች ይነሳሉ።

ወራሹ ቢሞትስ?

ወራሹ የሞተው ውርሱ ከተከፈተ ወይም አውራሹ ከሞተ በኋላ ከሆነ የወራሹ የወራሽነት መብት ለወራሹ ወራሾች የሚተላለፍ ይሆናል።[177]

አባትና ልጅ በተሽከርካሪ በመጓዝ ላይ እንዳሉ አደጋ ደርሶባቸው ሁለቱም ቢሞቱ እና ከሁለቱ ቀድሞ የሞተው ማን እንደሆነ ማወቅ ባይቻል በውርሱ ላይ የሚያመጣው ውጤት ምን ይሆናል?

ይህ ሊፈጠር የሚችል እንደሆነ ህጉ አስቀድሞ በመገመት መፍትሄ ያስቀመጠለት ጉዳይ ነው።አባት እና እናት እኩል ከሞቱ እና ማን ቀድሞ እንደሞተ ካልታወቀ ወራሹ ከአውራሹ በኋላ እንደሞተ ይቆጠራል። ይህ ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው የወራሹ ወራሾች ተተክተው ውርሱን እንዲያገኙ የሚደርግ ይሆናል። ይህ ሁኔታ አባት እና እናት እኩል ሲሞቱ ብቻ ሳይሆን ሌሎች አውራሾችም በተመሳሳይ ግዜ ሞተው ማን እንደቀደመ ባልታወቀ ግዜም ከአውራሹ በሀላ እንደሞቱ ይቆጠራል።

አቶ አበበ ባለቤቱ ነፍሰጡር በነበረችበት ጊዜ ህመም አጋጠመውና ህይወቱ አለፈ፡፡ በዚህ ጊዜ የተፀነሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል?

ለዚህ መልስ ለማግኘት የፍትሐብሔር ህጉ በጠቅላላ ስለ ሰዎች ያካተታቸውን ድንጋጌዎች ማየት ይጠይቃል። በዚህም የተፀነሰ ልጅ ተወልዶ በህይወት የሚኖር ከሆነ ለልጁ ጥቅም አስፈላጊ

---

[177] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 833

በሚሆንባቸው ሁኔታዎች ሁሉ (for the best intereset of the chiled) እንደተወለደ ይቆጠራል።[178] ስለዚህም እስከሚወለድ በዚህ የህግ ግምት የሚቆይ ሲሆን ከተወለደ በኋላ ግን ህጉ ያስቀመጠውን የገጌ ገደብ መኖር ይጠበቅበታል። ይኸውም ልጁ ተወልዶ ለ48 (አርባ ስምንት) ሰአታት በህይወት ከቆየ እንደኖረው የሚቆጠር እና የወራሽነት መብቱ የሚከበርለት ሲሆን ለዚህ ጊዜ በታች ከቆየ ግን እንዳልኖረ ይቆጠራል። ሆኖም ልጁ ለተጠቀሰው ጊዜ በፊት ሞተው በተፈጥሮ ጉድለት ካልሆነና ይህን ማስረዳት ከተቻለ ከአርባ ስምንት ሰአት በፊት ቢሞትም እንደኖረ ይቆጠራል።[179]

ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ልጅ እና የጉዲፈቻ ልጅ በጋብቻ ውስጥ ከተወለደ ልጅ አንፃር በውርስ ያላቸው መብት እስከምን ድረስ ነው?

ፆታ፣ እድሜና ዜግነትስ በውርስ ረገድ ልዩነት ያመጣል?

ሴት በውርስ ረገድ ከወንድ እኩል መብት አላት?

ከውርስ አንፃር የልጅ በጋብቻ ውስጥ ወይም ከጋብቻ ውጪ መወለድ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ መሆን የሚያመጣው ምንም ልዩነት አይኖርም።[180]

ለምሳሌ:-

በቀለ አባቱ አቶ ባልቻ ኑዛዜ ማድረጋቸውን እና በኑዛዜው ከሌሎች ወንድሞቹ ያነሰ ንብረት እንደተናዘዙለት አውቆ በመበሳጨት ኑዛዜአቸውን ቢያቃጥለው ወይም አብላጫ ውርስ ተሰጥቶታል የለውን ወንድሙን ለመግደል ቢሞክርይህ ድርጊት በቀለን ለወራሽነት ያልተገባ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡

[179] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 4

[180] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 836

ለረጅም ዘመናትበሀገራችን ለሴቶች ያለው አመለካከት የተዛባ ከመሆኑ የተነሳ በውርስም ረገድ በርካታ አድሎአዊ ተግባራት ሲፈፀሙ ቆይቷል። ከተሞች አካባቢ የተወሰነ ለውጥ የታየ ቢሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የሚሰጥበት ባህል የገሀዱ አለም ነፀብራቅ ነው። በህጉ ግን የወራሹ ፆታ፣ እድሜ እና ዜግነት ከወራሽነት መብት አንፃር ምንም አይነት ለውጥ የሚያመጣ ባለመሆኑ በፍትህ አካላት ዘንድ በመቅረብ የሴቶችን መብታቸውን ማስከበር ይቻላል ማለት ነው።[181]

ሌላኛው ለወራሽነት መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ለወራሽነት ያልተገባ (unworthy) አለመሆን ሲሆን አንድ ሰው ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚባለው ሟቹን ወይም ከሟቹን ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ወይም ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች አንዱን ወይም የሟቹን ባል ወይም ሚስት አስቦ በመግደል የተፈረደበት ከሆነ ወይም ለመግደል የሞከረ ከሆነ፤ ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱን በሀሰት በመወንጀል ወይም በሀሰት በመመስከር የሞት ፍርድ ወይም ከአስር አመት የበለጠ ፅኑ እስራት ቅጣትን ለማስከተል የሚያሰጋ ሆነ የተቀጣ እንደሆነ ነው።[182] ነገር ግን ወንጀሉ የተደረገዉ አዉራሹ ከሞተ በኃላ ከሆነ መብቱን የማያሳጣ አይደለም። በተጨማሪም

- የሟቹን የሰውነት ሁኔታ ምክንያት በማድረግ አውራሹ ከመሞቱ በፊት በአሉት ሶስት ወራት ውስጥ ኑዛዜ እንዲያደርግ፣ እንዳይለውጥ ወይም እንዳይሽር ከከለከለ
- አስቦ ያለ ሟች ፈቃድ የሟቹን የመጨረሻ ኑዛዜ ያበላሸ፣ እንዳይገኝ ያደረገ፣ ያጠፋ ወይም በማወቅ በሀሰት ኑዛዜ የተጠቀመ እንደሆነ የወራሽነት መብቱን ያጣል።
- ሟቹ ግልፅ በሆነ ፅሁፍ ለወራሽነት ያልተገባ የሆነውን ወራሽ ይቅርታ አድርጎለት ያሳወቀ ከሆነ ወይም ሟች ኑዛዝውን ያደረገው ለወራሽነት ያልተገባ የሚደርገው ድርጊት ከተፈፀመ በኋላ ሆኖ የድርጊቱን ፈፃሚ ወራሽ የኑዛዜው ተጠቃሚ ካደረገው ወራሹ የመውረስ መብቱን አያጣም።[183]

---

[181] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 837

[182] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 838

[183] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 841

### *5.2 ሳይናዘዝ የሞተ ሰው ውርስ*

***ከላይ እንደተገለፀው ኑዛዜ የሟችን ፍላጎት መሰረት አድርጎ ውርስ የሚፈፀምበት ሲሆን ኑዛዜ ማድረግ በተለይም አስቀድሞ መናዘዝ በሀገራችን በስፋት የተለመደ ነው ለማለት አይቻልም። ስለህም ኑዛዜ የማይኖርባቸው ጊዜያት በርካታ እንደሚሆኑ መገመት አያዳግትም።***

ኑዛዜ በሌለ ጊዜ ውርስ እንዴት ይፈፀማል?

***ለዚህ ህጉ የራሱን መፍትሄ አስቀምጧል። ይኸውም ውርስ በዝምድና ደረጃ መሰረት የሚፈፀም ሲሆን ህጉ አራት የዝምድና ደረጃዎችን ደንግጓል።***

➢***የመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና***

***የመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና የሚባለው ሟች ከልጆቹ ጋር የሚኖረው ዝምድና ሲሆን የሟች ልጆች የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ይሆናሉ። ልጆቹ እያንዳንዳቸው ትክክል ወይም የሆነ ድርሻ የመውሰድ መብት አላቸው። ትክክል ድርሻ ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ሲሆን የእንግሊዝኛ ቅጂው*** "equal portion" ***የሚል ሀረግ መጠቀሙ ህጉ እኩል መካፈልን ታሳቢ ያደረገ ለመሆኑ ማሳያ ነው። ከሟች ልጆች አንዱ የሞተ ከሆነ እና ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ትቶ ከሆነ በእርሱ ተተክተው ይወርሳሉ።***[184]

የሟች ወራሾች አንዱ ከአውራሹ ቀድሞ ሞቶ ቢሆን ተተክቶ መውረስ ይችላል?

***ከላይ እንደተገለፀው ወራሽ የአውራሹ ውርስ ሲከፈት በህይወት መኖሩ የወራሽነት ቅድመ ሁኔታ ነው። ሆኖም ከአውራሹ አስቀድሞ የሞተ ሰው ወራሽ መሆን ባይችልም ተወላጆቹ እሱን ተክተው መውረስ መቻላቸው ለቅድመ ሁኔታው ልዩ ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው። ይህም ምትክ ወራሽነት ለቅድመ ሁኔታው ልዩ ሁኔታ ነው ማለት ነው።***[185]

ምሳሌ:- አቶ አበበ በለጠ፣ ሞገስ እና ማህሌት የተባሉ ሶስት ልጆች ነበሯቸው:: ከልጆቻቸው መሀከል በለጠ ከዚህ አለም በሞት ይለያል:: አቶ አበበም ከአንድ አመት በኋላ ህይወታቸው አለፈ::

በዚህ ጊዜ በለጠ ከአቶ አበበ ቀድሞ በመሞቱ ወራሽ መሆን ባይችልም የበለጠ ልጆች እሱን ተክተው ወራሽ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው::

---
18

18

➢ሁለተኛ ደረጃ ዝምድና

ሚች ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች የሌሉት ከሆነ ውርስ ወደ እናትና አባት የሚሄድ ሲሆን  እናትና አባት ውርሱን እኩል ይካፈላሉ። ከሁለቱ የሞተ ቢኖር በእርሱ ፋንታ ልጆቹ ወይም ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆቹ እሱን ተክተው ወራሽ ይሆናሉ። በሞተው ወላጅ መስመር በኩል ወራሽ ያልተገኘ እንደሆነ ወደ ሌላኛው መስመር ይተላለፋል።[186]

ምሳሌ

ወ/ሮ መቅደስ ልጅ የላቸውም:: ያለ ኑዛዜም ከዚህ አለም በሞት ይለያሉ:: የወ/ሮ መቅደስ አባት በህይወት የሌሉ ሲሆን እናታቸው ወ.ሮ አለሚቱ ግን በህይወት አሉ::

ወ/ሮ መቅደስ ልጅ የሌላቸው እንደመሆኑ ውርሱ ወደ እናትና አባታቸው የሚሄድ ሲሆን አባትየው በህይወት የሌሉ መሆኑ የወ/ሮ መቅደስ እህትና ወንድሞች አባታቸውን ተክተው የአባታቸውን ድርሻ የሚወርሱ ይሆናል::

➢ሶስተኛ ደረጃ ዝምድና

በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ደረጃ ዝምድና ወራሽ እና ተተኪ ወራሽ በሌለ ጊዜ በሶስተኛ ደረጃ ያሉ አያቶች ወራሽ ይሆናሉ። አንድ ሰው በእናት በኩል ሁለት አያት በአባት በኩል ደግሞ ሁለት አያት

[186] የፍትሐ ብሔር ሕግ 1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952 በተለይ የወጣ፣ ቁጥር 843፣ 844

በድምሩ አራት አያቶች ይኖሩታል። ስለዚህም ግማሹ ውርሱ በአባት መስመር ላሉ አያቶች ወይም ወደ ታች ለሚቆጠሩ ተወላጆች የሚሆን ሲሆን የተቀረው ግማሽ በእናት በኩል ላሉ አያቶች ወይም ወደ ታች ለሚቶተሩ ተወላጆች የሚከፋፈል ይሆናል። ሆኖም በአንዱ መስምር ወራሽ ያልተገኘ እንደሆነ ውርሱ ወደ ሌላኛው መስምር ተላለፋል።[187]

➢አራተኛ ደረጃ ወራሾች

የሶስተኛ ደረጃ ወራሾች በሌሉ ጊዜ ውርስ ወደ አራተኛ ደረጃ ወራሾች የሚተላፍ ሲሆን አራተኛ ደረጃ ወራሾች የሚባሉት የሟች ቅድመ አያቶች ናቸው። አንድ ሰው በእናት በኩል አራት ቅድመ አያት በአባት በኩል ደግሞ አራት ቅድመ አያቶች በድምሩ ስምንት ቅድመ ኤቶች ይኖሩታል። ስለዚህም ውርሱ በአባት በኩል ላሉ እና በእናት በኩል ላሉ ቅድመ አያቶች በእኩል ካፈላል ማለት ነው። ቅድመ አያቶች በህይወት የሌሉ ከሆነ ደግሞ የእነሱ ተወላጆች ወራሾች ይሆናሉ ማለት ነው። ሆኖም በአንዱ መስምር ወራሽ ያልተገኘ እንደሆነ ውርሱ ወደ ሌላኛው መስምር ይተላለፋል።[188]

በአራቱም ዝምድና ደረጃ ወራሽ ባይኖር ውርሱ ምን ይሆናል?

ከላይ በተጠቀሱት የዝምድና ደረጃዎች አንድም ወራሽ የማይገኝ ከሆነ ውርሱ ለመንግስት የሚተላለፍ ይሆናል።[189]

5.3 በኑዛዜ የሚደረግ ውርስ

ኑዛዜ አንድ ሰው በህወት እያለ እሱ ከሞተ በኋላ ንብረቱ ለማን፣ በምን መጠንና ሁኔታ መከፋፈል እንዳለበት ፍላጎቱን የሚገልፅበት ነው። ኑዛዜ ለተናዛዡ ግላዊ የሆነና በራሱ በተናዛዡ ብቻ መደረግ ያለበት ሲሆን ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም መሻር በተናዛዡ ብቻ መደረግ አለበት።[190]

አንድ ሰው ለሌላ ሰው በኑዛዜ ንብረት ለመስጠት ቃል መግባት ይችላል?

187 ዝኒ ከማ

188 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 847፣ 848

189 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 852

190 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 857

አንድ ሰው ኑዛዜ ለማድረግ፣ ለመለወጥ ወይም ለመሻር የሚገባው ቃል ተፈፃሚነት የሌለው ሲሆን ተናዛዡ በፈለገው ጊዜ ኑዛዜውን ሊለውጥ ወይም ሊሽር ይችላል።[191] አንድ ሰው ለሌላ ሰው በኑዛዜ ተጠቃሚ እንደሚያደርገው ቃል ቢገባለት ወይም በተደረገ ኑዛዜ ውስጥ ተጠቃሚ የነበረ ከሆነ ኑዛዜውን እንደማያሻሽል ወይም ላለመሻር ቃል ቢገባ ተቀባይነት የለውም።

ምሳሌ

አቶ ደበበ እና ባለቤታቸው ወ/ሮ አልማዝ አምስት ልጆች ቢኖሯቸውም የምትንከባከባቸው አንዷ ልጃቸው ብቻ ናት፡፡

በሌሎቹ ልጆቻቸው ያዘኑት አቶ ደበበ ለዚህች ለልጃቸው የመኖሪያ ቤታቸውን ለእሷ ለማድረግ ኑዛዜ እንደሚያደርጉ ቃል ቢገቡላት በህግ በኩል ውጤት አይኖረውም፡፡

በሌላ በኩል አቶ ደበበ ቃል ሲገቡ ኑዛዜውን አድረገውት ቢሆን እና ይህንን ኑዛዜ  እንደማያሻሽሉት ወይም እንደማይሽሩ የውል ቃል ገብተው ቢሆንም ይህም በህግ ተቀባይነት የለውም፡፡

4.2.1. የኑዛዜ ፎርም

በፍትሐብሔር ህጋችን መሰረት ኑዛዜ በሶስት ፎርም ሊደረግ ይችላል።

[191] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 859

5.2.1 በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ፡-

ይህ የኑዛዜ ፎርም ተናዛዡ እራሱ ወይም ተናዛዡ እየተናገረ ሌላ ማንኛውም ሰው የሚፅፈው ነው። ይህ ኑዛዜ ተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብ፣ ፎርማሊቲው መሟላቱንና የተፃፈበትን ቀን የሚያመለክት መሆንና ወዲያውም በተናዛዡ እና በምስክሮች መፈረም አለበት። ምስክሮቹ አካላ መጠን የደረሱ፣ በህግ ወይም በፍርድ ያልተከለከሉ እና ኑዛዜው የተፃፈበትን ቋንቋ የሚውቁ፣ የተፃፈውን ለመስማት ወይም ለማንበብ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ከምስክሮቹ አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ሆኖ ኑዛዜው የተደረገው ይህ ሰው ሥራውን በሚያካሂድበት ክፍል ውስጥ ከሆነ ሁለት መስክሮች በቂ ይሆናሉ።[192]

## 5.2.2 በተናዛዡ ጽሁፍ የሚደረግ ኑዛዜ፡-

በዚህ ፎርም የሚደረግ ኑዛዜ በሙሉ በተናዛዡ የሚፃፍ ሆኖ ተናዛዡ ኑዛዜ መሆኑ በግልፅ አመልክቶ በእያንዳንዱ ወረቀት (ገፅ) ላይ ቀን ፅፎ በመፈረም የሚደረግ ኑዛዤ ነው። ተናዛዡ ኑዛዜውን በኮምፒውተር ወይም በታይፕ ፅፎት ከሆነ ይህንን የሚገልፅ ፅሁፍ እያንዳንዱ ገፅ ላይ በእጅ ፅሁፉ ማመለክት ይጠበቅበታል። በተናዛዡ የሚደረግ ኑዛዝ በተደረገ በ7 (ሰባት) አመት ጊዜ ውስጥ ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም ፍርድ መዝገብ ቤት ካልተቀመጠ ፈራሽ ይሆናል።[193]

5.2.3 የቃል ኑዛዜ፡-

ይህ ኑዛዝ ተናዛዡ መሞቻው መቃረቡ ተሰምቶት የመጨረሻ ቃሉን  አካለ መጠን ለደረሱ፣ በህግ ወይም በፍርድ ክልከላ ላልተደረገባቸው ምስክሮች ለሁለት የሚሰጥበ ት ፎርም ነው። ከላይ ከተጠቀሱት ኑዛዜዎች በተለየ ሁኔታ ዝርዝር የውርስ ክፍፍልን የማያካተት ነው። ይልቁንም የቀብር ሥነ ሥርአቱን የሚመለከቱ ትዕዛዞችን፣ የእንዳንዱ ግምት ከብር 500 (አምስት መቶ) የማይበልጡ ስጦታዎችን መስጠት፣ አካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች አስተዳዳሪ ወይም ሞግዚትን የተመለከቱ ትዕዛዞችን መስጠትን የሚያካትት ነው። ከዚህ ውጪ ያለ የኑዛዜ ቃል ፈራሽ የሚሆን ሲሆን የእያንዳንዱ ስጦታ ግምት ከብር 500 (አምስት መቶ) ከበለጠ ከግምቱ በላይ ያለው ስጦታ ተቀናሽ

---

[192] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 880፣ 881፣ 838፣ 884

[193] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 884፣ 885፣ 903

ይሆናል።[194] በተጨማሪም ተናዛዡ ኑዛዜው በተደረገ ከሶስት ወር በኋላ ተናዛዡ በህይወት ከቆየ ኑዛዜው ውድቅ ይሆናል።[195]

### 5.3 ኑዛዜ ፈራሽ ወይም ውድቅ የሚሆንባቸው ምክንያቶች

ኑዛዜ ህግ ተከትሎ ባለመደረጉ ወይም በሌሎች ምክንቶች ፈራሽ ሊሆን ይችላል። ለአብነት፡-አንድ ኑዛዜ ተጠቃሚውንና ጉዳዩን ካላመለከተ ወይም አፈፃፀሙን የማይቻል ከሆነ ፈራሽ ነው።[196] ለምሳሌ፡ አቶ ጫላ አምስት ልጆች አሏቸው። አድሜአቸው እየገፋ በመምጣቱም እሳቸው ካለፉ በኋላ በውርስ ተነሳ ግጭት እንዳይፈጠር በማሰብ ኑዛዜ አዘጋጁ ። ነገር ግን በኑዛዜአቸው ላይ እያንዳንዳቸው 20% ይውሰዱ ከማለታቸው ውጪ የኑዛዜ ተጠቃሚዎቹን አልገለፁም። ይህን መሰል ኑዛዜ ፈራሽ ነው።

- ብዙ ሰዎች በአንድ ፅሁፍ ላይ ቢናዘዙ ፈራሽ ይሆናል።[197]
- የኑዛዜው ቃል ለህግ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ ከሆነ ፈራሽ ይሆናል።[198]

ምሳሌ

ወ/ሮ አለምነሽ ልጃቸው አቤል የሽከላ ሥራ የተሰማራ መሆኑ ደስተኛ አላደረጋቸውም፡፡ በዚህም ባደረጉት ኑዛዜ ወንድማቸው አቶ ብርሀኑ ልጃቸው ይህን ሥራ እንዳይሰራ የሚያደርገው ከሆነ ብር 300,000 እንዲሰጠው ቢናዘዙ ይህ ኑዛዜ ልጃቸው በፈለገው የሥራ ዘርፍ የመሰማራት መብቱን የሚነፍግ በመሆኑ ፈራሽ ይሆናል ማለት ነው፡፡

- አንድ ሰው ኑዛዜ ያደረገው በሀይል ከሆነ ወይም ተገዶ ከሆነ ፈራሽ ይሆናል።[199]

---

194 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 892፣ 893፣ 894

195 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 902

196 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 865

197 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 858

198 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 866

199 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 867

ምሳሌ

ወ/ሮ ብርሀን ስድስት ልጆች አሏቸው፡፡ ሁሉም ልጆቻቸው በውጪ ሀገር የሚኖሩ ሲሆኑ እሳቸው ከሀገር መውጣት ስለማፈልጉ በአዲስ አበባ ከተማ ኖራሉ፡፡ በእርጅና እና በበጤና ችግር ምክንያት የሰው እርዳታ እያስፈለጋቸው ሲመጣ የእህታቸው ልጅ ወደ ሆነች ሄልን ጋር ሄደው መኖር ይጀምራሉ፡፡ ይህን እንደጥሩ አጋጣሚ የወሰደችው ሄለን ኑዛዜ አድርገው የውርስ ተጠቃሚ እንዲያደርጓት በተዳጋጋሚ እንደምትገላቸው ታስፈራራቸዋለች፡፡ በዚህም ምክንያት ኑዛዜ አድረገው የኑዛዜ ተጠቃሚ አደረጓት፡፡

በዚህ የሀይል ድርጊት ተደረገ ኑዛዜ ፈራሽ ነው፡፡

ይህ ብ... መፈጠር ኑዛዜ ፈራሽ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል። ይኸውም፡-

➢ <u>የልጅ መወለድ</u>

ኑዛዜ ያደረገ ሰው ከኑዛዜው በኋላ ሌላ ልጅ ቢወልድ እና ልጁ ውርስ ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነ ተቃራኒ ቃል ቢኖር እንኳን ኑዛዜው ፈራሽ ይሆናል። ሆኖም ተናዛዡ ልጅ መወለዱን ቢያውቅም ኖሮ ስጦታውን አያስቀርም ተብሎ የሚገመት ከሆነ ዳኞች በኑዛዜ የተሰጡት ስጦታዎች በከፊል ወይም በሙሉ እንዲፀኑ ማድረግ የሚችሉ ቢሆንም ልጁ የሚያገኘው ግን በማናቸውም ምክንያት እጅግ ቢያንስ ከሀብቱ ሶስት ሩብ ማነስ የለበትም።[200]

ሶስት ሩብ ማለት ምን ማለት ነው?

ከኑዛዜ በኋላ የተወለደ ልጅ የሚያገኘውን የውርስ ድርሻ በተመለከተ የፍትሐብሔር ህጉ በአማርኛ ቅጂው ግልፅነት ይጎድለዋል። አማርኛው ከውርሱ ሀብት ሶስት ሩብ በሚል ሲያስቀምጥ እንግሊዝኛው

[200] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 904፣ 905

"three fourths of the share which he would receive in the intestate succession" ማለትም ውርሱ ያለኑዛዜ ቢሆን ያገኝ ከነበረው ሶስት አራተኛ ማነስ እንደሌለበት ይደነግጋል። ስለዚህ ሶስት አራተኛ ከጠቅላላ ውርሱ መሆኑን መረዳት ያሻል።

- <u>የጋብቻ መፍረስ</u>

ለባል ወይም ለሚስት ጥቅም ተብሎ በኑዛዜ ተካቶ ከሆነ ጋብቻው በሞት ሳይሆን በሌላ ምክንያት ከፈረሰ ኑዛዜው ውድቅ ይሆናል።[201]

ምሳሌ

አቶ ጫካ እና ወ/ሮ ይመኙሻል ለ10 አመታት በጋብቻ ኖሯል:: በተጋቡ በ8ኛ አመት አቶ ጫካ ኑዛዜ ሲያደርጉ ከጋራ ንብረታቸው ላይ ከእርሳቸው ድርሻ ግማሹ ለለባለቤታቸው እንዲሆን ይናዘዛሉ:: ሆኖም በ10ኛ አመት አቶ ጫካ እና ወ/ሮ ይመኙሻል በመሀላቸው በተፈጠረ አለመግባባት በፍቺ ይለያያሉ::

የተለያዩት በፍቺ በመሆኑ ለወ/ሮ መኙሻል የተደረገው የኑዛዜ ስጦታ ውድቅ ሆኗል ማለት ነው::

- በኑዛዜ ስጦታ የተሰጠ ንብረትን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ

ሌላኛው ተናዛዡ በኑዛዜው ያካተተውን ንብረት ወዶና ፈቅዶ በሙሉ ወይም በከፊል ለሌላ ሰው ካስተላለፈው ኑዛዜው ፈራሽ ይሆናል። ቢመለስ እንኳን ኑዛዜው በከፊል መሻሩን አያስቀረውም።[202]

---

[201] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 906

[202] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 900

## 5.4 ወራሽነትን መተው (Renunciation)

አንድ ወራሽ ውርሱን ካልፈለገ ውርሱን መተው መብቱ ነው። ይህም በተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ለአብነት በኢኮኖሚ የተሻለ በመሆኑ ሌሎቹ ወራሾች እንዲጠቀሙ በመፈለግ ወይም አውራሹ ብዙ ሀላፊነቶች ያሉበት ከሆነ በወሰደው ውርስ ልክ የሚመጣበትን ሀላፊነት ላለመቀበል በመፈለግ ውርሱን ሊተው ይችላል። ምክንያቱም አንድ ሰው ወራሽ ሲሆን በደረሰው የውርስ ሀብት መጠን አውራሹ ለሚኖርበት ሀላፊነት ሀላፊ መሆኑ አይቀርም። ይህ ማለት ውርሱ ከተከፋፈለ በኋላ ከአውራሹ ላይ ገንዘብ ጠያቂ ቢመጣ ወራሾች እንደደረሳቸው የውርስ መ[illegible] ማለት ነው። በተጠቀሱት ወይም በሌላ ምክንያት ውርስ የተ[illegible] ሊወርሱ የሚችሉ ተወላጆቹም የወራሽነት [illegible]

ምሳሌ

አቶ ባልቻ የተዋጣላቸው የንግድ ሰው ሲሆኑ ሶስት ልጆች አሏቸው፡፡ ከልጆቻቸው አንዱ የሆነው መኮንን ኖህ የተባለ ልጅ ያለው ሲሆን መኮንን ባጋጠመው ህመም ምክንያት ይሞታል፡፡ በዚህ ጊዜ መኮንን ልጅ የሆነው ኖህ የአባቱን የመኮንን ውርስ ይተዋል፡፡ ከሁለት አመት በኋላ አቶ ጫካ ከዚህ አለም በሞት ይለያሉ፡፡

በዚህ ጉዳይ ኖህ የአባቱን የመኮንን ውርስ አልፈልግም በማለቱ እሱ ተወላጆቹ እሱን ተክተው የአባቱን ውርስ ሊወርሱ አይችሉም፡፡

በሌላ በኩል ግን የመኮንን አባት አቶ ባልቻ ሲሞቱ ውርሱ በልጁ አልፈልግም የተባለበት የመኮንን ልጅ ኖህ አናቱን መኮንን ተክቶት ሊወርስ ይችላል፡፡

➢ <u>ከወራሽነት መነቀል (Disherison)</u>

ከውርስ መነቀል ማለት አንድ አውራሽ ከወራሾቹ መሀከል አንድን ሰው በግልፅ ወይም በዝምታ ከውርሱ እንዳያገኝ የሚያደርግበት ነው። በግልፅ ከውርስ መንቀል ተደረገ የሚባለው ተናዛዡ እከሌን ከውርስ ነቅየዋለሁ በማለት በግልፅ በኑዛዜው ሲገልፅ ነው። በዝምታ የሚደረግ ከውርስ መንቀል ደግሞ በሁለተኛ፣ ሶስተኛ እና አራተኛ ዘመዶች ላይ የሚፈፀም ሲሆን በኑዛዜው ውስጥ ተጠቃሚ ካላደረጋቸውና ሌላ ሰውን የጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚ ካደረገ በዝምታ ከውርስ እንደነቀላቸው

ይቆጠራል። በዚህ ጊዜ ከውርስ የተነቀለው ወራሽ ከአውራሹ በፊት እንደሞተ ተደርጎ የሚፈፀም ሲሆን ይህም ከውርስ የተነቀለውን ሰው ከውርሱ እንዳያገኝ ያደርገዋል ማለት ነው።[203]

ሆኖም ተናዛዡ ከውርስ የነቀለው ልጆችን ወይም ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ከሆነ አውራሹ ከውርስ የነቀለበትን ምክንያት ካልገለፀ በስተቀር ከውርስ መንቀሉ አይፀናም። በዚህ ጊዜ ዳኛ ተናዛዡ በኑዛዜው የሚሰጠው ምክንያት እውነት ስለመሆን አለመሆኑ ማጣራት የማይችል ሲሆን የተሰጠው ምክንያት ግን በእርግጥም ከውርስ ለመንቀል በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ይመረምራል።[204]

## 5.5 ውርስ ማጣራትና የውርስ ክፍፍል

ውርስ ማጣራት ማለት የውርሱን ተቀባዮች ማንነት መለየት፣ የውርሱን ገሀብት መለየት፣ ለውርሱ መከፈልያለባቸውን ገንዘቦች መቀበል፣ ከውርሱ መከፈል የሚገባቸው እዳዎች ካሉ መክፈል እንዲሁም ሚች በኑዛዜ ስጦታ ለሰጣቸውን ሰዎች የተሰጣቸውን መክፈልን ያጠቃልላል።[205] ይህንን ሥራ ይሰራ ዘንድም የውርስ አጣሪ ያስፈልጋል። የውርስ አጣሪ በሶስት መንገድ ሊመደብ ይችላል።

የመጀመሪያው በህግ ሲሆን በዚህም ኑዛዜ ባይኖር ወራሽ ሚሆኑ ሰዎች አውራሹ ከሞተበት ቀን ጀምሮ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የውርስ አጣሪ ይሆናሉ። ሁለተኛው በኑዛዜ ሲሆን አውራሹ በኑዛዜው የውርሱ አስፈፃሚ እንዲሆን የመረጠው ሰው የውርስ አጣሪ ይሆናል። ተናዛዡ በግልፅ የውርስ አስፈፃሚው እከሌ ይሁን ብሎ ካላለ በጠቅላላ ኑዛዜ የተደረገለት ሰው ወይም ሰዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የውርስ አጣሪ ይሆናሉ። ሶስተኛ በፍርድ ቤት የውርስ አጣሪ የሚሾምበት ሲሆን ይህም ወራሾቹ የማይታወቁ ከሆነ፣ ያለኑዛዜ ወራሽ የሚሆኑት ሰዎች ውርስ ለማጣራት እንደማይፈልጉ ያስታወቁ በሚሆንበት ጊዜ፣ የንብረቱ ወራሽ መንግስት በሚሆንበት ጊዜ፣ ብዙ አጣሪዎች ኖረው ውርሱን ለማስተዳደርና ለማጣራት ያልተስማሙ እንደሆነ፣ የወርሱ አስተዳደር ወይም ማጣራት ችግር ሲነሳ እንደሆነ፣ አጣሪው ትጉህ ወይም ሀቀኛ ያልሆነ ወይም ሥራውን ለመፈፀም ችሎታ የሌላው እንደሆነ ከታወቀ፣ ውርስ አጣሪው የተመረጠበት ኑዛዜ ተቀባይነቱ ካከራከረ ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ውርስ አጣሪውን ለመለየት አጠራጣሪ ሲሆን እንዲሁም ከወራሾቹ መካከል አካለመጠን ያልደረሰ ወይም የተከለከለ ወይም በማንኛውም ምክንያት ጥቅሙን ማስከበር የማይችል ሰው ያለ እንደሆነ የሚፈፀም ነው።[206]

---

[203] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 937፣ 939

[204] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 938

[205] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 944

[206] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 947፣ 948፣ 950፣ 951

በዚህ መልኩ የሚሾመው ውርስ አጣሪ ኑዛዜ መኖር አለመኖሩን ከማጣራት ጀምሮ ንብረቶችን፣ እዳዎችን፣ ወራሾችን የመለየት እና ሌሎች ተያዥ ሥራዎችን ይሰራል። የውርስ ማጣራቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ እዳዎች ከፈላሉ በቂ ንብረቶችም ለወራሾች አፋፈላሉ ማለት ነው።

5.6 ወደ ውርሱ የሚመለሱ ንብረቶች (Collation by coheirs)

ውርሱን የሚቀበሉት የአውራሹ ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች በሆኑ ጊዜ ከመሀከላቸው ለአንዱ አስቀድሞ ከሟች ችሮታ አግኝቶ ከሆነ በአውራሹ መመለስ የለብህም ተብሎ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ወደ ውርሱ መመለስ አለበት። በዚህም እነዚህን መመለስ ያለባቸው ችሮታዎች ወደ ውርስ እንዲመልስ የህግ ግዴታ የተጣለው በአውራሹ ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች ሲሆን አውራሹ ግን በሌሎች ወራሾች ላይ ይህን ግዴታ ለማጣል ከፈለገ ህጉ ፈድዶለታል።[207]

ወደ ታች የሚቆጠር ተወላጅ መመለስ ያለበት ችሮታ

- ለማጫ (dowry) ገንዘብ
- ለወራሹ ትዳር መቋቋሚያ
- የወራሹን እዳ ለመክፈል

አውራሹ ለወራሹ ያወጣው የትምህርት ወጪ ወደ ውርሱ መመለስ አለበት?

የተሰጡ ችሮታዎች ናቸው።[208]

አውራሹ ወደ ታች ለሚቆጠሩ ተወላጆች ለትምህት ወጪ ያወጣውን ወጪ ወራሹ ወደ ውርሱ እንዲመልስ አይጠበቅበትም።[209] ሆኖም ከድንጋጌው እንደምንረዳው ወራሹ አውራሹ በህይወት በነበረበት የሰጠውን ሁል ጊዜ ይመልሳል ማለት አይደለም። ይልቁንም

- አውራሹ ችሮታውን ለወራሹ የሰጠው እንዳይመልስ ነፃ ከሆነ
- በልዩ ሁኔታ ከሚደርሰው ውጪ እንዲሆን አድርጎ ከሆነ
- ሟች ለወራሹ የሰጠው ችሮታ ከአንድ ነገር የሚገኘውን ገቢ ላይ ከሆነ
- ሟች ለውራሹ ጥቅም የኢንሹራንስ ዋጋ ከፍሎለት ከሆነም ይህን ክፍያ

---

[207] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1070

[208] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1065፣ 1066

[209] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1066(3)

ወደ ውርሱ መመለስ አይገደድም።[210] በተጨማሪም ወራሹ ከአውራሹ ጋር ባደረገው ስምምነት ወይም ከማህበረተኝነት ውል ያገኛቸው ትርፎች መመለስ የለበትም።[211]

ወራሽ የሆነ እና አስቀድሞ ከአውራሹ ችሮታ የተሰጠው ሰው ውርሱን አልፈልግም ቢል አስቀድሞ የተሰጠውን ችሮታ መመለስ ይጠበቅበታል?

የሟችን ውርስ አልፈልግም ያለ ሰው አስቀድሞ በሟች የተሰጠውን ችሮታ እንዲመልስ አይጠበቅበትም፡ ፡[212]

አስቀድሞ የተሰጠን ችሮታ ወደ ውርስ መመለስ የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው?

ወደ ውርስ መመለስ ያለበትን ንብረት ሲመለስ ወራሾች የሚከፋፈሉት የሟች ጠቅላላ የውርስ ንብረት ሟች የተዋቸው ንብረቶች እና በቁም ወይም በኑዛዜ የሰጣቸውን ንብረቶችን የሚጨምር ይሆናል። አስቀድሞ ችሮታ ውስዶ የነበረው ወራሽም በግምቱ ልክ አስቀድሞ ከድርሻው እንደወሰደ ይቆጠራል። [213] ግምቱን በተመለከተ አስቀድሞ የተወሰደው ንብረት ግምት በሰነድ ላይ የተሰጠው ግምት ሲሆን በሰነድ ላይ የተመለከለተ የዋጋ ግምት የሌለው እንደሆነ ስጦታው በተደረገ ጊዜ የነበረው ዋጋ ይሆናል። [214]

አቶ ኤርሴዶ አስር ልጆች ያሏቸው:: የመጀመሪያ የመጀመሪያ ልጃቸው ማቲዮስ ሲያገባ ለቤት ሟቋቋሚያ እንዲሆነው በማሰብ መኪና ገዝተው ሰጥተውታል::

ከጊዜ በኋላ አቶ ኤርሴዶ ህይወታቸው ያልፋል:: ሆኖም ማቲዮስ መኪናው ተሰርቆበታል::

መኪና ከጠፋበት ማቲዮስ መኪናውን ወደ ውርሱ መመለስ አለበት ወይስ የለበትም?

---

210 ዝኒ ከማ[illegible]

211 ዝኒ ከማ[illegible]

212 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1075

213 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1074

214 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1077

ወራሹ ቀድሞ የወሰደው ንብረት  ቢጠፋ ወይም ከተሰጠው ስጦታ መበልፀጉን ያቋረጠም ቢሆንም እንኳን የወሰደውን ንብረት ወደ ውርሱ መመለስ ይጠበቅበታል።[215]

5.7 ይርጋ

ይርጋ አንድን መብት በተመለከተ ባለመብቱ በህግ በአስገዳጅ መብቱን ሊጠይቅበት የሚችልበት የጊዜ ገደብ ነው። ዋነኛው የይርጋ አላማ መብቱን ለመጠየቅ ዳተኛ የሆነ ሰው መብቱን ለመጠየቅ ንቁ እንዲሆን እና የሚጠየቀው ወይም የሚከሰሰው ሰው ደግሞ ጊዜ ገደብ በሌለው በስጋት ውስጥ እንዳይኖር ለማድረግ በማሰብ ነው። በውርስ ረገድ እንደየጥያቄዎቹ አይነት የተለያየ የይርጋ ጊዜ ተቀምጧል።

አንድ የወራሽነት ማስረጃ የሌለው ሰው የውርሱን ንብረት ይዞብኛል የሚል ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት ንብረቶች እንዲመለሱለት የወራሽነት ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ንብረቶቹ በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሶስት አመት ውስጥ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ያላቀረበ እንደሆነ ስለ ወራሽነት ጥያቄ ክስ ቢያቀርብ ተቀባይት አይኖረውም።[216]

በሌላ በኩል ሟች ከሞተበት ወይም ወራሹ መብቱን ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ 15 (አስራ አምስት) አመት ያለፈው ከሆነ ደግሞ በማናቸውም አስተያየት የወራሽነት ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም።[217]

ከውርስ አከፋፈል ጋር በተያያዘም የአንዳንድ ንብረቶች ዋጋ በተሳሳተ ሁኔታ በመገመቱ ምክንያት የክፍያው ተጠቃሚ ከሆኑት ወራሾች አንዱ ሊደሰርሰው ከሚገባው ከሶስት ሩብ ሁለት ሶስተኛ) በታች ደርሶት ከደረሰው ወይም ከወራሾች መካከል አስቀድሞ ከአውራሹ ተቀብሎት የነበረውን ስጦታ መልሶ በውርስ ውስጥ ማስገባት ሲገባው ይህን ሁኔታ ለወራሾች ያላሳወቀ ወራሽ በሚኖርበት ጊዜ ሥርአቱ

---

[215] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1078

[216] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 999፣ 1000

[217] ዝኒ ከማሁ

እንዲቃና ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። መሰል ጥያቄ መቅረብ ያለበት ውርሱ ከተከፋፈለ በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም።[218]

## ክፍል ስድስት

## የውል ህግ

የሰዉ ልጆች የእለት ተዕለት ኑሮአቸውን ሲኖሩ የተለያዩ ህጋዊ ውጤት ያላቸዉን ድርጊቶች ያከናዉናሉ። ለምሳሌ እቃ ይገዛሉ ይሸጣሉ፣ ቤት ይከራያሉ ያከራያሉ፣ ጋብቻ ይፈፅማሉ፣ ስራ ተቀጥረው ይሰራሉ ሰዎችን ቀጥረው ያሰራሉ። ይህ ሲሆን ህጋዊ ዉጤትን ከሚያስከትሉ ተግባራት አንዱ ውል ነዉ። ውል ሰዎች በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሕይወታቸዉ ዉስጥ ከሚያከናውኗቸው የግንኙነት መገለጫዎች አንዱ ሲሆን የፍትሐብሔር ግዴታን ያስከትላል።

በፍትሐ ብሔር ህጉ ሰዎች ስንል የተፈጥሮ ሰዎች ወይም ህጋዊ ሰዉነት የተሰጣቸው ድርጅቶች ናቸዉ፡፡ በመቀጠል በተለያዩ ፅሁፎች ለውል የተሰጡ ትርጉሞችን ማየት ስለውል ጠቅላላ ግንዛቤ ለማግኘት ስለሚረዳ ትርጉሞቹን እንመለከታለን።

6.1 የውል ምንነት

ውል ማለት ስምምነት ማለት ሲሆን ይህም በሕግ ተፈጻሚነት ያለው ነው፡፡ እዉቁ የህግ መዝገበ ቃላት ብላክስ ሎዉ ላይ " ዉል ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በመካከላቸዉ አንድን ድርጊት ለማድረግ ወይንም ላለማድርግ በመስማማት ግዴታ የሚፈጥሩበት መንገድ ነዉ" ሲል ትርጉም ይሰጠዋል። በሌላ በኩል ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ የኢትዮጵያ የዉል ህግ መሰረተ ሀሳቦች በሚለዉ መፅሐፋቸዉ ዉስጥ " ዉል አንድን ግዴታ ወይም ከዚሁ ግዴታ ጋር የተያያዙ ሌሎች በርከት ያሉ ግዴታዎችን የሚያቋቁም ተግባርን የሚያመለክት አነጋገር ነዉ። በዚህ ግዴታ ባለገንዘብ የሆነዉ ወገን አንድ ነገር እንዲፈጸምለት የመጠየቅ መብት የሚኖረዉ ሲሆን ባለዕዳዉ ደግሞ አንድን ነገር የመፈጸም ግዴታ ይጠበቅበታል" በማለት አብራርተዉ ገልፀዉታል።

በተጨማሪ እንደ በ1952 ዓ.ም የወጣው የፍትህ ብሔር ህግ ለውል የሰጠውን ትርጉም ስንመለከት ውል ማለት ንብረታቸውን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው። ውል ለሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች መብት እና ግዴታዎችን የሚያስቀምጥ ሲሆን የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በተዋዋዮቹ ላይ ሕግ ይሆናል።ይህ ማለት ተዋዋዮቹ ግዴታቸውን አለመወጣታቸው የሚያስከትልባቸው

[218] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 1106

ሀላፊነት ይኖራል ማለት ነው።በመሆኑም ውልን በተመለከተ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገኖች በገቡት ቃል መሠረት በሕግ የተያዙ ናቸው ::

6.2 የውል ሕግ ዓላማ

የውል ህግ ብዙ ዓላማዎች ያሉት ቢሆንም በዋናነት የሚጠቀሰው ግን ማዕከላዊው የገበያ ኢኮኖሚን በጥቅል የሚያካትቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ስምምነቶችን መደገፍ እና መቆጣጠር ነው። ስለዚህ በክርክር አፈታት ዘዴ ውስጥ ይሰራል ማለት ነው። በተጨማሪም ህጉ የሚያስፈፅማቸውን ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች እንዲያደርጉ ስልጣን ይሰጣቸዋል። የውል ህግ ዓላማ የሸቀጦች እና አገልግሎቶች ኢኮኖሚያዊ ልውውጥ መሳሪያ በመሆን ማገልገል ነው።

6.3 የውል ህግ ወሰን (Scope of Contract Law)

የውል ህግ ወሰን ከሀገር ሀገር እና ከህግ ስርአት እንዲሁም እንደሚያስተዳድሩት የግዴታ አይነት ይለያያል። በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል በሚደረጉ ስምምነቶች የሚነሱ የውል ግዴታዎች ውሉን በመጣስ በእሱ ላይ በሚደርስበት ክስ መሠረት ቃል ሰጪው የገባውን ቃል የመፈጸም ግዴታ ውስጥ የሚያስገባ ነው።

የውል ሕግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንደ ኮንትራት ሥራዎች ተፈጥሮ እና አመጣጥ ላይ በመመርኮዝ አጠቃላይ(general ) ወይም ልዩ ( special )ተፈፃሚነት ሊኖረው ይችላል። ስለዚህ የውል በተፈጻሚነት ወሰን ላይ በመመስረት እርስ በርስ የሚደጋገፉ በሁለት ተፈፃሚነት ቦታዎች ሊከፋፈሉ ይችላሉ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1676(1) የጠቅላላ ውል አተገባበርና ወሰን ምንም ይሁን ምን ውል ተፈፃሚ እንደሚሆን ይደነግጋል። ስለዚህ የውል ሕግ አጠቃላይ ደንቦች በሁሉም ውሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ይሁን እንጂ ድንጋጌው ለልዩ ድንጋጌዎችንም እውቅና የሚሰጥ ሲሆን በፍትሐ ብሔር ሕግና በንግድ ሕጉ መጽሐፍ 5 ላይ እንደተገለጸው ለተወሰኑ ኮንትራቶች ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል። በዚህ መሠረት የውል ሕግ ከውል ውጪ ለሚደረጉ ግዴታዎች (ከውል ውጪ ሀላፊነት)፣ ያለአግባብ የማበልጸግ ግዴታ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል።ነገር ግን የጠቅላላ የውል ህግ ተፈጻሚነት ወሰን ለአንዳንድ ግዴታዎች በመነሻቸው ወይም በተፈጥሮአቸው ምክንያት ተፈጻሚ የሆኑትን ልዩ ድንጋጌዎች አይነዳውም ።

6.4 የውሎች አመሰራርት (Formation of Contracts)

ውል የግለሰቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር እውቅና ከሚሰጣቸው ዋና ዋና የህግ ዘርፎች አንዱ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ግለሰባዊ ራስን በራስ ማስተዳደር በስምምነት ይገለጻል።ውል ስምምነት መሆን እንዳለ ሆኖ ከሌሎች ስምምነቶች የሚለየዉ በአፈፀሙ ከበስተጀርባዉ የሕግ ድጋፍ ያለዉ ስምምነት በመሆኑ ነው። ይህም ማለት ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙበትን ነገር እንደ ስምምነታቸዉ ባይፈፅሙ ላልፈፀሙት

ነገር በህግ ተገደዉ እንዲፈፅሙ ይደረጋሉ። ይህም የሚያሳየን ዉል በተስማሚዎቹ አካላት መካከል እንደ ህግ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን ነዉ።

ዉል በተወያይ ወገኖች መካከል ህጋዊ ዉጤት እንዲኖረዉ አስቀድሞ የዉል አመሰራረቱ ህጋዊ መስፈርቱን ማሟላት አለበት። በመሆኑም የሰዎች ስምምነት መፈፀም እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ለመወሰን ህጎች መስፈርቶች ያካትታሉ። በዚሁ መሰረት በፍትሐብሔር ህጉ ስለ ዉል አመሰራረት በሚደነግገዉ ክፍል አንቀፅ 1678 ላይ በግልፅ እንደተቀመጠዉ የሚፀና ዉል ነዉ ለማለት መሟላት ያለባቸዉን ሁኔታዎች አስቀምጧል። እነሱም፡

➢ችሎታ (Capacity)

ዉል የሚፈፀመዉ ለመዋዋል ችሎታ ባላቸዉ ሰዎች መካከል መሆኑን ለውል መፅናት እንደ አንድ ዋና መስፈርት ተደንግጎ ይገኛል። ይህም ማለት በህግ ፊት የሚፀና ዉል ለማድረግ ተዋዋዮች በህግ ችሎታ ያላቸዉ መሆን አለባቸዉ። በፍትሐብሔር ህጉ ላይ ስለ ችሎታ በሚደነግገዉ ክፍል አንቀፅ 192 ላይ በመርህ ደረጃ ማንኛዉም ሰዉ በህግ ችሎታ እንደሌለዉ ካልተገለፀ በቀር ማንኛዉንም ህጋዊ ድርጊት ለማድረግ ችሎታ እንዳለዉ እንደሚቆጠር ያስቀምጣል። በዚሁ ህግ አንቀጽ 193 ላይ እንደተደነገገዉ እድሜዉ ለአቅመ አዳም፤ሄዋን ያልደረሰ/ሰች ወይም አይምሮዉ ህመም ያለበት ሰዉ ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ ሰዉ ችሎታ እንደሌለዉ ይቆጠራል። ከላይ እንደተገለፀዉ ዉል ህጋዊ ተግባር ስለሆነ እድሜዉ ለአቅመ አዳም ወይም ሄዋን ያልደረሰ/ሰች ወይም አይምሮዉ ህመም ያለበት ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ ሰዉ ዉል መዋዋል አይችልም።ይህም የሚሆነው ነፃ ፍቃዳቸውን ለመስጠት ያሉበት ሁኔታ ስለማያስችላቸው ነው።

➢ነፃ ፍቃድ (Consent)

ዉል የሚመሰረተው በተወያያቹ ነፃ ፍቃድ ብቻ ነው። ይህም ማለት ተወያይ ወገኖች ዉል ዉስጥ የሚገቡት ያለማንም ጫና አድራጊነት በራሳቸዉ ገዛ ፍቃድ መሆን አለበት ማለት ነዉ። አንድ የዉል ግዴታ የተቋቋመ(የተመሰረተ) መሆኑ የሚረጋገጠዉ የተዋዋዮቹ ፈቃድ በህግ አግባብ መገለፁ ሲታወቅ ነዉ። ተዋዋዮቹ በመሀከላቸዉ በህግ ፊት የሚፀና ግዴታ ለማቋቋምና ይህም ግዴታ በሚያስከትለዉ ዉጤት ለመገዛት ስምምነት ያላቸዉ መሆኑ ይፋ ሲያደርጉ ፈቃዳቸዉን ገለፁ ይባላል። በፍትሐብሔር ህጉ አንቀፅ 1679 ላይ እንደተደነገገው "ዉል ተዋዋዮች በገቡባቸዉ ግዴታዎችና እነዚህም አስገዳጅ እንዲሆኑ የተስማሙበትን በሚገልፀዉ የፈቃድ መስጠት ላይ የተመሰረተ ነዉ" ።

➢የሚዋዋሉበት ጉዳይ በእርግጠኝነት የሚቻል፣ ህጋዊና ሞራላዊ መሆን (Object)

ተወያይ ወገኖች የሚዋዋሉበት (ዉል ዉስጥ የሚገቡበት) ጉዳይ በእርግጠኝነት የሚቻል እና ህጋዊና ሞራላዊ ጉዳይ ላይ መሆን ይገባዋል። የዉሉ ፍሬ ነገር በሰዉ ልጅ አቅም መፈጸም የሚችል እና ህጋዊና ሞራላዊ የሆነ መሆን አለበት። በሰዉ ልጅ አቅም መፈፀም የሚቻል ተግባር ማለት የሰዉ ልጅ በተፈጥሮዉ ማከናወን የሚችለዉ ማለት ነዉ። ለአብነት የዉሉ ፍሬ ነገር እንደ እርግብ መብረር ቢሆን

በሰዉ ልጅ ተፈጥሮ የማይቻል ተግባር ነዉ። ሌላዉ የዉሉ ፍሬ ነገር በህግ ያልተከለከለ ወይም ህገ-ወጥ ያልሆነ እና በህብረተሰቡ ባህልና ወግ ተቀባይነት ያለዉ ነገር ላይ (በሌላ አባባል ከህብረተሰቡ ሞራል ጋር የማይቃረን) መሆን አለበት። ለምሳሌ የውሉ ፍሬ ነገር ሰዉ ለመግደል ቢሆን በህግ የተከለከለ እንዲሁም ከህብረተሰቡ ሞራል ጋር የሚቃረን ነዉ። በመሆኑም እንዲህ አይነት ውሎች በህግ ፊት አይፀኑም ወይም ተፈጻሚ አይሆኑም።

➢የዉል አቀራረፅ ወይም አፃፃፉ(ፎርም)

የውል አፃፃፍ እንደ ፍርድ ቤት ያሉ ሶስተኛ ወገኖች የተዋዋይ ወገኖችን ስምምነት እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል። ይሄውም የውሉ ይዘት እና የውሉ መኖር ለሌሎች የሚታይበት መንገድ ነው።

ለውል አቀራረፅ ፎርም በህግ ተለይተዉ የተቀመጡ ወይም ተዋዋይ ወገኖች ተለይቶ እንዲቀመጥ ከተስማሙበት የዉል ጉዳይ በቀር የተለየ የዉል ፎርም የማያስፈልግ መሆኑ ከፍትሀ ብሄር ህጉ መገንዘብ ይቻላል። በአንቀፅ 1678(3) ላይ እንደተደነገገዉ በግልፅ በህግ ይህን የዉል ፎርም ተከተሉ ተብሎ ካልተደነገገ በቀር ተዋዋይ ወገኖች ዉላቸዉን በፈለጉት አይነት ማድረግ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ ህግ አንቀፅ 1719(1) ላይ ተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ነፃነት እንዳላቸዉ ሁሉ የሚዋዋሉበትን ዉል አቀራረፅ የመወሰን ነፃነትም እንዳለቸዉ በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል። በመሆኑም በተለየ ሁኔታ በህግ ዉሉ በዚህ መልክ ይቀመጥ ካልተባለ በስተቀር ተዋዋዮቹ ወገኖች ዉላቸዉን በፈለጉት ፎርም ማድረግ ይችላሉ። በመሆኑም ፈቃድን በቃል ወይም በፅሁፍ ወይም በተለመዱ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሳ ግዴታ ለመግባት መፍቀዱን በማያጠራጥር አሰራር ለማስታወቅ ይችላል። ለሆነም ለውሉ አቀባበል አቅራቢው የተለየ አሰራር ለመወሰን ይችላል።

በህግ የተለየ የውል አቀራረፅ ፎርም የሚጠይቁ ውሎችን ለምሳሌ ብናይ፦ ከሊዝ ውል በስተቀር የማይንቀሳቀስ መብትን የሚነኩ ውሎች ሁሉ በጽሁፍ መፈፀም አለባቸው። ስለዚህ ቤትን ወይም መሬትን በሚመለከት ሽያጭ፣ አራጣ፣ አገልጋይነት፣ ሞርጌጅ፣ ፀረ-ክርሲስ ክፍፍል፣ ስምምነት እና የግልግል ስምምነት በጽሁፍ መቅረብ አለበት። ለምሳሌ፦ ወራሾች የማይንቀሳቀስ ንብረትን በመካከላቸው ቢከፋፈሉ የመከፋፈል ስምምነት በጽሑፍ መደረግ አለበት። ከዚህም በላይ; በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያሉ ተከራካሪዎች ይህንን ክርክር ወደ ግልግል ዳኝነት ለማቅረብ ከፈለጉ ስምምነታቸውን በጽሁፍ ማድረግ አለባቸው። ይሁን እንጂ የማይንቀሳቀሰውን የኪራይ ውል ወይም የኪራይ ውል በጽሁፍ ማድረግ አያስፈልግም። ማንኛውም የመንግስት ኤጀንሲ አካል የሆነበት ማንኛውም አይነት የስራ ውልን ጨምሮ በጽሁፍ መፈፀም አለበት። በተጨማሪ የዋስትና ውል፣ የኢንሹራንስ ውል፣ የጋብቻ ውል፣ ከ500 ብር በላይ የሚደረግ ብድር እና ሌሎችን በህግ በግልፅ

የተቀመጡ ደንጋጌዎች ውሎቹ በህግ ፊት እንዲፀኑ በፅሁፍ መደረግ አለባቸው። የዉል አመሰራረትን በተመለከተ ከላይ የተመከትናቸዉ ማለትም ችሎታ፣ ፍቃድ እና የውሉ ፍሬ ነገር ህጋዊና ሞራላዊ መሆን ለሁሉም አይነት ዉሎች በጋራ ተሟልተው መገኘት የሚገባቸዉ መሰረታዊ ነገሮች ሲሆኑ የዉል ፎርም ግን በህግ በግልፅ ተለይቶ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ፎርም ብቻ ሊከተሉ ይገባል ላላቸዉ የዉል አይነቶች ብቻ ተፈፃሚ የሚሆን ነዉ። ስለሆነም አንድ ዉል ሲመሰረት ተዋዋይ ወገኖች ወይም አንዱ ተዋዋይ ችሎታ የሌለዉ እንደሆነ፣ ተዋዋይ ወገኖች ወይም አንዱ ተዋዋይ ፍቃዱን በነፃነት ያልሰጠ ከሆነ ወይም የዉሉ ፍሬ ነገር የማይቻል፣ ህገወጥ ወይም ኢሞራላዊ ከሆነ እንዲሁም ዉሉ በግልፅ በህግ በተለየ ፎርም እንዲደረግ የሚያስገድድ ሆኖ ሳለ ተዋዋዮቹ ይህን ፎርም ካልተከተሉ ዉሉ ሙሉ በሙሉ ፈራሽ ይሆናል። ይህም ማለት ዉሉ እንዳለተፈፀመ ይቆጠራል።

ከዚህ በላይ የተመለከትነዉ የዉል ትርጉም እና የዉል አመሰራረት ለሁሉም አይነት ዉሎች የሚያገለግል ደንብ ነዉ። ይህም የዉል ጠቅላላ ደንብ በመባል ይጠራል። ይህም የሆነበት ምክንያት ይህ ደንብ ለጠቅላላ ዉልም ይሁን ለልዩ ዉሎች የሚያገለግል ስለሆነ ነዉ። በፍትሐብሔር ህጋችን ከጠቅላላ ዉል (General contract) በተጨማሪ ልዩ የዉል (special contract) ደንቦች ተደንግገዉ ይገኛሉ። ልዩ የዉል (special contract) አይነቶች ተብለዉ በህጋችን ከተጠቀሱት ዉስጥ ለአብነት የሽያጭ ዉል፣ የስጦታ ዉል፣ የስራ ውል፣ የቤት ክራይ ውል ወዘተ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

## 6.5 የውል ውጤት

ውል በህግ ፊት የፀና እንዲሆን መሟላት ያለባቸው በህግ የተቀመጡ መሰፈርቶች ማለትም የተዋዋዮች ችሎታ፣ ነጻ ፍቃድ፣የሚዋዋሉበት ጉዳይ በእርግጠኝነት የሚቻል፣ ህጋዊና ሞራላዊ መሆን እና እንዳስፈላጊነቱ መከተል ያለበት ፎርም አሟልቶ ከተመሰረተ በኃላ የሚከተሉት ውጤቶች ይኖረዋል። ይሄውም በህጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ ህግ ሲሆኑ በውል የማይለወጡና አዛዣ የሆኑ የህግ ቃሎች እንደተጠበቁ ሆነው በውሉ ውስጥ የሚገባው ቃል ተዋዋዮቹ የተስማሙበት ይሆናል። እንዲሁም ተዋዋዮቹ እንዳይፈፀምባቸው በማድረግ ያስቀሯቸው ባልሆኑ መጠን ወይም በውል እንዳይለወጥ የሚያዝ ህግ ባለ ጊዜ የውል ህጉ ጠቅላላ ደንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።[219]

## 6.6 ልዩ ውሎች

ልዩ ውሎች በፍተሀ ብሄር ህጉ አምስተኛ መፅሀፍ መብቶችን ማስተላለፍ የሚመለከቱ የተለያዩ አይነት ውሎችን አካቶ ይገኛል ።በመቀጠል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

---

[219] የፍ/ህግ አንቀፅ 1675፣ 1676

### 6.6.1 የሽያጭ ውል

የሽያጭ ውልን ምንነት ከማየት በፊት የሽያጭ ውል የሚገዛበትን የሽያጭ ህግ ማየት ጠቃሚ ነው። የሽያጭ ህግ በሽቀጦች ገገር እና ሻጭ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚቆጣጠር የንግድ ህግ ቅርንጫፍ ሲሆን የሽያጭ ውል መመስረትን፣ አፈጻጸምን እና መጣስን የሚመለከቱ ህጎች ስብስብ ነው። እንዲሁም በገገርዎች እና በሻጮች ላይ የተወሰኑ ግዴታዎችን በማስቀመጥ የግዴታዎቹ ጥሰት ተከስቶ እንደሆን መፍትሄን ያስቀምጣል። በገዥና በሻጭ መካከል ያለው አለመግባባት በፍርድ ቤት ክርክር ሲያስነሳ ፍርድ ቤቱ የሽያጭ ህግን እና አጠቃላይ የውል ድንጋጌዎችን በመመልከት ክርክሩን ይፈታል ወይም ይዳኛል። ምክንያቱም የፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1676 የአጠቃላይ የውል ድንጋጌዎች ከልዩ ድንጋጌዎች ጋር በማይቃረን መልኩ የሽያጭ ውልን ጨምሮ ውል ላይ ተፈጻሚነት እንዳላቸው በግልጽ ያሳያል። በዋናነት ለሽያጭ የሚውሉት "ዕቃዎች" ሲሆኑ ምንም እንኳን እቃዎች በተለያየ መንገድ ሊከፋፈሉ ቢችሉም፣ እቃዎች አሁን ባሉት እቃዎች (existing goods) ፣ የወደፊት እቃዎች( future goods) እና ተጓዳኝ እቃዎች( contingent goods) ሊከፋፈሉ ይችላሉ።በኢትዮጵያ የሽያጭ ውል ሕግ አንቀጽ 2266 እና 2267 ላይ እንዲህ ዓይነት ምደባ ባይኖርም በሽያጭ ውል ውስጥ የሚገኙት ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሳቃሾች መሆናቸውን ያሳያል።

#### 6.6.1.1 የሽያጭ ውል ትርጉም

በፍትሀ ብሔር ህጉ ስለ ሽያጭ የተሰጠውን ትርጉም ስንመለከት ሽያጭ ማለት ሻጭ የሆነው አንዱ ወገን ገገር ለሆነው ሌላ ወገን ዋጋው በገንዘብ የተወሰነውን አንድ ነገር ገገር ሊከፍለው ግዴታ በገባበት መሰረት ሊያስረክብና ሀብቱን ሊያስተላልፍ የሚገደድበት ውል ነው  በማለት ያስቀምጣል። የሽያጭ ዋናው ባህሪ ሻጩ ባለቤትነትን የማቅረብ እና የማስተላለፍ ግዴታ እንዲሁም ገዥው ዋጋ የመክፈል ግዴታ ውስጥ የሚገቡበት ውል መሆን ነው። በትርጉሙ ክፍል ከተካተቱት የሻጭና የገገር ግዴታዎች በተጓዳኝ ሁለቱም ወገኖች ሌሎች ግዴታዎች አሉባቸው። ለአብነት ያክል ሻጩ በአንቀጽ 2273 መሰረት ከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ንብረት መውረስ ፣ ጉድለቶች እና አለመስማማት በተመለከተ ዋስትና የመስጠት ግዴታ አለበት ። ይሁንና እነዚህ ግዴታዎች ግድ በውሉ ውስጥ መካተት ያለባቸው አይደሉም። ተዋዋዮቹ  በግልፅ ዋስትና ላለመግባት ሊስማሙ ይችላሉ።

በአጠቃላይ የሽያጭ ውልን በሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን እነሱም የሚንቀሳቀስ እቃ ሽያጭ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ናቸው።

#### 6.6.1.2 የሽያጭ ውል አመሰራረት

የሽያጭ ውል እንደማንኛውም ውል ተዋዋይ ወገኖች በውሉ ርዕሰ ጉዳይ(የሚዋዋሉበት ነገር) እና በዋጋው ላይ ያላቸውን ስምምነት ሲገልጹ ይቋቋማል። ውል ለመዋዋል ሀሳብ የቀረበለት ገዥ ወይም ሻጭ እንዲሁ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ፍቃዱን መግለጽ አለበት። ፈቃዱ ከጉድለት የጸዳ እና ተዋዋይ ወገኖች ለመታሰር ማቀድ ማሳየት አለበት ። ይህም ማለት የሽያጭ ውል የሚጠናቀቀው

ተዋዋይ ወገኖች በውሉ ስምምነት ላይ ያላቸውን ስምምነት ሲገልጹ ነው። ስለዚህ ስምምነት አለ ለማለት በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የቀረበው አቅርቦት(offer) በአጠቃላይ የውል ድንጋጌዎች ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚያሟላ መንገድ መቀበል (accepted) አለበት። በመሆኑም ለሽያጭ ውል ምስረታ አቅርቦ እና መቀበል ወሳኝ ጉዳች ናቸው። ይሄውም በገገርው ወይም ሻጩ ውል ለመግባት ሃሳብ ማቅረብ ያለበት ሲሆን አቅራቢው ተቀባይነት ካገኘ ከተጠቀሱት ውሎች ጋር ውል ውስጥ መግባት ይችላል። በፍትሐ ብሔር ሕጉ በአንቀጽ 1714, 1715, 1716 ድንጋጌዎች መሠረት የውሉ ዓላማ በበቂ ሁኔታ ሊገለጽ, ሕጋዊ, ለመልካም ጠባይ እና ሞራል ተቃራኒ ያልሆነ ሊሆን ይገባል። የሽያጭ ውል ዋናው ነገር እቃውን በማቅረብ እና ዋጋውን መክፈል ነው። ነገሩ የሻጩ ወይም የሶስተኛ ወገን የሆነ ነባር ነገር( existing thing) ወይም የወደፊት ነገር (future thing )ሊሆን ይችላል። በገገርው የሚወሰደው ተጓዳኝ ግዴታ የዋጋ ክፍያ ሲሆን ዋጋ እንደ አስፈላጊነቱ በሽያጭ ውል ውስጥ ልዩነትን በሚፈጥር መንገድ ሊቀመጥ ይችላል። ነገር ግን ተዋዋይ ወገኖች የነገሩን ዋጋ ካልወሰኑ እና ዋጋው የማይታወቅ ከሆነ የሽያጭ ውል የለም።

6.6.1.3 የሚንቀሳቀስ እቃ ሽያጭ ውል አፈጻጸም (Performance of movable property sale contract)

የሽያጭ ውል አፈጻጸም በተዋዋይ ወገኖች የሚታዘዙትን ግዴታዎች መፈጸምን፣ የሻጩን ግዴታዎች፣ የገገርውን ግዴታዎች እና የሻጩንና የገገርውን የጋራ ግዴታዎች በባሕሉ፣ በቅን ልቦና እና በድንጋጌዎቹ ላይ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የጣሉትን የጋራ ግዴታዎች መተንተን ነው። በሽያጭ ውል አፈፃፀም ሻጭ እና ገዢ የየራሳቸው ግዴታዎች እንዲሁም መብቶች አሏቸው። እነሱም፡-

- የሻጭ ግዴታች
  1. የተዋዋሉበትን እቃ የማስረከብ ግዴታ፣
  2. ባለቤትነትን የማስተላለፍ ግዴታ፣
  3. ዋስትና የመስጠት ግዴታ( የባለቤትነት መብትን፣ ጉድለቶችን እና አለመስማማትን ዋስትና የመስጠት ግዴታ)፣ ዋና ዋና የሻጩ ግዴታዎች ሲሆን በተጨማሪም የሻጩ ሌሎች የግዴታዎች ሰነዶችን እና ኢንሹራንስን ከማስተላለፍ ጋር የተያያዙ ናቸው። ስለሆነም ሻጩ የተሸጠውን ነገር በተመለከተ ሰነዶችን ለገገርው ማስረከብ የተለመደ ከሆነ ሻጩ ከማቅረቡ በተጨማሪ እነዚህን ሰነዶች ማስረከብ አለበት።
- የገገርው ግዴታ
  1. ዋጋ የመክፈል ግዴታ
  2. የሽያጭ ንብረቱን የመረከብ ግዴታ
- የሻጩ እና የገገርው የጋራ ግዴታዎች

1. ወጪዎችን የመክፈል ግዴታ፡-ለምሳሌ የሽያጭ ውል ወጪዎች፣ የክፍያ ወጪዎች፣ የመጓጓዣ ወጪዎች

2. እቃው እንዳይበላሽ የመጠበቅ ግዴታ ወዘተ ይጠቀሳሉ

6.6.2 ውልን ያለመፈፀም ህጋዊ ውጤት

ውል ስላለመፈፀም በፍትሀ ብሔር ህጉ ትርጉም ያልተሰጠ ቢሆንም ከተለያዩ የህጉ ድንጋጌዎች ውል ያለመፈፀምን ምንነት መገንዘብ እንችላለን። ለአብነት፡- በፍት ብሄር ህጉ ቁጥር 2329 የመረካከብን ግዴታ ስላለመፈፀም በሚደነግገው አንቀጽ ስር ሻጩ የሸጠውን ነገር በደንብ ያላስረከበ እንደ ሆነ የተዋዋለበት ውል በግድ ሲፈፀም ልዩ የሆነ ጥቅም የሚያስገኝለት ሆኖ ሲታየው ገዢው ውሉ በግድ እንዲፈፀምለት ለማስገደድ እንደሚችል ያስቀምጣል። እንዲሁም ዋጋን አለመክፈል በሚለው አንቀፅ 2333 ስር ገዢው ዋጋውን ያልከፈለ እንደ ሆነ ለእቃው የተደረገው የሽያጩ ስምምነት በንግድ ልማድ መሰረት ሁለቱን ባለጉዳዮች በሚያቻችል ሽያጭ ለመሆን የሚችል ካልሆነ በቀር ሻጩ ዋጋው እንዲከፈለው ለማስገደድ መብት አለው።

በመሆኑም በሽያጭ ውል ገዥም ሆነ ሻጭ ወይም ሁለቱም በውሉ ላይ የተጣለባቸውን ግዴታ ሳይፈፅሙ ሲቀሩ ወይም ግዴታን ሲጥሱ (non-performed or breached) የውል ያለመፈፀም ይባላል። አብዛኛውን ጊዜ ለዕቃ ሽያጭ ውል ሁለቱም ወገኖች በውሉ ውስጥ የተስማሙባቸውን ግዴታዎች ይፈጽማሉ። አልፎ አልፎ ግን ከውል ተዋዋይ ወገኖች አንዱ በተለያዩ ምክንያቶች ግዴታውን ሳይወጣ ሊቀር ይችላል። ለምሳሌ አንድ ገዢ የግዢ ዋጋ በተስማማበት ቦታ ወይም ጊዜ መክፈል ወይም ማጓጓዣ ሳይወስድ ወይም መቀበል ላይችል ይችላል።

በተመሳሳይ መልኩ ሻጭ ሀሳቡን በመቀየር የተሸጠውን እቃ ለገዥው አላቀርብም ወይም አላስረክብም ሊል ይችላል ወይም በተገዛው ነገር ገዢ እየተጠቀመበት በሶስተኛ ወገን ጠያቂ ሊረበሽ ይችላል ወይም ያቀረበው ነገር ጉድለት ያለበት ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ ተዋዋይ ወገን ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር ብቻ ሳይሆን አፈፃፀሙን በተለየ ሁኔታ ሳይቀበል ሲቀር የውል አለመፈፀምም አለ። በአንቀፅ 1779 ስር እንደተደነገገው ያለበቂ ምክንያት የተስማሙበትን እቃ ያለመቀበል ውልን እንዳለመፈፀም እንቀሚቆጠር መገንዘብ ይቻላል።

በውል ህግ ከሚከናወኑ መሰረታዊ ተግባራት መካከል ውሉን ላለመፈጸም መፍትሂዎችን መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ውሉ ሳይፈፀም ሲቀር ህጋዊ መፍትሄ የማይኖር ከሆነ ተዋዋይ ወገኖች ውል ለመዋዋል ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ። የውል አለመፈፀምን የሚመለከተው የኮንትራት ህግ አላማ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ውላቸው እንዳይፈፀም በመፍራት አለመፈፀም የሚያስከትሉትን እንቅፋት ውጤቶች ማስወገድ ነው።

የውል ያለመፈፀም ህጋዊ መፍትሄ ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የተጎዳውን ወገን ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው። ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ውሉ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ሊገኝ ይችል የነበረው ጥቅሙ ነው።

በዚህ መሠረት መፍትሂዎቹ ውል ላልተፈፀመላቸው ሰዎች የአፈፃፀም ጥቅማጥቅሞችን ሊያቀርቡ ወይም ጥቅሙ የተጎዳውን አካል ውሉ ተፈፅሞ ቢሆን ኖሮ ወደነበረበት ቦታ እንዲያስገባ ማድረግ ነው። እንዲሁም በአፈፃፀም አለመቻል ጥቅሙ ከተጎዳው አካል በተጨማሪ አለመፈፀምን በሚመለከት የውል ሕግ አፈጻጸምን ያላከናወነው አካል ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል። ስለሆነም የአፈጻጸም ጉድለትን ማስተካከል ከሚጠበቀው ምክንያት በላይ ሊሆን የማይገባ እና የተጎዳው አካል ሊካስ ከሚገባው መጠን በላይ መሆን የለበትም በዚህ መልኩ ጉዳቱን የሚያስተካክለው አካል የህግ ጥበቃ ይደረግለታል።

በመሆኑም በሽያጭ ውል ያለመፈፀም ግዴታ መፍትሄ ውል ያልተፈፀመለትን ወገን እና ውሉን ባልፈፀመው አካል መካከል ያለውን ጥቅም ሚዛን እንዲጠብቅ ማድረግም ያካትታል። እነዚህን ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት አብዛኛዎቹ ሀገራት በግዴታ መፈፀም (forced performance)፣ የውል መሰረዝን (cancellation) እና የጉዳት ኪሳራ እንዲከፈል ማድረግ compensation of damage)እንደ ያለመፈፀም መፍትሄ ይጠቀማሉ።

በኢትዮጵያ የውል ህግ የተለያዩ የአፈፃፀም መፍትሂዎች የሚወሰዱ ሲሆን እነዚህም በፍትሀብሄር ህጉ አንቀፅ 1771 ስር የተቀመጡ ሲሆን ከተዋዋዮቹ አንዱ የውል ግዴታ ያልተፈፀመ እንደሆነ ሌላኛው ወገን እንደውሉ እንዲፈፅምለት መጠየቅ፣ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ እንዲሁም በውሉ ያለመፈፀም የደረሰው ጉዳት ኪሳራ መጠየቅ ሊሆን ይችላል። ይሁንና እነዚህ መፍትሂዎች ከመወሰዳቸው በፊት እንደውሉ ሳይፈጸምልኝ ቀርቷል በማለት ክርክር ለማቅረብ የሚፈልገው ወገን ተዋዋዩ ውሉን እንዲፈፅምለት ለማድረግ የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይገባል ( በፍ/ህ/ቁ1772)። በተጨማሪም እነዚህ እያንዳንዳቸው መፍትሂዎች በምን ሁኔታ ወይም ምን ሲሆን መፈፀም እንደሚችሉ ህጉ ያስቀምጣል።

- ተገዶ ውልን መፈፀም( forced performance)፦

ሻጭ ተገዶ ውሉን እንዲፈፅም የሚገደደዉ ፍርድ ቤትን መጠየቅ የሚቻለው ውሉ ያለተፈፀመለት አካል ወይም ገዢ ያንን እቃ ከሌላ ሰው ወይም ቦታ ማግኘት የማይችል ሲሆን ነው። ገዢው ግዢውን ያለምንም ችግር ወይም ያለ ከፍተኛ ወጪ ሊፈፀም የሚችል ከሆነ እና ይህም የተለመደ አሰራር ከሆነ የግዳጅ አፈፃፀም ሊጠይቅ አይችልም። እንዲሁም መዘግየቱን ካረጋገጠ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሻጩ ሳያሳውቅ ሲቀር ገዥው የግዳጅ አፈጻጸምን የመጠየቅ መብቱን ያጣል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በዚሁ ህግ በአንቀጽ 2333 መሠረት ገዢው ዋጋውን ሳይከፍል ሲቀር ሻጩ የግዳጅ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል። ነገር ግን እቃው ለገዢው ካልደረሰ ሻጩ የግዳጅ አፈጻጸምን ሊጠይቅ የማይችል ሲሆን ሻጩ እንደ ገበያው ልማድ የማካካሻ ሽያጭ ማድረግ ይችላል። የማካካሻ ሽያጭ የሚቻለው ነገሩ ለሌሎች ሰዎች መሸጥ ሲቻል ነው።

- የውል መሰረዝ፦

በሌላ በኩል የውል መሰረዝ በሁለት መንገድ ሊከናወን ይችላል፡- በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚደረግ ውል መሰረዝ እና የአንድ ወገን ወይም የተናጥል የሚደረግ መሰረዝ ናቸው። በመሠረታዊ የጥሰት ጉዳዮች ብቻ በፍርድ ቤት መሰረዝ የሚታዘዝ ሲሆን ይህም ለምሳሌ የብረት ወንበር እንዲሸጥለት ተስማምተው የእንጨት ወንበር ቢያቀርብለት ፍርድ ቤት ውሉ እንዲሰረዝ ሊያዝ ይችላል። ፍርድ ቤት መሄድ ሳያስፈልግ በአንድ ወገን መሰረዝ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች በህግ የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም በውል ውስጥ የተናጥል መሰረዝ አንቀፅ የተካተተ( unilateral cancellation clause) እንደሆነ፣ የውሉ መፈፀሚያ የጊዜ ገደብ ያበቃ እንደሆነ (expiry of time limit) ፣ አፈፃፀም የማይቻል ከሆነ (impossible performance)፣ የሚገመት ያለመፈፀም ካለ (anticipated non performance) ፣ ንብረት መውረስ (dispossession)፣ ከፊል ርክክብ (partial delivery) ካለ ፣እቃው ጉድለት ያለበት እንደሆነ(defect)፣ ዋጋ አለመክፈል( non-payment of price) ናቸው። ይውም ለገገርው እና ሻጩ ውሉን ለመሰረዝ ስልጣን የሚሰጡ የተለያዩ ሁኔታዎች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል። እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች በአንድ ወገን ውልን በመሰረዝ የሽያጭ የውል ማፍረሱ የውሉን ይዘት የሚነካ መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

- የጉዳት ኪሳራ መክፈል( Compensation)

ከግዳጅ አፈጻጸም እና ከመሰረዝ በተጨማሪ የሽያጭ ውልን ያለመፈጸም መፍትሄ የጉዳት ኪሳራ መክፈል (Compensation) ነው። ባለመፈፀሙ ምክንያት ማካካሻ መስጠት ወይም ኪሳራ መክፈል ተጎጂውን ውሉ ተፈጽሞ በነበረበት ቦታ ላይ ለማስቀመጥ መሞከር ነው። በመሆኑም በአንቀጽ 1771(2) በንኡስ አንቀጽ (1) ከተቀመጡት ሌሎች መፍትሄዎች በተጨማሪ ጉዳት ኪሳራ ፈቅዷል። ይህንን ድንጋጌ ከአንቀጽ 1790 ጋር ሲገናዘብ ኪሳራ መክፈል ውሉን ላለመፈጸም አማራጭ እና ድምር መፍትሔ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል።

### 6.6 .3 የማይንቀሳቀስ ንብርት ሽያጭ ውል

የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል አመሰራረት አፈጻጸም እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያለውን ልዩ ባህሪ ለመረዳት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ማየት አስፈላጊ ነው። የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ከመሬት፣ ከህንጻ እና ሌሎች ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ሽያጭ ጋር የሚገናኝ ሲሆን እነዚህ ንብረቶች የማይንቀሳቀሱ ተብለው በሚጠቀሱ ናቸው። የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በራሳቸው የማይንቀሳቀሱ ወይም ሊንቀሳቀሱ የማይችሉ እቃዎች ከአንቀጽ 1127 ተቃራኒ ሲሆን በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1130 መሠረት መሬትና ሕንፃ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ናቸው።

በፍትሐ ብሔር ሕጉ ትርጓሜ መሠረት የውሉ ዕቃ የማይንቀሳቀስ የሆነበት የሽያጭ ውል የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ይባላል። ይሁን እንጂ አንድ ግለሰብ በመሬት ላይ ባለቤትነት መብት ሊኖረው ስለማይችል መሬት ለሽያጭ የማይቀርብ መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ምክንያቱም በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40(3) መሰረት የመሬት ባለቤትነት መብት የኢትዮጵያ ብሄሮች

ብሄረሰቦችና ህዝቦች ነው። ይህ ድንጋጌ ሽያጭን ወይም ሌላ ማንኛውንም የመለዋወጫ ዘዴን በግልፅ ይከለክላል። ይህንና አርሶ አደሮች መሬቱን መውረስ የሚችሉበት፣ አርብቶ አደሮች ለግጦሽ እና ባለሀብቶች በክፍያ ሊጠቀሙበት ከሚችሉበት ልዩ ሁኔታዎች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል።

### 6.6.4 የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ህጎች

አጠቃላይ የውል ድንጋጌዎች ተፈጥሮቸው ምንም ይሁን ምን በሁሉም ውሎች ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ እነዚህ ድንጋጌዎች የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። በአንቀጽ 2894 መሠረት የሽያጭ ውል ድንጋጌዎች በማይንቀሳቀስ ውል ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ምንም እንኳን አጠቃላይ የውልና የሽያጭ ውል ድንጋጌዎች የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ የሚመለከቱ ቢሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በተመለከተ የተወሱ ልዩ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ። በተለይ ከፎርማሊቲ(አፃፃፍ) እና ከምዝገባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ስለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ሽያጭ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡ መስፈርቶች ናቸው። በመሆኑም በፍትሀ ብሄር ህጉ አንቀጽ 2876 ስለ ውል ፎርም በሚገልፀው ክፍል ስር የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በፅሁፍ ሳይደረግ የቀረ እንደሆነ ፈራሽ ነው ይላል። በተጨማሪ በአንቀጽ 1723 የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች በጽሑፍ የተመዘገቡ መሆን እንዳለባቸው በግልጽ ያሳያል። የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኝ በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም።

ሌላው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ሽያጭ ውል የጸና እንዲሆን መሟላት ያለበት መስፈርት የማይንቀሳቀሰው ንብረት መኖር ያለበት (existence of the immovable) መሆኑ ነው። ለአብነት ያህል ከተከራካሪዎቹ አንድ ቤት፣ የቤት ክፍል ወይም ገና የሌለ አንድ የሚሰራ ሕንፃ ለሌላው አካል ለማቅረብ ግዴታ የገባበት ውል የአንድ ህንፃ ስራ ውል ወይም የጉልበት ውል ይባላል እንጂ የሽያጭ ውል አይደለም። በመጨረሻ የማይንቀሳቀስ የንብረትን ሽያጭ ገዢው ወይም ሻጩ ተጎዳው በማለት ምክንያት ሊያፈርሱት አይችሉ[220]

### 6.6.5 የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል አፈጻጸም

የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውልን በተመለከተ ልዩ ከሆኑ የአፈፃፀም ስርዓት ውስጥ የሻጩ የመተባበር ግዴታ ይገኝበታል። በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2879 መሠረት የሻጩ የመተባበር ግዴታ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ነው። ይህውም ገዢው የገዛውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሀብትነት በስሙ ለማዞርና ለማስመዝገብ እንዲችል ሻጩ የንብረቱን ሰነድና ማንኛውንም ማስረጃ ሁሉ ሊሰጠው ይገባል፡ ፡ እንዲሁም በማንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ሳይፃፍ በገዢ ላይ መቃወሚያ ሊሆኑበት የሚችሉን የተሸጠውን ንብረት የሚመለከቱ የ3ኛ መገን መብቶች ሻጩ ለገዢ ማሳወቅ አለበት።

---

[220] የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1723፣ 2894፣ 2876

- የገገርው መብት፡-

በማይንቀሳቀሰው ንብረት ውስጥ የተገኘው ሀብት ይገኛል ተብሎ ከተረጋገጠው በታች የሆነ እንደሆነ ገገርው በዚሁ በጎደለው ሀብት መጠን የዋጋ ቅናሽ እንዲደረግለት ለመጠየቅ የሚችል ሲሆን የማይንቀሳቀስ ንብረት የገዛ ሰው ውሉ እንደቃሉ አይነት እንዲፈፀምለት ለማድረግ የተለየ ጥቅም እንደለው ሆኖ ይገመታል።

- የሻጩ መብት፡-

የተሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ልክ በውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ከፍ ያለ ሆኖ ቢገኝም እንኳ ሻጭ ዋጋ እንዲጨመርለት ለመጠየቅ አይችልም። ነገር ግን ሻጭ ስህተት የደረሰበት በገገርው ወይም በእንደራሴው አታላይነት እንደሆነ ሻጭ መብቱ በመደበኛ ህግ ይጠበቅለታል።

### 6.6.6 የብድር ውል

#### 6.6.6.1 የብድር ውል ምንነት

ብድርን በተመለከተ ሁሉንም ሊያግባባ የሚችል አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም የማናገኝ ሲሆን የተለያዩ ፅሑፎች የተለያየ ትርጉም ሰጥተውት እንመለከታለን።

የፍትሐብሔር ህጉ ብድርን ከአንቀጽ 2471- 2489 የተመለከተ ሲሆን ብድር የሚያልቅ ነገር ብድር በማለት ትርጉም ሰጥቶታል። "የሚያልቅ ነገር ብድር ማለት ከተዋዋዮቹ አንዱ ወገን አበዳሪው ሌላውን ተበዳሪ ሰው የተበደረውን ነገር በዓይነቱ ለመመለስ ተገዳጅ በማደረግ ገንዘብ ወይም በማገልገል የሚያልቅ ሌላ ነገር ለተበዳሪው ለመስጠትና ሀብትነቱን ለማስተላለፍ የሚገደድበት ውል ነው" ይላል። ከዚህ ትርጓሜ መረዳት እንደሚቻለው ብድርን በሚመለከት ሕጉ በሚያልቅ ነገር ላይ ብቻ እንጂ ከዛ ባለፈ ማለትም በማያልቅ ነገር ወይም ቋሚ የሆነ ንብረትን የማያካትት መሆኑን ነው። የድንጋጌውን አጠቃላይ ይዘት ስናይ አመላለሱ በዓይነት ወይም በአገልግሎት ሊሆን እንደሚችል እና ውሉ አስገዳጅ መሆኑንም ያሳያል።[221]

#### 6.6 .6 .2 የብድር ዉል አመሠራረት፡-

የብድር ውል የውል አንድ አካል እንደመሆኑ መጠን አመሰራረቱም ሆነ አፈፃፀሙ በጠቅላላው የውል ሕግ መርሆች የሚገዛ በመሆኑ የብድር ውልን እንደ አንድ ውል የሚፀና ውል ነው ለማለት የሚከተሉትን መርሆች ማሟላት አለበት፡- 1ኛ ዉል የሚፈፀመዉ ለመዋዋል ችሎታ ባላቸዉ ሰዎች መካከል ብቻ መሆኑ ለምሳሌ እድሜዉ ለአቅመ አዳም ወይም ሄዋን ያልደረሰ ወይም አእምሮዉ ህመም ያለበት ሰዉ ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ ሰዉ ችሎታ እንደሌለዉ ይቆጠራል። 2ኛ ዉል የሚደረገው በተወያያቹ ነፃ ፍቃድ ብቻ የሚደረግ መሆኑ። 3ኛ ተወያይ ወገኖች የሚዋዋሉበት ጉዳይ

[221] የፍትሐብሔር ህጉ ከአንቀጽ 2471-2489

በእርግጠኝነት የሚቻል እና ህጋዊና ሞራላዊ ጉዳይ ላይ መሆን የሚገባው መሆኑ። 4ኛ የዉል አቀራረጹ ወይም አፃፃፉ (ፎርም) በህግ ተለይተዉ የተቀመጡ ወይም ተዋዋይ ወገኖች ተለይቶ እንዲቀመጥ ከተስማሙበት የዉል ጉዳይ በቀር የተለየ የዉል ፎርም አያስፈልግም።[222]

6.6 .6 .3 የአበዳሪና ተበዳሪ ግዴታዎች፡-

አበዳሪና ተበዳሪ የራሳቸው የሆኑ ሊያከብሯቸው የሚገቡ ግዴታዎች አሉባቸው። በቅድሚያ የአበዳሪው ግዴታዎችን ስናይ ሕጉ የአበዳሪውን ግዴታዎች በተመለከተ የሽያጭ ውልን በሚደነግገው ክፍል ላይ የሻጩ ግዴታዎች ተብለው የተገለፁት ደንቦች በአበዳሪ ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ ይላል። ቀደም ባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው በፍትሐብሔር ሕጉ የሻጭ ግዴታዎች ናቸው የተባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ ዕቃ የማስረከብ ግዴታ፡- የሽያጭ ውል ከተከናወነ በኋላ ሻጭ የግብይት ምክንያት የሆንውን ዕቃ/ንብረት ለገዥ የማስረከብ ግዴታ አለበት። 2ኛ ስመ-ሀብት የማስተላለፍ ግዴታ፡- ከላይ ለማንሳት እንደተሞከረው የሽያጭ ውል ልዩ መገልጫ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ ሻጩ የሽጭ ምክንያት የሆነውን ንብረት ስመ-ሀብትን የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት መሆኑ ነው። የባለቤትነት መብት መተላለፍን በተመለከተ የብድር ውል ከሽያጭ ውል ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር የብድር ውሉ በትርጉም ክፍሉ ላይ እንደሰፈረው አላቂ ዕቃን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ ዕቃውን ለተበዳሪው በሚያስረክብበት ወቅት የባለቤትነት መብትም አብሮ መተላለፍ መቻሉ ነው። 3ኛ ዋስትና የመስጠት ግዴታ፡- ሌላኛው የሻጭ ግዴታ ከተሸጠው ዕቃ ጋር በተገናኘ ለሚፈጠሩ ችግሮች ለገዥው ዋስትና የመስጠት ግዴታ ነው።

የተበዳሪውን ግዴታዎች በተመለከተ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ሁኔታ ዕዳውን መልሶ ከመክፈል ጋር የሚገናኝ ነው። ተበዳሪ የብድር ውል ውስጥ ሲገባ የተበደረውን ነገር በዓይነቱ ለመመለስ ወይም በገንዘብ የሚመለስ ሲሆን እነዚህን በወቅቱ የመመለስ ግዴታ አለበት። የብድሩ አመላለስ በማገልገል የሚያልቅ ሲሆን ደግሞ ለአበዳሪው ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የሚገደድበት ውል ስለመሆኑ በፍትሀ ብሄር ህጉ ተደንግጓል። ሌላኛው የተበዳሪ ግዴታ ብድሩን ወይም ወለዱን ለመክፈል ካዘገየ በጠቅላላው የውል ሕግ በተደነገገው መሰረት ለዘገየበት ጊዜ ሊከፈል የሚገባውን ወለድ የመክፈል ግዴታ ነው።

6.6.6.4 የብድር ውል ማስረጃ

ማስረጃ ማለት አንድ በፍርድ ቤት ምርመራ ላይ ያለ በጭብጥ የተያዘ አከራካሪ ጉዳይ እውነት መሆንና አለመሆኑን በሚያሳምን ሁኔታ ማረጋገጥ እንዲያስችል በግብአት የሚቀርብ ፍሬ ነገር ስለመሆኑ

[222] የፍትሐብሔር ህጉ ከአንቀጽ 1676

ብ/ጀነራል ታጠቅ ታደሰ "የማስረጃ ሕግ መሰረተ ሀሳቦች"[223] በሚለው መፅሐፋቸው ገልፀውታል። ማስረጃ ማለት ይህ ከሆነ በሁለት ሰዎች መካከል የብድር ውል ተደርጓል ወይስ አልተደረገም የሚለውን ጥያቄ በምን ማረጋገጥ እንችላለን? የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ቀጥለን እናያለን። የፍ/ሕጋችን በአንቀጽ 2472 ስር የብድር ማስረጃ በሚል ርእስ የሚከተለውን ደንግጓል፡-

(1) በብድር የተሰጠው ገንዘብ ከብር 500 በላይ ሲሆን የብድሩን ውል በፅሑፍ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ካልሆነ በስተቀር ለማስረዳት አይቻልም፣

(2) ለብድር ውል ማናቸውም ሌላ ዓይነት ማስረጃ ለማቅረብ አይቻልም፣

(3) እንዲሁም ከብር 500 የበለጠ ገንዘብ የመክፈል ነገር በዚህ ዓይነት ይፈፀማል። በዚህም መሰረት የብድሩ መጠን ብር 500 እና ከዛ በታች ከሆነ በማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ለምሳሌ በቦታው የነበረ የሰው ምስክር በመስማት ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን እና መጠኑ ከዛ በላይ ከሆነ ግን ከሦስቱ የማስጃ ዓይነቶች መካከል በአንዱ ካልሆነ በስተቀር በሌላ በምንም መንገድ ማረጋገጥ የማይቻል መሆኑን ነው መረዳት የሚቻለው። እነዚህን ሦስት የማስረጃ ዓይነቶች ቀጥለን እንመልከት።

የመጀመሪያውና የበለጠ አስተማማኝ የሆነው ማስረጃ የፅሑፍ ማስረጃ ነው። ይህም ማለት ገና ከጅምሩ የብድር ውሉ ሲደረግ በፅሑፍ የተደረገ ሲሆን ያንን ፅሑፍ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል። በሌላ አነጋገር ከብር 500 በላይ የሆነ የብድር ውል በፅሑፍ እንዲሆን ሕጉ አስገዳጅ የሚመስል ድንጋጌ ያስቀመጠ በመሆኑ ከላይ ካነሳነው የውል አመሰራረት መርሆች መካከል የተለየ ፎርም የሚፈልግ መሆኑን ማየት ይቻላል። ሁለተኛው የማረጋገጫ መንገድ በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ነው። ይህም ማለት ተበዳሪው በፍርድ ቤት ቀርቦ በከሳሹ የቀረበበትን ክስ ማለትም ከከሳሹ ገንዘብ የተበደረ መሆኑን፣ መጠኑ ምን ያክል እንደሆነ በማያሻማ መንገድ ካመነ በቀላሉ የብድሩ መኖር የሚረጋገጥ ይሆናል። ሦስተኛውና የመጨረሻው የማረጋገጫ መንገድ በመሐላ የማረጋገጥ ሂደት ነው። መሐላ ማለት በክርክር ወቅት አንድ ተከራካሪ ወገን በሚያቀርበው ማስረጃ ወይም በሚናገረው ፍሬ ነገር እውነትነትን ለማረጋገጥ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ቅፅ ላይ የሚሰጡት ማረጋገጫ ነው።

### 6.6.6.5 የብድር መመለሻ ጊዜ

ብድር ውል እንደመሆኑ መጠን ለተዋዋይ ወገኖች ሰፊ ነፃነት መሰጠት አለበት። በመሆኑም ሕጉ ስለብድር መመለሻ ጊዜ በተዋዋይ ወገኖች የተወሰነ ጊዜ በሚኖርበት ወቅት ይህንኑ ዕውቅና በመስጠት ክፍያው በዛ ጊዜ መሆን እንደሚገባው ሕጉ አፅንኦት ሰጥቶበታል። ከዚህም ባለፈ ብድሩ ወለድ የሌለበት ከሆነ የተበደረውን ገንዘብ ለመመለስ ማሰቡን ለአበዳሪው ከአንድ ወር በፊት አስታውቆ የመመለሻ ጊዜው ከመድረሱ በፊት ሊመልስለት እንደሚችልም ሕጉ ይደነግጋል። የብድሩ መመለሻ

[223] ብ/ጀነራል ታጠቅ ታደሰ "የማስረጃ ሕግ መሰረተ ሀሳቦች

ጊዜ በተዋዋይ ወገኖች ያልተወሰ በሚሆን ጊዜ ሕጉ ብድሩ በምን ያክል ጊዜ ውስጥ ሊከፈል እንደሚገባው ደንግጓል። ይኼውም አበዳሪው መልስልኝ ሲል ከጠየቀበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መመለስ እንዳለበት ተደንግጓል። ተበዳሪውም በአበዳሪው ሳይጠየቅ መክፈል ቢፈልግ ለመክፈል ያለውን ሀሳብ ከአንድ ወር በፊት ካስታወቀ በኋላ ዕዳውን መመለስ እንደሚችል እንዲሁ ተደንግጓል (በፍትሀብሔር ህግ ቁ 2482)።

6.6.6.5 በብድር ላይ ሊኖር ስለሚችል ወለድ

በብድር ውል ላይ ሊኖር ስለሚችል ወለድም ለተዋዋይ ወገኖች ነፃ ፈቃድ የተተወ ጉዳይ ነው። ብድሩ ወለድ የሚከፈልበት ስለመሆኑ በውሉ በግልጽ ካልተገለፀ ግን ተበዳሪው በምንም መልኩ ወለድ እንዳይከፍል ሕጉ ጥበቃ ያደርግለታል። ሕጉ በብድር ውሉ ላይ ወለድ ይኑር አይኑር የሚለውን ጉዳይ በተዋዋይ ወገኖች እንዲወሰን ነፃነት የሰጠ ቢሆንም በወለድ መጠኑ ልክ ላይና ስለሚከፈልበት ጊዜ ወይም ወለዱ ስለሚሰላበት ጊዜ ግን ገደብ አስቀምጧል።
በዚህም መሰረት ተዋዋይ ወገኖች የወለዱን መጠን በዓመት ከ12 በመቶ በላይ ማድረግ እንደማይችሉ ገደብ ጥሏል። እንዲሁም የወለዱ መጠን በውሉ ላይ ካልተገለፀ እና ወለድ የሚከፈልበት ብድር መሆኑ ብቻ ተገልፆ ከሆነ ወይም ወለዱ ከ12 በመቶ በላይ ይሆናል የሚል የውል ቃል ካለ መክፈል የሚችለው የወለድ መጠን በዓመት 9 በመቶ ብቻ እንደሚሆንና የሚሰላውም ተቃራኒ የሚሆን የውል ቃል ከሌለ ብድሩ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በየዓመቱ መጨረሻ ላይ መሆን ይገባዋል ይላል።[224]

6.6.6.6 የብድር አከፋፈል (የሚከፈለው ነገር)

በብድር አመላለስ ወቅት ሌላው ግለፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ብድሩ በየትኛው ሀገር የገንዘብ ዓይነት ነው? ከብድሩ በኋላ የምንዛሬ ዋጋ መለዋወጥ ቢያጋጥምስ ምን ይሆናል? የሚለው ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የፍትሐብሔር ሕጉ ግልፅ ድንጋጌዎች አሉት። በዚህም መሰረት የብድር ውሉ የተደረገው በኢትዮጵያ ብር ከሆነ ብድሩ በሚመለስበት ወቅት ባለው ሕጋዊ የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ ወይም ለዚህ የገንዘብ መጠን የሚተካ የውጭ ምንዛሬ በማቅረብ ከዕዳው ነፃ እንደሚሆን ተደንግጓል። የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የብድር ውሉ በሚከናወንበት ጊዜ በትክክል የተበደረውን ያክል እንጂ ሌላ ነገር እንደማያካትትና በመሀል ሊያጋጥም የሚችለውን ወይም ያገጠመውን የገንዘቡ ዋጋ መለዋወጥ ግምት ውስጥ መግባት እንደሌለበትም ሕጉ አያይዞ ይገልፃል።

---

224 በፍትሀብሔር ህግ ቁ 2479፣2481

ብድሩ በውጭ አገር ገንዘብ ተደርጎ ከነበረ ደግሞ ብድሩ በሚከፈልበት ጊዜ በዛ አገር ሕጋዊ መገበያያ በሆነው የገንዘብ ኖት መከፈል ያለበት ሲሆን መጠኑም የተበደረውን ያክል ብቻ መሆን እንዳለበት ሕጉ አመልክቷል። የብድር ውሉ የተደረገው ከገንዘብ ውጪ ባሉ የሀብት ዓይነቶች በሚሆንበት ጊዜ ለምሳሌ፡ - ለምግብ የሚሆኑ ነገሮች፣ ሸቀጦች ወይም መዓድናት ሲሆኑ ተበዳሪው በተበደረው ልክ ብዛቱንና ዓይነቱን በመክፈል ከዕዳው ነፃ ይሆናል። በተመሳሳይ መልኩ ከብድሩ በኋላ በሚኖር የዋጋ መለዋወጥ የብድድር አመላለሱን መጠንና ዓይነት ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ የለም።[225]

### 6.6.7 የቤት ኪራይ ውል

ልዩ የዉል አይነት ከሆኑት ዉስጥ በማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ላይ ከሚደረጉ የዉል አይነቶች ዉስጥ አንዱ የቤት ኪራይ ዉል ነዉ። የቤት ኪራይ ዉልን በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጋችን አምስተኛ መፅሃፍ አንቀፅ አስራ ስምንት የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሚመለከት በሚለዉ ክፍል ዉስጥ የቤት ኪራይን የሚመለከቱ ልዩ ደንቦች በሚል ርዕስ ስር ከቁጥር 2945 እስከ 2974 ድረስ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ይሆኑበታል። በመቀጠልም ዋና ዋና የሆኑ ነገሮችን በዝርዝር እንመለከታለን። [226]

#### 6.6.7.1 የቤት ኪራይ ዉል ትርጉም

በህጋችን ላይ የቤት ኪራይ ዉል ማለት ይህ ነዉ በማለት ትርጉም ባይሰጠዉም ከህጉ ድንጋጌዎች በመነሳት ምንነቱን ወይም ትርጉሙን መረዳት እንችላለን። በመሆኑም የቤት ኪራይ ዉል "አንድ የቤት ወይም ህንፃ ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሆነ ሰዉ (አከራይ ተብሎ ለየሚጠራው) ቤቱን ወይም ህንፃዉን ሙሉ በሙሉ ወይም የተወሰኑ ክፍሎችን ወይም አንዱን ክፍል ለሌላ ሰዉ (ተከራይ ተብሎ ለሚጠራው ከነዕቃዉ ወይም ባዶዉን የተወሰነ የኪራይ ዋጋ በመቀበል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ አስተላልፎ ማስጠት /ማከራየት/" ማለት ነዉ በማለት በግርድፉ ትርጉም ሊሰጠዉ ይችላል። ነገር ግን የሆቴል ክፍልን ለተወሰነ ጊዜ ተከራይቶ መኖርን አያካትትም።

#### 6.6.7.2 የተፈፃሚነት ወሰን

ቤት በተፈጥሮዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነዉ። በፍትሐብሔር ህጉ ዉስጥም ቤት የማይቀሳቀሱ ንብረቶች ዉስጥ አንዱ እንደሆነ ተደንግጓል። በፍትሐብሔር ህጉ የቤት ኪራይን በተመለከተ ልዩ

---

[225] በፍትሀብሔር ህግ ቁ 2485፣2486

[226] በፍትሀብሔር ህግ ቁ 2945 እስከ 2974

ደንቦች ተብለዉ ከቁጥር 2945 እስከ 2974 የተደነገጉት ተፈፃሚ የሚሆኑት የአከራይና ተከራይ ዉል ቤትን ከነዕቃዉ ወይም ያለ ዕቃ ወይም አንድ ባለክፍሎች ቤት ወይም አንድ ክፍል ቤት ወይም ማናቸዉንም አንድ ሌላ ሕንፃ ወይም የሕንጻ አንዱን ክፍል ላይ በሚደረግ የቤት ኪራይ ዉል ላይ ይሆናል። ይህም ማለት አከራይ የሆነዉ ሰዉ እና ተከራይ የሆነዉ ሰዉ አንድን ቤት በጠቅላላዉ ወይም ከቤቱ አንዱን ክፍል ወይም የቤቱን የተወሰኑ ክፍሎች ባዶዉንም ሆነ ከነእቃዉ ወይም አንድን ሕንፃ ሙሉዉን ወይም የሕንፃዉን ክፍል ላይ የኪራይ ዉል ቢፈፅሙ ይህን ዉላቸዉን የሚገዛዉ ወይም የሚመራበት ህግ ከቁጥር 2945 - 2974 የክራይ ውል ህግ ይሆናል[227]።

ነገር ግን በፍትሐ ብሔር ህጋችን ስለሆቴል ስራ ዉል ከቁጥር 2653 - 2671 የተደነገገዉ እንደ ቤት ኪራይ ዉል ስለማይቆጠር በቤት ኪራይ ዉል ደንብ መሠረት አይገዛም። በሌላ አነጋገር የቤት ኪራይ ዉል ደንብ ተግባራዊ የሚሆነዉ የቤት ኪራይ ዉል ላይ ብቻ ነዉ። በመሆኑም አንድ ሰዉ ሆቴል ሄዶ ለአነድ ቀን ወይም ለተወሰነ ቀን የሆቴሉን ክፍል ተከራይቶ ቢቆይበት እንደ ቤት ኪራይ ዉል ተቆጥሮ በዚህ ደንብ መሰረት አይመራም። ይህን አባባላችንን በፍትሐብሔር ህጋችን አንቀፅ 2945(2) ላይ "በዚህ ህግ አገልግሎት መስጠትን ስለሚመለከቱ ዉሎች የተነገሩት ስለ ሆቴል ዉል የተደነገጉት ደንቦች የተጠበቁ ናቸዉ" በሚል ተደነገገዉ ያጠናክርልናል።

6.6.7.3 ስለሞዴል የቤት ኪራይ ዉሎች

የቤት ኪራይ ዉልን በተመለከተ ተዋዋይ ወገኖች በፈለጉት አይነት (ለምሳሌ በፅሁፍ ወይም በቃል) ማድረግ ይችላሉ። ይህን በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጉ በጠቅላላ ዉልን በሚመራዉ ክፍል ቁጥር 1678(3) ላይ አቀራረጹ ወይም አፃፃፉ በህግ (ፎርም) ተለይተዉ የተቀመጡ ወይም ተዋዋይ ወገኖች ተለይቶ እንዲቀመጡ ከተስማሙበት የዉል ጉዳይ በቀር የተለየ የዉል ፎርም የማያስፈልግ መሆኑ ተደንግጓል። በመሆኑም በልዩ ክፍል ዉስጥ የቤት ኪራይ ዉል በዚህ መልክ ይቀመጥ ተብሎ ያልተደነገገ በመሆኑ ተዋዋይ ወገኖች በፈለጉት አይነት ማድረግ ይችላሉ።

ተዋዋይ ወገኖቹ የቤት ኪራይ ዉላቸዉን በፅሁፍ ለማድረግ ከተስማሙ ግን የኪራይ ቤት ዉል ሞዴልን በተመለከተ በአንድ ከተማ ዉስጥ ባሉ ቤቶች ላይ የሚደረግ የኪራይ ቤት ዉል ሞዴልን የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ሊያዘጋጅ ይችላል። ተዋዋይ ወገኖችም እነዚህን የቤት ኪራይ ዉል ሞዴሎችን ተጠቅመዉ የቤት ኪራይ ዉል ሊፈፅሙ ይችላሉ። ነገር ግን በፍትሐብሔር ህጋችን ቁጥር 2946(3) ላይ እንደተደነገገዉ ተዋዋይ ወገኖች የቤት ኪራይ ዉልን በተመለከተ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ባዘጋጀዉ የዉል ሞዴል ብቻ ዉል እንዲፈፅሙ የማይገደዱ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። በመሆኑም

[227] የፍ/ህግ አንቀፅ 2945(1)

ተዋዋይ ወገኖች (አከራይና ተከራይ) የዉልን ሞዴል ከፈለጉ በራሳቸዉ ማዘጋጀት ይችላሉ ማለት ነው፡
፡

6.6.7.4 የኪራዩ ክፍያ መጠን እና ጊዜ

ተዋዋይ ወገኖች (አከራይ እና ተከራይ) በቤት ኪራይ ዉላቸዉ በስምምነት ከሚወስኗቸዉ ነገሮች ዉስጥ ዋነኞቹ ዉሉ የሚቆይበትን ጊዜ፣ የቤቱ ኪራይ ዋጋ እና ኪራዩ የሚከፈልበትን ጊዜ ናቸው። ተዋዋዮቹ ለፈለጉት ጊዜ ያህል በዉላቸዉ እንዲቆይ፣ በፈለጉት ዋጋ እና በተስማሙበት ጊዜ ክፍያዉ እንዲፈፀም በዉላቸዉ ዉስጥ ሊስማሙ ይችላሉ። ነገር ግን ተዋዋይ ወገኖች (አከራይ እና ተከራይ) በዉላቸዉ ዉስጥ እነዚህን ነገሮች ካልገለፁ በህጉ የተቀመጠው ተፈፃሚ ይሆናል። ይህንንም በተመለከተ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2950(2) ላይ ተዋዋይ ወገኖች በዉላቸዉ ዉስጥ የኪራዩን መጠን ካላስቀመጡ ወይም በሚያጠራጥር ጊዜ የማዘጋጃ ቤት ባለስልጣናት በወሰኑት ታሪፍ ወሠረት ወይም የተወሰነ ታሪፍ የሌለ እንደሆነ የቦታዎቹን ልማድ በመከተል የሚወሰን መሆኑ ተደንግጓል። የዉሉን ቆይታ ጊዜ በተመለከተ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊሆን እንደሚችል በዚሁ ህግ ተመላክቷል።

የኪራዩ ዋጋ የሚከፈልበትን ጊዜ በተመለከተ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2951 ላይ ተዋዋይ ወገኖቹ በዉላቸዉ ዉስጥ ያልተስማሙበት ከሆነ፡-

1.የቤት ኪራይ ዉሉ ለአንድ ወይም ለብዙ አመታት ተደርጎ እንደሆነ ኪራዩ በሶስት ወር መጨረሻ የሚከፈል ይሆናል። ይህ ማለት ተዋዋዮቹ በቤት ኪራይ ዉል ዉስጥ ለአንድ ወይም ከአንድ አመት በላይ ሆኖ ለታወቀ ጊዜ ያክል ለምሳሌ ለአምስት፣ ለአስር አመት፣ ወዘተ ተብሎ የተስማሙ ከሆነና የክፍያ ጊዜዉን ካልተስማሙ በየሶስት ወር መጨረሻ የሚከፈል መሆኑ ተደንግጓል።[228]

2.የቤት ኪራይ ዉሉ በጣም አጭር ለሆነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ተደርጎ እንደሆነ በየወሩ መጨረሻ ላይ የሚከፈል ይሆናል (በህጉ ቁጥር 2951/2/)። ነገር ግን በማንኛዉም ሁኔታ ቢሆን ክፍያዉ የቤት ኪራይ ዉሉ ሲያልቅ (ሲያቆም) መከፈል አለበት። ይህም ማለት ተዋዋዮች በቤት ኪራይ ዉላቸዉ ዉስጥ ኪራይ የሚከፈልበት ጊዜ ባይቀመጥም እንዲሁም ከላይ በተቀመጡት ሁኔታም ክፍያዉ ባይፈፀም እንኳን የቤት ኪራይ ዉሉ ሲያልቅ (ሲያቆም) የሚከፈል ይሆናል።

6.6.7.5 የተከራዩትን ቤት ስለማደስ

ተዋዋይ ወገኖች የቤቱ እድሳት በተመለከተ በዉላቸዉ ዉስጥ በስምምነት ሊወስኑት ከሚችሏቸዉ ጉዳዮች ዉስጥ አንድ ነዉ። በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች በቤት ኪራይ ዉሉ ዉስጥ የቤቱን እድሳት

[228] ፍ/ሕ/ቁጥር 2951/1/

በተመለከተ (ማን ያድሳል፣ ማን ምኑን ያድሰል፣ የእድሳቱን ወጪ ማን ይሸፍናል፣ ወዘተ) ከተስማሙ በዉሉ መሰረት የቤቱ እድሳት ይፈፀማል ማለት ነዉ። ነገር ግን ተዋዋዩቹ ስለ ቤቱ እድሳት በዉላቸዉ ላይ የገለፁት ነገር የሌለ ከሆነ የፍትሐብሔር ህጉ የቤት ኪራይን የሚመራዉ ልዩ ደንብ ክፍል የሆነዉ ከቁጥር 2953- 2956 ያለዉ ተግባራዊ ይሆናል። በዚህ ህግ መሰረት ማድስ ማለት የቤቱ መዝጊያዎችን ወይም መስኮቶችን፣ የቤቱን ወለሎችን ወይም ንጣፎችን፣ የዉሃ መስመሮችንና የፍሳሽ ማስወገጃዎችን ማደስ እና ቤቱን የማፅዳት እና በደንብ መያዝ መሆኑን በህጉ ተመልክቷል[229]። ይህ ህጉ የሰጠዉ ትርጉም ቢኖርም ተዋዋዮቹ ትርጉሙን በዉላቸዉ ከዚህ በላይ ማስፋት ይችላሉ።

በቤት ኪራይ ዉሉ ዉስጥ ተከራዩ ማደስ ይገባዋል የተባሉት (የሚባሉት) በኪራይ ዉል ተከራዩ ይፈፀማቸዋል ተብለዉ የተወሰኑት ናቸዉ። ተከራዩ ሊያድሳቸዉ የሚገባዉን የተከራያቸዉን ቤቶች በራሱ ኪሳራ ለማደስ ይገደዳል በማለት በፍትሐብሔር ህጉ ቁጥር 2953 ላይ ተደንግጓል። ይህም ማለት ተከራዩ በኪራይ ዉሉ ዉስጥ ለማድስ በተስማማዉ መሰረት በራሱ ወጭ ለማድስ ይገደዳል ማለት ነዉ። ነገር ግን ቤቶቹ በማርጀት ወይም ካቅም በላይ በሆነ ነገር ብቻ የተበላሹ ሲሆኑ ተከራዩ ማናቸዉንም ቤቶችን የማደስ ስራዎች መፈፀም አይጠበቅበትም። ይሁንና በቤት ኪራይ ዉላቸዉ ዉስጥ በማርጀት ወይም ካቅም በላይ በሆነ ነገር የተበላሹትንም ጭምር አድሳለዉ በማለት ተከራዩ የተስማማ ከሆነ ብቻ ነው እንዲያድስ የሚገደደዉ።

በተዋዋዮች መካከል የፀና የቤት ኪራይ ዉል ባለበት ጊዜ ዉስጥ አከራዩ የቤቱን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚያድስበት ጊዜ የማደስ ስራዉ ከአስራ አምስት ቀን በላይ የፈጀ ከሆነ ተከራዩ ለዚህ ለተወሰነ ጊዜ በቤቱ ሳይገለገልበት የቆየ ከሆነ ለዚህ ሳይገለገልበት ለቆየዉ ጊዜ ከቤት ኪራዩ ይቀነስለታል[230]።

### 6.6.7.6 የተከራዩትን ቤት ስለማከራየት

በመርህ ደረጃ ተከራይ የተከራየዉን ቤት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለማከራየት ይችላል። ነገር ግን አንድ ሰዉ የተከራየዉን ቤት ሊያከራይ የሚችለዉ አከራዩ ለዚህ የኪራይ ኪራይ ተቃዉሞ የሌለዉ ከሆነ ብቻ ነዉ። የቤቱ አከራይ ዉል ዉስጥ "ተከራዩ የተከራየዉን ቤት እንዲያከራይ ወይም ተከራዩ ከማከራየቱ በፊት የአከራዩን ፈቃድ መቀበል ያስፈልጋል" በማለት መስማማት ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ ተዋዋይ ወገኖች ተስማምተዉ ሳለ ተከራዩ የተከራየውን ቤት ሲያከራይ አከራዩ ያለ ምክንያት ፈቃዱን የከለከል እንደሆነ ተከራዩ የኪራይ ዉሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ይችላል[231] ። አከራዩ ተከራዩ

---

229 ፍ/ሕ/ቁጥር በቁጥር 2954(2) እና (3)

230 ፍ/ሕ/ቁጥር ቁጥር 2956(1)

231 ፍ/ሕ/ ቁጥር 2959(2)

የተከራየዉን ቤት እንዲያከራይ ፍቃዱን ቢሰጥም እንኳን ተከራዩ ያለበትን ግዴታዎች አያስቀርም። ይህም ማለት በኪራይ ዉሉ መሰረት ለአከራዩ ለገባቸው ግዴታዎች ተገዳጅ ይሆናል።

ከተከራይ የተከራየ ሰዉ በኪራይ የተሰጠውን ቤት በተመለከተ የዋናዉ የቤት ኪራይ ዉል ዉስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች በሙሉ የማክበር ግዴታ አለት። አከራዩን በዋናዉ ዉል የተቀመጡ ግዴታዎችን እንዲፈፅም ከተከራይ የተከራየ ሰዉ በቀጥታ ሊጠይቅ ይችላል። ይህን ማለት ለምሳል በዋናዉ ዉል ዉስጥ ተከራይ ቤቱን የማደስ ግዴታ ቢኖርበት አከራዩ ከተከራይ የተከራየ ሰዉ ቤቱን እንዲያድስ ሊጠይቀዉ ይችላል ማለት ነዉ። ዋናዉ አከራይ ከተከራይ የተከራየ ሰዉ ላይ የተከራየበትን ዋጋ በቀጥታ በእጁ ለርሱ እንዲከፍለዉ ለማስገደድ እንደሚችል በቁጥር 2962/2/ ላይ ተደንግጓል። ነገር ግን ከተከራይ የተከራየ ሰዉ እርሱ ከተስማማበት የኪራይ ዋጋ በላይ ላለዉ ተጠያቂ አይሆንም።

ዋናዉ የኪራይ ዉል (በአከራይና በተከራይ መካከል ያለዉ) ቀሪ ሲሆን ከተከራይ የተከራየ ሰዉ ከተከራይ ጋር (የተከራይ ተከራይ ዉል) ያደረገዉን ዉል ቀሪ እንደሚሆን በቁጥር 2964/1/ ላይ ተደንግጓል። ይህም ማለት ዋናዉ እና የመጀመሪያዉ የቤት ኪራይ ዉል ሲፈርስ በዚሁ ቤት ላይ በተከራይ እና ከተከራይ የተከራየ ሰዉ መካከል የተደረገዉ ዉል ይፈርሳል ማለት ነዉ። ነገር ግን አከራዩ በግልፅ ተከራዩ እንዲያከራይ ፈቅዶ እንደሆነ ዋናዉን የኪራይ ዉል ለመፈፀም ሁለተኛ ተከራይ (ከተከራይ የተከራየ ሰዉ) በዋናዉ ተከራይ ፋንታ ሊተካ ይችላል[232] ። ይህም ማለት አከራዩ በግልፅ ተከራዩ እንዲያከራይ ፈቅዶ ቀጣዩ ዉል በተከራይ እና ከተከራይ የተከራየ ሰዉ መካከል ዉሉ የተፈፀመ እንደሆነ ዋናዉ ዉል ቢፈርስም ቀጥሎ የተደረገዉ ዉል በዋናዉ አከራይ እና ከተከራይ የተከራየ ሰዉ መካከል እንደተደረገ ተቆጥሮ ዉሉ ይቀጥላል ማለት ነዉ።

የቤት ኪራይ ክፍያን በጊዜዉ አለመክፈል ዉጤት፡- ተከራይ የቤት ኪራይ ክፍያዉን በጊዜዉ ያልከፈለ ወይም ሳይከፍል የቆየ እንደሆነ የሚያስከትለዉ ዉጤት በፍትሐብሔር ህጉ ላይ ተቀምጧል። ይሄው[233]፡-

- የቤት ኪራይ ዉሉ ለአንድ ወይም ከአንድ ዓመት ለበለጠ ጊዜ ተደርጎ እንደሆነ አከራዩ የሠላሳ ቀን ማስጠንቀቅያ በመስጠት፣
- የቤት ኪራይ ዉሉ አጭር ለሆነ ጊዜ ተደርጎ እንደሆነ አከራዩ የአስራ አምስት ቀን ማስጠንቀቅያ በመስጠት፣

በዚህ ጊዜ ዉስጥ ተከራዩ ኪራዩን ያልከፈለ እንደሆነ አከራዩ ዉሉን የሚያቋርጥ መሆኑን መንገር ይችላል። በዚህ በተሰጠዉ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ዉስጥ ተከራዩ ያልከፈለ እንደ ሆነ አከራይ ዉሉን

[232] ፍ/ሕ/ሕ/ ቁጥር 2964/2/

[233] ፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2952

ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ይሆናል። ተዋዋይ ወገኖች በማንኛዉም ሁኔታ እነዚህን ከላይ የተቀመጡ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የሚያሳጥሩ ወይም ኪራዩ ባለመከፈሉ ምክንያት ወዲያዉ ዉሉን የማፍረስ መብት ለአከራዩ የሚሰጡ የዉል ቃሎች ፈራሾች ናቸዉ[234]።

6.6.7.7 የቤት ኪራይ ዉል የሚፈርስባቸው ምክንያቶች

አከራይ እና ተከራይ በመካከላቸዉ ያደረጉት የቤት ኪራይ ዉል በተለያየ ሁኔታ ሊቋረጥ ይችላል። የቤት ክራይ ውል ከሚቋረጥባቸዉ ምክንያቶችም፡-

1. የቤት ኪራይ ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ ተደርጎ የውል ጊዜዉ ሲያበቃ።

2. ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት ዉላቸዉን ለማቋረጥ ከተስማሙ።

3. ተከራይ ኪራዩን በጊዜዉ ባለመክፈሉ አከራዩ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሰጥቶት በዚህ ጊዜ ዉስጥ ሳይከፍል በመቅረቱ አከራዩ ዉሉን ካቋረጠዉ።

4. አከራዩ ቤቱን ሲያድስ ለተከራዩና ለቤተሰቡ አስፈላጊ የሆነዉን መኖሪያ ሊጠቀምበት የማይችል ያደረገዉ እንደሆነ ተከራይ አከራዩን በመጠየቅ ሲያፈርስ።

5. አከራይ ቤቱን ፈልጎት ለተከራይ ማስጠንቀቂያ ጊዜ በመስጠት ወይም ተከራዩ ቤቱን መልቀቅ ፈልጎ ለአከራዩ ማስጠንቀቂያ ጊዜ በመስጠት ሲያቋርጥ ናቸው። ነገር ግን አከራይ ቤቱን ፈልጎት ለተከራይ ማስጠንቀቂያ ጊዜ በመስጠት ሲያቋርጥ አከራዩ ሊሰጥ የሚገባዉ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ምን ያክል መሆን አለበት የሚለዉ በህጉ መልስ አልተሰጠዉም። ይህ ጉዳይ በህብረተሰቡ ዉስጥም የተለያየ ዉዥንብር እና ጭቅጭቅ ሲፈጠር ይታያል። ይህ ጉዳይ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ መሆኑ እሙን ነዉ። በፍትሐ ብሔር ህግን ስንተረጉም የምንከተለዉ መርሆች ዉስጥ አንዱ ለተመሳሳይ ጉዳይ ተመሳሳይ ሁኔታን (አናሎጂ) በመጠቀም መተርጎም ይቻላል። በዚሁ መሰረትም አከራይ ቤቱን ፈልጎት ለተከራይ ማስጠንቀቂያ ጊዜ በመስጠት ሲያቋርጥ አከራዩ ሊሰጥ የሚገባዉ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ተከራዩ ኪራዩን በጊዜዉ ባለመለክፈሉ አከራዩ በፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 2952 መሠረት የሚሰጠዉ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ለዚህም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት፡

1. የቤት ኪራይ ዉሉ ለአንድ ወይም ለአንድ ለበለጠ ጊዜ ተደርጎ እንደሆነ አከራዩ የሠላሳ ቀን ማስጠንቀቅያ በመስጠት፣

2. የቤት ኪራይ ዉሉ አጭር ለሆነ ጊዜ ተደርጎ እንደሆነ አከራዩ የአስራ አምስት ቀን ማስጠንቀቅያ በመስጠት፣ ዉሉን ሊያቋርጥ ይችላል።

6.6.7.8 ቤቱን የገዛ ወይም ያገኘ ሰዉ መብት

---

[234] ፍ/ህግ/ቁጥር 2952/3/

የፀና የቤት ኪራይ ዉል ባለበት ቤት ላይ ሌላ ሰዉ የባለቤትነት መብት (ገዢ ወይም በስጦታ) ቢያገኝ ቤቱን የገዛዉ ወይም ያገኘዉ ሰዉ የነበረዉ የኪራይ ዉል ለማቋረጥ እንዲችል መብት ተሰጥቶት እንደሆነና የኪራይ ዉሉ እንዲቋረጥ የፈለገ እንደሆነ ቤቱን የተከራየዉ ለአጭር ጊዜ ከሆነ ይህ ጊዜ ሲያበቃ፣ እንዲሁም የቤት ኪራይ ዉሉ ለአንድ ወይም ከአንድ ዓመት ለበለጠ ጊዜ ተደርጎ እንደሆነ አከራዩ የሠላሳ ቀን ማስጠንቀቅያ በመስጠት ይህ ጊዜ ሲያበቃ ዉሉን ማቋረጥ የሚቻል መሆኑ በአንቀፅ 2967/1/ ተደንግጓል። ይህን ድንጋጌ በመቃረን የሚደረግ ዉል ፈራሽ እንደሆነም በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል።[235]

## 6.7 ውክልና

በኢትዮጵያ የፍትሀብሄር ህግ ከተካተቱ ጉዳዮች ውስጥ እንደራሴነት ወይም የውክልና ስልጣን አንዱ ሲሆን ይህም በሀገራችን በብዛት ሲሰራበት ይስተዋላል። የሌላ ሰው እንደራሴ በመሆን ስራዎችን የመፈፀም ስልጣን የሚመነጨው ከህግ ወይም ከውል ነው። ለአካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ ሞግዚት መሆን ወይም ንብረት ለማስተዳደር በሕግ የፈቀደላቸው ጠባቂ ወይም አሳደሪ የመሆን የእንደራሴነት ስልጣን ለምሳሌ ከህግ የሚገኝ የውክልና ስልጣን ነው ። በሌላ በኩል አንድን የህግ ጉዳይ ጠበቃ ፍርድ ቤት ይዞ እንዲከራከርለት ባለጉዳይ ለጠበቃ የሚሰጠው የእንደራሴነት ስልጣን ደግሞ ከውል የሚገኝ የውክልና ስልጣን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

### 6.7.1 የውክልና ትርጉም

በፍትህ ብሔር ህጉ ለውክልናን በተሰጠው ትርጉም መሰረት "ውክልና ማለት ተወካይ የተባለ አንድ ሰው ወካይ ለተባለው ሰው እንደራሴ ሆኖ አንድ ወይም ብዙ ህጋዊ ሥራዎች በወካዩ ሥም ለማከናወን ግዴታ የሚገባበት ውል ማለት ነው [236]። ከትርጉሙ ለመረዳት እንደምንችለው
ውክልና ከልዩ ውሎች መካከል አንዱ ሲሆን ውክልና የሚደረገው በወካይና በተወካይ መካከል በሚደረግ ስምምነት ነው። በተጨማሪም በውክልናው የሚከናወኑት ስራዎች ህጋዊ መሆን አንዳለባቸው መገንዘብ ይቻላል። ይህ ማለት ደግሞ ህጋዊ ባልሆኑ ነገሮች ላይ የሚደረግ ውክልና ተቀባይነት የለውም ማለት ነው።

### 6.7.2 የውክልና አስፈላጊነት

አንድ ሰው አንዳንድ ተግባሮችን በራሱ ከማድረግ ይልቅ ሌላን ሰው በመወከል ተግባሮቹ እንዲከናወኑለት ሊፈልግ ይችላል። ለዚህም ምክንያቱ የጊዜ ጥበት፣ የቦታ ርቀት ወይም የሁኔታዎች

---

[235] ፍ/ህግ/ቁጥር 2967/1/

[236] ፍ/ህግ/ቁጥር 2199

አለመመቻቸት፣ የእውቀት ወይም የክህሎት አለመኖርና የችሎታ ማነስ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ሌሎችም በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ዉክልና ከውል የሚመነጨው መብት ነዉ። በፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 2200 እስከ 2207 በተቀመጠው መሠረት ለማየት እንሞክራለን።

### 6.7.3 የውክልና ውል አመሰራረት

ውክልና እንዴት ይቋቋማል? ምን ምን  የውክልና አይነቶች አሉ። ግባቸውስ ምንድን ነው? የሚለውን በመቀጠል እንመለከታለን።

ውክልና በግልፅ ማለትም ወካይ የውክልና ስልጣኑን ለተወካይ እንደሰጠው በግልፅ በማሳወቅ ወይም በዝምታ ሊሰጥ ይችላል (expressly or impliedly)።ተወካዩም ሊፈፅመው የሚገባው የሥራ ተግባር ስለአፈፃፀሙ በአንደንድ ህጋዊ ፎርም ውስጥ እንዲገባ የሚያስፈልገው ሲሆን ውክልናው ለተወካዩ ሊሰጠው የሚገባው ይኸው ሕግ በሚያዘው ፎርም መሠረት ነው[237]። ለምሣሌ ተወካዩ ከተወከለ በኋላ ሊያከናውናቸው የሚችሉት ጉዳዬች ወይም የሚዋዋላቸው ውሎች በፅሁፍ መሆን ግድ የሚላቸው አይነት ከሆኑ ከወዲሁ የሚደረገው የውክልና ውልም በፅሁፍ መሆን አለበት ነው። ይሄውም የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን በተመለከተ የሚወከል ሰው ውሉ በጽሁፍ መሆን ስላለበት የውክልና ስልጣን ውሉም በፅሁፍ ይሆናል ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ውክልናውን የሚቀበለው ተወካይ መቀበሉን በግልፅ ወይም በዝምታ ሊፈጽም ይችላል። ውክልናውን መቀበል የማይፈልግ ከሆነ ደግሞ በግልፅ እንደማይቀበል በመግለፅ ከኃላፊነት እራሱን ማግለል ይችላል። ስለሆነም ተወካይ ውክልናውን የማይቀበል መሆኑን ከወዲሁ በግልፅ ካላስታወቀ በስተቀር የተወከለበት ነገር ከሚያካሂደው ሥራ ጋር ግንኙነት ያለው ጉዳይ መሆኑ በግለፅ የታወቀ ከሆነ፣ ወይም ከሙያ ሥራው አመራር ጋር የሚመሣሠል ጉዳይ ከሆነ፣ ወይም ይህንን የመሠለውን ጉዳይ ለመሥራት ፍቃደኛ ለመሆኑ በአደባባይ ገልጾ ሀሳብ በማቅረብ አስታውቆ እንደሆነ ውክልናውን እንደተቀበለ ይቆጠራል[238]።

በመሠረቱ አንድ ሰው ለቀረበለት ውል ምላሽ ሳይሰጥ ዝም ቢል የቀረበለትን የውል ሀሳብ እንደተቀበለ እንደማያስቆጥርበት(silence doesn’t amount to exceptance) የፍትሐብሔርሕግ[239] ይደነግጋል፡ ፡ ነገር ግን የውክልና ጉዳይ እንደ ልዩ ሁኔታ የሚወሠድ ስለሆነ እና እንደ ልዩ ውል ስለሚቆጠር አንድ ሰው በቀረበለት የውክልና ውል ላይ ግልፅ የሆነ ያለመቀበል ሃሣብ እስካላቀረበ ድረስ ዝምታው የውክልናውን ውል እንደተቀበለ የሚያስቆጥርበት መሆኑን የፍ/ብ/ህ//ቁ 2201 (2) ደንግጓል። ስለዚህ የውክልናው ውል ውክልናውን ባቀረበውና በተቀበለው ሰው መካከል ይመሠረታል ማለት ነው።

---

[237] ፍ/ብ/ህ/ቁ.2200

[238] ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2201

[239] ፍ/ብ/ህ/ቁ.1682

ውክልናው የሚሰጠው ለብዙ ሰዎች ከሆነ ግን የውክልና ስልጣኑን ሁሉም ባንድነት መቀበላቸው ካልተረጋገጠ በቀር ውክልናው እንደጸና አይቆጠርም[240]። በመሆኑም ውክልና ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ይቋቋማል ማለት ነው።

### 6.7.4 የውክልና ወሰን

ውክልናው ሲቋቋም የውክልናው ወሰን እስከምን ድረስ ነው የሚለው ደግሞ በፍትሃ ብሄር ህጉ አንቀፅ 2202 ላይ ተቀምጧል። በዚህም መሠረት የውክልናው ወሰን በውሉ ላይ በግልፅ ተጠቅሶ ካልተቀመጠ በስተቀር ለውክልናው የሚሰጠው ወሰን እንደ ጉዳዩ አይነት ይሆናል[241]። ወካዩ የውክልናውን ወሰን በውክልናው ውል ላይ በግልፅ ካስቀመጠ ደግሞ ወሰኑ በግልጽ በተቀመጠው መሠረት ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ ውክልናው ለአንድ ልዩ ጉዳይ ወይም ለእያንዳንዱ ጉዳዮች ወይም ለወካዩ ጉዳዮች ሁሉ ጠቅላላ ውክልና ሊሆን ይችላል (ፍ/ብ/ህ/ቁ 2202 (2)። ይህ ማለት አንድ ሰው ለአንድ ለተወሠነ ጉዳይ ብቻ ወይንም ለተለያዩ ከአንድ በላይ ለሆኑ ጉዳዮች ወይንም ለሁሉም ጉዳዮቹ ውክልና ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሰውን የውክልና ወሰን መሠረት በማድረግ ውክልናን ጠቅላላ ውክልና ልዩ ውክልና ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል።

### 6.7.5 የውክልና አይነቶች

#### 6.7.5.1 ጠቅላላ ውክልና

ጠቅላላ ውክልና ማለት በጠቅላላ አነጋገር የተደረገ ውክልና ሲሆን የአስተዳደር ሥራዎች ለመፈፀም ብቻ ለተወካዩ የሚሰጥ ውክልና ነው[242]። ይህ ማለት ወካይ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በዝርዝር ሳይገለፅ እንዲሁ በጠቅላላ አነጋገር ወክየዋለሁ የሚል ከሆነ ተወካዩ ከአስተዳደር ሥራዎች ውጭ የመሥራት ሥልጣን አይኖረውም ማለት ነው። ይህ ማለት ለተወካዩ በውክልና እንዲያከናውን የተሰጠው ተግባር በእለት ተእለት ከሚያከናውነው የግል ተግባሩ ጋር ግንኙነት ይኑረው አይኑረው መረዳት ካልተቻለ የሚሰጥ ውክልና ማለት ነው።ተወካዩ የተወከለበት ነገር ከማያካሂደው ነገር ግንኙነት ካለው ግን ተወካዩ ከአስተዳደር ሥራዎች ይልቅ ከራሱ የዕለት ስራዎች ጋር የሚገናኘውን ሥራ ነው መስራት ያለበት። ስለዚህ ተወካዩ የሚተገብረው ሥራ ወካዩ ከወከለው ጉዳይ ጋር ያለውን ግንኙነት መረዳት ካልተቻለ ተወካዩ በተሠጠው ሥልጣን መሥራት የሚችለው የአሰተዳደር ስራዎችን ብቻ ነው የሚሆነው፡

---

240 ፍ/ብ/ህ/ቁ.2218/1

241 ፍ/ብ/ህ/ቁ 2202 (1)

242 ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2203

የአሰተዳደር ሥራ ተብለው በፍትሀ ብሄር ህጉ የተቀመጡት ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው[243]።

- ✓ የወካዩን ሀብት የማስቀመጥ ፣ የመጠበቅ ሥራ
- ✓ ከሶስት አመት ለማያልፍ ዘመን የማከራየት
- ✓ በብድር የተሰጠውን ሀብት የመሰብሰብ
- ✓ ከሀብቱ የሚመጣውን ገቢ ተቀብሎ የማስቀመጥና
- ✓ ለተከፈሉ ዕዳዎች ደረሰኝ የመሥጠት ሥራዎች ናቸው።

በመሆኑም በጠቅላላ ውክልና የውክልና ሥልጣን የተሰጠው ተወካይ ከላይ ከተዘረዘሩት ሥራዎች ውጭ የመሥራት ወይንም የመከወን ሥልጣን የለውም። ይህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ በብዙ ሰዎች ዘንድ በአግባቡ ያለመረዳት ይስተዋላል። ስሙ ጠቅላላ ውክልና ስለሚል ብቻ ለተወካይ አጠቃላይ የወካዩን ተግባሮች የመከወን ሥልጣን የሰጠው አድርጐ የመረዳት ሁኔታ አለ። ያላግባብ መረዳት ብቻም ሳይሆን ወካዮች አጠቃላይ ሥራዎችን መወከል ሲፈልጉ ጠቅላላ ውክልና ወይም ሙሉ ውክልና ብለው የውክልና ስልጣን የመስጠት ሁኔታዎች ያጋጥማሉ። ጠቅላላ ውክልና ግን ሰዎች በሚያስቡት ወይም በሚገነዘቡት መልኩ ሳይሆን ህጉ ባስቀመጠው መሠረት የአስተዳደር ስራዎችን ብቻ የሚያካትት ነው። ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሱት የአስተዳደር ሥራዎች ውጭ ያሉ ሥራዎችን ማሠራት የፈለገ ወካይ ስራዎቹን በልዩ ውክልና መሠረት ለተወካይ ማስተላለፍ አለበት ማለት ነው።

### 6.7.5.2 ልዩ ውክልና

ልዩ ውክልና ማለት አንድ ሰው ከአስተዳደር ሥራ ውጭ ያሉ ሥራዎችን በወኪሉ ለማሠራት የሚያስችለው የውክልና አይነት ነው[244]። ስለሆነም በልዩ ውክልና የውክልና ስልጣን የተሰጠው ተወካይ ተለይተው በዝርዝር የተመለከቱ ጉዳዮችንና እንደ ጉዳዩ አይነትና እንደ ልማድ አሰራር ከጉዳዩ ጋር ተከታታይነትና ተመሣሣይነት ያላቸው ነገሮችን ማከናወን ይችላል ማለት ነው[245] ። ከዚህ ባሻገር አንድ ተወካይ ልዩ የውክልና ሥልጣን ከሌለው በስተቀር ሊፈጽማቸው የማይችላቸው ተግባራቶች አሉ፡ ፡ እነሱም[246] ፡-

- ✓ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን መሸጥ ወይም አሲይዞ መበደር
- ✓ ካፒታሎችን በአንድ ማህበር ውስጥ ማስገባት
- ✓ የሀዋላ ሰነዶችን መፈረም (sign bill of exchange)
- ✓ መታረቅ

---

[243] ፍ/ብ/ሀ/ቁ. 2204)

[244] ፍ/ብ/ሀ/ቁ 2205(1)

[245] ፍ/ብ/ሀ/ቁ 2206/1/)

[246] በፍ/ብ/ሀ/ቁ 2205(2)

- ✓ ለመታረቅ ውል መግባት
- ✓ ስጦታ ማድረግ ወይም
- ✓ በአንድ ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ መከራከር ናቸው።

ስለዚህ ተወካይ ያለ ልዩ ውክልና ሥልጣን ከላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን መፈጸም የለበትም። ነገር ግን ከተሠጠው የውክልና ሥልጣን ውጭ አልፎ ተግባሮቹን ቢፈጽም የፈፀመውን ተግባር ወካዩ ካላፀደቀው ወይም በሥራ አመራር መሠረታዊ ደንብ መሰረት ካልሆነ በቀር ወካዩን አያስገድደውም [247]። ይህ ማለት ወካዩ ተወካዩ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በሰራቸው ተግባራቶች ተጠያቂ አይሆንም ማለት ነው። በፍትሐ ብሔር ህጉ እንደተደነገገው በሥራ አመራር (unauthorized agency ) መሠረታዊ ደንብ ማለት[248] አንድ ሰው የነገሩን ሁኔታ እየተገነዘበ ይህን እንዲፈፅም ሳይገደድ፤ የወኪልነትም ሥልጣን ሳይሠጠው የሌላውን ሠው ጉዳይ በመምራት ሥራ ውስጥ ገብቶ ጉዳዩን ያካሄደ እንደሆነ የሥራ ጉዳይ አመራር እንዳለ ይቆጠራል። ለምሳሌ አበበ እና በላይ ጎረቤቶች ናቸው አበበ በሌለበት ሀይለኛ ዝናብ እየጣለ ነው። ወደ አበበ ቤት ጎርፍ እንዳይገባ በማሰብ በላይ ለውሃ መውረጃ ከአበበ ግቢ ውስጥ ቦይ ቢያስቆፍር በላይ ስራውን የሰራው አበበ ሳይወክለው ቢሆንም እንኳ የስራ ጉዳይ አመራር እንዳለ ይቆጠራል።

ይሁንና እነዚያ በተወካዩ ከስልጣን ውጭ የተደረጉ ተግባራቶች ተቀባይነት እንዲኖራቸው አንድም ከላይ በተገለጸው መልኩ በሥራ አመራር መሠረታዊ ደንብ ሥር መሆን አለባቸው ወይንም ድርጊቶቹ በወካዩ መጽደቅ ግድ ይላቸዋል ማለት ነው። ሆኖም ግን ከውክልና ስልጣን ውጭ የተደረጉ ተግባሮችን በወካይ የማፅደቅ ሁኔታ እንዳንንድ ጊዜ በግዴታ የሚሆንበትም ሁኔታዎች አሉ። ይህም ፡-

1. ተወካዩ በውክልና ከተሰጠው ሥልጣንና ወካዩ ከሰጠው ትዕዛዝ ውጭ በማለፍ ሠርቶ የተገኘ ቢሆንም ስራውን የሠራው በቅንልቦና ሆኖ ሲገኝ ወካዩ ሥራውን የማጽደቅ ግዴታ አለበት።[249]
2. ወካዩ የሥራውን አረማመድና መልካም አካሄድ ሁኔታ ቢረዳው ኖሮ ለተወካዩ የሥራውን የሥልጣን ወሰን ማስፋት የሚያስፈልግ መሆኑን መገመት ይችል ነበር ተብሎ በአዕምሮ ግምት የሚታመን ሆኖ ሲገኝም ወካዩ ከስልጣን ውጭ የተደረገውን ተግባር የማፅደቅ ግዴታ ይኖርበታል [250]። ነገር ግን ተወካዩ ያለተፈቀደለትን ሥራ በገዛ አሳቡ ከመፈፀሙ አስቀድሞ የሥልጣኑን ወሰን እንዲያሰፋለት ወካዩን ለመጠየቅ የሚያስችለው ምቹ መንገድ እያለው ፈቃድ ሳይጠይቅ ቸል ብሎ በራሱ አሳብ ስራውን ሠርቶ እንደሆነ ወይም አስፈላጊ ተግባሩን

[247] በፍ/ብ/ህ/ቁ 2205(2)

[248] በፍ/ብ/ህ/ቁ 2257-2265

[249] ፍ/ብ/ህ/ቁ.2207(1)

[250] ፍ/ብ/ህ/ቁ2207(2)

ከፈፀመ በኋላ ለወካዩ ሳያስታውቀው ቀርቶ እንደሆነ ያለፈቃድ የፈፀምኩትን አጽድቅልኝ ብሎ ወካዩን የመጠየቅ መብት አይኖረውም።[251]

➢ የተወካይ ግዴታዎች

✓ ጥብቅ የሆነ ቅንልቦና መኖር /ቅን የመሆን ግዴታ/[252]

ተወካዩ ውክልናውን በመጠቀም ለወካዩ በሚሠራቸው በማንኛውም እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለወካዩ የተሻለ ጥቅም ሲል በቅንነት ሊሠራ ይገባዋል። ተወካዩ የሚሠራቸው ድርጊቶች ሁሉ ወካዩን ተጠያቂ የሚያደርጉ ስለሆነ ተወካዩ 'እኔ ምን ቸገረኝ እኔ አልጠየቅ፣እኔ አልጐዳም በሚል ስሜት ሥራውን በፍጹም መሥራት የለበትም። የራሱን ጉዳይ ሲሰራ ሊወስደው የሚችለውን ጥንቃቄና ጭንቀት ለወካዩም በሚሠራበት ጊዜ ማድረግ አለበት።

በስነ ሕግ ቅን ልቦና ማለት በአስተያየት ወይም ግላዊ አመለካከት እውነታነት ወይም ውሸትነት ላይ፣ ወይም በአንድ ተግባር ትክክለኛነት ወይም ህገወጥነት ላይ ያለ እዕምሯዊ ወይም ግብረ ገባዊ ቅንነት ወይም ፅኑ እምነት ነው።

የውክልናውን ሥልጣን የሚያስቀሩትን ምክንያቶች ወይም በውክልና ውስጥ ካሉ ነገሮች የተወሰነውን ማሻሻል አስፈላጊ የሚሆንበትን ምክንያት ለወካዩ ማሳወቅ አለበት[253]። አንድን ሥራ ለመሥራት በውክልናው ውስጥ ያልተካተተ ነገር እያለ እንዲሁም ነገሩን ለመሥራት ያልተካተተው መካተት ያለበት እንደሆነ እያወቀ ለወካዩ ሣያሣውቀው ቀርቶ ሥራው ሳይሰራ ቢቀር ተወካዩ ቅን ልቦና ይጐለዋል ማለት ነው። ነገር ግን ተወካይ ሊቆጣጠረው ባልቻለው ምክንያት ግዴታውን መፈፀም ሳይችል ቢቀር ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። ቅንልቦና ተወካይ እንደሚሠራቸው ሥራዎች የተለያየ ሊሆን ስለሚችል የቅንልቦና መኖሩንና አለመኖሩን ለማወቅ ተወካዩ የሚሠራቸውን ሥራዎች ባህሪ መረዳት መቻል ያስፈልጋል።

1. ታማኝነት/ታማኝ የመሆን ግዴታ[254]

ታማኝ የመሆን ግዴታ የተወካዩን ከፍተኛ የሥነ-ምግባር ደረጃ የሚጠይቅ ነው። ተወካዩ ሥራውን በሚፈፅምበት ወቅት ሙሉ በሙሉ ለወካዩ ጥቅም ሊሠጥ በሚችልበት መንገድ ብቻ መሆን አለበት። ስለሆነም ተወካዩ ወካዩ ሳያውቅ በውክልናው በሚሠራው ሥራ አንድም ጥቅም ለግሉ ማዋል ወይም መውሰድ የለበትም። ስለዚህ ተወካዩ የወካዩን ጥቅም ሊጎዳ ወይም ሊቀንስ የሚችል ተግባር ከፈጸመና ጥቅሞችን ለግሉ ከወሰደ የታማኝነት ግዴታውን አልተወጣም ወይም ታማኝ አይደለም ማለት ነው።

---

[251] ፍ/ብ/ህ/ቁ 2207(3)

[252] ፍ/ብ/ህ/ቁ 2208(1)

[253] ፍ/ብ/ህ/ቁ.2208 (2)

[254] ፍ/ብ/ህ/ቁ.2209/1/

2. ሚስጥር ጠባቂነት /ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ/[255]

ተወካዩ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከተለያየ አቅጣጫ የሚያገኛቸውን መረጃዎች መጠቀም ያለበት ወካዩን በማይጎዳ መልኩ መሆን አለበት።

3. የሂሳብ አያያዝና ሂሣብ የማቅረብ ግዴታ

ይህ ግዴታ ከተወካዩ ግልፅነት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ተወካይ ስራውን በሚሰራበት ወቅት ከስራው ጋር የተያያዘ ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ በተወካዩ የሚሰበሰብም ገንዘብ ሊኖር ይችላል፡፡ በመሆኑም ተወካይ የሚሰበስባቸው ገንዘቦች ለወካይ የማይገቡት እንኳ ቢሆኑ ተወካይ ሥራውን በሚሠራበት ወቅት ገቢ ያደረገውን ገንዘብና ትርፍ ሂሣብ መያዝ አለበት።፡፡ የተሰበሰበውን ገንዘብም ለራሱ ጥቅም ማዋል የለበትም፡፡ ይህን ማድረግ ሲገባው ታዲያ ተወካዩ ገንዘቡን ለራሱ ጥቅም ያዋለ እንደሆነ ገንዘቡን ከወሠደበት ቀን አንሥቶ እስከነወለዱ ለወካይ እንዲከፍል ይገደዳል[256]፡፡ ከዚህም ባሻገር ደግሞ ተወካዩ ወካዩ በጠየቀው ጊዜ የስራውን አካሄድ መግለጫና ሂሳብ በየጊዜው የማቅረብ ግዴታ አለበት [257]

4. ታታሪነት /ትጉህ የመሆን ግዴታ/

አንድ ተወካይ ስራውን የሚሰራው ሙያዊ ብቃቱን ተጠቅሞ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የወካዩን ጉዳይ ለማሥፈፀም ተወካዩ ያለውን አስፈላጊ ሙያዊ ብቃት አሟጦ መጠቀም እንዳለበት የፍትሃብሄር ህጉ ይደነግጋል። በሌላ አነጋገር ለጉዳዮች መሳካት ተወካዩ ትኩረት መሥጠት አለበት ማለት ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2211 (1) እንዳስቀመጠው ተወካዩ በውክልና ሥራው ላይ በሚገኝባቸው ጊዜዎች ሁሉ በውክልናው የተሠጠውን አደራ አንድ መልካም የቤተሠብ አባት ቤተሰቡን ለመጠበቅ እንደሚያደርገው ሁሉ በትጋትና በጥንቃቄ መጠበቅ አለበት። ብዙ ጊዜ የተወካዩ ታታሪ የመሆን ሁኔታ ተወካይ ከወካዩ ጋር ባለው ቅርበት፣ ዝምድና ወይም በሚከፈለው ክፍያ ይወሰናል። ያም ሆነ ይህ ግን ተወካዩ አሰፈላጊ የሆነ ትጋትና ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ህጉ ደንግጓል። በመሆኑም ተወካዩ በማታለል በሠራው ሥራ ብቻ ሣይሆን ሥራውን በሚያከናውን ጊዜ በፈፀማቸው ጥፋቶችም ተጠያቂ እንደሚሆን በፍትሃ ብሄር ህጉ አንቀፅ 2211(2) ላይ በግልፅ ተቀምጧል። ነገር ግን የውክልናውን ሥልጣን በነፃ (ያለክፍያ) የተቀበለ ተወካይ የወካዩን ጉዳዮች እንደራሱ ጉዳይ አድርጐ ተጠንቅቆ እስከሰራ ድረስ በተፈጠሩት ጥፋቶች ተጠያቂ አይሆንም (ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2211(3))፡፡ እዚህ ጋርም ቢሆን

---

[255] ፍ/ብ/ህ/ቁ 2209(2)

[256] ፍ/ብ/ህ/ቁ 2210

[257] ፍ/ብ/ህ/ቁ.2213/1/

ተወካዩ ለሚሠራው ሥራ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ለሚፈጠሩ ጥፋቶች ተጠያቂ መሆኑ እንደማይቀር መረዳት ይቻላል።

5. ስራን በራስ የመፈፀም ግዴታ/obligation to act personally/

የተወካይን ኃላፊነቶችና ግዴታዎችን ስንመለከት ሌላው መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ውክልናን ለ3ኛ ወገን የማስተላለፍ ጉዳይ ወይም በተለምዶ የውክልና ውክልና ተብሎ የሚጠራው ጉዳይ ነው። ተወካይ የተሰጠውን የውክልና ስልጣን ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ወይንም ሌላን መወከል የሚችለው በፍ/ብ/ህ/ቁ 2215 በተቀመጠው መሰረት ብቻ ነው። ተወካይ ውክልናውን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚችለው ወካዩ ፈቅዶለት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ወካዩ ካልፈቀደለት ግን የተወከለበትን ሥራ እራሱ መፈፀም እንዳለበት በህጉ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ይህን ሳይከተል ሌላ ሠው ተክቶ ያሠራ እንደሆነ ግን ለተሠሩት ሥራዎች በሙሉ ተጠያቂ የሚሆነው ራሱ ተወካዩ ብቻ ነው[258]። ሆኖም ተወካዩ የተሠጠውን የሥራ ጉዳይ እንዳይፈፅም የሚያግድ ድንገተኛ መሰናክል ቢገጥመውና የወካዩንም ሥራ መስራት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ብሎም ሁኔታውን ለወካዩ ለማሣወቅ የማያስችል ሁኔታ ላይ ከሆነ ሥራውን ሌላ ሠው ተክቶ ማሠራት ይኖርበታል። ይህን በማድረጉም ያለወካዩ ፍቃድ ሌላ ሰው ወክለሀል ተብሎም አይጠየቅም[259]

።

- የወካይ ግዴታዎች

1. ለተወካዩ ደሞዝ /የድካም ዋጋ/የመክፈል ግዴታ

አንድ ወካይ ለተወካይ ደሞዝ የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ከተወካዩ ጋር ስለድካም ዋጋ/ ደሞዝ/ተዋውለው ከሆነ ነው። ማለትም ተወካዩ ስራውን ከማከናወኑ በፊት ደሞዝ እንደሚከፈለው ተነግሮት ከነበረ ወካዩ ያን እከፍልሃለሁ ያለውን ክፍያ መክፈል ግዴታ ይሆንበታል ማለት ነው። ይህም በፍትሀብሔር ህጉ ቁጥር 2219 ላይ በግለፅ ተቀምጧል። ነገር ግን ተወካዩ በውክልናው እንዲያከናውን የተሠጠውን ተግባር ያከናወነው በግል ሙያው ውስጥ ከሆነ ወይንም የሰራው ሥራ በልማዳዊ አሠራር መሠረት ክፍያ የሚያስፈልገው ከሆነ በውሉ ላይ ለተወካዩ ክፍያ እንደሚከፈለው ባይገለፅም እንኳን ወካይ ለተወካይ ይህን የድካም ዋጋ /ደሞዝ/ መክፈል ግዴታ ይሆንበታል። በዚህ ጊዜም የክፍያው መጠን በታወቀው የሥራ ዋጋ ልክ ወይም በልማዳዊው አሠራር መሠረት ይሆናል [260]።

ከዚህ ውጭ ግን ወካይ የሥራው ጉዳይ መልካም ወይም ጥሩ ውጤት አላመጣም በሚል ምክንያት ለተወካዩ ሊከፍለው የሚገባውን ገንዘብ አልከፍልም ለማለት አይችልም። ይሁን እንጅ በተወካዩ ግዴታ

---

[258] የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2216(1)

[259] የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2215(3)፥

[260] ፍ/ብ/ሕግ/ቁ.2220(1)እና (2)

ላይ እንዳየነው ተወካይ በራሱ ጥፋት በወካይ ላይ ለደረሰ ጉዳት ለወካዩ የሚከፍለው ክፍያ አለ። ታዲያ በዚህ ጊዜ ወካዩ ከተወካዩ የሚቀበለውን ገንዘብ እና እሱ ለተወካዩ ሊከፍለው ያሰበውን ገንዘብ (የተወካይ ደሞዝንና ተወካይ ላወጣቸው ወጭዎች የሚከፈሉትን ገንዘቦች) ማቻቻል ይችላል። ለምሣሌ ተወካዩ ላጠፋው ጥፋት ለወካዩ 5000 ብር መክፈል ያለበት ቢሆንና ወካዩ ለተወካዩ የሚከፍለው ገንዘብ 8000 ብር ቢሆን 5000 ብሩን አቻችሎ ቀሪውን 3000 ብር ሊሠጠው ይችላል ማለት ነው [261]።

2. ወጭ የመሥጠትና የማወራረድ ግዴታ

ተወካይ በውክልና ስልጣን የተሠጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ወይንም ተግባሮቹን ለማከናወን ወጭ ማውጣት ያስፈልገው ይሆናል። ስለዚህ ወካዩ ለሥራው ማስኬጃና ማከናወኛ የሚሆን ወጭ ተወካዩ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ወይንም አስቀድሞ ሊሠጠው ይገባል። ከዚህ ውጭም የተሠጠውን ሥራ በጥሩ ሁኔታ ለመሥራት ሲል ተወካይ ያወጣቸውን ሌሎች ወጭዎችም ወካይ ለተወካይ መክፈል ይኖርበታል [262]።

3. ተወካይን ከግዴታ ነፃ ማውጣት

ተወካይ በወኪልነቱ ለወካዩ ጥቅምና ለውክልናው ሥራ መልካም አካሄድ ሲል ከገባው የውል ግዴታ ወካይ ነፃ ሊያወጣው ይገባል። ይህ ማለት ተወካይ በተሠጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት ተግባሮችን በሚያከናውንበት ወቅት ለወካዩ ጥቅምና ለውክልናው ሥራ መልካም አካሄድ ሲል የውል ግዴታ ሊገባ ይችላል ወይንም ውል ሊዋዋል ይችላል። ውሎቹን ደግሞ መፈፀም ያስፈልጋል። ስለዚህ ወካይ ውሎቹን በመፈፀምም ይሁን በሌላ መንገድ ተወካይን ከነዚህ አይነት የውል ግዴታዎች ነፃ ማውጣት አለበት (የፍትሐብሄር አንቀፅ ቁ 2222 (1)።

4. ለተወካይ ኪሣራ መክፈል (የካሣ ክፍያ ግዴታ)

አንድ ተወካይ በውክልና ስልጣን መሠረት የተሠጠውን ተግባር ሲያከናውን አደጋ(ለምሳሌ የአካል ጉዳት) ሊደርስበት ይችላል። በመሆኑም ይህ የደረሰበት አደጋ የተከሠተው በራሱ ጥፋት እስካልሆነ ድረስ ወካዩ በተወካዩ ላይ ለደረሠው አደጋ ካሣ ወይንም ኪሣራ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል። ነገር ግን ተወካዩ በራሱ ጥፋት ለደረሰበት አደጋ ወካዩን ኪሣራ ወይንም ካሣ የመጠየቅ መብት የለውም።[263]

6.7.6 **የጥቅም ግጭት** (conflict of interest)

በወካይ ተወካይ ሂደት ውስጥ የጥቅም ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ተወካይ በተሠጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት የወካይን መብት በማስጠበቅና የራሱን የጥቅም በማስጠበቅ መካከል ግጭት ሊፈጠር

---

[261] ፍ/ብ/ሕግ/ቁ 2223(1) እና (2)

[262] ፍ/ብ/ሕግ/ቁ 2221(1) እና (2)

[263] የፍ/ብ/ሕግ/ቁ 2222 (2)

ይችላል። የፍ/ብ/ህ/ቁ 2187(1) እንደሚያብራራው ተወካይ ከ3ኛ ወገን ጋር በፈፀመው ውል ምክንያት የወካዩና የተወካዩ ጥቅሞች የሚጋጩ የሆኑ እንደሆነና ይህን ውል የፈረመው 3ኛ ወገን ይህን ሁኔታ ያወቀና ሊያውቀውም የሚገባ የሆነ እንደሆነ በወካዩ ጥያቄ መሠረት ይህ በተወካይና በ3ኛ ወገን መካከል የተፈፀመው ውል ሊፈርስ ይችላል። እዚህ ጋር ተወካይ ከ3ኛው ወገን ጋር የፈፀመው ውል ሲባል ተወካይ ከወካይ ባገኘው የውክልና ሥልጣን መሠረት ከ3ኛ ወገኖች ጋር የገባቸውን ውሎችን ለማመልከት ነው። ወካዩም ከላይ የተገለፀውን አይነት የጥቅም ግጭት መፈጠሩን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ውሉን ለማፍረስ አሳቡን ማስታወቅ እንዳለበት የፍ/ብ/ህ/ቁ 2187(2) ይደነግጋል።

በዚህም መሠረት ወካዩ ውሉን የማፍረስ አሳቡን ቢያስውቅና ከተዋዋዮቹ መካከል አንዱ ከተወካዩ ወይም ከ3ኛው ወገን አንዳቸው የወካዩን ማስታወቂያ ከተቀበለ ወዲህ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ውሉን የመቀጠል አሳቡን ቢያሳውቅና ከተዋዋዮቹ መካከል አንዱ ማለትም ከተወካዩ ወይም ከ3ኛው ወገን እንዳቸው የወካዩን ማስታወቂያ ከተቀበለ ወዲህ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ውሉን የመቀጠል አሳቡን ያልገለፁ እንደሆነ ውሉ ይፈርሳል። እሱም የጥቅም ግጭት መኖሩ ተረጋግጦ 3ኛው ወገንም ይህን የጥቅም ግጭት ያወቀው መሆኑ ሲረጋገጥና ወካዩ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2187(2) መሠረት የውል መፍረስ ሃሳቡን ቢያሳውቅ እንዲሁም በፍ/ህ/ቁ 2187(3) መሠረት 3ኛው ወገን የውሉን መቀጠል መፈለጉን ቢያሳውቅ የወካዩንና የ3ኛው ወገን ፍላጐት እንዴት እኩል ማስኬድ ይችላል የሚለው ጉዳይ ነው። በዚህ አይነት ሁኔታ ነገሩ ወደ ፍርድ ቤት ነው ማምራት ያለበት። ፍርድ ቤቱም በፍ/ብ/ህ/ቁ 2187(1) መሠረት የነገሮችን ሁኔታ አይቶ ውሉን ሊያፈርሰው ይችላል። በህጉ አንቀጽ 2187ን ስንመለከተው የጥቅም ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ ውሉ መፍረስ አለበት ሳይሆን ሊፈርስ ይችላል ነው የሚለው ሃሳብ ተቀምጧል። ይህ ማለት ውሉ የመፍረስ ሆነ ያለመፍረስም ዕድል እንዳለው ያመለክታል። ነገር ግን ተወካዩ የራሱን ጥቅም አስቀድሞ የወካዩን ጥቅም የሚጐዳ ሥራ በመስራቱ የተጣለበትን ግዴታ አልተወጣም (በፍ/ብ/ህ/ቁ 2209) ማለት ነው። ስለሆነም ወካዩ ያጣቸውን ጥቅሞች በህጉ መሠረት የማግኘት መብት ይኖረዋል።

6.7.7 ከራስ ጋር መዋዋል (contract with oneself)

ከራስ ጋር መዋዋል ማለት ተወካይ ለራሱ ጉዳይ በመሥራትም ሆነ ወይም በሌላ ሰው ስም ለሌላ ሰው ጉዳይ ለመሠራት ውሉን ከራሱ ጋር ሲያደርግ ነው[264]። ይህ ማለት ከራስ ጋር መዋዋል በሁለት መልኩ ሊፈጠር ይችላል።

1ኛ አንድ ወካይ ተወካዩን የሆነ ዕቃ እንዲሸጥለት ውክልና ቢሰጠውና ያን ዕቃ ተወካዩ ራሱ ቢገዛው ተወካዩ ከራሱ ጋር የሺያጭ ውል ተዋዋለ ማለት ነው።

[264] ፍ/ብ/ቁ.2188 (1)

2ኛ አንድ ሰው ለሁለት ወካዮች ተወካይ ቢሆን ማለትም ከሁለቱም ወካዮች የውክልና ስልጣን ቢያገኝና አንድኛው ወካይ የሆነ ዕቃ እንዲሸጥለት ቢያዘው ያኛው ወካይ ደግሞ ተመሣሣይ ዕቃ እንዲገዛለት ቢያዘው ያኛው ሸጥልኝ ያለውን ለዚህኛው ወካይ ቢሸጥለት ለሁለቱም ተወካይ ራሱ ስለሆነ ውሉን ከራሱ ጋር እንደተዋለለ ይቆጠራል ማለት ነው። ስለዚህ በሁለቱም ሁኔታ ተወካይ ይህን ባደረገ ጊዜ ወካዩ ይህ ውል እንዲፈርስ ለመጠየቅ ይችላል ።

እዚህ ጋር ለምን ተወካይ ከራሱ ጋር የተዋዋለውን ውል ፈራሽ ማድረግ አስፈለገ የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። ይህ ውል እንዲፈርስ የሚፈለገው ተወካይ ከራሱ ጋር ሲዋዋል የጥቅም ግጭቶች ይፈጠራሉ ተብሎ ሰለሚገመት ነው። ህጉም ይህን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል በፍትሃብሔር ሕግ ቁጥር 2188 ውስጥ ይህን ሁኔታ ያካተተው። በዚህም ሂደት ውስጥ ወካዩ ያጣቸው ጥቅሞች ወይንም የደረሰ ጉዳት ካለ በውል ሕግ መሠረት ውል መፍረስን ተከትለው የሚመጡት ወጤቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ ማለት ነው።

### 6.7.8 የውክልና ስልጣንን አላግባብ መጠቀም

አንድ ተወካይ በተሰጠው የውክልና ስልጣን ሊሰራው ከሚገባው ተግባር ባሻጋር ሌላ ወካዩ እንዲሰራ የማይፈልገውን ተግባር ቢያከናውን ተወካዩ የተሰጠውን የውክልና ሥልጣን ያለአግባብ ተጠቅሟል ሊባል ይችላል። ይህ ደግሞ ተወካዩ የተጣለበትን አደራ በአግባቡ አለመወጣቱን ያሣያል። የተሰራውን ስራ በተመለከተ ደግሞ ወካዩ ተወካዩ የፈፀመውን ተግባር ማፅደቅ ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል [265]።

### 6.7.9 ጊዜው ባለፈበት የውክልና ሥልጣን መገልገል

አንድ ተወካይ የተሰጠው የውክልና ስልጣን ዘመን ካበቃ በኋላ ወይንም የውክልናው ሥልጣን ከተሻረ በኋላ በውክልናው ሥልጣን የሚገለገል ከሆነ ጊዜው ባለፈበት የውክልና ሥልጣን ተገልግሏል ለማለት ያስችላል። በተሻረ የውክልናው ስልጣን አማካኝነት የተሰራውን ስራ ደግሞ ወካይ ሊያፀድቀው ወይንም ሊሽረው ይችላል[266]።

### 6.7.10 ስለውክልና ሥልጣን መቅረት ወይም መቋረጥ

የውክልና ሥልጣን ከዚህ በታች በተቀመጡት ሶስት ምክንያቶች መሠረት ሊቀር ወይንም ሊቋረጥ ይችላል። እነሱም ፡-

#### 6.7.10.1 የውክልናው ሥልጣን በወካዩ መሻር

አንድ ወካይ ለተወካይ የሰጠውን የውክልና ሥልጣን በፈለገው ጊዜ መሻር እንደሚችል እንዲሁም ተወካዩ የውክልና ሥልጣኑን የተቀበለበትን የውል ፅሁፍ እንዲመልስለት ሊያስገድደው እንደሚችል

---

[265] ፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2190/1

[266] ፍ/ብ/ሕግ/ ቁ 2190/2/

የፍ/ብ/ህ/ቁ 2226(1) ደንግጓል። በሌላ መልኩ ደግሞ ይህን የውክልና ሥልጣንን በፈለገ ጊዜ የመሻር መብት ሊቃረን የሚችል ቃል በውላቸው ውስጥ ቢያካትቱ ቃሉ ፈራሽ እንደሚሆን በዚሁ የሕግ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ በግልፅ ተደንግጓል። ወካዩ የውክልና ሥልጣኑን ለመሻር ለተወካዩ ምንም አይነት በቂ ምክንያትም ማቅረብ ሆነ ቅድመ ማሥጠንቀቂያ መስጠት አይጠበቅበትም። መሻር በፈለገ ጊዜ ብቻ መሻር ይችላል። ነገር ግን የውክልናው ሥልጣን የተሠጠው በብዙ ወካዮች ከሆነ የውክልናውን ስልጣን በአንዱ ወኪል ብቻ ለመሻር በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የውክልናውን ስልጣን ለመሻር ሁሉም ወካዮች መስማማት አለባቸው። በቂ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ግን አንዱ ወካይ ብቻውን ተወካዩን ሊሽረው  እንደማይችል በፍ/ብ/ህ/ቁ 2228 ተደንግጎ ይገኛል። ስለሆነም በዚህ መልኩ የውክልና ሥልጣን ከተሻረ በውክልናው ስልጣን መሻር ምክንያት የውክልናው ሥልጣን ይቀራል ወይም ይቋረጣል ማለት ነው። ነገር ግን የውክልናው መሻር በተወካይ ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2227 መሠረት ወካዩ ለተወካዩ የጉዳት ኪሣራ መክፈል አለበት።

6.7.10.2 የተወካዩ የውክልና ስልጣኑን መተው

ተወካዩ የውክልና ሥልጣኑን ካልፈለገ በማንኛውም ጊዜ የውክልና ሥራውን ትቻለሁ ሲል ለወካዩ ማሳወቅ ይችላል። ለወካዩ ሳያሣውቅ ግን የውክልና ሥራውን መተው የለበትም። የተወካዩ የውክልና ሥራውን መተው በወካዩ ላይ ጉዳት የሚያደርስበት ከሆነ ተወካዩ በወካዩ ላይ ለደረሠው ጉዳት ኪሣራ መክፈል አለበት። ነገር ግን ተወካዩ የውክልናውን ሥራ መቀጠሉ በራሱ ላይ ከፍ ያለ ግምት ያለው ጉዳት የሚያደርስበት መሆኑ ከታወቀና ሥራውንም ለመቀጠል በፍፁም የማያስችል ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ስራውን በመተዉ በወካዩ ላይ ለደረሠው ጉዳት ኪሣራ ለመክፈል አይገደድም (የፍ/ብ/ሕግ/ቁ.2229)[267]

6.7.10. 3 የወካዩ ወይም የተወካዩ መሞት እና ከአካባቢ መጥፋት

ተወካይ የሞተ እንደሆነ፣ በስፍራው ያለመኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ለመሥራት ችሎታ ያጣ እንደሆነ ወይም ኪሣራ ደርሶበት በንግድ ኪሣራ ላይ መውደቁ የተረጋገጠ እንደሆነ የውክልና ሥልጣኑ ወዲያውኑ ይቀራል። ተወካዩ በስፍራው አለመኖሩ ተረጋገጠ የሚባለው ሰውየው ከአካባቢው እንደተሰወረ ወይንም እንደጠፋ ህጉ ላይ በተቀመጠው መሠረት ከተረጋገጠ ነው። ተወካዩ ለመሥራት ችሎታ አጣ የሚባለው ደግሞ ተወካዩ የአካል ጉዳት ደርሶበት ሥራውን መሥራት እንዳይችል ከሆነ ወይም በሕግ ጥላ ሥር ወድቆ (ታስሮ) ስራውን መሥራት የማይችል ሲሆን ነው። ነገር ግን እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ቢከሰቱም የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ እንዳይሆን የሚገልፅ ተቃራኒ ቃል በውክልና ውሉ ውስጥ ተቀምጦ ከነበረ ይህ በተወካዩ ላይ የደረሰው ክስተት የውክልና ሥልጣኑን ቀሪ ላያደርገው ይችላል268።

---

[267] የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2229

[268] የ/ፍ/ብ/ህ/ቁ 2230(1)

በሌላ በኩል ወካይ የሞተ እንደሆነ፣ በሥፍራው አለመኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ለመሥራት ችሎታ ያጣ እንደሆነ ወይም በንግድ መውደቅ ኪሣራ የደረሰበት እንደሆነ የውክልና ሥልጣኑ ወዲያውኑ ይቀራል። ይህ በእንዲህ እንዳለ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ቢከሰቱም የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ እንዳይሆን የሚገልፅ በውክልና ውሉ ውስጥ ተቃራኒ የውል ቃል ካለ ግን በወካዩ ላይ የደረሰው ክስተት የውክልና ሥልጣኑን ቀሪ አያደርገውም /የ/ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2232 (1)።[269] በዚህ ጊዜ ግን ተወካዩ ይህ ክስተት እስኪነገረው ድረስ ስራውን መቀጠል አለበት (ፍ/ብ/ቁ.2232 (2)።[270]

## ክፍል ስምንት

## አሰሪ እና ሰራተኛ ህግ

በ1919 ዓ.ም ሠራተኞች በሥራ ከሚደርስባቸው ጉልበት ብዝበዛ የተነሳ ካደረጉት የበርካታ አመታት ትግሎች ቡኃላ በሂደት ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት (ILO) ማቋቋም ተችሏል። በ1923 ኢትዮጵያ የዓም አቀፍ የሥራ ድርጅት አባል የሆነች ሲሆን ከወጡ ኮንቬንሽኖች ውስጥ 23ቱን አጽድቃለች። የሰራተኛው መብት ከማስከበር አንፃር መነሻ ተደርጎ የወጣ የኢትዮጵያ የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ ከአሰሪ ይልቅ ለሰራተኛው ያደላል ይባላል። አሁን በስራ ላይ ያለው የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች በቅጥር ጊዜና በሥራ ላይ አድልዖን ማስቀረት፣ የሴቶችን መብት ማጠናከር፣ የወል መብቶችን ማጠናከር፣ አሠሪና ሠራተኛን አሳታፊ ባደረገ ሁኔታ አለመግባባትን በተቋም ደረጃ መቆጣጠር በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የአሰሪ እና ሰራተኛ የስራ ግንኙነታቸውን በተመለከተ በሚኖረው አካሄድ በህግ የተደገፈ ስርአት መኖሩ ሰላም እና የተሻለ መተማመን ለመፍጠር ወሳኝ ነው። በመሆኑም ይህንን ግንኙነት ለመምራት የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም ተደንግጓል። በዚህ አዋጅም ከአሰሪ እና ሰራተኛ ግንኙነት ጋር የተያያዙ ግንኙነት ያላቸው ትርጓሜ ተቀምጧል ይኸውም አሠሪ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን ቀጥሮ የሚያሠራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሲሆን ሠራተኛ ደግሞ ከአሠሪው ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው። የስራ ግንኙነት የሚለየው ተጨባጭ የሰራተኛውና የአሰሪው ግንኙነት ምን እንደሆነ ለመለየት ነው። ማንኛውም ግለሰብ ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ

[269] ፍ/ብ/ህ/ቁ 2230(1)

[270] ፍ/ብ/ቁ/.2232 (2)

ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት ቢስማማ በሁለቱ መካከል የሥራ ውል አለ ለማለት ይቻላል።[271]

## 8.1 የሥራ ውል ምንነት እና ይዘቱ

የሥራ ውል ትርጓሜ በግልፅ ባይቀመጥም በይዘት ደረጃ የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ 1156/2011 ዓ.ም ትንታኔ አስቀምጧል። ማንኛውም ግለሰብ ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት ቢስማማ በሁለቱ መካከል የሥራ ውል ይመሠረታል፤ማናቸውም የሥራ ውል ተዋዋይ ወገኖች በውሉ መሠረት የሚኖራቸውን መብትና ግዴታ በማያጠራጥር አኳኋን በሚያውቁበት ሁኔታና በግልጽ መደረግ ይኖርበታል፤ ማንኛውም የሥራ ውል የሥራውን ዓይነትና ቦታ፣ ለሥራ የሚከፈለውን ደመወዝ መጠን፣ የስሌቱን ዘዴ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታና ጊዜ እና ውሉ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መያዝ ይኖርበታል፤የሥራ ውል ሕግን ወይም ሞራልን ተቃራኒ ለሆነ ሥራ አይደረግም፤ የሥራ ውል በሕግ በኅብረት ስምምነት ወይም በሥራ ደንብ ለሠራተኛው ከተሰጡት ጥቅሞች ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም። ከዚህ አረፍተ ነገር የምንረዳዉ የአሰሪ እና የሰራተኛ ግንኙነት በስራ ውል ማለትም የአሰሪ እና የሰራተኛ ግንኙነት በሚመራበት ውል መንገድን ተከትሎ መደረግ እንዳለበት ያመላክታል።

### 8.1.1 የአሰሪዎች ግዴታዎች

አሰሪ መብት እንዳለው ሁሉ ለአሰሪዉ የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ በአንቀፅ 12 ግዴታ እንዳለበት ግዴታ አስቀምጧል። በዚህ መሰረት

- ሥራ የመስጠትና ውሉ በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር መሣሪያና ጥሬ እቃ የማቅረብ ግዴታ
- ደሞዝና ሌሎች ክፍያዎችን የመፈጸም ግዴታ
- የሰራተኛውን ሰብአዊ ክብር፣ ከስራ ጋር የተያያዘ ጤንነትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ
- ሕጉ በሚያዘው መሰረት የተለያዩ ሁኔታዎችን በመዝገብ የመያዝ እና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ መዝገብ የማቅረብ ግዴታ፤
- የሠራተኛው ጤንነት እንዲመረመር በሕግ ወይም አግባብ ባለው አካል ግዴታ በሚጣልበት ጊዜ ለምርመራው የሚያስፈልገውን ወጪ የመቻል፤
- የስራ ዓይነቱን ዘመንና ሲከፈለው የነበረውን ደሞዝ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ለሰራተኛው የመስጠት ግዴታ እንዲሁም የአዋጁን፣ የህብረት ስምምነቱን፣ የስራ ውሉን ደንቦች እና በሕግ የሚተላለፉ መመሪያዎችን እና ትእዛዞችን የማክበር ግዴታዎች ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ።

---

[271] የአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ 1156/2011

### 8.1.2 የሰራተኞች ግዴታዎች

አሰሪ ግዴታ እንዳለበት ሁሉ ሰራተኛም በተመሳሳይ ሁኔታ በሚሰሩበት ቦታ እና በሚሰራው ስራ ግዴታ እናዳለባቸወ አዋጅ ደንግጓል። በመሆኑም

- በሥራ ውሉ ላይ የተመለከተውን ሥራ ራሱ የመሥራት፤
- በሥራ ውሉና በሥራ ደንቡ መሠረት በአሠሪው የሚሰጠውን ትእዛዝ የመፈፀም፤
- ለሥራው የተሰጡትን መሣሪያዎችና ዕቃዎች ሁሉ በጥንቃቄ የመጠበቅ፤
- ለሥራ ብቁ በሆነ የአእምሮና የአካል ሁኔታ በሥራ ላይ የመገኘት፤
- በራሱ ሕይወትና ጤንነት ላይ አደጋን ሳያስከትል በሥራው ቦታ በሕይወትና በንብረት ላይ አደጋ ሲደርስ ወይም አስጊ ሁኔታ ሲፈጠር ተገቢውን ዕርዳታ የመስጠት፤
- ራሱንም ሆነ የሥራ ባልደረቦቹን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የድርጅቱን ጥቅም የሚነካ ሁኔታ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ ለአሠሪው የማስታወቅ፤
- የአዋጁን ድንጋጌዎች፣ የኅብረት ስምምነትን፣ የሥራ ደንብንና በሕግ መሠረት የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር።

## 8.2 የሥራ ውል መቋረጥ

የሥራ ውል በተለያዩ ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል። ምክንያቶቹ ሕጋዊ ምክንያቶች ወይም ሕጋዊ ያልሆኑ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። የስራ ውል መቋረጥ ምክንያቶች ሁሉም በህግ ፊት እኩል ተቀባይነት የላቸውም።

| |
|---|
| ለምሳሌ<br>የስራ ውል ለማቋረጥ የአንድ ድርጅት ከሌላው ጋር መቀላቀል ወይም መከፋፈል ወይም የባለቤትነት መብት ወደ ሌላ መተላለፍ በቂ ምክንያት ሊባል አለመቻሉ ነው። |

የስራ ውል የማይቋረጥባቸውን ምክንያቶች ከሰራተኛው መሰረታዊ መብት ጋር የተያያዘ ሲሆን ማለትም አሰራተኛው በአሰሪው ላይ ቅሬታ ማቅረቡ ወይም አሰሪ ስለተከሰሰ በክሱ ላይ ተካፋይ መሆኑ፣ ሰራተኛው የሰራተኛ ማህበር አባል መሆኑ ወይም በማህበሩ ህጋዊ ተግበሮች ተካፋይ መሆኑ፣ሠራተኛው የሰራተኞች ተጠሪ ሆኖ ለመስራት መፈለጉ ወይም መስራቱ እና የሠራተኛው ብሔር፣ ፆታ፣ ሐይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዘር፣ ቀለም፣ የቤተሰብ ኃላፊነት፣ የዘር ሐረግ፣ እርግዝና፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ወይም ማኅበራዊ አቋም ምክንያት በማድረግ የሥራ ውልን ለማቋረጥ ተገቢ ምክንያቶች ሆነው ሊቆጠሩ የማይችሉ ናቸው።

### 8.2.1 የስራ ውል የሚቋረጥባቸው ዋና ዋና መንስኤዎች፡-

1. በአሰሪ ወይም፣
2. በሰራተኛው አነሳሽነት ወይም፣

3. በህግ በተደነገገው መሰረት ወይም በህብረት ስምምነት ወይም፣

4. በተዋዋይ ወገኖች በሚደረግ ስምምነት ነው።

በአሰሪ አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች

1. ችሎታ ማጣት፣

2. የሠራተኛው ፀባይ (ምግባር)፣

3. የድርጅቱ አሠራር፣

4.ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎትና ከድርጅቱ አመሠራረት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ብቻ መሠረት (ከድርጅቱ ድርጅታዊ አቋም ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ባላቸው ምክንያቶች ብቻ) ሊቋረጥ ይችላል።

የስራ ውል በህጉ በተደነገገው መሰረት የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች፡-

- ስራው ለተወሰነ ግዜ በስራ ውል ተዋውለው ያ የተወሰነው ግዜ ሲያልቅ እና የስራ ውል ሲቋረጥ፣
- ሰራተኛው ሲሞት፣
- ሰራተኛው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ጡረታ ሲወጣ/ሲገለል፣
- በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ድርጅቱ ለዘለቄታው ሲዘጋ፣
- ከፊል ወይም ሙሉ ዘላቂ የአካል ጉዳት በመድረሱ ምክንያት ወራተኛው ለመስራት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

የሥራ ውልን በስምምነት ስለማቋረጥባቸው ምክንያቶች፡-

- ✓ ተዋዋይ ወገኖች የሥራ ውላቸውን በስምምነት ማቋረጥ ይችላሉ። ሆኖም ሠራተኛው በሕግ የተሰጠውን መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት የሕግ ውጤት አይኖረውም። ለምሳሌ ሰራተኛው በማህበር የመደራጀት መብት እያለው ሌላ ማህበር ወይም ጭራሽ በማህበር መብቱን በመከልከል የሚደረጉ ስምምነቶች ለማድረግ እንዲስማሙ ማድረግ አይቻልም።
- ✓ የሥራ ውል በስምምነት መቋረጥ የሚጸናውና በሠራተኛውም ላይ አስገዳጅ የሚሆነው የተደረገው ስምምነት በጽሑፍ ሲሆን ነው። በስምምነት የሚደረግ የስራ ውል በቃል ሊፈፀም አይችልም።

ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ስለማቋረጥ

- ❖ በኅብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚቻለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው:-

- ✓ ሠራተኛው የሥራ ሰዓት ለማክበር የማይችልባቸው ሁኔታዎች ተብለው በኅብረት ስምምነት በሥራ ደንብ ወይም በሥራ ውሉ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጭ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው በስድስት ወር ውስጥ በጠቅላላው ለስምንት ጊዜ የስራ ሰዓት አለማክበር፤
- ✓ በአዋጁ ከተመለከቱት እረፍቶች እና ልዩ ልዩ ፈቃዶች ውጭ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው በስድስት ወር ውስጥ ለአምስት ቀናት ከስራ መቅረት፤
- ✓ በሥራው ላይ የማታለል ተግባር መፈፀም፤
- ✓ የራሱን ወይም የሌላ ሰው ብልጽግናን በመሻት በማንኛውም የአሠሪው ንብረት ወይም ገንዘብ አለአግባብ መጠቀም፤
- ✓ ሠራተኛው ሥራውን ለመሥራት ችሎታ እያለው የሥራ ውጤቱ ባለማቋረጥ በኅብረት ስምምነት ወይም በሥራ ደንቡ ወይም በሁለቱ ወገኖች መግባባት ከተወሰነው የምርት ጥራትና መጠን በታች ሲሆን፤
- ✓ እንደጥፋቱ ክብደት በሥራው ቦታ አምባጓሮ ወይም ጠብ አጫሪነት ተጠያቂ መሆን፤
- ✓ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና በጥፋቱም ምክንያት ለያዘው ሥራ ብቁ ሆኖ አለመገኘት፤
- ✓ በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ሥራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤
- ✓ በሠራተኛው ላይ ከሰላሳ ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የእሥራት ፍርድ ተወስኖበት ከሥራ ሲቀር፤
- ✓ ለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ለማቋረጥ ያስችላሉ ተብለው በኅብረት ስምምነት የተወሰኑ ሌሎች ጥፋቶችን መፈፀም፣
- ✓ አንድ አሠሪ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሥራ ውል በሚያቋርጥበት ጊዜ የሥራ ውሉ የሚያቋረጥበትን ምክንያትና ቀን በመጥቀስ ለሠራተኛው በጹሑፍ መግለፅ አለበት፣
- ✓ አንድ አሠሪ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሥራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መኖሩን ካወቀ ከሰላሳ የሥራ ቀናት በኋላ በይርጋ ይታገዳል፣
- ✓ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሠራተኛው የሥራ ውል እንዲቋረጥ ከመደረጉ በፊት ሠራተኛውን ከሥራ አግዶ ማቆየት ስለሚቻልበት ሁኔታ በኅብረት ስምምነት ሊወሰን ይችላል። ሆኖም የዕገዳው ጊዜ ከሰላሳ የሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም።

በማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ስለማቋረጥ

- ❖ የሠራተኛው የሥራ ችሎታ ማጣት ወይም ሁኔታን በሚመለከት የሚከተሉት ምክንያቶች ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ይሆናሉ:- ሠራተኛው የተመደበበትን

ሥራ ለማከናወን ችሎታው ቀንሶ ሲገኝ ወይም የሥራ ችሎታውን ለማሻሻል አሠሪው ያዘጋጀለትን የስልጠና ዕድል ባለመቀበሉ ምክንያት ሲሰራ የቆየውን ሥራ ለመቀጠል የሥራ ችሎታ የሌለው ሆኖ ሲገኝ ወይም ስልጠና ከተሰጠው በኋላ አስፈላጊውን አዲስ የሥራ ችሎታ ለመቅሰም የማይችል ሲሆን፤ ሠራተኛው በጤንነት መታወክ ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት በሥራ ውሉ የተጣለበትን ግዴታ ለመፈጸምለዘለቄታው የማይችል ሆኖ ሲገኝ፤ ድርጅቱ ወደሌላ ቦታ ሲዛወር ሠራተኛው ወደአዲሱ ቦታ ተዛውሮ ለመሥራት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር፤ ሠራተኛው የያዘው የሥራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲሰረዝና ሠራተኛውን ወደሌላ ሥራ ማዛወር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ነዉ። የተመለከተው ማንኛውም የሥራ ችሎታ ማጣት በኅብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር በየወቅቱ በሚደረግ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት መረጋገጥ አለበት።

❖ ድርጅታዊ አቋም ወይም የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የሚከተሉት ምክንያቶች የሥራ ውልን በማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ ይሆናሉ፤ ሠራተኞች የተሰማሩባቸው ሥራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና ለዘለቄታው የሚያስቆም የሥራ ውል መቋረጥ የሚያስከትል ሁኔታ ሲከሰት፤ አሠሪው በሚያመርታቸው ምርቶች ወይም በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተፈላጊነት መቀነስ ምክንያት የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በመቀዝቀዙ ወይም ትርፍ እየቀነሰ በመሄዱ የሥራ ውል ማቋረጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤ የሠራተኞችን ቅነሳ በሚያስከትል ምክንያት የሥራ ውሉ ይቋረጣል።

### 8.2.2 በሕገወጥ መንገድ የሥራ ውል ሲቋረጥ ያለው ህጋዊ ውጤት

የስራ ውል በተለያዩ ምክንያቶች ከተቋረጡ በኋላ እንደመቋረጡ አይነት የየራሳቸው የሆነ ውጤት አሉአቸው።

1/ ወደ ሥራ መመለስ

የስራ ውል በህገወጥ ምክንያት ከተቋረጠ አሰሪው ሰራተኛውን ወደቀድሞው ስራ መመለስ አለበት። ይሁንና ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው ግዜ አሰሪ እና ሰራተኛው መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ከሆነ የስራ ውሉ የተቋረጠው በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት ለኢንዱስትሪ ሰላም በማለት ማለትም ሰራተኛው ወደስራው ቢመለስ ሰራተኛው በሰላማዊ መንገድ ከአሰሪው ጋር አይሰራም በማለት ወደስራ ሳይመለስ ለህገውጥ መባረሩ ክፍያዎች እንዲፈጸሙ ትእዛዝ እና ውሳኔ ያሳርፋሉ።

2/ ክፍያዎች

በህገወጥ መንገድ የስራ ውል መቋረጥ ወቅት የሚከፈሉ ክፍያዎች በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ ከነስሌቱ ተቀምጧል። የስራ ስንብት ክፍያ ሰራተኛው በተለያዩ መንገዶች ሲታመም፣ የስራ ላይ ጉዳት ሲደርስበት፣ በስራ ላይ እያለ በአሰሪው ተቀንሶ ቢሆን፣ በአሰሪው ወይም በዛው ባለ ሰራተኛ ጥቃት

ደርሶበት እርምጃ ሳይወሰድ ሲቀር እና በህጉ በተዘረዘሩት ሌላ ምክንያቶች ይከፈላል። የአመት እረፍት ፈንታ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ ያልወሰደው የዓመት ፈቃድ ታስቦ በገንዘብ ይከፈለዋል። ካሳ እና ውዝፍ ደመወዝ ክፍያ ሲሆን ካሳ በተመከለከተ አንድ ሰራተኛ ከስራው ሲለቅ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሰሪው ስለሚሰጥ የስራውል ሲቋረጥ የካሳ ክፍያም በተጨማሪነት ሊያገኝ ይገባል።

## 8.3 በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳትና በህጉ የተቀመጡ መፍትሄዎች

የሥራ ቦታ ደህንነት እና የሠራተኞችን ጤና መጠበቅ የአሠሪም የሠራተኛም ግዴታ እንደሆነ ከአዋጁ አንቀጽ 13 (2-6) እና አንቀጽ 93 እንረዳለን። የሥራ ላይ ጉዳት ከደረሰ አሠሪው ለሠራተኛ ካሳ የመክፈል ግዴታ አለበት (strict liability) አንቀጽ 96 (1)። የሥራ ላይ ጉዳት ደርሶ አሠሪው ከተጠያቂነት የሚተርፈው ጉዳቱ የደረሰዉ ሠራተኛው ሆነ ብሎ በራሱ ላይ ጉዳት ካደረሰ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ሰራተኛው በአሠሪው አስቀድሞ በግል የተሰጡትን የደኅንነት መጠበቂያ መመሪያዎች መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ፤ ወይም አካሉን ወይም አዕምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በሥራ ላይ መገኘት።

| |
|---|
| ለምሳሌ ወ/ሮ አበበች በምትሰራበት አቶ አጥናፉ ድርጅት ካለው ፊትን፣፣ አካላትን ከሚጎዱ ኬሚካሎች እራሷን እንድጠብቅ የተሰጣትን የፊት እና የአካል መጠበቂያ ይሞቃል በሚል ወይም በሌላ ምክንያት ሳትጠቀም ቀርታ በአካሏ ላይ ጉዳት ቢደርስባት አቶ አጥናፉ ሊጠየቅ አይችልም። ምክንያቱም ለጥንቃቄ የሚሆኑ እቃዎችን አስቀድሞ በመስጠቱ ሀላፊነቱን ተወጥተዋል ። |

### 8.3.1 የስራ ላይ ጉዳት ምንነት

በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ የስራ ላይ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። ስለዚህ የስራ ላይ ጉዳት፣ በሽታ ወይም አደጋ ሊከሰት እንደሚችል በግልፅ ተደንግጓል።

### 8.3.2 በስራ ላይ የሚደርስ በአደጋ

በስራ ላይ ከሚደርስ በሽታ የስራ ላይ ጉዳት የሚለየው ማንኛውም ሠራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ሥራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የሚደርስበትን ጉዳት የመሚለከት ነው። አዋጁ ከዘረዘራቸው ውስጥ የሚከተሉትን ዐይነቶች ናቸው :-

- ❖ ሠራተኛው ከሥራ ቦታው ወይም ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭም ቢሆን የአሠሪውን ትዕዛዝ ሥራ ላይ ያውል በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት፤

❖ ሠራተኛው ከሥራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሳ ከሥራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ሥራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራው ቦታ ወይም በድርጅቱ ግቢ ውስጥ እያለ የደረሰበት ማንኛውም ጉዳት፤

❖ ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው ወደ ድርጅቱ ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም ድርጅቱ ለዚሁ ተግባር በተከራየውና በግልፅ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ማንኛውም ጉዳት፤

❖ ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በአሠሪው ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ወ.ዘ.ተ ናቸዉ.

## 8.4 በሥራ ምክንያት ስለሚመጣ በሽታ

በሥራ ምክንያት ስለሚመጣ በሽታ ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ከሚያከናውነው ሥራ አካባቢ የተነሳ በሽታው ከተከሰተበት ዕለት አስቀድሞ በነበረው የተወሰነ ጊዜ ውስጥ በፊዚካል፣ ኬሚካል ወይም ባዮሎጂካል ነገሮች አማካኝነት በሠራተኛ ላይ የሚደርስ የጤና መታወክ ነው። በልዩ ሁኔታ ሥራቸው በሽታውን ማጥፋት ብቻ ለሆነ ባለሙያዎች ካልሆነ በስተቀር በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ሥራ በሚከናወንበት አካባቢ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም። በተወሰነ የሥራ መስክ የተሰማሩ ሰዎችን ብቻ በተደጋጋሚ የሚይዝ በሽታ አንድ ሠራተኛን የያዘው እንደሆነና ይህም ሠራተኛ እንደዚህ ባለው የሥራ መስክ ተሰማርቶ የነበረ ከሆነና በሽታው መኖሩ በሐኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ በሥራ ምክንያት እንደመጣ በሽታ ይቆጠራል።

### 8.3.3 በስራ ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት

ሰራተኛ ከስራው አስቸጋሪነት እና አይነት የተነሳ የስራ ላይ የአካል ጉዳት ሊደርስበት ይችላል። የአካል ጉዳት ማለት የመስራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በስራ ላይ የደረሰ ጉዳትን ሲያመለክት የዚህም የጉዳት ውጤት ጊዜያዊ የአካል ጉዳት፣ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት፣ ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት እና የሞት ጉዳት የሚያስከትሉ ናቸው። ስለዚህ እንደየጉዳቱ አይነት በመጀመሪያ አሰሪ ለሰራተኛው ከመጀመሪያ እርዳታ ጀምሮ የህክምና መድሀኒት ቀዶ ጥገና እና ለካል ጉድለት ተተኪ መሳሪያ እስከመሟላት ድረስ ግዴታ አለበት። በቀጣይም ሰራተኛው ስራውን በጡረታ እስኪተው ወይም ከጉዳቱ እስኪድን ድረስ አሰሪ ለሰራተኛው በየግዜው የሚያስፈልገውን እገዛ ማድረግ ማለትም ደሞዙን አዋጁ ባስቀመጠው ስሌት መሰረት በየግዜው መክፈል ግዴታዉ ይሆናል። ሌላው የጉዳት ካሳ ሲሆን ይህም ከድንገተኛ እና በየግዜው ከሚደረገው ክፍያዎች ውጭ አሰሪው በሰራተኛው ወይም በስራው ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ተመመጣጣኝ ካሳ የሚከፍል ይሆናል።በአዋጁ መሰረት ክፍያው በኅብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ ድርጅቶች

ሠራተኞች የሚሰጠው የጉዳት ካሣ አሠሪው በገባበት የመድህን ዋስትና ወይም በጡረታ ሕግ መሠረት ይሆናል።

በአጠቃላይ ጎልማሶች ይህን የህግ ግንዛቤ በመዉሰድ መብታቸዉን ማስከበር፤ የሌሎችን መብት ማክበርና ማስከበር እንዲሁም የሀገር ሰላምና ደህንትን ማስጠበቅ በማስጠበቅ ሃላፊነታቸዉን ሊወጡ ይገባል።

## ዋቢ መጻሕፍት


1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢትየጵያ ፌዴራላዊ ሞክሪያሲያዊ ሕግ መንግስት፣ Proclamation of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia 1Year No.1 ADDIS ABABA – 21 August, 1995

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414,1996

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ አዋጅ ቁጥር 1156፣2011 ዓ.ም

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ዓ.ም

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2012 ዓ.ም

1954 ዓ.ም የወንጀል መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ

የኢትዮጵ ንጉሰ ነገስት የፍትሐብሔር ሕግ, 1952

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ, ፍትሕ ሚኒስቴር, የካቲት 25/2003 ዓ.ም

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ልዩ እትም 1

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1070/2010፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 24 አመትመ ቁጥር 26ኛ፣ [1] የጸረ ሙስና ልዩ የስነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁ 434/97 በአዋጅ ቁጥር 882/07 አንቀጽ 48

በተሻሻላው የፌደራል ፀረ- ሙሽና ኮሚሽን ማቋቋምያ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 883/2007

የሽብር ወንጀልን ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 1176/12

በሰዉ መነገድና ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 23 መ/ቁ 153228

የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ 699/2003

Mellese Damtie, Solomon Kikre, Law of Successions, 2009, 27

የፍትሐ ብሔር ሕግ 1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952 በተለይ የወጣ፣

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቀ. 943/2008

Materials on Introduction to Law & Ethiopian Legal System Tesfaye Abate, Oct, 08

N.V. PARANJAPE 2001:

Universal Declaration of Human Rights, (UDHR) 1948

የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት (International Covenant on Civil and Political Rights, (ICCPR)፣

የጥላቻ ንግግር የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል የወጣው አዋጅ ቁጥር 1185/2012

አዋጅ ቁጥር 378/1996የፌዴራል ጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ 1249/2013 አንቀፅ 31/1

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2012፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 18ኛ አመት ቁጥር 58፣ ነሐሴ 16፣ 2004 ዓ.ም፣

የቤተሰብ ህጉ ሀተታ ዘምክንያት፣

Ion harel, public and private law, Jul 14 2014,

Jaap Hage & Bram Akkermans, Introduction to law, April 2014, እና

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

+251115-51-50-99

6044

0115-51-77-75

1370

info@eag.gov.et

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia